# በቅርብ ሊሆን ያለው የመከራው ዘመን ትንቢታዊ ክስተቶች
# The tribulation period Prophetic Events - in Amharic



# መግቢያ

ይህ በአማረኛው "በቅርብ ሊሆን ያለው የመከራው ዘመን ትንቢታዊ ክስተቶች" እንዲሁም በኢንጊሊዘኛው "The tribulation period Prophetic Events " በሚል ርዕስ የተሰጠው መፅሐፍ ካሮል ጄንጊስ ከምትባል ነቢይት ስድስት መልዕክቶች በስተቀር ሁሉም መልዕክቶች የተወሰዱትና የተተርጎሙት ሲስተር ክሌር ከምትባል የ74 ዓመት አሜሪካዊት ነቢይት ነው፡፡ ይህችም ሴት ከጌታ ኢየሱስ መልዕክቶችን በመቀበል ከፈረንጆች አቆጣጠር ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ መንገድ መልዕክቶቿን እያስተላለፈች ትገኛለች፡፡

ዘ ኤንድ ዴይስ ሚኒስትሪስ/ The End Days ministries / አንዱ ዓላማው በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና ህዝባችን ሊሰማቸው የሚገቡ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን ትንቢታዊ መልዕክቶችን በመተርጎም ለህዝባችን ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም አንፃር ከሲስተር ክሌር መልእክቶች ውስጥ በቅርብ ሊሆን ስላለው የታላቁ መከራ ዘመን ክስተቶች ተመርጦና ተተርጉሞ በዚህ መልኩ ቀርቧል ፡፡ የመልክቶቹም ይዘት በቅርብ ንጥቀት እንደሚካሄድ፣ ከንጥቀት በኋላ በምድር ላይ ለሰባት አመት የታላቁ የመከራ ዘመን እንደሚሆን፣ በንጥቀቱ ተካፋይ የማይሆኑ ሰዎች በዚህ የመከራው ዘመን እንደሚያልፉና የእግዚአብሔር መንግስት ተካፋዮች ሆነው እንዲቀጥሉና ወደ ገሃነም እንዳይጣሉ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመላክቱ ወሳኝ መልዕክቶች ናቸው፡፡ ጠቅላላ መልዕክቶችን በሚከተሉት ቻናሎችን ማግኘት ትችላላችሁ፡፡

(1) በአማረኛ የተተረጎሙ መልዕክቶችን ለማግኘት Youtube - The End Days ministries channel

(2) በአማረኛ የተተረጎሙ ትንቢታዊ መልዕክቶች በመፅሐፍ መልክ ተጠናቅረው heartdwellers.org – Book በሚለው ውስጥ ታገኛላችሁ

- The Rapture was real Book Amharic pdf - ንጥቀቱ እውን ነበር መፅሐፍ
- Tethered Book Amharic pdf- ቴተርድ መፅሐፍ
- Events in the tribulation and the measures to be taken in Amharic pdf- በቅርብ ሊሆን ስላለው የታላቁ የመከራ ዘመን ክስተቶችና ምን መደረግ እንዳለበት ማስጠንቀቂያዎች
- My Bride get ready I am on my way - Amharic 1st book pdf – ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! 1ኛ መፅሐፍ!!!
- My Bride get ready I am on my way - Amharic 2nd book pdf – ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! 2ኛ መፅሐፍ
- My Bride get ready I am on my way - Amharic 3rd book pdf- ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! 3ኛ መፅሐፍ

(3) በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ መልዕክቶቹን ለማግኘት

- heartdwellers.org - pdf
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

**ጌታ ዘመናችሁን ይባርክ!!!**

# Introduction

This book in titled in Amharic "በቅርብ ሊሆን ያለው የመከራው ዘመን ትንቢታዊ ክስተቶችና መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች" translated to Engilish with the title "The tribulation Period Prophetic Events and the Measures to be Taken", all the messages are taken and translated from sister Clare dubois, except six messages from Carol Jenngis. Sister Clare is a 74 years old American prophetess who hears and transmites messages from God to the world through different Medias since 2014.

One of "The End days ministries" goals is to acceses prophetice messages spoken in Engilish and are relevant to our people. In this respect we have selected and translated same of Sister Clare's messages which talks about events of the tribulation period and measures to be taken when passing through this period. Th contents of the messages include- rapture will be taken in the near future, after rapture the seven years tribulation will began, people who leftbehind will pass the tribulation period and clarifies the measures to be take in order to remain in the kingdom of God. You can get all messages on the following chananles.

(1) Translated messages in Amharic on Youtube - The End Days ministries channel
(2) Traslated prophetic messages and compiled in books essages heartdwellers.org – Book

- The Rapture was real Book Amharic pdf
- Tethered Book Amharic pdf
- My Bride get ready I am on my way 1st book Amharic pdf
- My Bride get ready I am on my way 2nd book Amharic pdf
- My Bride get ready I am on my way 3rd book Amharic pdf
- The Tribulation Period Prophetic Events and the Measures to be Taken pdf,

(3) You can get messages in Engilish

- heartdwellers.org – recorded and in pdf
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## God Bless You

| ተራ ቁ. | የመልዕክቱ ዝርዝር ርዕሶች | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | የሙሽሮቼ ንጥቀት ለሁሉም የሚታ ይሆናል / The rapture of My Bride will be visible to all | 5 |
| 2 | ሳይነጠቁ ለሚቀሩ የጌታ ሶስት ደብዳቤዎች/ Three post rapture letters from God | 8 |
| 3 | በኒኩላር ጦርነት ውስጥ የተተዉ / Left Behind in Nuclear War song and dramatization | 11 |
| 4 | ገሃነም በምድር ላይ / Hell on Earth | 13 |
| 5 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 1 / What is to come after the raprure event 1 | 15 |
| 6 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 2 / What is to come after the raprure event 2 | 20 |
| 7 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 3ና4 / What is to come after the raprure event 3&4 | 23 |
| 8 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 5/ What is to come after the raprure event 5 | 28 |
| 9 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 6/ What is to come after the raprure event 6 | 30 |
| 10 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 7/ What is to come after the raprure event 7 | 35 |
| 11 | ̈ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት 8/ What is to come after the raprure event 8 | 39 |
| 12 | ከንጥቀት በኋላ ሚከናወን ክስተት 9/ What is to come after the raprure event 9 | 42 |
| 13 | ̈ከንጥቀት በኋላ ሚከናወን ክስተት 10/ What is to come after the raprure event 10 | 46 |
| 14 | ̈ከንጥቀት በኋላ ሚከናወን ክስተት 11/ What is to come after the raprure event 11 | 49 |
| 15 | በእምነት ላይ ተቃውሞ እየመጣ ነው/ Attacks Against The Faith Are On The Way | 54 |
| 16 | ሁሉ ነገር እንዳለ የሚቀጥል ይመስላል / It seems business as usual, April 7, 2015 | 59 |
| 17 | ስፍራን ላዘጋጅላችሁ ሄጀለሁ / I went to prepare a place for you | 63 |
| 18 | ሁሉን ነገር ለመተው አሁን ጊዜው ነው / It is time to let it go | 66 |
| 19 | በክርስቶስ የሚገኘውን ህይወት ምረጡ / Seek life in Jesus | 68 |
| 20 | የንጥቀት ተካፋይ ለማይሆኑት መልዕክት - በሥጋ ላይ አትደገፉ | 69 |
| 21 | የቀረው እጅግ ጥቂት ጊዜ ስለሆነ ወደ እኔ ኑ / There is very little time left come to Me | 71 |
| 22 | አለም ፍርክስክሱ ሲወጣ እናንተ ትቆሙ ይሆን? / Will you stand when the world crumbles? | 73 |
| 23 | ለእናንተ ያለን ፍቅር እጅግ ታላቅ ነው / How great is My Love for you | 74 |
| 24 | "አሁን ምረጡ ገንዘብንና በራስ መተማመንን ወይስ እኔን?" / Money, self- reliance or Me, you must decide | 78 |
| 25 | ኢየሱስን ተከተሉ እንጂ የአውሬውን ምልክት አትወሰዱ / Follow Jesus , do not take the mark of the beast | 80 |
| 26 | የገሃነም መንጎች ወደ ምድር ተለቀዋል/ The hordes of hell haave been released | 81 |
| 27 | ከንጥቀት ለሚቀሩት መልዕክት/ Messages for those left behind | 83 |
| 28 | ከንጥቀት ወደኋላ ለሚቀሩት የአቅርቦት መመሪያ/ Provision and Instruction For Those Left Behind | 84 |
| 29 | ሊመጣ ያለውን ታላቁን የመከራ ዘመን እንዴት ማለፍ እንደሚቻል | 87 |
| 30 | የመጨረሻው መጨረሻ ከፋች ክስተት / The turn key event | 90 |
| 31 | በቅርቡ ሊሆኑ ያሉ የክስተቶች ቅደም ተከተል/ Order of Events | 93 |
| 32 | ከሰማያት እሳት ስለሚወድቅ ተዘጋጁ እንጂ አትፍሩ / Fire will fall from Heaven | 99 |
| 33 | የፍርስራሾች ደመና/ Debris from the sky | 105 |
| 34 | ጥፋት እየመጣ ስለሆነ ጩኹ ንስሐም ግቡ / Shout Devastation is coming | 107 |
| 35 | እንጉዳይ ቅርፅ የመሰለ ዳመና በኒዮርክ ከተማ ላይ / Musheroom cloud on the sky of Newyork city | 112 |
| 36 | ታይቶ የማይታወቅ ጊዜ ከፊታችን እየመጣ ነው/ Time is coming never before | 113 |
| 37 | የወደቁ መላዕክቶች ወደ ምድር መምጣትና መደረግ ያለበት ጥንቃቄ / | 117 |
| 38 | ግሬት አዋከኒነግ ምንድነው? What is great awakening? / What is the great awakning? | 121 |
| 39 | የወደቁ መላዕክት መጓጓዣዎች አየሩን ይሞሉታል / | 125 |

**የሙሽሮቼ ንጥቀት ለሁሉም የሚታይ ይሆናል - ሜይ 28 ቀን 2016 ዓ. ም**

**The Rapture Event Will Be Visible, May 28, 2016**

ክሌር፡- ለመነጠቅ የምንጠባበቀው ትልቁ ተስፋችን እርሱን ተጠንቅቀን  እንደንጠብቀው ያድርገን፡፡

አሁን ስለ መነጠቅ የተዘጋጀውን አጭር ፊልም በቦብ ባርበርስን ቻናል አይቼ መጨረሴ ነው፡፡ በእርግጥ ፊልሙ በደንብ ተደርጎ ነው የተሰራው፡፡ ያንን በአዕምሮዬና በልቤ ይዤ ነበር ጌታን ለመስማት የመጣሁት፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ... "እስካሁን ምንም አላየሽም፡፡ ለመሆኑ እነዛ የተተኮሱት አንፀባራቂ ስራዎች አስደነቁሽ? እኔ ያቀድኩትን ሙሉ ሥራውን እስከታዬ ድረስ ጠብቂ፡፡ ያ ማንም የፊልም አዘጋጅ ከሚያስበው በላይ የሚሆነው ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ለማለት የምፈልገው ነገር የተሰራው ፊልም በጣም ጥሩ ሙከራ ነው፡፡ በእርግጥም ስለ ንጥቀት የማታውቂውን ትንሽ ብልጭ እንዲልልሽ አድርጓል፡፡ ዳዊት ታማኝ አገልጋዬ ነው፡፡"

ጌታ የተናገረው ፊልሙን ስለሰራው ስለ ዴቪድ ኤ.ር ዋይት /David A.R. White/ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሰው እግዚአብሔር አልሞተም የሚለውን አጭር ፊልም የሰራ ሰው ነው፡፡

"ቢሆንም እኔ ለሙሽራዬ ያዘጋጀሁት አይን ያላየው ጆሮ ያልሰማውና በማንም ልብ ውስጥ ያልታሰበ ነው፡፡ መግለፅ ከሚቻለው በላይ የከበረና ልብ ከሚችለው በላይ ቆንጆ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ቀናቶች መዋዠቅና ችግር የበዛባቸው ናቸው፡፡ ለአንዳንዶቻችሁ መጠበቅ ፍፁም የማትችሉት ሆኖባችኋል፡፡ ነገር ግን የኔ ፀጋ እንድትችሉ ያደርጋችኋል፡፡ ያ በጣም ቆንጆና ምስጋና የሚገባው ነገር ጠላት በዓለም ቆሻሻ ተሸፍኖ እንዳይታይ አድርጎታል፡፡ ነገር ግን ለጥቂቶች ለአጭር ጊዜ  ሽፋኑ ተነስቶ የሚያያችሁን ታዩታላችሁ፡፡"

"እንደዚህ ዓይነት ነገር ሆኖ አያውቅም፡፡ ወደፊትም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ስትውርደ ካልሆነ በቀር አይሆንም፡፡ ይህ ክስተት መቼም ጊዜ ቢሆን የማንረሳው ክስተት ነው፡፡ የኔ ሙሽራ ወደ ሰማያት ተወስዳ! ተለውጣ ማየት እንዴት እንደምጓጓ!፡፡ ሊሆን ያለው ነገር አይን ያላየውና በሰው ልብ ውስጥ ያልታሰበ ነገር ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ብዙ በክብር የተሞላን ነገር አይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ሊሆን ያለው ነገር ከታየው ሁሉ የሚልቅ ነው፡፡

"የኔ ሙሽሮች እኔ ለእናንተ ያዘጋጀሁት ነገር ካልታየ በስተቀር በፍፁም የሚታመን ነገር አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ እንኳን ሁኔታው ለጠላት ጥቅም እንዲውል ተደርጎ ተጣሞ ይቀርባል፡፡ እንዲህ ቢሆንም ግን አንዳንዶች የሆነውን ነገር በፍፁም በማመን ራሳቸውን ለእኔ አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ በተለይም የንጥቀት ተካፋይ የሆኑት ዘመዶቻቸው፡፡ ዘመዶቻችሁን ስለዚህ ነገር ስላዘጋጃቸዋቸው ይህ የትንቢቱ መፈፀም መሆኑን ሊክዱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ይህ ክስተት በውስጣቸው በመቀረፁ ቀሪ ዘመናቸውን ሁሉ ይዟቸው ይጓዛል፡፡

"ስለዚህም ከዚህ በኋላ እኔ እውነት እንደሆንኩና መጥቼም እንደምገዛ ጥርጣሬ አይኖራቸውም፡፡  በአሁኑ ጊዜ ሁሉም በዓለም ጉዳይ ስለተጠመዱ ማንም ይህንን ሊቀበል የሚችል የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ክስተት ነገሮችን ሁሉ ቀይራል፡፡ ልባቸው እጅግ የደነደነ ብቻ በወቅቱ ምን እንደተከሰተ ጥያቄ ይፈጥርባቸውና ዓለም የምትሰጠውን ትንታኔ ለመስማት በመፈለግ በዛ ይተኩታል፡፡"

"ለዚህ ነው ይህንን ክስተት ሁሉም ህብረተሰብ እንዲያየው የሚደረገው፡፡ የምድር ወገን ሁሉ ያን ጊዜ ያዝናል፡፡ <u>በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል፡፡ የምድር ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ፡፡ የሰው ልጅም በሰማይ ደመና ሆኖ በኃይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩታል</u>(ማቴዎስ 24፡30)፡፡"

"ይህ አሁን የምናገረው ቀጥታ የሚመለከተው የእስራኤልን ወገን  ነው፡፡ እነሱ አዳኛቸውን ገድለዋል ስለዚህም ይህ እነርሱ የሚሰበሩበት ጊዜ ነው፡፡ ከአሁን ወዲያ ህዝቤን የሰው ኩራት አይገዛውም፣ ህዝቤ የመጨረሻውን ትህትና ይላበሳል፡፡ ከእነርሱ ትልቅ የሆነው ራሱን እጅግ ኃጢያተኛ አድርጎ ይመለከታል፡፡ የፃህፍትና የፈሪሳውያን ትምህርት የኔን እውነተኛ ማንነት እንዲያውቁ አላዘጋጃቸውም፡፡ በሰው የሚደረገው የፅድቅ ሥራ ይፍረከረካል፡፡ እናም ሴተኛ አዳሪዎች ከእነርሱ ቀድመው መንግስተ ሰማያትን ይወርሳሉ፡፡"

"ነገር ግን ይህንን የምለው ላሳፍራቸው አይደለም፡፡ እኔ ለህዝቤ ያለኝ ፍቅር ትልቅ ነው፡፡ እነርሱ እኔ የህጉ ዋና ቁንጮ ወይም ልብ እንደሆንኩና ነቢያት የተናገሩትን ለመፈፀም እንደመጣሁ ወደፊት ገብቷቸው ለማየት እጓጓለሁ፡፡ እኔ ለእነርሱ ከአዳኛቸው በላይ ነኝ፡፡ እኔ በሥጋ የመጣሁ ህያው አምላካቸው ነኝ፡፡ እናም በምድር በኖርኩት ህይወት የእምነታቸውን ምንነትና እንዴት መኖር እንደሚጠበቅባቸው አሳይቻቸዋለሁ፡፡"

"ከአሁን ወዲያ ማንም ሰው በራሱ ሥራና በምድራዊ እሴት ፍርድ ሊሰጥበት አይገባም፡፡ የምድር ባለጠጋዎች ሁሉ እስካሁን ዋጋ ባልተሰጠው ክቡር ደሜ ሥር ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ አለባቸው፡፡ ሽባው፣ አንካሳውና ደካማው ስለምፈወሳቸው በእኔ ልዩ ሥፍራ አላቸው፡፡ ህጉ ንፁህ አይደሉም ብሎ የደነገገባቸውን እነዚህን በደሜ ታጥበው ለዘላለም ይነፃሉ፡፡"

"በምድር ትልቅ የሚባሉት ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ በዝቅታቸው ደስ ይላቸዋል፡፡ እንዲሁም በምድር የሚገኙ ድሆች ደግሞ ወደ ትክክለኛው የህይወት እሴት በመመለስ ከፍ ብለው ይታያሉ፡፡ ሁሉም በደሜ ስለተገዛ ከዚህ ወዲያ  ማንም ሰው ይሽኛው ከዛኛው ይሻላል ብሎ ሊፈርጅ አይችልም፡፡"

"ከሌር የኔ ልጅ የህግ ዋናው ነገር ፍቅር እንደሆነ ታውቂያለሽ? በእኔ ልብ ውስጥ ሥፍራ ለማግኘት ምንም "መንገድ" የለም፡፡ የኔን ደም አስቀድማችሁ ተቀብላችሁ በደም ሥራችሁ ውስጥ እየተዘዋወረ ነው፡፡ ስለዚህም እናንተ ውድ ከመሆናችሁ የተነሳ ዋጋ ሊተመንላችሁ አይችልም፡፡ እና ደግሞ የመንግሰተ ሰማያት ገንዘብ ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር ለመንግስተ ሰማያት እጅግ ዋጋ የሚሰጠው ባህርይ ነው፡፡ ስለዚህም በፍቅር የሚመላለሱ በአባቴ ደረት ውስጥ የሚገኙ ዋጋ የማይተመንላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የዚህን ዓለም ጉዞና   ፈተና ጨርሰው ወደ ተፈጠሩበት ንፅህና የተመለሱ ናቸው፡፡"

"ይህ ታላቅ ሚስጥር ነው፡፡ በሥጋ የተገለጠና ወደ አብ ያረገ፣ በሰማይ መላዕክት የታየና የከበረ፣ በወደቁት ገሃነም የተፈራ ነው፡፡ ሰዎች ራሳቸውን አሳልፈው ለእኔ ሲሰጡ የኔ ህይወት፣ ሞትና ትንሳዔ ተደጋገሞ እንደቀረበ ዓይነት ነው፡፡ በእውነትም ፍፁም አደርጋቸዋለሁ፡፡ እነሱ መላዕክቶች ሊኖራቸው የማይችለውን ፍፅምና አላቸው፡፡ እነርሱ ማንም ፍጥረት ሊደርስበት የማይችለውን አንድነትና ህብረት ከእኔ ጋር ይሰማቸዋል፡፡ አዎን ይህ እኔ ራሴን ለፍጥረቴ የሰጠሁት ታላቅ ሚስጥር ነው፡፡ አዎ እኔ ወደ ምድር ተጥዬ ለመታጨድ የደረሰ ብዙ የበሰሉ ፍሬዎችን ያፈራሁ የስንዴ ቅንጣት ነኝ፡፡

"በፍፅምና ተፈጥሮ የነበረው ፍጥረት የራሱን መንገድ ጨርሶ ወደ እኔ ተመልሷል፡፡ ነገር ግን አሁን ራሱን ለሞት አሳልፎ ለእኔ ለሚሰጠው ለእያንዳንዱ ክብር ይሆናል፡፡ ኦ! ስንቶች በዚህ ሚስጥራዊ ሞት ተጣብቀዋል? ለእያንዳንዳችሁ ራሴን አሳልፌ የሰጠሁት በግል በእናንተ ውስጥ ለመኖር መሆኑን፣ እንዲሁም እናንተም በሞትና በትንሳኤ የክርስቶስ አካል መሆናችሁን በእውነተኛው መንገድ ልትረዱ የምትችሉት በመንግስተ ሰማይ ብቻ ነው፡፡"

"ይህ እንዲገባችሁ አሁን እራሳችሁን አታስጨንቁ፡፡ በቅርብ ጊዜ እንደ ውኃ ጥርት ብሎ ይታያችኋል፡፡ አሁን ግን ጊዜው ህዝቤን መረጋገጫ ያደረጉትን የዚህን ምድር ክፉ ኃይላት መቋቋም ነው፡፡ አሁን ግን ጊዜው ገና የፈተናና የመፈተኛ ወቅት ሲሆን በዚህም የኔ ክብር በአሸናፊዎች ላይ የሚፈነጥቅበት ወቅት ነው፡፡ አውቃለሁ ከእናንተ ማንኛችሁም አሸናፊዎች ነን ብላችሁ አታስቡም፡፡ ነገር ግን ታምኑኛላችሁ? አሸናፊዎች ናችሁ፡፡ አውቃለሁ ለራሳችሁ ትንሽ ግምት እንደምትሰጡት፡፡ ይህ ደግሞ ትክክልና እንዳትወድቁ የሚጠብቃችሁ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን በሌላው አንፃር ራስን ከሚገባው በላይ ማሳነስ ነው፡፡"

"ቢሆንም ስለ መዳናችሁ ሲባል እንዲህ ዓይነቱን ነገር በጣም አተኩሮ መመርመር ቢቀር ይሻላል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ምድር እስካላችሁ ድረስ ለኩራት፣ ለቅናትና ከሌላው እበልጣለሁ ብሎ ለመገኘት የተጋለጣችሁ ናችሁ፡፡ እናንተ ከእነዚህ የምታመልጡት ራሳችሁን ትንሽ አድርጋችሁ ስትቆጥሩ ነው፡፡ እናም በትንሽነታችሁና ምንም ባለመቻላችሁ በእውነት ከልባችሁ ደስታ የሚሰማችሁ ከሆነ ጦርነቱ በድል እንደተጠናቀቀ ማሰብ ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ያልኩበት ምክንያት ለሌሎች ምንም መስላችሁ ብትታዩም፣ በዚህ ነገር ለመውደቅ እናንተም የተጋለጣችሁ በመሆናችሁ ከውድቀት እንድትጠበቁ የእናንተ ውበት ያለው በእኔ ውስጥ ስለሆነ ነው፡፡"

"እናም ሙሽሮቼ በዚህ ሐሳብ ላይ ልታርፉ ትችላላችሁ? ሁሉንም እንደነበረ ወደ አብ ለመመለስና ቁንጅናችሁ እንደተጠበቀ ለማድረግ፣ እንዲሁም በጦርነቱ የቆሰላችሁት ቁስል ታይቶ እንደማይታወቅ ዕንቁ እንዲያበራ ለማድረግ በሚደረገው ራዕይ ላይ ልታርፉ ትችላላችሁ? አዎ ! ይህንን ቃል በልባችሁ ያዙት፡፡ በየቀኑ ራሳችሁን አዘጋጁ፣ ደግሞም በዚህ ሥራ ላይ አብሮ ሰራተኞች መሆናችንን እወቁ፡፡ እናም ወደ ፍፅምና እያመጣኋችሁ እንደሆነ ተገንዘቡ፡፡

"የጌታ እጅ ያልተዳሰሰውን የእናንተን ማንነት ለማስተካከል ሲንቀሳቀስ ከብዙ አንዱን ፍጥረቱን መንካቱ ስለሆነ ልታደርጉ የምትችሉት ጥቂት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን በመገንዘብ በዚህ ሐሳብ ላይ እረፉ፡፡ እናንተ ምንም ልታደርጉ አትችሉም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን አጋጣሚ በመውደድ፣ በእያንዳንዱ ውድቀት ንስሐ እየገባችሁ ተከተሉኝ፡፡ እንዴት እንደማነሳሳችሁና እንደምመራችሁ አውቃለሁ፡፡ ለአንድ ደቂቃ እንኳን አትፍሩ፣ ይህ የኔ ስራ ነው፡፡ ደግሞም በሚገባ እሰራዋለሁ፡፡"

"በእናንተ ውስጥ በተትረፈረፈው መገኘቴ የምትሮጡትን ሩጫ በአሸናፊነት እንድትጨርሱ የበቃ ይሁን፡፡ እኔም ይህንን እከታተላለሁ፡፡"

## ሳይነጠቁ ለሚቀሩት ጌታ የላከው ሦስት ደብዳቤዎች - ኦክቶበር 7 ቀን 2014 ዓ.ም/

## Three Post Rapture Letters from God - October 7, 2014

**ደብዳቤ ቁጥር 1 / Letter 1**

"ልባችሁን በማፅናናት እየጠራኋችሁ ነው፡፡ እኔ አልተውኳችሁም ደግሞም መቼም አልጥላችሁም፡፡ ምን ያህል ከባድ ሐዘንና ባዶነት እንደተሰማችሁና አንዳንዴም የተከዳችሁ የሚመስላችሁ ወቅት አለ፡፡ የተሞላችሁት ለምን? የት? ለምንድነው እስካሁን እዚህ ያለሁት? ለምንድነው የተተውኩት? አሁንስ ምንድነው የማደርገው? በሚሉ ጥያቄዎች ነው ፡፡"

"በዚህ ወቅት ብዙዎች በኢንዱስትሪው፣ በንግዱና ገንዘብን በሚያስገኙ መስኮች ሁሉ የተፈጠሩትን ብዙ ክፍት የሥራ ቦታዎች አዲስና የሚያጓጉ አጋጣሚና ሙያዊ እድል እንደሆነ ቆጥረውታል፡፡ እናንተ ግን ወደ አለም በጥልቅ ዘልቃችሁ በመግባት በሥራ ለመጠመድ ከሚፈታተናችሁ የልብ ምኞት ራሳችሁን መቆጣጠር አለባችሁ፡፡"

"በህመማችሁና ግራ በተጋባችሁ ጊዜ እንኳን ከእነዚህ ነገሮች በፍፁም መራቅ አለባችሁ፡፡ ካልተረጋጋ ከዚህ አለም እርቃችሁ በአሥር እጥፍ እኔን በሙሉ ልባችሁ መፈለግ አለባችሁ፡፡ በእውነተኛ ንስሐና የልብ ለውጥ ጠንክራችሁ ወደ እኔ ጩኹ እኔም እረዳችኋለሁ፡፡ እኔም እጆቼን ዘርግቼ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት እቀበላችኋለሁ፣ ከፍርሃታችሁም አረጋጋችኋለሁ፡፡"

"የጠፋችሁ አይደላችሁም፡፡ አሁንና በሚመጡት ቀናቶች ውስጥ ምን ያህል እንደምወዳችሁ በይበልጥ እያያችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ እናት ልጇን ልትተው ትችላለች፡፡ እኔ ግን አልጥላችሁም፡፡ እኔ ላድናችሁ ሁልጊዜ እዚሁ ነኝ፡፡"

"አሁንም ለእኔ በጣም ተወዳጅና ከፍተኛ ዋጋ ያላችሁ ልጆቼ ናችሁ፡፡"

"አሁንም እናንተ ትልቅ ኃብቶቼ ናችሁ፡፡ ስለዚህ አሁንም እንኳን ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡"

"ለፈጠርኩት ለየትኛውም ነፍስ እኔ እዚህ ነኝ፡፡ አልለወጥም፣ አልተኛም ወይም አላንቀላፋም፡፡ ያለማቋረጥ እያየኋችሁ፣ እየጠበኳችሁና ከእናንተ ጋር ጊዜ ለማሳለፍና የልቤን ልነግራችሁ በመጓጓትና በናፍቆት እየጠበኳችሁ ነው፡፡ አሁን የሚያስፈልጋችሁ እንደምንም በርትታችሁ መሞከር ነው፡፡ እኔ ግን የማረጋግጥላችሁ ፍላጎታችሁ የእውነት ከልብ ከሆነና የራሳችሁ ሌላ ተጨማሪ ሐሳብ ከሌለበት ሙከራችሁን ተግባርያዊ እንዲሆን አደርጋለሁ፡፡

ሙሉ ፈቃዳችሁን፣ እውቀታችሁንና የማሰብ ችሎታችሁን ሁሉ ለእኔ አሳልፋችሁ ስጡ፡፡ ተመልሳችሁ እንደ ህፃን ልጅ ለመሆን ጠይቁ፡፡ በመረጋጋትና በትዕግስት ጠብቁ፡፡ ያን ጊዜ አስባችሁ በማታውቁት መንገድ እጎበኛችኋለሁ፡፡ ብቻ ለእኔ ሥፍራ ስጡኝ፡፡ እኔ የምፈልገው ልባችሁን ሁሉ ነው፡፡ ትልቁ ፍላጎታችሁና በጥብቅ የምትፈልጉት እኔንና እኔን ብቻ መሆን አለበት፡፡ ከዚያም የተትረፈረፈ ቅባት እሰጣችኋለሁ፡፡ ነገር ግን ራሳችሁን ማቅረብና ማዘጋጀት አለባችሁ፡፡"

**ደብዳቤ ቁጥር 2/ Letter 2**

"ግን ለምን ? የሚል ጥያቄ በአይምሯችሁ እየተመላለሰ አስቸግሯችሁ ከሆነ? የኔ ጌታ ለምን? ለምን? ለምን እዚህ ተውከኝ ? የሚል ጥያቄዎች ካሏችሁ፡፡"

"ልጆቼ ከንጥቀቱ ተለይታችሁ እዚህ እንድትቀሩ በፍፁም የታቀደ አይደለም፡፡ ይህ ለልጆቼ ሁሉ፣ በእውነትም ለአካሌ ይህም ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሙሽራዬ የተዘጋጀ የኔ ምህረት የተሞላበት ስጦታ ነበር፡፡ እናንተም በንጥቀቱ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ከዚህ ታይቶ ከማይታወቅ ወደፊትም ሊከሰት ከማይችል አሰቃቂና ስቃይ የበዛበት ህይወት ታመልጡ ነበር፡፡"

"አጀማመራችሁ ጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ጊዜ በሄደ ቁጥር ከአለም ጋር ተቆራኛችሁ፡፡ በስም ብቻ ክርስቲያን ተብላችሁ የአንድ ቤተክርስቲያን አባል በመሆን ጊዜ ማሳለፊያ ብታደርጉትም ብዙ ጥፋትን ያስከተለ ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን እናንተ በየጊዜው እየራቃችሁ ሄዳችሁ፡፡ ከእኔም ጋር አብረን የምንሆንበት ጊዜ እያነሰ እያነሰ መጣ፡፡ በእምነታችሁ ጉዳይ ላይም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአለም ጋር እየተስማማችሁ እንደመጣችሁ እናንተም ታውቁታላችሁ፡፡ ስለዚህም ስለ እኔ መናገሩን አቆማችሁ፡፡

"እንዲሁም አዲስ የጀመራችሁት ግንኙነትና ነፃ የሆነ አመለካከታችሁ ተደምሮ በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ነፍሶች ዓይታችሁ በእነርሱ ላይ እንድትፈርዱ አስቻላችሁ፡፡ እነርሱንና ለእነርሱ ውድ አድርገው ያዙትን የበታች አድርጋችሁ ተመለከታችሁ፡፡ በእኔ መምጣት በመደሰታቸው እንኳን ደስታቸው ዋጋ እንደሌለው በመቁጠር በግልፅ በመተቸት ነቀፋችኋቸው፡፡"

"እኔ ልክ ስደርስ ሁላችሁም ማድረግ የምትችሉት የነበረው በፍርሃትና በሃፍረት መቆምና ለማመን ያቃታችሁ ነገር በፊታችሁ ሲፈፀም ማየት ብቻ ነበር፡፡ ምክንያቱም እናንተ አላመናችሁም፣ ስላልጠበቃችሁ አልፀለያችሁም፡፡ ስለዚህም ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እኔም መጣሁ፡፡ እናንተ ግን አልተዘጋጃችሁም ነበር፡፡ ስለዚህም ልወስዳችሁ አልቻልኩም፡፡

**ደብዳቤ ቁጥር 3/ Letter 3**

"አሁን ምን እናድርግ ብላችሁ ጠይቁኝ፡፡ ከምንጊዜውም በበለጠ ወደ እኔ ቅረቡ፡፡ ሁልጊዜ እኔን በልባችሁና በአይምሯችሁ ለማሰብ እንድትችሉ፣ ስሜን ሁልጊዜ በአንደበታችሁ ላይ እንዲሆን ፀጋ እንዲሰጣችሁ ፀልዩ፡፡ የልብሴን ጫፍ አጥብቃችሁ

ያዙ፡፡ ከአሁን ወዲያ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ከአጠገባችሁ እንድሄድ አትፍቀዱ፡፡ በየትኛውም ቦታ ሁልጊዜ እኔን የማሰብ ልማድ አዳብሩ፡፡ ሁልጊዜ በሐሳበ ህሊናችሁ እኔን ተመልከቱ፡፡ ስለዚህም ደግሞ ፀልዩና እኔ እንዲሆንላችሁ አደርጋለሁ፡፡

እንደ ተለመደው እኔ ቀደሜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ነገር ግን መኖሬ ሊሰማችሁ፣ አብልጦ ታማኝ እንደሆነ ጓደኛ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ግንኙነት መፍጠርና ከእኔ ጋር መነጋገር  አለባችሁ፡፡ በእያንዳንዱ ሐሳባችሁና ስሜቶቻችሁ ላይ በብልሃት የምፈፅመው ፍላጎት አለኝ፡፡ ይህም ራሳችሁን ዝቅ፣ ትሁትና ትንሽ ለማድረግ ጥረት እስካደረጋችሁ ድረስ ነው፡፡

"እኔ ምንጊዜም ቢሆን ከሁሉም በላይ ታማኝና ሚስጥረኛ ጓደኛ ነኝ፡፡ ደግሞም ራሱን እንደ ህፃን ታናሽ ከሚያደርግ የበለጠ ወደ እርሱ እንድቀርብ የሚያደርገኝ ነፍስ የለም፡፡ ከራሳቸው ቆዳ በበለጠ ለእነርሱ ቅርብ እሆናለሁ፡፡ እናም ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ እስካሁን ድረስ ገና ግራ እንደተጋባችሁና በዙሪያችሁም ያለው አለም ሁሉ  መጥፎ  ትርምስ ውስጥ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

ነገር ግን ደግሞ እናንተ ልትገልፁት የማትችሉት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሰላምና ፀጥታ በውስጣችሁ እየተሰማችሁ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይህንንም ስጦታ በመስጠት እቀጥላለሁ፡፡ በዚህም በትክክል እንድታስቡና ግልፅ በሆነና በሚያስደንቅ ሁኔታ ማገናዘብ እንድትችሉ ያደርጋችኋል፡፡

"ስለሚያስፈልጋችሁ ነገር አትጨነቁ፡፡ እንዳያችሁት የሚያስፈልገውን ሁሉ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ ከአሁን ወዲያም የሚያስፈልጋችሁን ከየት መጣ ሳትሉ በማይመስል ሁኔታ ሰዎች ይሰጧችኋል፡፡ በዚህም እውነተኛውን የእምነት ህይወት ቶሎ በመለማመድ ከተለመደው ውጪ በሆነ ሁኔታ እንኳን ሆናችሁ እንዴት ውብ እንደሆነ በተግባር ታዩታላችሁ፡፡

ከእኔ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ ስለዚህም እኔ ሳልፈቅድ በእናንተ ላይ የሚከናወን ምንም ነገር የለም፡፡ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ቀድሜ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ስለምንም ነገር መረበሽ የለባችሁም፡፡ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ አይናችሁንና ልባችሁን በእኔ ላይ መጣል ነው፡፡

እናንተ ለእኔ በጣም ውድና ውድ ልጆቼ ናችሁ፡፡ ስለዚህም ማንም፣ ምንም ነገር እንዲጎዳችሁ አልፈቅድም፡፡ በቀን በሌሊት እንዲጠብቋችሁ መላዕክቶቼን መድቤያለሁ፡፡ የሚያስፈልጋችሁን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የተትረፈረፈ አቅርቦት ይኖራችኋል፡፡

በዚህም ለእናንተ ያለኝን ፍቅር፣ ክብካቤና ታማኝነቴን ታውቃላችሁ፡፡ ንስሐ በመግባታችሁ ደስ የሚላቸውን ሌሎች ሰዎች ታገኛላችሁ፡፡ እነዚህም ልባቸው ተሰብሮ የነበር ነገር ግን ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ስብራታቸው ተጠግኖ ሙሉ ልባቸውን ለእኔና ለእግዚአብሔር መንግስት ብቻ የሰጡ ናቸው፡፡

እናት ህፃናት ልጆቿን እንደምትሰበስብ ከዚህ ከአስቸጋሪና ፈተና ከበዛበት ህዝቤን በድል እንደገና እሰበስባለሁ፡፡ እነርሱም በመንግስተ ሰማያት እንደ ከዋክብት ደምቀው ያበራሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ጊዜ የጠሩ ናቸው፡፡ በመከራው ዘመን ፀንተው በክብር የመጡ ስለሆነ እኔ በምድር ስነግስና ስገዛ አብረውኝ ይነግሳሉ ደግሞም ይገዛሉ፡፡

## በኒኩላር ጦርነት ውስጥ የተተዉ - ሰፕቴምበር 2 ቀን 2014 ዓ.ም

## Left Behind in Nuclear War – September 2, 2014

የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። ማቴዎስ 24፡37

ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፡፡ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፡፡ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፡፡ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፡፡ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። ማቴዎስ 24፡6

በቃሉ እንዲህ ተፅፏል "እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። . . ." 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡51

የሰው ልጅ በሚመጣ ጊዜ የሚሆነው እንዲህ ነው፡፡ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች። ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ። ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና። ይህ የጌታ የራሱ ቃል ነው፡፡ ማቴዎስ24፡40

(ከዚህ በታች ያለው በወቅቱ ሊሆን የሚችለውን ለማሳየት  በድራማ መልክ የቀረበ ነው፡፡ አንዲት እናት የአንድ ዓመት ህፃን ልጇ ስለተነጠቀ ግራ ገብቷት ትታያለች)፡፡

"በጣም ግራ ገብቶኛል፣ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም፣ እጅግ ደንግጫለሁ፡፡ አንድ ሰው እባካችሁ እርዱኝ፡፡ እባካችሁ ምን እየሆነ ነው ያለው? በሁሉም ቦታ ስዘዋወር ወላጆች ተስፋ በመቁረጥና በምሬት እያለቀሱ የልጆቻቸውን ልብስ ይዘው ነው የማየው፡፡ ይህ ሊሆን የማይችል ነገር ነው፡፡ እየቃዠሁ ነው! ከቅዠቴ እነቃለሁ! ከተኛሁበት እነቃለሁ!! ነገር ግን ህልም ላይ አይደለሁም፡፡ እውነት ነው፡፡ ምን እንደሆነ ማንም ሰው አያውቅም፡፡ መንቀጥቀጤን ማስቆም አልቻልኩም፡፡ በትልቅ ድንጋጤ ላይ ነው ያለሁት፡፡  ከትንሽ ደቂቃ በፊት ልጄ በእጄ ታቅፌያት ደህና ነበረች፡፡ የፀሐዩ ነፀብራቅ ፀጉሯን ብድግ ሲያደርግ በንፋሱ ሳቀች፡፡

"በጣም ደስተኞች ነበርን፡፡ ምንም የማታውቅ የዋህ ነበርች፡፡ አሁን ግን ልብሷ ብቻ በእጄ ላይ ቀርቶ ይገኛል፡፡ ሰንደል ጫማዎቿም በመሬት ላይ ወድቀዋል፡፡ ከአሁን ወዲህ የለችም ማለት ነው? አንድ ሰው እርዱኝ . . . ምንድነው የሆነው? ምንድነው የሆነው?

"እግዚአብሔር የሚባለው ካለና መኖሩም እውነት ከሆነ ፣ የኔ ትንሿ መላዕኬ፣ ትንሿ ልጄ ምን እንደሆነች ንገረኝ፡፡ የት ነው ያለችው?

"ይህ አይሆንም . . . ተነጥቃ ሊሆን አይችልም ሊሆን አይችልም፡፡ ያ ዝም ብሎ አፈታሪክና የማይታመን ወሬ ነው፡፡ ያ ሊሆን አይችልም፡፡ ብልህ ሰው ያንን ነገር ያምናል? ነገር ግን . . . እርሷ ሄደች፡፡ ደግሞም በሁሉ ሥፍራ ያሉ. . . ልጆቻችን ሄደዋል፡፡

ከሌላ አለም የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ? ሊሆን ይችላል? . . . ሁሉም ልጆች ተነጥቀው ሊሆን ይችላል? . . . ለምን? ለምን? ለምን እግዚአብሔር?

**መዝሙር**

ባህሩ በተራሮች ሲናወጥ፣
ፍቅርህ ግን መቼም ስለማይናወጥ፣
ትመጣለህ ልታድነን፣ ሲወጣ ብትንትናችን፣
በጦርነት የሞት ስጋት ውስጥ በምጣችን፡፡
የሰዎች ልብ በማዕበል ውስጥ ሲጥላቸው፣
የሚሰቀጥጥ የመለከት ድምፅ ጩኸት ሲሰማቸው፣
ብልጭታ በሰማይ ሲበርቅባቸው፣
እውነተኞቹን ሰማያት ሲያረጋግጥላቸው፣
አንተን ሲጠብቁ የነበሩ ቀና ይላሉ ቀን ወጥቶላቸው፡፡
በዙሪያችን የከበቡን ቅዱሳን በሰማይ ሲታዩ፣
ሙሽራዪቱን ሊወስድ ንጉሡ ሲመጣ በታላቅነቱ፡፡
በምድር የቀሩት በጨለማና በማዕበል ውስጥ፣
ብርሃን በሌለበት፣
በታሰረ ጦርነት፣ በአረጁ ገመዶች በተበጣጠሱ፣
በራቸው ላይ ቆመው ሲያለቅሱ፣
ለጥያቄያቸው መልስ ሲፈልጉ፣ሲያፈላልጉ፣
መልሳቸውን ፍለጋ በታላቅ ጩኸት ሲጮሁ፣
ያን ጊዜ የጠፉት በትክክል እንዲያስቡ ይደረጋሉ፡፡
አሁንም ለመስተካከል አልረፈደምና፣
ግራ ከመጋባት ከመደንበር ይልቅ ንስሐ ግቡና፣
ምህረቱ ከማዕበል፣ቸርነቱ ከጨለማ ያነሳችኋልና፡፡
ሙብራት አዘጋጁ ቁሙ በተጠንቀቅ፣
መቼ እንደሚመጣ ቀኑም አይታወቅ፡፡
ብቻ የቆመውን በአጠገባችሁ፣
እጁን ያዙና አጥብቃችሁ፣
እርሱ እንደሆን ይመጣል አይዘገይባችሁ፡፡

**ገሃነም በምድር ላይ/ ዲሴምበር 13 ቀን 2014 ዓ.ም**

**Hell on Earth**, - **December 13, 2014**

ጌታ መልዕክቱን እንዲህ በማለት ጀመረ... "ገሃነም በምድር ላይ፣ በትክክል አነጋገር ገሃነም በምድር ላይ፡፡ በምድር ላይ ሊከሰት ያለው ነገር ሆሊውድ ሊያልመውና ሊፈጥረው ከሚችለው አሰቃቂ ፊልም በላይ እንዲሁም ማንም ሊያምነው ከሚችለው በላይ ሊሆን ያለ ነገር ነው፡፡ ስለሚመጣው ነገር ከባድነት ማንም ሰው ሊያውቀው ከሚችለው በላይ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎች በዚህ ውስጥ ሊያልፉ ነው፡፡"

"በጣም በዙ የዋሆች፣ አይነስውሮች፣ ምንም የማያውቁና ደካማዎች ስለዚህ ጉዳይ ምንም ፍንጭ የላቸውም፡፡ የታወቁ የትምህርት ተቋማትም ስለዚህ ነገር ምንም የነገሯቸው ነገር የለም፡፡ እኔ ግን ለልጆቼ ስፈልገው የነበረው አሁን በምድር ላይ እየተደረጉ እንዳሉት ዲዳና ምንም የማያውቁ ሆነው እንዲኖሩ አልነበረም፡፡ ይህም በፍፁም እኔ የፈለግሁትና ያቀድኩት አልነበረም፡፡ እኔ ለህዝቤና ለልጆቼ ያቀድኩት ምድረ ገነትን እንጂ ይህንን አይደለም፡፡ እኔ የፈለኩት ልክ እንደ ገነት የሆነችን ምድር ነበር፡፡ እኔ ሰው በራሱ ፈቃድ እንዲገዛ ነፃነትን መስጠት ነበረብኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ነፃ ፈቃድ የሚያስከትለው ውጤት አለ፡፡ ስለዚህም ሰው በራሱ ፈቃድ ከትምህርት ተቋማትም ይሁን ከዘመኑ የሙዚቃ ባህል /Pop culture/ በላይ እኔን መምረጥና መጥራት መማር አለበት፡፡"

"ወደ ውስጥ ህሊናቸው በጥልቀት ማድመጥ አለባቸው፡፡ እኔ በጥልቅ ማንነታቸው ብዙ ጊዜ ተጣርቻለሁ፤ ቃሌን አስቀምጫለሁ፡፡ በጥልቁ ህሊናቸው ብዙ የጥሪ ካርዶችን፣ ፍቅሬንና ማስጠንቀቂያዎችን አስቀምጫለሁ፡፡ ነገር ግን በአንፀባራቂው ባህላችሁ የተነሳ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በህይወት ያሉት ለመሞት ቢመኙም በሰውነታቸው የሚቀበር ቺብስ (RFID) ሞትን እንዳይቀምሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ቴክኖሎጂው ሰዎች በቺብሱ አማካኝነት በህይወት እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች በሚደርስባቸው ስቃይ ለመሞት ቢፈልጉም በውስጣቸው የሚቀበረው ቺብስ ግን እንዳይሞቱ ይከለክላቸዋል፡፡

(ክሌር) በዚህ ወቅት ጌታን አቋረጥኩትና ገብቶኛል ነገር ግን ከድልድይ እራሳቸውን መጣል አይችሉም ? አልኩት፡፡

"አይምሮን የሚቆጣጠረው በውስጣቸው እስካለ ድረስ አይችሉም፡፡ ወደፊት የሚሆነውንና ለመግለፅ የሚያዳግተውን ስቃይ በራሴ አምሳል ለፈጠርኳቸው፣ ህይወቴን አሳልፌ እስከ መስጠት ለወደድኳቸው ለሰው ልጆች በሰይጣን አማካኝነት እንዴት እንደተቀነባበረ ምንም አልገባሽም፡፡ እኔን ለማጥፋት አይችልም፡፡ ነገር ግን ሰዎች እንዲሰቃዩ በማድረግ ሊጎዳኝ ይችላል፡፡ ክሌር፣ በማይነገር ስቃይ ... ነገር ግን እንዲህም ሆኖ ምህረቴ ድል ያደርጋል፡፡ ወደ እኔ የሚጮሁትን በምህረቴ ነፍሳቸውን ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡

(ክሌር)፦ ነገር ግን ጌታ ሆይ አንዴ በሰውነት ውስጥ ቺፕሱ ከተቀበረ መዳን የሌለ መስሎኝ ነበር፡፡

"አዎ እንደዛ ነው የተፃፈው፡፡ ነገር ግን እኔ ምህረት የማላደርግ ነኝ? እነርሱ በጣም ዘግይተዋል፡፡ በጣም ዘግይተዋል፣ ነገር ግን እነርሱን ከዚህ ስቃይ የሚገላግላቸው ሞት ነው፡፡ ስለዚህም ነፍሳቸውን ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡ ከዚህ ክፉና ሰይጣንን ከሚያመልክ ትውልድ በምህረቴ የእነሱን ነፍስ፣ መንፈስ ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡"

(ክሌር) ጌታዬ ይህ መልዕክት ከተለመደው የወጣ ስለሆነ ምንድነው የማደርገው?

"ይህንን በአንክሮ ውሰጂው፡፡ በጣም፣ በጣም፣ በጣም በአንክሮ ውሰጂው፡፡ በህይወት ያሉት በሞቱት ይቀናሉ፡፡ ይህ ክፉና ጨካኝ ትውልድ ያመጣው ነገር በፍፁም ውሸት የተሞላበት ነው፡፡ እነርሱ ቺብሱን ያቀረቡት ሰው ለሚገዛው ነገር እንደ ደረሰኝ አድርጎ እንዲቆጥረው ነው፡፡ይህ የሚደረገው ነገር ሊሆን ካለው ነገር ጋር ሲወዳደር ምንም አይመሳሰልም፡፡ ሰይጣን የእነርሱን ስስታምነት ተጠቅሞ ለራሳቸው መጥፊያ የሚሆነውን እንዳዘጋጁ አልገባቸውም፡፡ በዚህም ሥራቸው ወረርሽኝና ቸነፈር በምድር እንዲመጣ ምክንያት ስለሆኑ እነርሱም በዛው ወረርሽኝና ቸነፈር ይጠፋሉ፡፡ እንዲሁም በምድር ውስጥ ብዙ ገንዘባቸውን አፍስሰው አሳምረው በገነቧቸው ከተሞቻቸው በእሳት ባህር ውስጥ መዋጣቸው ተስማሚ ነው፡፡ እጅግ ተስማሚ ነው፡፡"

"ይሁን እንጂ እኔ ሰውን ወደ ምድር ያመጣሁት ለዚህ አይደለም፡፡ በፍፁም፣ በፍፁም ይህ የኔ እቅድ አይደለም፡፡ ነገር ግን የእነርሱ /ከዲያቢሎስ ጋር የተባበሩ ሰዎች/ ትዕቢትና አመፀኝነት ለእውሸት አባት አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ እናም እርሱ ሥራውን በሚገባ ተወጥቷል፡፡"

"እነርሱ የሚጠብቁት በአስተሳሰብ የላቀና ያሸበረቀ ህይወት የሚኖርበት ቆራጥ አዲስ ዓለምን ነው፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው ከብዙ አታላዮች ጋር በመሆን በእሳት መቃብሮቻቸው ውስጥ ይሞታሉ፡፡ ይገባችኋል? እኔ ስመለስ ፍፁም ድብልቅልቅ ይሆናል፡፡ ምድርን ለማዳን ሲባል በምድር የሚገኙ ግዙፍና አስቀያሚ ፍጥረታት ሁሉ ሊገደሉ ይገባል፡፡"

(ክሌር) ነገር ግን ጌታ ሆይ ከመከራው በኋላ በምድር ላይ ለሶስት ቀናት ጨለማ የሚሆነው እና ምድርን የሚያነፃውስ እሳት?

"አዎ በትክክል ምድርን በእሳት አነፃታለሁ፡፡ ነገር ግን በእሳቱ ሁሉም አይሞቱም፡፡ ከጉድጓድ የሚወጡ ሌሎች መንፈስ የሌላቸው ፍጥረታት አሉ፡፡ እነርሱ ሊገደሉ ይገባቸዋል፡፡ ኢጋንንቶች ይታሰራሉ፡፡ ነገር ግን በአርቲፊሻል መንገድ፣ እንዲሁም ሰውና እንስሳትን በማደባለቀ የተፈጠሩ ፍጥረታት በምድሪቱ ላይ ስላሉ እነዚህ ከምድረ ገፅ ሊወገዱ ይገባቸዋል፡፡ በትክክል ለመናገር ዓለም እጅግ ትቆሸሻለች፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ሥራው ብዙ ቢሆንም ምድርን እንደገና አድሳታለሁ፡፡"

"እኔ የማለቅሰው አልሰማ ብለውኝ ለስቃይ ለሚዳረጉ ለብዙ ህዝብ ነው፡፡ የሚነገረው መልዕክት ለእነርሱ የማይመች ስለሆነ አልሰማ ብለው ጀርባቸውን አዙረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ህይወታቸውን የሚያድነውን መልዕክት በመስማት ራሳቸውን እንዳያስተካክሉና እንዳይድኑ ሆነዋል፡፡"

"እነዚህ እልቂቱ ወይም መቅሰፍቱ ከመምጣቱ በፊት ወደ እኔ አይመለሱም፡፡ በዚያ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱት ለቅድስና ሳይሆን ራሳቸውን በመውደድና ከጥፋቱ ለማምለጥ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ከእሳቱና ከአባቴ ቁጣ ለማምለጥ ጊዜው ስለሚያልፍባቸው ከጥፋት አያመልጡም፡፡"

"ይህንን አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ይህ እኔ ለሰው ልጆች በፍፁም ያቀድኩት አይደለም፡፡ እኔ ለወንድና ለሴት ልጆቼ የፈጠርኩት የአትክልቱን ሥፍራ ነው፡፡ ወደፊት ሊሆን ያለው ነገር እንዲሆን በሐሳቤም የሌለ ነው፡፡ ይህ የሆነው ሁሉ በሰይጣንና በተከታዮቹ አቀናባሪነት ነው፡፡ ልትረዱኝ ሞክሩ ይህ እቅድ በፍፁም የኔ አይደለም፡፡

"አያችሁ ብዙ ክፉዎች በእኔ ላይ ያሳብባሉ፡፡ ምክንያቱም ራሳቸው ለተሸነፉበት ሥራ ኃላፊነቱን መውሰድ አይፈልጉም፡፡ እነርሱ የሚፈልጉት በተቻለ መጠን ፍጥረታት ሁሉ በእኔ ላይ እንዲሳ ማድረግ ነው፡፡ ይህ አሁን ያለ ትውልድ ሊያውቀው የሚገባው ነገር ይህ ሊሆን ያለ ነገር የኔ እቅድ ሳይሆን የሰይጣን መሆኑን ነው፡፡ በእኔ ላይ በማመካኘት ልትወቅሱኝ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን እውነቱን ስታውቁ እኔ በፍፁም እንዳላቀድኩት ትረዳላችሁ፡፡

"ከሰይጣን ጋር የወገናችሁ እናንተ የሰው ልጆች፣ ይህንን ያመጣችሁት እናንተ እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ ምድርን ያጠፋችሁ እናንተ ስትሆኑ ሰዎች ግን ክንዳቸውን ወደ ሰማይ እያነሱ እኔን ይሳደባሉ፡፡ ነገር ግን ምድርን ያጠፋሁት እኔ ሳልሆን እናንተ የሰው ልጆች መሆናችሁን የሚያመለክት ተፅፎ ይቀመጥ፡፡

(ክሌር) ነገር ግን አንተ እኮ ነህ የቁጣውን ፅዋ የደፋኸው፡፡ እናም ሰይጣን ባያቀነባብረው ኖሮ ከፅዋው ውስጥ ምንም የሚደፋ ነገር አይኖርም ነበር፡፡ አንተ ሰይጣን በመሬትን እንዲገዛ ስላደረከው ይኸው እንዲህ ሆነ፡፡

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት አንድ - ማርች 2 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 1 - March 2, 2015

ኢየሱስ እንዲህ ይላል . . . "መጨረሻው ከመድረሱ በፊት አጥፊው (ፕላኔት ኒብሩ) ወደ ምድር አይመጣም፡፡ ያየሽው የሚሆነው ከተመወሰዳችሁ በኋላ ነው ይህም ሙሽራዬ ከተነጠቀች በኋላ ነው፡፡ ይህ ለሚቀሩት ተዘግቦ እንዲቀርና ከእኔ ውጪ የሚሆን ነገር እንደሌለ በግልፅ እንዲያውቁትና ተስፋ እንዳይቆርጡ ነው፡፡ ያሉበት ሁኔታ ተስፋ የሌለው እንዳልሆነ በቃሌ መታመን ይችላሉ፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ በእኔና በምህረቴ እንዲተማመን እፈልጋለሁ፡፡

"ይህ ክስተት እንደሚፈጠር ቢያንስ ከፊሉን በቅድሚያ ቢነገራቸው የወደፊቱን አቅጣጫ በመረዳት ደህንነት ሊሰማቸው ስለሚችል ለዚህ ነው ነገሮችን ቀድሜ በግልፅ የምነግራቸው፡፡ ይህንንም በመረዳት ሁሉም ነገር በእኔ ቁጥጥር ስር እንደሆነ እንዲያውቁት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ይህንን ነገር ተናግሬው ነበር፡፡ አልተናገርኩም?

"ነገር ግን እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ አሁንም እደግመዋለሁ፣ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ተስፋ ለመቁረጥ ሁኔታው እጅግ ስለሚያስገድድ በዚህ የተስፋ መቁረጥ ወቅት ዲያቢሎስ ብዙዎችን ነጥቆ ይወስዳል፡፡

"በምድር የምትቀሩ ሁሉ ይህንን ልታውቁ ይገባል፣ ይህ ሁሉ አሳዛኝ መከራ አብቅቶ ሁሉም እንደገና ንፁህ ሆኖ የሚታደስበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በዚያን ጊዜ ክፉ ምንም ጉዳት ሊያመጣ አይችልም፡፡ በዚያ ወቅት ማንኛውም ክፋት የሚመነጨው ከሰው ልብ እንጂ ከአጋንንት በሚመጣ ተፅዕኖ አይሆንም፡፡ ከዚህም የተነሳ ምድርንና የሰውን ልብ የማነፃው በእሳት ይሆናል፡፡ በዚህም ወቅት በህይወት ተገኝተው የክስተቱ ተካፋይ የሚሆኑት በፍፁም ሊረሱት የማይችሉት ገጠመኝ ይሆናል፡፡

"ነገር ግን ውሎ ሲያድር ሰዎች በመሪባ ውኃ የሆነውን እንደረሱ፣ በዚህ ወቅት የሚሆነውንም ስለሚረሱት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ክፉን ከምድር በማስወገድ ምድርን ለማንፃት እገደዳለሁ፡፡

"እንደተናገርኩት አጥፊው ፕላኔት ኒብሩ እናንተ ሙሽሮቼ ከምድር እስከምትወሰዱ ድረስ አይመጣም፡፡ እናንተ ልክ እንደተወሰዳችሁ ግን በምድር ላይ ትርምስምስ ይሆናል፡፡ እናም አንዱ አገር ሌላውን ድል ለማድረግ በሚደረገው ረብሻ ሰበብ የሸርያ ማርሻል ህግ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በዚህም ወቅት እኔን የማይክድ በሰይፍ ይገደላል፡፡ የአውሬውን ምልክት የሚቀበል ደግሞ ይጠፋል፡፡ ማወቅ ያለባችሁ በነዚህ ጊዜያት እንኳን ስሜን ብትጠሩ የኔ ምህረት ገደብ ስለሌለው ምህረትን አደርጋለሁ፡፡

"ህዝቤ ተነስና ስሜን ጥራ አድንሃለሁ፡፡ ህዝቤ እኔን እመነኝ፣ በጭንቀላትህ እንኳን እመነኝ፡፡ በምድር ላይ የምትሰቃየው ስቃይ ከምትቀበለው ምልክት ጋር ሲወዳደር ምንም አይደለም፡፡

"ስለ አውሬዎቹ የጠየቅሽኝን ለመመለስ እነርሱ የሚራቡት በምድር ውስጥ ሲሆን የክፋት ቁጭታቸውን ለመወጣትና ጥፋትን ለማምጣት በትክክለኛው ሰዓት ካሉበት ይወጣሉ፡፡

"በዚያን ጊዜ በህይወት ያለው በሞተው ይቀናል፡፡ ይህ የሚሆነው ለሰው ዘር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ፍጥረታት ነው፡፡ እኔ እያንዳንዱን ፍጥረት በፍቅሬ አልወድምን? ደግሞስ በእያንዳንዱ ቀን ለሚዋኙበት ውኃ፣ ለሚበሉት ምግብና ለሙቀት ፀሐይን አልሰጠኋቸውምን? አቅርቦቴ የተትረፈረፈ ቢሆንም ነገሩ እየባሰ ሲመጣ ብዙዎች በገነት ከእኔ ጋር ተደስተው እንደሚኖሩ  ሁሉ እነርሱም ወደ እኔ መጥተው ይኖራሉ፡፡ ከሌር እኔ ሁሉንም ፍጥረታቴን እወዳለሁ፡፡ ደግሞም እመኘኝ ስቃያቸውን እንዴት ማቅለል እንደምችል አውቃለሁ፡፡

"ፍጥረታት ሁሉ በዚህ ኃጢያተኛ ትውልድ ምክንያት በመሰቃየት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ሁሉ የተከሰተው ክፉ ከመጀመሪያውም ጀምሮ ባደረገው ከፍተኛ ጥምረት ምክንያት ነው፡፡

"ኒብሩ ፕላኔት ወደ ምድር እየቀረበች ስትሄድ ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ እየተባባሱ ይሄዳሉ፡፡ ሰይጣንም የራሱን አጀንዳ በሰው ዘር ላይ በቶሎ ለመፈፀም ይሯሯጣል፡፡ የአውሬውንም ምልክት በሰዎች ላይ በግድ ለመጫን ይሞክራል፡፡ ይህ ደግሞ የቤተሰብን መከራ የሚያበዛ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ ሁኔታውንም ተቋቁመው እንዲያልፉ ጥንካሬን እሰጣቸዋለሁ፡፡ በመጨረሻውም የተዘጋጀላቸውን የአሸናፊነት አክሊል ይጭናሉ፡፡

"ሰዎች ከአሁን ወዲያ ምንም ተስፋ የለንም ብለው በቆረጡበት በዛን ጊዜ እኔ እመጣለሁ፡፡ ያን ጊዜ ነው መጥቼ ሁሉን የማድሰው፡፡ ልክ በዚያን ጊዜ፣ ጨለማው በበረታ ጊዜ፣ ህዝቁኤል በህልሙ እንዳየው እመጣለሁ፡፡

"አንዳንድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በስራ ላይ እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ፡፡ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች እንዳይበላሹ ያደረኩት ከህዝቤ ጋር ለመገናኘት ስለሚጠቅሙ ነው፡፡ ህዝቤን መልዕክት እንዲደርሰው ለማድረግ ኢንተርኔትን፣ ሬድዮንና ሌሎች የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን መጠቀሜን እቀጥላለሁ፡፡ ለዚህ ነው እነዚህ መገናኛ ብዙኃንን ሊያጠፋ የሚችለውን ኢ-ቦንብ እንዲያፈነዱ  የማልፈቅደው፡፡

ክሌርም . . . ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ?እያልኩ እየተገረምኩ ነው፡፡

"የቴክኖሎጂው መጠበቅ ጉዳይ አፖካልፕስ 10.5 (10.5 Apocalypse) በሚለው ፊልም ላይ እንዳየሽው ዓይነት ነው የሚሆነው፡፡

"ንጥቀት የመጨረሻው መጀመሪያ ይሆናል፡፡ የመነጠቅን ክስተት የሚጠብቁት ስለ መነጠቅ ጥያቄ የሚፈጥርባቸው ብቻ ሳይሆኑ ክፉ ራሱ እየጠበቀው ነው፡፡ በዚህም ክስተት ብዙ ሰዎች ስለሚጠፉ ይህንን ምክንያት በማድረግ ክፉ መዋቅሩን ለመዘርጋት ለራሱ ጥቅም ያውለዋል፡፡ ቢሆንም ይህንን ለማድረግ ጊዜ ይወስድባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለትንሽ ጊዜ ሰላም ይሆናል፡፡

"የአንቺ አገር (አሜሪካ) ሙሉ ለሙሉ አትወድምም፡፡ የመሬት መሸራተት፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የግዙፍ መሬቶች ቦታ መልቀቅ፣ እንዲሁም የሃገራት መከፈል የሚሆነው በመጨረሻው ነው፡፡ በዚህ መሃከል በአሜሪካ ምድር ላይ ጦርነት ይከሄዳል፡፡ ስለ ማያሚ ነግሬሻለሁ፡፡ እኔ የነገርኩሽ ትክክል ስለሆነ የሌላውን ድምፅ አትስሚ፡፡

"አሁን እንኳን ራሺያ አገራችሁን ለመምታት እቅድ እያወጣች ትገኛለች፡፡ በዚህ ወቅት ራሽያኖች በአሜሪካ ምድር ላይ እያደቡና እየቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገውን ነገር በአሜሪካ ምድር ላይ በየቦታው ደብቀው አስቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም የጦር መሳሪያዎችን በየጫካው ደብቀዋል፡፡ ከባድና ሌሎች የጦር መሳሪያዎቻቸውን ወደ አሜሪካ ለማስገባት መግቢያ በሮች በመሬት ውስጥ ይከፈታሉ፡፡ የሚካሄደው ጦርነት በአብዛኛው እንደተለመደው ዓይነት ነው፡፡

ክሌርም እንዲህ በማለት ጠየቀች . . . የኒውዮርክ ከተማ ይመታል ወይስ በሱናሚ ነው የሚጥለቀለቀው?

"አዎን ይመታል"

ክሌር . . . ታዲያ ስለ ሱናሜና ስለ መሬት መንቀጥቀጥ የሚነገረውስ ሁሉ ?

"ከተማው በቦንብ ከተመታ በኋላ የተረፈው ደግሞ በውኃ ውስጥ ይሰምጣል፡፡ በእውነቱ ከሆነ ሁለቱም በአንድ ጊዜ የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው፡፡ ሁለቱም በአንዴ"

ክሌር . . . ኢየሱስ ምንም የማያውቁትም ሁሉ?

"አዎ የኔ ውድ ምንም የማያውቁት ሁሉ፡፡ ክሌር ይህንን አስታውሺ አንቺ ከምታስቢው በላይ እወዳቸዋለሁ፡፡ እናም ቶሎ በምህረቴ እወስዳቸዋለሁ፡፡ በምድር የሚቀሩት ናቸው ምድር እንደ ገሃነም በሆነችበት ሁኔታ ውስጥ የሚቆዩት፡፡

"እንዳየሽው ኮርያኖችና ራሽያኖች በሁሉ ቦታ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም ምልምል አሜሪካን ሙስሊሞች ከዳተኞች ይሆናሉ፡፡ ሰዎች የራሳቸው ዜጎች እንኳን ስለሚከዷቸው በሰው ልጆች ላይ እምነት ያጣሉ፡፡

"እነዚህ የተመለመሉት ሰዎች ሴቶችን፣ ወንዶችንና ህፃናትን በአላህ ሥም በመግደላቸው ጥሩ ሥራ እንደሰሩ እንዲያምኑ ተደርገዋል፡፡ እነዚህም በራስ ወዳድ ሰዎች ምክንያት ያሳለፉትን ከባድ ህይወትና የፈጠረባቸውን ንዴት ማብረጃ አድርገው በመቁጠር የሰው ልጆችን የመበቀያ መንገድ አድርገው ይወስዱታል፡፡ በበታችነት መታየታቸው ስላደነዘዛቸው ይህንን የመግደል ጥማታቸውን በኃይል ካልሆነ በቀር ማንም ሊያስቆማቸው የሚችል የለም፡፡

"ይህም ቢሆን ግን ለበአል ያልሰገዱና በህይወት የሚቀሩ እዚህም እዛም አሉኝ፡፡ እነዚህንም እኔ እጠብቃቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን መሰቃየታቸው አይቀሬ ነው፡፡ በእሳት ውስጥ በማለፍ ይፈተናሉ፡፡ እናም ስመጣ ዋጋ ያላቸው ሆነው አገኛቸዋለሁ፡፡ እነዚህ ቅሬታዎች ከሰው ልጆች በጥቂት መቶኛ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የአንቺ ቤተሰቦች አሉበት፡፡ አንቺ ያስተማርሻቸው ትምህርት ስለሚያሳድጋቸው ለዚህ ጊዜ ዝግጁ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ብዙ ስብራትና ብዙ ንስሐ መግባት ይሆናል፡፡

"ትተሽላቸው የምትሄጅው የሚነበበውና የሚደመጠው ሁሉ ለእነርሱ እንደ ወርቅ ማዕድን የሚቆጠር መመሪያ ይሆናቸዋል፡፡ ነገር ግን መንፈሴም አብሯቸው ይሆናል፡፡ እናም ብዙ የሚያደርጉት ነገር ከአንቺ የተማሩትን ይሆናል፡፡ ስለሚያድጉም መራራና ፍርድ ሰጪ ከመሆን ይፈወሳሉ፡፡ ገና ማመዛዘን ሲጀምሩ ሁለታችሁም እውነተኞች እንደሆናችሁ ይረዳሉ፡፡

"ብዙ የተረዳሻቸው፣ ያወቅሻቸውና የራስሽ ሐሳብ የመሰለሹ አብዛኛዎቹ የአንቺ ሳይሆኑ የኔ ናቸው፡፡ እኔ ለአንቺ የተናገርኳቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ሐሳቦች ተመዝነውና ሚዛናቸውን ጠብቀው ከታዩ በኋላ ከእውነት ጋር ይቆጠራሉ፡፡ እውነት የአንቺ መለኪያ በመሆኑ ይህንን አጥብቀሽ ከያዝሽ አትስችም/አትቃጠይም፡፡"

ክሌር. . . ጌታ የቢጫው ድንጋይ ጉዳይስ ? /Yellow stone/ አሜሪካን የማጥፋት ችሎታ አለው፡፡

"ቢጫው ድንጋይ የሚሰራበት ንድፍ አለው፡፡ መፈንዳት ይፈነዳል፣ ፍንዳታው ግን እንደታሰበው በትልቅ መጠን አይሆንም፡፡ ይህም የኔ ሥራና ምህረት ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ከውስጡ የሚወጣው የቀለጠው ድንጋይ ወደ ውጪ የሚወጣበት ብዙ ቀዳዳዎች ስላሉት በእነዛ መውጫዎች ከመሬት ውስጥ እየወጣ ብዙ ማይሎች ይጓዛል፡፡ ልክ በውቅያኖሱ ላይ እንዳየሽው፡፡

"እኔ አሁንም ቢሆን ለአሜሪካ እቅድ አለኝ፡፡ እሰብራትና ትሁት አደርጋታለሁ፡፡ እናም እደገና አድሳታለሁ፡፡ አቆስላታለሁ ደግሞም እጠግናታለሁ፡፡ አዎ ይህ ምድር እጅግ የተበላሸ ነው፡፡ ብዙዎች በአሰቃቂ ወንጀል ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል፡፡ ቢሆንም ግን መልካም ቅሬታዎች ስላሉ ይህንን መልካምነት አበዛዋለሁ፡፡ በኃይል እሰብራትና አስተሳሰቧን እንደገና አስተካክለዋለሁ፡፡

"ለፃነት የሚዋጉ የሚሊሊሺያ ቡድኖች ይኖራሉ፡፡ እነሱ የጠላትን አካባቢ ወረው ድል ሲያደርጉ የኔን ህዝብ ይመስላሉ፡፡ እኔም ለቆሙለት ዓላማ ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ አብሬያቸው እቆማለሁ፣ እዋጋላቸዋለሁ ደግሞም እጠብቃቸዋለሁ፡፡ እነሱ ለዚች አገር የጀርባ አጥንት ይሆናሉ፡፡ አገሪቷ በታደሰች ጊዜም ከእነዚህ ብዙዎቹ ጀግኖችና ቅዱሳን ይሆናሉ፡፡"

ከሌር . . . ጌታ ይህንን ሁሉ የምትመለከተው ልክ "ሚሽን" በሚለው ፊልም ላይ እንዳለው እጅን ለጠላት ከመስጠት ይልቅ መሞት ይሻላል የሚለውን ሐሳብ የሚያንፀባርቅ ይመስለኛል፡፡

"አይ እንደሱ እንኳን አይደለም፡፡ ለቆሙለት ዓላማ እኔ ኃይል እሰጣቸዋለሁ፣ ከእነርሱም ጋር እሆናለሁ፡፡ ዙሪያውን ሁሉ ቀላል ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ ከውስጣቸውም ትልቅ ስጦታ ያላቸው ተዋጊዎች አሉኝ፡፡ በትክክለኛው ሰዓትም ሥራቸውን ይጀምራሉ፡፡ እነርሱም ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ጥበብ ይሰጣቸዋል፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሚተማመኑት እኔን እንጂ መሳሪያቸውን ስላልሆነ ነው፡፡ "

"በዚያን ጊዜም ከተሞች ለደህንነት አያስተማምኑም፡፡ ከከተሞች ይልቅ በረሃው ደህና ይሆናል፡፡ ይህም ቢሆን ግን በየጫካውና በየሸለቆው ሰውን የሚያድኑ አውሬዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ትልቅ ጥበብ የሚያስፈልገው፡፡ ብዙዎች የኔን ሥም በመጠቀም ከእነዚህ አውሬዎች ያመልጣሉ፡፡ እኔም ከግዙፎችና አድነው ከሚያጠፉ ፍጥረታት እጠብቃቸዋለሁ፡፡"

ከሌር . . . እኔ እዚህጋ አስደንጋጭ አውሬ ስለገጠማቸው ሁለት ወጣቶች እውነተኛ ታሪክ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ከእነዚህም ወጣቶች አንዱ ጌታን የተቀበለው ከአንድ ቀን በፊት ነው፡፡ ወቅቱ ፀደይ ወራት በመሆኑ እርሱና ወንድሙ ተራራ ለመውጣት ወደ ጫካው እየሄዱ እያሉ እነሱ እንደመሰላቸው አንዲት ልጇን የምትጠብቅ አውሬ ጩኸት ይሰማሉ፡፡

እናም ይህቺ አውሬ እነርሱ ካሉበት 40 ጫማ ርቀት ላይ ብቻ በመቆም አካባቢውን ሁሉ ተቆጣጥረዋለች፡፡ በዚያን ጊዜ እነርሱ ሊያደርጉ የሚችሉት አንድ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስን ሥም መጥራት ብቻ ነበር!!! ስለዚህም ሁለቱም በአንድ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም አቁሚ በማለት ተናገሩ፡፡ በዚያኑ ደቂቃ ጩኸቷን በማቆም በማጉረምረመረና አቧራውን በመበተን ቀስ ብላ በመጣችበት ተመልሳ ሄደች፡፡

ስለዚህም በእነዚህ ጊዚያት ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥም ተጠቀሙ፡፡ ምናልባትም በወቅቱ የሚኖራችሁ ምርጫ ይኸው ብቻ ነው፡፡

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ሁለት - ማርች 4 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 2 - March 4, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ ስለ የሎውስቶን /Yellowstone/ ጉዳይ መናገር አሁን ትክክለኛው ጊዜ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የዚህ ክስተት ጉዳይ ከባድ ይሆናል ብለው እየጠበቁ ነው፡፡ ሁኔታውም ይህንን ስለሚናገር ስለዚህ ነገር ማውራቱ ተገቢ ነው፡፡ ሰዎች ግን ያልተገነዘቡት ነገር ለአሜሪካ ያለኝን ፍቅርና የማሳያትን ምህረት ነው፡፡ አዎን ከሁሉም አገሮች ሁሉ የምወዳት አገር ነች፡፡ እናም ትሁት ከሆነችና ፍፁም ከታደሰች በኋላ ለእርሷ ትልቅ እቅድ አለኝ፡፡

"እርሷ ሙሽራዬን እጅግ ስለምትመስል ከታደሰች በኋላ እጠቀምባታለሁ፡፡ ፡፡ ደግሞም ህዝቤን እስራኤልን ወደ ባቢሎን በግዞት እንዲሄዱ ባደርግ እንኳን እስከመጨረሻው እንዳልጣልኳቸው ሁሉ ለአሜሪካም  የወደፊት የክብር ተስፋ ሳይኖራት ፍፁም ባዶ ላደርጋት እቅድ የለኝም፡፡ በእኔ ለሌላ ጥቅም ትውላለች፡፡

ሰዎች ሁሉ አንድ ያልገባቸው ነገር ቢኖር የአሜሪካ አጀማመር እንዴት እንደነበረ ነው፡፡ አሜሪካን የመሰረቷት ብዙ አባቶች ማሶኖች /Masons/ ሲሆኑ እነዚህም መንፈሳዊ ህይወታቸው የተበከለ ነው፡፡ ጠቅላላውን የዋሽንግተን እስቴት (የኮሎምቢያ ዲስትሪክት) የተመሰረተው በአረማዊ መመሪያ መሰረት ነው፡፡ ስለዚህም በዚያን ጊዜ የተመሰረተችበት መመሪያ ፍሬ እያፈራ ነው፡፡ የዘራችውን ነው እያጨደች ያለችው፡፡ ስለዚህም ይህንን የተበላሸና የተበከለ ነገሯን በማጥፋት የእውነተኛ አምልኳን ቅርስ በመገንባት ለዓለም የመልካም ነገር ኃይል እንድትሆን ጥቅም ላይ እንድትውል ትደረጋለች፡፡"

"ከሌር እኔ ለመግዛት ወደ ምድር ስመጣ በምድር ላይ እኩልነትንና ፍትህን አደርጋለሁ፡፡ መንግስት ሁለተኛ በዘር፣ በቀለምና በእምነትን የተነሳ የሰው ዘርን እንዲጨቁንና ዝቅ እንዲያደርግ በፍፁም አልፈቅድም፡፡ ምንም እንኳን ምድር እኔን በማወቅ ብትሞላና ክብሯ ቢሆንም የሰው ልጅ ከራስ ወዳድነትና ከስስት የተነሳ  የሌሎችን ሰዎች ነፃነት ለመንጠቅ ይነሳሳል፡፡ ይህ በፍፁም የማልፈቅደውና ሁለተኛ ሊመለስ የማይቻል ጉዳይ ነው፡፡ ስስት መልካም የሆነውን ነገር ወደ ክፉ የሚመልስ ነገር ነው፡፡

ነገር ግን እስከዚያን ጊዜ ድረስ ብዙ ውበትና ሰላም የሚታይበት ይሆናል፡፡ ትውልዱ መልካምነትን በመፈለግ ያብባል፡፡ እኔ ለሰው ልጅ እንዲሆን የምፈልገው እውነተኛው እምነት ሁሉንም ወደ ብርሃን በማውጣት የኔን ክብር ያመጣል፡፡ ደግሞም ለእኔ መኖር እንደ መተንፈስ ያህል ቀላል ይሆናል፡፡ ደስታ በቤተሰብ፣ በሰፈርና በከተሞች መካከል ይትረፈረፋል፡፡ ምክንያቱም እኔን ማወቅና ለሰው ልጆች ያለኝ ፍቅር ግልፅ ሆኖ ስለሚታይና ስለሚታወጅ ነው፡፡"

"የአሜሪካ ምዕራብ ክፍል ከሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች ሳይወድም ይቀራል፡፡ ከዚህም ሥፍራ አዲስ አስተዳደር ይነሳል፡፡ የአሜሪካ የምዕራቡና የደቡብ ምዕራቡ ክፍል በቢጫው ድንጋይ/Yellowstone/ ፍፁም እንዳይደመሰስ የማደርገው አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ግብርናና ቴክኖሎጂ የእግዚአብሔርን ፍፁም መርህ የተከተለና በመላዕክቶቼም ተግባርያዊ የሚሆን ይሆናል፡፡

"እንዲሁም እንዲያስተዳድሩ አደራ የተሰጣቸው፣ ጠቃሚና ሁሉንም ከግል ፍላጎትና ጥቅም ውጪ በእኩልነት ለመንከባከብ ብቁ  መሆናቸውን ያስመሰከሩና በራስ ወዳድነት ውስጣዊ ፍላጎት ያልተጠመዱ ለዚህ ሥራ ብቁ የሆኑ በሥራው ላይ ይሰማራሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን ሁኔታ የሮም መንግስት በመጀመሪያ ከአስማት በመነጨ የውስጥ ፍላጎት ምክንያት የመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለ ሮም በማወራ ወቅት ስለ መንግስት እያወራሁ እንጂ ስለ ቤተ ክርስቲያን እያወራሁ አይደለም፡፡"

"የቤተ ክርስቲያኔ መገንባት የሚጀምረው ከአካሉ ውስጥ እያንዳንዱን ሰፈርና ከተማ ለመምራት በተመረጡት ነው፡፡  ለልዩ መሰባሰብ ካልሆነ በቀር ቁጥራቸው ትንሽ ነው የሚሆነው፡፡ እኔም ራሴ በመገኘት አንዱ ከሌላው እንዴት በሰላምና በፍቅር እንደሚኖር አዳዲስ መረዳቶችንና መገለጦችን የማካፍልበት ነው፡፡

"ይህም ቢሆን ግን ገና ከጅምሩ እኔ ካቋቋምኩት በመሸሽ ሌሎች አማራጮችን የሚፈልጉ አሉ፡፡ ይህም ጉልበት እንዳይበረከክ የሚያደርግ በምንም መርካት ያለመቻል ፍሬ ነው፡፡ አመፃውንም የሚያነሳሱ የእነዚያ አባቶች ይገኛሉ፡፡ ክሌር ከሰው ውስጥ ክፉን እስካለወጣሁ ድረስ ስግብግብነትና ኩራት በሰዎች ውስጥ ይኖራል፡፡"

"እኔ ስላዘጋጀሁት ስለ ወደፊቱ ተስፋ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ እርግጥ ነው የኔ መንግስት ወደዚህ ምድር እስኪመጣ ድረስ ረዥም፣ ጨለማና ደም የበዛበት መንገድ አለ፡፡ ነገር ግን ሁሉ ሰው እንዲያውቀው የምፈልገው የኔ መንግስት ይመጣል፡፡ አዎ ይመጣል፡፡ ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ተስፋ አለ፡፡ ሰላም  የሁለቱን ፍላጎት ባማከለ ወንድማማች ፍቅር ይመሰረታል፡፡

"ምንም እንኳን አገሮች የራሳቸው ልዩ መለያዎቻቸውን ይዘው ቢቆዩም ለሃብት ምንጭ እና ለኃይል አቅርቦት በመካከላቸው ጥልና ንትርክ አይኖርም፡፡ በቀላል አገላለፅ ይህ በፍፁም አይፈቀድም፡፡ ምንም እንኳን የሰው ተፈጥሮ በዚህ መንገድ ለመሄድ ቢያመዝንም እኔ ግን እውነተኛ ነፃነትና ፍትህን በሥራ ላይ እንዲውል አደርጋለሁ፡፡ ማንም አይናቅም፣ እንድም እንኳን፡፡ በጣም ታናናሾች እንኳን ቢሆኑም፡፡ ምክንያቱም መንፈሴ ምድርን ሁሉ ይፈትሻል፣ ያያል፣ ያልተስተካከለውን በማስተካከል ለድሆች፣ ለታናናሾችና ለተገፉት ፍትህን ያሰፍናል፡፡

የኔ አጋር በዚህ ጉዳይ ላይ አንቺም ተሳታፊ ነሽ፡፡ አንቺን የሚያስደስት ብዙ ሥራ አለኝ፡፡ ደስታሽ ከባህር እስከ ባህር ይዘረጋል፡፡ አገሮች ይከፋፈላሉ፣ ነገር ግን ርቀታቸው ግን በጣምም ብዙ አይደለም፡፡ ምናልባት አንድ ጀልባ የማትጠቀሚበት ርቀት ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም የአየር ንብረት፣ የባህልና የእንዱስትሪ ልዩነቶች ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም በሁለት በተከፈሉ ከተሞች መካከል የንግድ ልውውጦች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን በነዳጅ የተነሳ ሰዎች እንደገና መልሰው አይጣሉም፡፡ ምክንያቱም ምድር ከነፃች በኋላ ወዲያውኑ አዲስ የኃይል መዋቅር ይተከላል፡፡

"የመገናኛ ዘዴ ከምንጊዜውም በበለጠ ቀላል ይሆናል፡፡ የአየር መበከል ጉዳይ የቀረና ያለፈ ታሪክ ይሆናል፡፡ ፍጥረታትን ወይም ሰውን የሚያጠፋ ነገር ማንም እንዲያከናውን አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሰዎች ከሞኝነታቸው የተነሳ ይህንን ውብና ቆንጆ ህይወታቸውን በመጣል ይጫወቱበታል፡፡ እኔም ይህንን እንዲያጠራቅሙት፣ አንድ ላይ እንዲያስሩትና ምናልባትም ሁለተኛ ተመልሰው በዚች ምድር ላይ እንዳይኖሩባት እፈቅድላቸዋለሁ፡፡

(ክሌር) ጌታዬ ስለ ኤሊያኖች ጠቅላላ አጀንዳ /የወደቁ መላእክቶች/ ምን እንደሆነ በደንብ እንዲገባኝና አንተ ስለእነርሱ ምን ለማድረግ እንዳሰብክ ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡

"እነሱ የፈለሰፉትና በእጃቸው የሚገኘው ቴክኖሎጂ የተጣመመ፣ የመጨረሻውን ጭካኔ የያዘና አስቀያሚ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የተደረገው ከስስት፣ ከጥላቻ፣ ለስልጣን ባለ መስገብገብና ለመልካም ነገር ሁሉ ግድየለሽ ከመሆን ከውስጥ ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን አንዱም ሳይቀር በጠቅላላ ከምድረ ገፅ እጠርገዋለሁ፡፡ እነዚህ አታላይ ኢጋንንቶችና የተጣመሙ ቴክኖሎጂስቶቻቸው ህይወትን መፍጠር እንደሚችሉ ራሳቸውን ከእኔ ጋር ለማወዳደር በመሞከር ዓለምን ለማሳመን የሚሞክሩት ከአሁን ወዲያ አይኖርም፡፡ የእነሱ ችሎታ ህይወትን ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡

በፈረንጆች አቆጣጠር በ2015 ዓ.ም መንግስታችሁ የተደራደረው ነገር የማይጠገን ዋጋ ያስከፍላቸዋል፡፡ ይህም ህይወታቸውን፣ ነፍሳቸውንና ዘራቸውን ነው፡፡ እንደገናም ተመልሰው ወደ ስልጣን መምጣት አይችሉም፡፡ ዓለም ሁሉ ወደታች ተገልብጦ ክፉ ሁሉ ከውስጧ ይደፋል፡፡ ይህንንም እኔ ስመጣ አየዋለሁ፡፡ እኔ ከመምጣቴ በፊት ግን የሶስት ቀን ጨለማ ይሆናል፡፡ ይህ ጊዜ የሰው ልጆች ሁሉ ፍፁም ተስፋ የሚቆርጡበትና ከአሁን ወዲያ ምንም ተስፋ የለም የሚሉበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ነው መላዕክቶቼን በመላክ የክፉውን ሥራ የሚያስፈፅሙትን በሙሉ፣ የሽብርና የማጥፋት አጀንዳቸውን ሁሉ እንዲገቱና እንዲያጠፉ የማደርገው፡፡"

"ኤደን ገነት በምድር ሁሉ ላይ እንደገና ተመልሳ የመጣች እስኪመስል ድረስ ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው ህይወት አዲስ የሚሆነው፡፡ በነዚያም ቀናት የሚታየው የብርሃን ፀዳል የኔን ምህረትና ክብር ያውጃል፡፡ በዚያን ጊዜ በብዙ የምድር ክፍል ሁሉ ነገር በአንድ ጊዜ እንደ አዲስ መብቀል ይጀምራል፡፡ በእውነትም አዲስ የንጋት ቀን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ክፉ ከዚያን ወዲያ መግዛት የማይችልበት ስለሆነ ነው፡፡ ሰዎች ብጥብጥንና ክፋትን ቢፈልጉም እንኳን አያገኙትም፡፡

(ክሌር) ወደ ቅድስቲቱ ከተማ መግባት የማይችሉት - ዝሙትን የሚፈፅሙ፣ ውሸታሞች፣ ሌቦችና የመሳሰሉትስ?

"በተዛባ ህይወት ውስጥ የሚኖሩትን መልሶ ለማቋቋም ብዙ ሙከራዎች ይደረጋሉ፡፡ ለመስተካከል ለሚፈልጉት ፍቅሬ፣ ደግነቴና ምህረቴ ያነፃቸዋል ደግሞም ይፈወሳሉ፡፡ አዲስን ህይወት እንዲኖሩ የሚረዳቸውን ምንም ነገር አልሰጣቸውም፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን በዛን ጊዜ እንኳን ብዙዎች የዱሮ ነገራቸውን እንዳለ ይዘውታል፡፡ አንድን ነገር የሚያደርጉትም በዱሮው መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም በመጨረሻውም መቀጣታቸው አይቀርም፡፡ ክፉ ሰዎች ክፋታቸውን እንዲያበዙ በእኔ አስተዳደር አልፈቅድም፡፡ ስለዚህም ትክክልና መልካም የሆነውን የሚከተሉትን ከማበላሸታቸው በፊት እንዲያቆሙ ይደረጋሉ፡፡"

"መጓጓዣዎች ለኃብታሞች ብቻ መሆኑ ከዚያን ጊዜ በኋላ ያበቃለት ጉዳይ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሰው ያሰበውን ለማከናወን የሚበቃውን ያህል ለማግኘት የሚያስችል እኩል መብት ይኖረዋል፡፡ በቀደመው ጊዜ ውጤታማ የነበሩና ህጌን የጠበቁ፣ ከመወለዳቸው ጀምሮ እንዲሰሩ የተመደበላቸውን ሥራ ሊፈፅሙ የተነሱትን ሌሎችን ለማሳደግ ሥፍራ ይሰጣቸዋል፡፡"

"በእኔ መንግስት ውስጥ እንቅፋት፣ ፖቲካ፣ አድልኦ፣ ጉቦና የመሳሰሉት እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ ሁሉም የራሱ ድርሻና ደስተኛ ህይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን ያህል ይኖረዋል፡፡ ታያላችሁ ኮሚኒዝም ይህንን ተግባርያዊ ለማድረግ ሐሳብ ነበረው፡፡ ነገር ግን ከሰው ልጅ የተበላሸ ተፈጥሮ ምክንያት ሊሰራ አልቻለም፡፡ ከእኔ ህግና ስርዓት ውጪ እንደዚህ ዓይነቱ

ሊያብብ፣ ሊያድግና ሊቀጥል አይችልም፡፡ የሰው ልጅ ምንጊዜም ራስ ወዳድነት ያጠቃዋል፡፡ ስለዚህም ኃይል ያላቸውና ሌላ የሰራውን ለመስረቅ የሚፈልጉ ውጤታማ የሆነውን ሰው ጎትተው ወደታች ይጥሉታል፡፡"

"እነዚህን ጠቃሚ ጉዳዮች ለብዙዎችን በመንገር ነው ተስፋ እንዳለ በመንገር ልረዳቸው የምፈልገው፡፡ ምክንያቱም ለሰው ልጆች የመጣውን የጨለማ ጊዜ ወደኋላ ሳይመለሱ በፅናት ተቋቁመው እንዲያልፉት ነው፡፡ "

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ሦስትና አራት - ማርች 5 ቀን 2015 ዓ.ም/

## What is to come after the rapture event 3&4 - March 5, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ.... " ልብሽን በቅርብ እያደመጥኩት ነበር፡፡ በልብሽ ከሌላ ዓለም መጡ ስለተባሉ ፍጥረታት ማለትም ስለ ኤልያንስ /ET'S/ ይህም በብዙ ዓይነት መልክ ስለተገለጡት የኤጋንንት ዓይነቶች እያሰብሽ ነበር፡፡ እናም ክሌር ስለዚህ ነገር ልነግርሽ ይገባል፡፡ አንዳቸውም መልካም አይደሉም፡፡ ሁሉም የወደቁ መላዕክቶች ናቸው፡፡ እየሰሩ ያሉትም እኔንና የሰው ልጆችን በመቃወም ነው፡፡ አንዳንዶቹ መልካም ገፅታ እንዳላቸው ለማሳመን እየሞከሩ ነው፡፡ ነገር ግን አትሞኚ፡፡ አጀንዳቸው በጣም ወደ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ከሰዎች ጋር በመግጠም ትጥቅ ማስፈታት ነው፡፡

"እነዚህኛዎቹ ግራጫ መልክ ካላቸው እጅግ አደገኞች ናቸው፡፡ ስለዚህ ነገር ማውራት እንዴት እጠላለሁ፡፡ ቢሆንም ግን ይህንን ነገር ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም፡፡

"እያንዳንዳቸው እጅግ ክፉዎች ናቸው፡፡ ህዝቤን የበለጠ ቅዱስና ጠንካራ ለማድረግ ከምጠቀምባቸው በስተቀር አንድም መልካም ነገር ከእነርሱ አይገኝም፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ለእኔ ሎሌዎቼ ናቸው፡፡ በራሳቸው ለብቻቸው የሚሰሩ ቢመስሉም ነገር ግን መፈፀም የያዙት ከጥንት ጀምሮ እንዲያከናውኑ የታቀደባቸውን ነው፡፡

"የሚመጡት በተለያየ ዓይነት ቅርፅና መጠን ነው፡፡ እንዲሁም የሚጠቀሙበት መጓጓዣ አንዱ ከሌላው ይለያል፡፡ እናንተ እንዳሰባችሁት በፊኒክስና በአሪዞና ታይቶ ለብዙ ጊዜ የቆየው ይህ መጓጓዣ ኒብሩ ከሚባለው ፕላኔት በመምጣት ምድሪቱን ለመመልከትና ለማጥናት ቆይታ ያደረገ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ይህ የመንግስት እጅ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ነው በቦታው ላይ ብዙ ቢቆዩም እንኳን ወታደራዊ ኃይሉ ጣልቃ ያልገባው፡፡

"ህዝቡ ግን አሁንም ጉዳዩ ምን እንደሆነ ትክክለኛውን አያውቅም ፡፡ የተሰጠው መረጃ የተሳሳተ መረጃ ነው፡፡ እነርሱ(ET'S) በጣም ተንኮለኞች በመሆናቸው የሰውን ደካማ ጎን በመጠቀም ለራሳቸው ጥቅም ያውሉታል፡፡ እነዚህ ፍጥረታት መታመን እንደሌለባቸው ሰዎች ባለማወቅና ባለማመዛዘን በነፃነትና በደስታ ይቀበሏቸዋል፡፡ እነዚህም ግራጫዎቹን ለማጣጣል ቢሞክሩም ዋናው ኃሳባቸው ይህንን ዕድል በመጠቀም ምንም የማይጎዱ እንደሆኑ ሰዎችን ለማሳመን ነው፡፡

"በቁጥርና በዓይነት ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ በዚህም ሰዎችን ግራ ለማጋባት አስችሏቸዋል፡፡ እነዚህ ክፉዎች ምንም እንኳን ምድርን ለማጥፋት አቅሙ ቢኖራቸውም ማስታወስ ያለባችሁ ግን እነርሱ ካቴና የታሰረባቸው ውሾች ናቸው፡፡ ስለዚህም ይህንን ለማድረግ ፈቃድ አልተሰጣቸውም፡፡ ክሌር እኔ ምድርን እወዳታለሁ፡፡ እርሷ ቆንጆና የኔ ድንቅ የፈጠራ ሥራዬ ናት፡፡ እናም እንድትጠፋ አልፈቅድም፡፡

ክሌር. . . ነገር ግን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የተባለውስ ?

"በልቤ እንዳለው ራዕይ ለውጥን ወዲያው አደርጋለሁ፡፡ ሁሉም ሰው የጌታን ክብር ያያል፡፡ የነበረ እንደነበረ አይቀጥልም፣ ሁሉ አዲስ ይሆናል፡፡"

ክሌር. . . በባህር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትስ?

"በሁሉም ሥፍራ ሐይቅ ይኖራል፡፡ ከዚህ በኋላ ሁከትና ብጥብጥ የለም ስለዚህም የሁከት አካባቢዎችና ሁኔታዎች አይኖሩም፡፡ ምክንያቱም ከአሁን ወዲያ አመፃ በሰው ልጆች መካከል አይሰራምና ነው፡፡ ሁሉ ነገር በደህና ሁኔታ በገነት የአትክልት ሥፍራ እንደሆነው ይሆናል፡፡

"ሰዎች ማዕድናትና ለማውጣት ይቆፍራሉ፡፡ ነገር ግን የምድር ከርስን በሚጎዳ መልኩ አይሆንም፡፡ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው እያንዳንዱ ብረትና አስፈላጊ ነገር ሁሉ ይቀርብለታል፡፡ በልብ የታሰበና የተቀረፀ ፕሮጀክት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ የሚውል ይሆናል፡፡

"ወራቶች እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር የምናገረውን ወደ ማመን እየመጣሽ ነው፡፡ ምን ያህል በግልፅ ትሰሚኝ እንደነበር፣ ነገር ግን እኔ እንደምናገርሽ ምን ያህል እንዳላስተዋልሽ ብታውቂ በጣም ትደነግጪ ነበር፡፡ ነገር ግን የኔ ውድ በየጊዜው ንስሐ በመግባትሽና እንዲሁም በእኔ በመታመንሽ ብዙ ተጉዘሽ እዚህ ደርሰሻል፡፡

ክሌር. . . ጌታዬ አመሰግናለሁ!

"እሺ ስለ ቢጫው ድንጋይ/Yellw stone/ ጉዳይ ደግሞ የኔ አንዱ የምህረት ክፍል መሆኑን እገልፅልሻለሁ።፡፡ እንዲሁም የክርስቲያኖች ፀሎት ሰይጣን ምድርን ድምጥማጧን ለማጥፋት እንዳሰበው እንዳይሆንና ጉዳቱ መጠነኛ እንዲሆን አስተዋፅዎ አድርጓል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፣ የክርስቲያኑ ፀሎት በሚድኑትና በሚነጠቁት ሰዎች ላይ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ዘመኑ ዝም የሚባልበት አይደለም፡፡ በአሁኑ ዘመን ዝም ማለት ሞትን ያስከትላል ፡፡ አሁን ዘመኑ ጣራ ላይ ወጥቶ ንጉሣችሁ ሊመጣ ነው!!! ንጉሣችሁ ሊመጣ ነው!!! በማለት የሚጮህበት ጊዜ ነው፡፡

"ፕላኔት X (ኤክስ) የተባለችው ወደ ምድር ቀርባ በታየች ጊዜ ፣ በዚያን ጊዜ የሰው ልጆች ምንም ማድረግ የማይችሉበት ጊዜ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የመትረፋችሁ ጉዳይ በፍፁም አጋጣሚ ላይ ይወሰናል፡፡ በእርግጥ የኔ ምህረት እንዳለ ሆኖ፡፡ ነገር ግን የኔን ምህረት የሚያገኙት እጅግ ጥቂቶች ናቸው፡፡

"ነገር ግን በዓለቶች፣ በንቃቃትና በሸለቆ ውስጥ በመሆን ከዚያ ጥፋት የተረፉትን ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ መንገድ ጥበቃ የማደርግላቸውና የሚያስፈልጋቸውን የማቀርብላቸው እኔ ነኝ፡፡

"በዚያን ጊዜ መንፈሳዊ  ህይወታቸው በእጥፍ ያብባል፡፡ ምክንያቱም የሚሆነው ነገር ሁሉ በእኔ አቅርቦት ላይ የተደገፈ ስለሆነ ነው፡፡ ወደ እኔ ፊታቸውን ፍፁም ለመለሱት ትንሹ ምግብ ይባዛላቸዋል፣ የውኃ አቅርቦት፣ ፈውስና ማንኛውንም ዓይነት ጥበቃ ከእኔ ያገኛሉ፡፡

"የመከራው ዘመን አብቅቶ እኔ በምመለስበት ጊዜ እንደ ወርቅና እንደ ብር ነጥረው እንደ ቅዱሳኔ በመንግስቴ ውስጥ ያበራሉ፡፡ እኔ የመረጥኳቸው ለዚህ ጊዜ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ አሁን ካሉበት ህይወት የበለጠ ክፉ ነገር ይከሰታል ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

"አንዳንዶቹ ተዘጋጅተዋል፣ አንዳንዶቹ ግን ገና ክርስቲያን አልሆኑም፡፡ ምንም እንኳን በልባቸው ድምፄን ቢሰሙም በቤተክርቲያን ያለው ህጋዊነት እንዲሁም የእነሱ ነፃነትን መውደድና ህግና ደንብን መጥላት ወደ እኔ እንዳይቀርቡ አድርጓቸዋል፡፡

"ነገር ግን እኔ በመጣሁላቸው ጊዜ ይህ ሁሉ ይቀየራል፡፡ በዚያን ጊዜ የተቀጣጠለ እምነት ይኖራል፡፡ በተለይም በጌታ ተነጠቀው ልጆቻቸውና የትዳር አጋሮቻቸው በዚህ የቀሩት እስከ ጥልቅ ልባቸው፣ እንዲሁም አጥንትና መቅኒያቸው እስኪለያይ ድረስ ጥልቅ የሆነ እምነት ይሆናል፡፡ ከዚያም ምድር እየነፃችና እየጠራች ስትሄድ ብዙዎች ለእኔ ያላቸው ፍቅርና ቅድስና እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህም እንዲያብቡና እንዲያፈኩ ያደርጋቸዋል፡፡

"ብዙዎቹ ለራሳቸው መኖርን በማቆም ከእኔ ጋር ለመኖር በማሰብ ሞትን ይመርጣሉ፡፡ ተነጥቀው በሄዱትም ይቀናሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ፍላጎታቸው የመነጨው መከራንና ችግርን ከመሸሽ ሳይሆን ለእኔ ካላቸው ፍቅርና ከእኔ ጋር ለመኖር ካደረባቸው ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ባለመሰልቸትና ወደ ኋላ ባለማለት በተዘጋጀላቸው ይቀጥላሉ፡፡

"በዚያ ወቅት ልጆቼ በእኔ ላይ በተደገፉ መጠን ታምራቶቼን ያያሉ፡፡ ነገር ግን በራሳቸው በተደገፉ መጠን ለአደጋ ይጋለጣሉ፡፡ የእኔ እጅ በደንብ የሚንቀሳቀሰው በፍፁም እምነት ውስጥ ነው፡፡ እኔ ጣልቃ በመግባት ክፍተትን መሙላት የምችለው ለሚፈልጉኝ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ለራሳቸው አቅርቦት ለሚፍጨረጨሩ የእኔ እጅ ጣልቃ ለመግባትና ለመንቀሳቀስ ታጥራለች፡፡ ስለዚህም  በእኔ ላይ መደገፋቸው እየጨመረ መሄድ አለበት፡፡ በወቅቱ ብዙ ነገሮች ተስፋ እያስቆረጣቸው ስለሚሄድ ያላቸው ምርጫ ትንሽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን በእኔ ላይ መደገፋቸውን ባፋጠኑት ቁጥር የሚፈልጉትን ለማግኘት ይቀላቸዋል፡፡

"ነገር ግን ለሽንፈት አሳልፌ አልሰጣችሁም፡፡ እንዳውም ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሲጋጠም አብሬው እንደነበርኩ ሁሉ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ ብትመለከቱ ህዝቤ እስራኤል አንድ ለአሥር በሆነ ቁጥር ጠላቶቻቸው ብልጫ

ቢኖራቸውም በጦርነት ወቅት ግን ቀኝ እጄ ስለረዳቻቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እንዴት እንደተቀዳጁ በጣም ብዙ ብዙ ምሳሌዎችን ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ እናም በእኔ ላይ እምነታችሁን እስከጣላችሁ ድረስ ሁሉን እንድታልፉት አደርጋለሁ፡፡

"በወቅቱ ከዳተኞች ስለሚኖሩ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እርስ በእርስ ልትተዋወቁ ይገባል፡፡ ብዙዎች ከእናንተ ጋር ለመቀላቀል ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን አሁን የማስጠነቅቃችሁ ምንም እንኳን ጠያቂዎቹ ከእናንተ አስቸኳይ ምላሽ የሚፈልጉም ቢሆን እኔ ሳልፈቅድ አንድም ሰው ወደ ህብረታችሁ እንዳትቀላቅሉ ነው፡፡

"አያችሁ በበጎ ፈቃዳችሁ ወይም በመልካምነታችሁ ላይ በመነሳት በቡድኑ ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ፡፡ ከዚያም ከእናንተ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ ስለሌላቸው እናንተ የምታደርጉትን ነገር ሁሉ ቦታ አይሰጡትም፡፡ እኔ ካልፈቀድኩ በቀር ማንንም ወደ ቡድኑ አታስገቡ፡፡ የሎጥን ምሳሌ በመውሰድ መንፈስ ቅዱስ እንዲመርጥላችሁ ፀልዩ፡፡ ሎጥ ወደ ቤቱ ያስገባው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩትን መላዕክቶችን ነበር፡፡ በራሳችሁ ሐሳብ መደገፋችሁን ፍፁም ጣሉት፡፡ እምነታችሁን በእኔ ላይ ብቻ አድርጉ፡፡ እኔ ብቻ ነኝ የወንዶችንና የሴቶችን እንዲሁም የህፃናትን ልብና የውስጥ ፍላጎት ምን እንደሆነ የማውቅ፡፡

"ዲያቢሎስ በተንኮልና በድብቅ የሚሰራ በመሆኑ በመልካምነታችሁ ላይ በተቃራኒው ይነሳባችኋል፡፡ ስለዚህም በእኔ ላይ ብቻ ተደገፉ፡፡ በሰው ምክኒያታዊነት ላይ አትደገፉ፡፡

"በእነዚያ ወቅቶች ውስጥ አንዳንድ ጊዜ እርስ በእርሳችሁ በመተያየት 'ጠፋን አለቀልን መሞታችን ነው' ባላችሁ ጊዜ ተስፋችሁንና እምነታችሁን በእኔ ላይ ስለጣላችሁ እኔ አስመልጣችኋለሁ፡፡ ለጠላቶቻችሁ እንዳትታዩ በማድረግና በአውሬዎቹ ላይ ማስፈራትን በማምጣት እናንተን ሊያጠፋ የመጣውን እመልሳለሁ፡፡

"ሁልጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ስሜን ለመጠቀም አትርሱ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጠላቶቻችሁ እናንተን ለመፈለግ ወደ ጫካው ሲመጡ ለጠላቶቻችሁ እንዳትታዩ በማድረግ በአጠገባችሁ እንዲያልፉ አደርጋለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እናንተን ሊፈልጉ በመጡት ላይ ፍርሃትን በመፍጠር ካላችሁበት ሥፍራ እንዲርቁ አደርጋለሁ፡፡

"ልጆቼ እናንተን ለማዳን የምጠቀምበት ብዙ ብዙ መንገዶች አሉኝ፡፡ እናንተን ለማዳን መሬት እንኳን አፈዋን ከፍታ የምትደብቅበት ጊዜ ይኖራል፡፡

"ስለዚህም በፍፁም ተስፋ እንዳትቆርጡ፡፡ በእኔ ላይ ታመኑ፡፡ እንዲሁም እኔ ድግሞ እናንተን እንደማፈቅራችሁ እምነት ይኑራችሁ፡፡ በእናንተ ላይ ካለኝ ፍቅር የተነሳ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እንደምሆን እመኑ፡፡ የደሙን ኃይል ይኸውም የኔን የደም ኃይል ጥሩ፡፡ እንዲህም ብላችሁ አውጁ "የኢየሱስ ደም ሸፍነን፣ ጠብቀን፣ ለጠላቶቻችን እንዳንታይ አድርገን፣ ከልለን፡፡"

"ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን በደንብ ካዘጋጁትና በእኔ ላይ ታምነው ምንም ካላዘጋጁት መካከል ምንም ብልጫ አይኖርም፡፡ ከሌር ለወደፊቱ ምንም ቅድመ ዝግጅት እንዳታደርጊ የከለከልኩሽ አንዱ ምክንያት ይህ ነው፡፡ እኔ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አቀርባለሁ፡፡ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ ድምፄን በትክክል መስማትና መመሪያዬን መከተል ነው፡፡

"አንዳንድ ጊዜ አድርጉ የምላችሁ ነገር የማይመስልና ከተለመደው ውጪ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እኔ የማዛችሁ ያ ድርጊት ለእናንተ አማራጭ የሌለው የመዳን መንገድ ሊሆን ስለሚችል የአልኳችሁን ብቻ አድርጉ፡፡ ፀሎት ማንም ምንም ሊያሸንፈው የማይችል የእናንተ መሳሪያ ነው፡፡ ስትፀልዩም በልሳን ፀልዩ፡፡ በልሳን ስትፀልዩ ዓለም በራሱ ካሰለጠናችሁ አስተሳሰብና አመለካከት በላይ በጥበብ አይምሮአችሁን እንዲያነቃቃ ያደርጋል፡፡ የኔ መንገድ እንደ ዓለም መንገድ አይደለም፡፡

"ፀሎት የእናንተ ትልቅ መሳሪያ ነው፡፡ ከፀለያችሁም በኋላ የምናገረውን በደንብ አዳምጡ፡፡ መመሪያ፤ ራዕይ፣ የፀሎት መልስና መረዳትን በውስጣችሁ ስለምሰጣችሁ ከእኔ ጠብቁ፡፡ የምናገራችሁን ነገር በጊዜውና በወቅቱ ለመረዳት ተለማመዱ፡፡ ምክንያቱም እኔ የምሰጣችሁን ጥበብ በጊዜው መቀበል ከአደጋ ያድናል፡፡ እኔ እንዴት እንደምትከናወኑ፣ እንደምትሄዱ፣ አስተምራችኋለሁ ደግሞም እመራችኋለሁ፡፡

"መፅሐፍ ቅዱስን በማንበብ በቃሉ መገለጥ /ሬማ/ ወደ አይምሯችሁ በሚመጣው ቃል ተጠቀሙ፡፡ እኔ የማስታውቃችሁን ነገር ምንም ሳያመልጣችሁ ተጠንቅቃችሁ አድምጡ፡፡ እኔ በተለያየ ዓይነት መንገድ እናገራለሁ እናንተ ብቻ በትጋት ነቅታችሁ ጠብቁ፡፡ ደግሞም ከፊታችሁ አደጋ እንዳለ ለማስጠንቀቅ ምልክቶችንና ስዕሎችን እልክላችኋለሁ፡፡

"የኔ ልጆች በፍቅር እወዳችኋለሁ፡፡ ከምትወዷቸው ጋር እናንተንም አብሬ ለመውሰድ ብችል በወሰድኳችሁ ነበር፣ አዎ እችል ነበር፡፡ ነገር ግን በራሳችሁ ምክንያት እንቢተኛ ሆናችሁ፡፡ አሁን ግን ልባችሁንንና አይምሯችሁን በመክፈት፣ እንቢ ሳትሉ፣ ሳትጠራጠሩና በሙሉ እምነት እኔን ለመቀበል መማር አለባችሁ፡፡

"ምንም ነገር መስራት ያቆመ በመሰላችሁ ጊዜ በመደጋገም እንዲህ በሉ .... 'ኢየሱስ አምንሃለሁ'፡፡ ይህንንም የምትሉት እኔ አጠገባችሁ እንዳለሁና እንደምሰማችሁ በዓይነ ህሊናችሁ በማሰብ ይሁን፡፡ በዚህ ጊዜ የውስጥ ሰውነታችሁ በእርግጠኝነት ይሞላል፡፡ ይህ እርግጠኝነታችሁ በእኔ ላይ ያላችሁን እምነት የሚገልጥ ስለሆነ በጉዳያችሁ ላይ ለመንቀሳቀስ ይገፋፋኛል፡፡

"ይህንን ሁልጊዜ አስታውሱ በምንም ነገር ላይ እርዳታ የሚሰጣችሁ ብጠፋ እኔ አለሁላችሁ፡፡ ደግሞ ይህንን አስታውሱ እናንተ፣ ከአብ፣ ከእኔና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ላይ ሆነን ከየትኛውም በምድር ላይ ካለ ኃይል የኛ ድምር ኃይል የላቀ ነው፡፡
እናንተና እኔ ሆነን ብልጫ ያለን ነን፡፡ አንዳንድ ጊዜም እንዲረዷችሁ መላዕክቶቼን ልኬ ሲረዷችሁ ትመለከታላችሁ፡፡ ለዚህም አይናችሁን እከፍታለሁ እመኑ፡፡
"እመኑ"

## ንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት አምስት -ማርች 6 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 5 - March 6, 2015

ኢየሱስ እንዲህ ይላል .... "ከእናንተ ጋር አብሬ እንድሆን የምትፈልጉ ከሆነ ትህትና፣ ራስን መግዛት፣ ታማኝነትና የበጎ ፈቃድ ሥራ እጅግ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ በፊት በራሳችሁ መንገድ ሌሎችን ስትመሩ ከነበራችሁ አሁን በዛ መንገድ መቀጠል አትችሉም፡፡ ነገር ግን በራሳችሁ እርግጠኞች ካልሆናችሁና በአሁኑ ጊዜ ከማንኛውም በበለጠ እኔ እንደማስፈልጋችሁ ካወቃችሁ እናንተ በመምራት ትልቃላችሁ፡፡

"ልጆቼ በዓለም የተማራችሁት የመሪነት ዘዴ አሁን ለተሰጣችሁ አገልግሎት በፍፁም ተስማሚ አይደለም፡፡ እኔ ጥበቃ ላደርግላቸው የምችለው ራሳቸውን ዝቅ ለሚያደርጉት ነው፡፡ ነገር ግን ለሁሉም መልስ ለማግኘት ወዲያና ወዲህ ለሚፈነጨው ለእርሱ ጥፋት ይገጥመዋል፡፡ እኔ በእናንተ እምነቴን ልጥል የምችለው ከጓደኛም ሆነ ከቤተሰብ እስካሁን የተማራችሁት ነገር ምንም ዋጋ እንደሌለው ስታውቁና ከዚህ አስተሳሰብ ሰብራችሁ ስትወጡ ነው፡፡ በእናንተ እምነት የሚኖረኝ ያላችሁን ኩራትና ዕብሪት በመጣል በፊቴ ተደፍታችሁ ይቅርታ ስትጠይቁኝ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው በበራችሁ ላይ የመጣውን ፈተና እንድትወጡና በሥጋም ሆነ በነፍስ በህይወት እንድትኖሩ ለማድረግ ሥራ የምጀምረው፡፡

"በእኔ ፊት ራሳችሁን ብታዋርዱ በእርግጠኝነት ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ ምንም እንኳን ኩራትና ዕብሪታችሁ ከእናንተ ጋር ለብዙ ጊዜ የቆየ ቢሆንም ይህ ግን ኃጢያት መሆኑን አውቃችሁ ከዚህ ነፃ ለመሆን ከፈለጋችሁ ከእናንተ ጋር በመሆን እሰራለሁ፡፡ ነገር ግን አሁንም በራሳችሁ ጥበብ ለመቀጠል ብትፈልጉ እኔ ልረዳችሁ የምችለው ጥቂት ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ከራሳችሁ በበለጠ በተቻለ መጠን ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

"እኔ ወደ ምድር በመጣሁ ጊዜ እራሴን በሌሎች ላይ ጌታ ለማድረግ አልመጣሁም፡፡ ነገር ግን ራሴን ዝቅ አድርጌ የደቀመዛሙርቶቼን እግር አጠብኩ፡፡ መሪ ለመሆን የሚገባው እንደዚህ ዓይነቱ ነው፡፡ መሪ የሆነ ሰው የሌሎቹን ፍላጎት ማስቀደም አለበት፡፡

"አንዳንዶቻችሁ የመጣችሁት ትሁት ከሆነ ቤተሰብ ስለሆነ ስለዚህ ነገር ስናገር በደንብ ይገባችኋል፡፡ አንዳንዶቻችሁ ግን ለዚህ ምሳሌ የሚሆናችሁ ሰው ስላላገኛችሁ ትሁት ለመሆን ትግል ይገጥማችኋል፡፡ ይህ ግን እንናተን ተስፋ ሊያስቆርጣችሁ አይገባም፡፡ እኔ እናንተን እንደገና ለመሥራት በትጋት እሰራለሁ፡፡ ለዕብሪታችሁ አሳልፌ አልሰጣችሁም፡፡ እናንተ በእውነት መለወጥ ከፈለጋችሁ እኔ አስተምራችኋለሁ፣ እመራችኋለሁ፡፡ እናንተና የእናንተ የሆኑት ህይወታችሁ የሚተርፈው በእኔና እኔ በማሳያችሁ መንገድ ላይ ፍፁም ስትደገፉ ብቻ ነው፡፡ ራሳቸውን በፊቴ ባዋረዱትና በእኔ ላይ ለተደገፉት ሁልጊዜ መውጫ መንገድ አዘጋጃለሁ፡፡

"ተራሮች ቢንቀጠቀጡ፣ ባህር ቢናወጥ እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፣ በፍፁም አልተዋችሁም፡፡ ሐቀኛ የሆኑትን በፍቅራቸውና በትህትናቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡ ትህትናቸው ደግሞ የእውነት መሆኑንና ያለመሆኑን መለየት ትችላላችሁ፡፡ ንዴት፣ ሐሜት፣ ሁከትን የሚፈጥሩና በመንገዳችሁ ላይ የሚቆሙ እነዚህ ለመውደቅ መንገድ ከፋቾች ናቸው፡፡

"ከሁሉ በላይ ህይወታችሁን ለእኔ በመስጠት ነፍሳችሁን ጠብቋት፡፡ ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያስገባው ራስን ዝቅ የማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ በራሳችሁ ህይወትን መምራት አለመቻላችሁን ማወቅ ነው፡፡ ይህም ኃጢያት መሥራታችሁን፣ ሌሎችን መጉዳታችሁን፣ በህይወታችሁ ትክክለኛና ያልበሰለ ውሳኔ መወሰናችሁንና ማክበርና መደገፍ ያለባችሁን ችላ ማለታችሁን ማወቃችሁ ነው፡፡ እንዲሁመ መስማት ያለባችሁን በተለይም ሽማግሌዎችን ያለመስማታችሁ ነው፡፡"

"ስለዚህም ይህንን የተመሰቃቀለ ህይወታችሁን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲህ በማለት ለእኔ አሳልፋችሁ መስጠት አለባችሁ፡፡ "ጌታ ሆይ እኔ ደጋግሜ ኃጢያትን ሰርቻለሁ፡፡ እኔ ለአንተ የምገባ አይደለሁም፡፡ ለዚህም ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ፡፡ ራስ ወዳድነትና ዕብሪት ስለተሞላው ህይወቴ ንስሐ እገባለሁ፡፡ ይቅር በለኝ፡፡ በደምህ አጥበህ አንፃኝ፡፡ ውስጤ ካለው ክፉ ነፃ አውጣኝ፡፡ እኔ አዲስ የሆነውን ማንነት ይኸውም የአንተን መልክ የሚመስለውን ለመሆን እንደገና መወለድ እፈልጋለሁ፡፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ህይወቴን አሳልፌ ለአንተ እሰጣለሁ፡፡ ተቀበለኝ፡፡ ምራኝ ደግሞም አድነኝ፡፡"

"ከዚህ ፀሎት በተጨማሪ እኔ ያስተማርኩትን የአባታችን ሆይ ፀሎት ፀልዩ፡፡ ከዚያም በእናንተ ፀባይ ላይ ቅፅበታዊ ማስተካከያ ወይም ለውጥ እንደማመጣ ተጠባበቁ፡፡

"እኔ በልቤ የዋህና ትሁት ስለሆንኩ ከእኔ ተማሩ፡፡ እኔ እጅግ ብዙ የፍቅር ደብዳቤዎችን ትቼላችኋለሁ፡፡ እነርሱን አንብቡ፣ የተናገርኩትንም እመኑ፣ በልባችሁ ውስጥም ሥር እንዲሰድ ፍቀዱ፡፡ እኔን ከማወቅና ከመውደድ ከሚመጣ ደስታ ጋር የሚወዳደር ምንም ሌላ ደስታ የለም፡፡ አሁን ባላችሁበት ደረጃ ባይገባችሁም፣ እኔ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር ማወቅ ብቻ የሚያጋጠማችሁን ፈተና ሁሉ ጥሳችሁ እንድታልፉ ይረዳችኋል፡፡ በምንም ሁኔታ ብታልፉ እኔ ቀኝ እጃችሁን ይዤ፣ እያነጋገርኳችሁና እያፅናናኋችሁ ነው፡፡ ከእኔ ፍቅር ሊለያችሁ የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡"

"ምንም"

"በምድር ቢሆን፣ ከምድር በላይ ፣ ኤሊየን ቢሆኑ፣ ሞት ቢሆን፣ ብትወድቁ እንኳን ከእኔ ምንም ሊለያችሁ አይችልም፡፡ እኔ ላነሳችሁ በአጠገባችሁ ቆሜያለሁ፡፡ ከእኔ ፍቅር ምንም ሊለያችሁ የሚችል የለም፡፡"

"ስለዚህ በምትወድቁ ጊዜ አትፍሩ፡፡ በመንገዳችሁ ስህተት ልትሰሩ እንደምትችሉ እወቁ፡፡ ልትወድቁ እንደምትችሉና እኔ ደግሞ እናንተን አንስቼ እንደገና እንደማቆማችሁ እወቁ፡፡ በምትወድቁ ጊዜ ከእኔ አትሽሹ፣ ወደ እኔ ተመለሱ እንጂ ከእኔ አትሽሹ፡፡ እንዲያውም ወደ እኔ ሩጡ፡፡ እኔ ወደ እቅፌ አስገባችኋለሁ፣ እንባችሁን አብሳለሁ፡፡ እኔ አልወቅሳችሁም፣ የምፈርድባችሁ ሰው አይደለሁም፡፡ በፍፁም፣ እኔ እወዳችኋለሁ፡፡ እኔ ገና ሳትወድቁ እንደምትወድቁ ስለማውቅ እናንተን ለማንሳት ተዘጋጅቻለሁ፡፡

"መቼም ቢሆን እንደማልጥላችሁ እወቁ፡፡ ይህንን በሙሉ እውቀት ተረዱ፡፡ የእኔ መገኘት በማይሰማችሁ ጊዜ እንኳን እናንተን ለመርዳትና ለማገዝ እንዲሁም ይቅር ልላችሁና ላድሳችሁ እዚያው አጠገባችሁ ነኝ፡፡ በዚህ እውቀት በመመርኮዝ

በእኔ ላይ ፍፁም ተደግፋችሁ ወደፊት ቀጥሉ፡፡ ከዚህ ቀን በኋላ እናንተ የራሳችሁ አይደላችሁም፡፡ ነገር ግን ልንከባከባችሁ፣ ልመራችሁና ከእኔ ጋር በመንግሰተ ሰማይ ወደ ክብር ላመጣችሁ የኔ ናችሁ፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር ስለሆንኩ ምንም አትፍሩ፡፡ እኔ ባለሁበት በዛ እንድትሆኑ እኔ ሥፍራ ላዘጋጅላችሁ ከእናንተ ቀድሜ ሄጃለሁና፡፡ እኔና እናንተ ለዘላለም አብረን የምንሆንበትና የእናንተ ብቻ የሆነ ልዩ ሥፍራ ተዘጋጅቶላችኋል፡፡ እኔ እንደ ሰው ብቻ የምወዳችሁ ሰው አይደለሁም፡፡

"እኔ አምላካችሁ ነኝ፡፡ ፍቅሬም መጨረሻ የማይገኝለት ነው፡፡ ምክንያቱም ለፍቅሬ መጨረሻ የለውም፡፡ ለዘላለም የእናንተው ነኝ፡፤ አሁን ደግሞ እናንተም ለዘላለም የኔ ናችሁ፡፡"

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ስድስት - ማርች 8 ቀን 2015 ዓ. ም

## What is to come after the raprure event 6 - March 8, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "እስቲ ስለ እሳተ ጎሞራ እናውራ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቢጫው ድንጋይ /Yellowstone/ እሳተ ጎሞራ የበለጠ እየተነቃቃ ነው፡፡ በዚህም የአሜሪካን አብዛኛውን ክፍል ለማጥፋት የሚችል ኃይል አለው፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን የእሳተ ጎሞራው አወጣጥ መካከለኛ እንዲሆን እንደማደርገውና ጥፋቱም የተወሰነ ብቻ እንደሚሆን ነግሬሻለሁ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ይህንን ብዙዎች አያምኑም፡፡ አብዛኛው አለም የሚጠብቀው ስሜት የሚቀሰቅስና አሳተ ጎሞራው በከፍተኛ ደረጃ ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ቀላል ነው፡፡ በእግዚአብሔር ስለማያምኑ ወይም አገራችሁን ለማዳን የማደርገውን ባለማመን ነው፡፡ ይህ አገር ደግሞ ታውቂያለሽ የእናንተ ብቻ ሳይሆን የኔም አገር ነው፡፡

ክሌር . . . ጌታ አንተን ለመቀበል እንኳን እንቢ ቢሉም ?
"ሞኞች ብቻ ናቸው እንቢ የሚሉት፡፡ ነገር ግን በአሜሪካ ብዙ ብዙ ክርስቲያኖች ምንም እንኳን ከድሮው ከፍሪማሶን /Freemason/ የአምልኮ ቤተ መቅደሳቸው ፍፁም በሆነ መልኩ ትተው ባይወጡም መንፈሴ ግን በልባቸው ከእነርሱ ጋር አለ፡፡ በተለይም ነገሮች እየተጋጋሉ በሄዱ ቁጥር ብዙዎች ከልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉ፡፡"

ክሌር . . . በዚህ ጊዜ አንድ ነገር በልቤ እያሰብኩ ሳለ . . . ጌታ አይሆንም በሚል መልክ ራሱን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ነቀነቀ፡፡ እኔም ባልተረጋጋ ሁኔታ ነገር ግን እኮ ጥሩ ነቢያቶች ሁሉ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዳለ ተናግረዋል . . .

"ክሌር ይህ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ እያንገራገርሽ ያለሽው ድንገት ልክ ባትሆኚ የሚያመጣውን ኃፍረት እያሰብሽ ነው፡፡ ይህንን ልበል እኔን በትክክል ካልሰማሽኝ የመንፈሳዊ መነቃቃት መኖር የአንቺን 'መንፈሳዊ መነቃቃት የለም' የሚለውን ትንቢት ይጋርደዋል፡፡ ልድገመውና ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት በአሜሪካ የለም፡፡

"አዝናለሁ፡፡ የሚሆነው እንደዛ ነው፡፡ የኔ አጀንዳ እንደዚያ ነው፡፡"

ክሌር. . . ከእግዚአብሔር ጋር ማን ይከራከራል?

" አንቺ ነሻ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የኔ ውድ ሁልጊዜ አንቺ ነሽ፡፡"

ክሌር. . . እኔም ሳቅሁ

"አንገተ ደንዳናዋ!! አዎ እንደዛ ነሽ፡፡"

ክሌር. . . "ጌታ ለዛ ይሆን አንገቴን የሚያመኝ?"

"ያለጥርጥር"

ክሌር. . . እሺ፣ ይህ ግን የሚሳቅበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ብዙ ነቢያቶች ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት ይኖራል ብለው ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን እኔ ሁልጊዜ መንፈሴን እመረምራለሁ፡፡ እናም አሁን እየተደነቅሁ ነው . . .

"ንስሐ ቢገቡ መጨረሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ነው?"
አዎ

"በዚህ አገር ነዋሪ ለሆኑ ሁሉ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲመለሱ ብዙ እድሎችን ሰጥቻለሁ፣ ብዙ እድሎች፡፡ ስለዚህ ነው ሌላ የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት /Revival/ በአገሪቱ ውስጥ በማድረግ እንደ ወራዳ ነገር እንዲቆጠርና እንዲናቅ ማድረግ የማልፈልገው፡፡ እነዚህ አምላካቸውን ቁሳዊ ነገር ያደረጉና ልባቸውን ያጠነከሩ ስለሆኑ ልባቸውን የሚያለሰልስ አንድ ነገር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለዚህ ነው የምጠብቀው፡፡"

ክሌር. . . የኢኮኖሚውስ ውድቀት?

"እሱም ቢሆን የሚከሰተው ከንጥቀት በኋላ ነው፡፡"

ክሌር. . . የሚደንቅ ነው !

"ወደር የሌለው የጭንቅ ጊዜ! ነገር ግን ይህ ደግሞ ምንም የሌላቸውን፣ ስለ መፅሐፍ ቅዱስና ስለትንቢት ንቀትና ውርደት የደረሰባቸውን ታናናሾችን፣ ተራ ሰዎችን ፣ አምላካቸው ብቻ ሁሉ ነገራቸው ለሆነ ጀርባን የሚሰብር ነው፡፡ እነዚህ የሚኖሩት ለእኔ እንጂ ኃብት አግኝተው ለማካበት አይደለም፡፡ ለእነርሱ እኔን ማግኘት ማለት ሁሉ ነገራቸው ነው፡፡ ስለዚህም የእነዚህን ህይወት ከዚህ በላይ አሰቃቂ ማድረግ አልፈልግም፡፡ በመሆኑም እነርሱ ከዚህ ወደ ሰማይ እስኪወሰዱ ድረስ እጠብቃለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ መዶሻው ይወድቃል!"

ክሌር. . . መዶሻ?

"አዎ የፍርዱ መዶሻ በዚህ አገር ላይ ይወድቃል፡፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ ነው የሚወድቀው፡፡ ይህ በነገራችን ላይ በእውቀት ከላቁት መሪዎች/Ruling Elites/ አጀንዳ ጋር ይስማማል፡፡ መንግስት ከሚያቀርበው ሌላ የሚበላ ምግብ ሲጠፋ ሁሉን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ለእነርሱ አመቺ ሁኔታን ይፈጠርላቸዋል፡፡

"ወደ እሳተ ገሞራው ጉዳይ ስመለስ፣ በምድሪቱ ላይ የሰው ዝውውር የሚደረግበትን፣ አደንዛዥ ዕፆች የሚዘዋወሩበትን ቦታዎች እንዲሁም የከፋ የፍትህ መጓደል በሰው ልጆች ላይ የሚከናወኑባቸውን ቦታዎች ሁሉ ኢላማ አድርጌያለሁ፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥና የእሳተ ገሞራ ክስተቶች የብዙ ሰዎች ህይወትን መቅጠፍና ብዙ ጥፋትን ያመጣል፡፡ የሰው ልጆችን ስቃይ ማየት የኔ ፈቃድ አይደለም፡፡ ነገር ግን በሰዎች ላይ የሚፈፀመውን ግፍ ምንም ልታውቁ አትችሉም፡፡ እነዚህ ቦታዎች የተገደሉ ሰዎች ደም ከምድር ወደ እኔ ከሚጮኸው ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም አልዘገይም፣ ፍትህን አመጣለሁ፡፡

"እንዲሁም እነዚህ እሳተ ገሞራዎች ከምድር በታች ወዳለው ዓለም መግቢያ መስመሮች ሲሆኑ ከገሃነም ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም ገሃነም እየሞላ ሲሄድ ምድር እየተለጠጠች ትሄዳለች፡፡ ይህ አንቺ በራስሽ ያሰብሽው የመሰለሽ ሐሳብ ከአንቺ የመነጨ ሳይሆን እኔ ራሴ እንደትረጂ ያደረግሁት ነው፡፡ ይህ ከእኔ የመጣ ሐሳብ ነው፡፡"

ክሌር . . . ጌታ ሆይ! ይህ የሚያሰቅቅ ነው፡፡

"በተጨማሪም የወደቁ መላዕክቶች ወደ ምድር በግልፅ ከመውጣታቸው በፊት እንቅስቃሴ ይጨምራል፡፡ ዓለምን ሁሉ ሊገዛ በምድር ላይ ሊመጣ ያለውን የመጨረሻውን መንግስት ለማምጣት ሁሉ ነገር እንደሚገባው ተስተካክሎ ተቀነባብሯል፡፡

"የሚመጣው መንግስት የወደቁ መላዕክቶችን በመመልመልና በየቦታው ደብቀው በማስቀመጥ ጊዜው ሲደርስ ከሚያወጧቸው ክሎኖች ጋር አንድ ላይ በማሰማራት የመንግስቱ ተቃዋሚ የሆኑትን ህብረተሰብ አድነው እንዲያጠፉ አቅደዋል፡፡ አሁን እንኳን እነዚህ ፍጥረቶች እጅግ ገጠር የሆኑ አካባቢዎች ሳይቀር ይገኛሉ፡፡ የሚጠብቁትም ወጥታችሁ ፈልጉና አጥፉ የሚላቸውን አንድ ትዕዛዝ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚቋቋመው አዲስ የዓለም መንግሰት ከእነዚህ ክሎኖች እርዳታ ውጪ ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት በፍፁም ባልቻለም ነበር፡፡

"በወቅቱ አየሩ ሁሉ በእነዚህ በወደቁ መላዕክቶች ስለሚሞላና በሰዎች መካከል በብዛት ስለሚታዩ ሰዎች እነርሱን በማየት ይደነግጣሉ፣ ወዮ በማለት ይጮሃሉ፡፡ በመጀመሪያው ጊዜያቶች ግን ምንም የማያደርጉና ገራ ገር ሆነው ይቀርባሉ፡፡ በኋላም ያለምንም ማስጠንቀቂያ 'ክፉ' የሚባሉት ምድሩን ይወሩና ጦርነት በሰማይ ይጀመራል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት አገሮችን ሁሉ ለማቀጣጠልና አንዱን የአለም አቀፍ መንግስት ለማምጣት የሚፈጥሩት ዘዴ ነው"

ክሌር . . . ጌታ ስለዚህ ነገር ራዕይ ማየት እችላለሁ?

ክሌር. . . እኔ አያለሁ ብዬ የጠበኩት ብዙ ቀለማት ያለው ነገርን ነበር፡፡ ነገር ግን ያየሁት የምድር ከባቢን አየር ማየት እስከምችለው ድረስ የብረት መልክ ያላቸው ዲስክና ሌሎች እንግዳ የሆኑ ቅርፅና መጠን ያላቸው መጓጓዣዎች አየሩን በሙሉ በክለውት ነው፡፡

"እሳተ ጎሞራና ኃጢያት የበዛባቸው ስፍራዎች ቅርብ ለቅርብ መገኘታቸው የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም፡፡ የእሳተ ጎሞራ መገኘት ከአጋንንት እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ይህም በዚያ አካባቢ ክፍት የገሃነም በር እንዳለ ያመለክታል፡፡ በሃዋይ/Hawaii/ የሆነው ሁኔታም በትክክል ይኸው ነው፡፡

"የኔ ውድ ብዙ የማታውቂው ነገር አለ፡፡ በራስሽ ግንዛቤ እንዲገባሽ ለማድረግ መሞከሩን ተይና የሰማሽውን ዝም ብለሽ ፃፊ፣ እባክሽ?"

ክሌር . . . እሺ፣ ስለዚህ የእሳተ ጎሞራ፣ አጋንታዊ እንቅስቃሴና ኃጢያት ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ማለት ነው?

"እንዲሁም ጥንቆላ፣ እንግዳ የሆነ የአምልኮ ስርዓት ማካሄድ አለበት፡፡ ይህም በአብዛኛው ሰዎችን መስዋዕት አድርጎ ማቅረብን ይጨምራል፡፡ በልጅነትሽ ያየሻቸው እነዚያ ፊልሞች ዝም ብለው ፊልሞች አይደሉም፡፡ እውነትን በመመርኮዝ የተሰሩ ናቸው፡፡ እናም ሰው መስዋዕት ሆኖ በሚቀርብበት ቦታ ሁሉ በአካባቢው ሰይጣን አብሮ እንዳለ እርግጠኛ መሆን ትችያለሽ፡፡"

ክሌር. . .  አዎ አስታውሳለሁ በፊልሙ ውስጥ የነበሩትን ኢንካዎችና ፖሊንሺያኖች

"አዎ እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆኑ ሰይጣንን የማምለኪያ ልዩ መንገድ አለው፡፡ ነገር ግን የትኛውም ቢሆን የሚወስደው ያው ወደ እርሱ ነው፡፡"

ክሌር. . . በዚህ ጊዜ ሳስብ የነበረው የወንድ ዘር በመውሰድ ጠልፈው ከወሰዷት ሴት ዘር ጋር በማገናኘት ወይም በኢንኩቤተር ውስጥ ሰው የሚፈጥሩበትን መንገድ ነበር፡፡

"በትክክል ተረድተሻል፡፡ ህይወትን እንዴት አድርገው እንደሚፈጥሩ በኢንተርኔት በበቂ ሁኔታ ተመልክተሻል፡፡"

ክሌር፡- ነገር ግን ነፍስን . . .?

"የወሰዱት ዘሩን ብቻ በመሆኑ እነርሱ በአጋንንት ሰውነት ውስጥ የሚገኙ ነፍስ አልባ ፍጥረታት ናቸው፡፡ አጋንንቶች እንደ መላዕክትና እንደ ሰው ተመሳሳይ ንድፍ /pattern/ ያላቸው ናቸው፡፡

ክሌር፡- ነገር ግን የወንድና የሴት ዘር ሲገናኝ ነፍስ ከአንተ አይደለም የምትገኘው?

"በትክክል፡፡ ስለዚህም ነፍስን አልሰጠኋቸውም፣ ከልክያቸዋለሁ፡፡ በአንፃሩ ግን በመቶዎችና በሺህዎች የሚቆጠሩ አጋንንቶች ሰውነትን እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡"

ክሌር፡- በዚህን ጊዜ የዚህ ሂደት ምን እንደሚመስል አሰብኩ

"አዎን ፣ አዎን . . ."

ክሌር፡- ስለዚህ አጋንንቶች ቅርፅ የሚይዙት ባዶ ሰውነት ሲያገኙ ነው?

"ያ ትክክል ነው"

ክሌር፡- ነገር ግን የፍጥረታቱ ወርድና ስፋት ልዩነትስ?/ inter-dimensionality/ ልክ ክብር እንዳለው ሰውነት ነው?

"የተለያየ ወርድና ስፋት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም በተለያየ ወርድና ስፋት ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የተሰሩበትን መሰረታዊ ቅርፅ/ substance/ ሳይለቁ ማለት ነው፡፡

ክሌር፡- የሚገርም ነው! ጌታ ይህ ከትንሿ ጭንቅላቴ በላይ ነው፡፡

"አውቃለሁ፡፡ ደግሞ የተባረክሽ ነሽ፡፡ ምክንያቱም ለሰውኛ ማንነትሽ በሚመጥን መልኩ በማረም እየሰማሽኝ ስላልሆነ ነው፡፡ አየሽ አዲስን ነገር የሚፈጥሩ ሰዎች በእንዲህ ዓይነት መልክ ነው የሚሰሩት፡፡ በአይምሯቸው ውስጥ አንድን ሐሳብ አኖራለሁ፡፡ ከዚያም ይሰሩትና አዲስ የሳይንስ ግኝት መጣ ማለት ነው፡፡ ሁሉም በዚህ ዓይነት መንገድ እንዲሰራ ተፈቅዶ ነው የሰው ልጅ አሁን ባለበት ከፍተኛ ደረጃ እየደረሰ ያለው፡፡ ይህ ጊዜ ግን እጅግ ወሳኝ ጊዜ ነው፡፡

ክሌር፡- "ኡሁ!

"አዎ አውቃለሁ፡፡ አየሽ ለዚህ ነው አጋንንቶች መታሰር እንጂ መጥፋት የማይችሉት፡፡ በመጨረሻውም ለዘላለም ወደ እሳቱ ባህር ይጣላሉ፡፡ ይህም ለሁልጊዜና ለዘላለም ይሆናል፡፡ አየሽ? ህይወትን ማጥፋት አይቻልም፣ ነገር ግን አንድ ቦታ ማገድ ይቻላል፡፡ እነሱ የፈጠሩትን ሰውነት ማጥፋት ይችላል፡፡ ነገር ግን በውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገውን አጋንንት ማጥፋት አይችልም፡፡ ቢያንስ ይህኛውን አማራጭ አልሰጠሁም፡፡

"መማር ያለብሽ ብዙ ትምህርቶች አሉ፡፡ ወህኒ ቤት ጠንካራ ፍቅር እንዳለ ሰምተሻል አይደል?

ክሌር፡- "አዎ ሰምቻለሁ፡፡"

"ክፉን የመረጡ እድል ፋንታቸው ምን እንደሆነ እንዲረዱት ለማድረግ የእሳት ባህሩን ለማየት የሚካሄድ ጉብኝት ይኖራል፡፡

"<u>የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም</u>።"ራዕይ 14፡11

"በእኔ የተነገረው ቃል ሁሉ ሊፈፀም ግድ ነው፡፡ ምድር በጌታ ክብር ትሞላለች፡፡ ከአሁን ወዲያ ክፉ በምድር ላይ ሊኖር የሚችልበት ምንም ቦታ የለውም፡፡ ሁሉም ነገር እኔ ባቀድኩት በዘላለም እቅዴ መሰረት አዲስ ሆኖ እንደገና ይበቅላል፡፡
"የኔ ውድ ለዛሬ ምሽት ይህ ይበቃል፡፡ አውቃለሁ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚዘብቱ እንደሚኖሩ፡፡ ነገር ግን ስለ እነርሱ ራስሽን ምንም እንዳታስጨንቂ፡፡ እኔም ብሆን ግድ የለኝም፡፡

"በራሳቸው ጊዜ አይናቸው ይከፈታል፡፡ ይህንን ለአንቺ እየገለጥኩልሽ  ያለሁት መልዕክቱ ገብቷቸው ለሚቀበሉት እና በመጨረሻም መልካም እንደሚያሸንፍና ወደ ፊትም ብዙ ተስፋ እንዳለ መመልከት እንዲችሉ ነው፡፡
"ይህ መልዕክት የተዘገበው ሌሎች ሰዎች ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን በአግባቡ አከናውና ቢሆን ኖሮ ይህ ባላስፈለገ ነበር፡ ነገር ግን በፖለቲካ ግፊት ምክንያት እስካሁን እንዳይገለጥ ሆኖ ነበር፡፡ አሁን ግን ሊገለጥ ግድ ነው፡፡
እንደተፃፈውም "ዳንኤል ሆይ፥ ቃሉ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ነውና ሂድ፡፡ ብዙ ሰዎች ሰውነታቸውን ያጠራሉ ያነጡማል ይነጥሩማል ክፉዎች ግን ክፋትን ያደርጋሉ ክፉዎችም ሁሉ አያስተውሉም፥ ጥበበኞች ግን ያስተውላሉ።"(ዳንኤል 12፡9-10)

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ሰባት - ማርች 10 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the raprure event 7 – March 10, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . .   ጌታዬ እኔ የሚያንፀባርቅ ጥቁር ልብስ ለምን እንደለበስኩ አልገባኝም፡፡ እንዲህም ሆኖ ደግሞ አንድ ትልቅ ክብረ በዓል  እንደምናከብር እየደነስን ነው፡፡

"ጥቁር የለበሽበት ምክንያት አለም ሁሉ ስለሚያዝን አንቺም አብረሽ ስለምታዝኚ ነው፡፡ ነገር ግን ደግሞ ትልቅ ደስታ በውስጥሽ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በውስጥሽ ያለውን ደስታ አለም ከአንቺ ነጥቆ ሊወስድው ስለማይችል ነው፡፡

"የኔ ፍርድ በዚህ አገርና /በአሜሪካ/ በምድር ሁሉ ላይ በሚመጣበት ጊዜ እኛ ግን በዛ ወቅት እንደንሳለን፡፡ ይህም አንድ አይናችንን አለምን እያየን በአንድ አይናችን ደግሞ መንግስተ ሰማይን አሻግረን እናያለን፡፡

"ነገሮች ወደዚህ ምድርና/ወደ አሜሪካ/ ወደ አለም ሁሉ እየቀረቡ ሲሄዱ እናንተ ደግሞ ወደ ሰማዩ አገራችሁ እየተጠጋችሁ ትሄዳላችሁ፡፡

"ክሌር  ነገሮች ሁሉ እየቀረቡ እንደሆነ በመንፈስሽ እየተረዳሽ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ በእርግጥም እየቀረቡ ነው፡፡ የኔ ውድ ይህ በቅርብ ይሆናል፡፡ ከእኔ ጋር እወስድሽና ለዘለአለም ከእኔ ጋር ትሆኛለሽ፡፡ የፍቅሬን መገለጫ ስጦታዎች ሁሉ አትረፍርፌ በመስጠት ከዚያ በኋላ ለዘላለም አብረን በደስታ እንኖራለን፡፡

ክሌር፡- ጌታ  ሆይ! ይህ በጣም ውድና የሚያስደስት ነገር ነው፡፡ የውስጥ ማንነቴ በዚህ ተስፋ እጅግ ዘለለ፡፡ ይህ በእርግጥ አንተ የተናገርከውና በቅርብም የሚፈፀም ነገር ነው?

"ስለጥርጣሬና ስለ ማመን ምን ብዬሽ ነበር?"

ክሌር፡- እንደሚመስለኝ ይህንን ነገር ከምንም ጋር ላወዳድረው የምችለው ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ እጅግ መልካም ከመሆኑ የተነሳ እኔ ካለሁበት እውነታ ሩቅና ለማመን አስቸጋሪ የሆነ ነገር ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ሳቅ አለና "አዎ የኔ ውድ ምን እንደሚሰማሽ በደንብ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እውነት ነው፡፡ እኔ እርግጥ እንደሆንኩ ሁሉ ይህም እርግጥ ነው፡፡ ይህ ከምትገምችው በላይ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ይህ ደግሞ እኔን የበለጠ ያስደስተኛል፡፡ ምክንያቱም አንቺ ባልጠበቅሽው መንገድ የፍቅር ስጦታዬ ሲያስደስትሽና ሲያስደንቅሽ ስለሚያሳየኝ ነው፡፡"

ክሌር፡- ስለዚህም አለም ያዝናል፣ እኛ ግን አንድ አይናችንን አለምን እያየ አንድ አይናችን ደግሞ መንግስተ ሰማይን ያያል ማለት ነው?

"በትክክል "

ክሌር፡, ጌታ! የሰው ልጅ በምድር ስቃይ ላይ መሆኑን እንዲሁም አንተ ከእነርሱ ጋር እየተሰቃየህ መሆኑን እያወቅሁ እንዴት ደስተኛ ልሆን እችላለሁ? ይህንንና ደግሞም . . . በእርግጥ እየጠየኩህ ነው፡፡

" . . . ተመልሶ መጥቶ መርዳትን?"

ክሌር፡- አዎ! ማለቴ ስለ እኛ ብዙ የሚባሉ ነገሮች አሉ፡፡ ይህም ሰልጥነን በመከራው ዘመን ወደ ምድር በመምጣት እንደምንረዳ ፡፡

"ወደ እረፍቴ ትገብያለሽ፡፡ እስካሁን ለፍተሻል አሁን ደግሞ ታርፊያለሽ፡፡ በየትኛውም መልኩ ቢሆን የሚመጣውን ፍርድ ተካፋይ እንድትሆን ሙሽራዬን አልጠራኋትም፡፡ እኔ ከዚህ የምወስድሽ በሰማይ ሆነሽ የምድርን ስቃይ እንድትጋሪ አይደለም፡፡ አሁን ግልፅ ሆነልሽ?

"አላደርገውም፡፡ የአንቺ ሥራ እኔ ለመግዛት ወደ ምድር እስክመለስ ድረስ አልቋል፡፡ ላፅናናሽ እመጣለሁ እንጂ ለምድራዊ ስቃይ አላጋልጥሽም፡፡ ማድረግ አልችልም ደግሞም አላደርገውም፡፡"

ክሌር፡- ጌታ በዚህ ላይ አንድ ጥበብ ልጠይቅህ እችላለሁ?

"ለምን አትችይም? ሁልጊዜ ትጠይቂኛለሽ የዛሬው ለምን ልዩ ይሆናል? እምም?"

ክሌር፡- ይህ የሚያስቅ ነገር አይደለም! ግን እንድስቅ እያደረግኸኝ ነው፡፡

"አንዳንድ ጊዜ አብረን የጨዋታ ጊዜ ሊኖረን ይችላል፡፡ ከባድ በሆነና የሁለታችንም ልብ በተሰበረ ጊዜ እንኳን፡፡ በእኔ አምላካዊ እቅድ መሰረት የእያንዳንዳችን አካሄድ ልክ አለው፡፡ ዓላማ አለኝ ደግሞም ልክ አለኝ፡፡ የኔ ውድ አትጠይቂ፣ ያልኩሽን እንዲሁ ተቀበይ፡፡ ከዚህ አለም ስቃይ ባይተዋር እንድትሆኚ የሰጠሁሽን ነፃነት እንዲሁ ተቀበይ፡፡"

ጌታ ውስጤን ሳቅ ሳቅ እያለኝ ነው፡፡

"ክሌር ያ እምነት ከማጣት የተነሳ ነው፡፡"

"የኔ ውድ ብዙ ሰዎች  የቅጣቱ ዘመን የጀብዱ ሥራ የሚከናወንበት ስለመሰላቸው ተመልሰው  መጥተው መገኘት ይፈልጋሉ፡፡ ስለምን እንደሚያወሩ እንኳን አያውቁትም፡፡  ስለሚመጣው ዘመን መላዕከቶቼ  ተዘጋጅተዋል፡፡ ሊሆን ባለው ነገር ላይ እነሱ ብቻ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

ክሌር፡- በመንግስተ ሰማይ የምናደርገውስ ፀሎት? አንተ እዛ ሆነህ ስትፀልይ ስናይህ . . .  እኛም አብረንህ በእርግጥ እንፀልያለን? ልጆቻችንስ! ለዛስ እንዴት ምላሽ እንሰጥም?

"የምትፀልዩላቸው ጊዜ ይኖራል፡፡ ነገር ግን እውቀታችሁ አሁን ካለው አጅግ የላቀና በዚያን ጊዜ የምትፀልዩት ፀሎት ለእነሱ የሚበጃቸውን ነው፡፡ አሁን እንዳላችሁ ዓይነት መተሳሰር ከእነሱ ጋር አይኖራችሁም፡፡ እንዳውም የምታዩአቸው እኔ እንደማያቸውና ከኃጢያት መንፃት እንዳለባቸው የሰው ዘር አድርጋችሁ ነው፡፡ ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅር አይቀንሰውም ነገር ግን አመለካከታችሁ ከመንግስተ ሰማይ አንፃር ይሆናል፡፡"

ክሌር፡- ስለዚህ አሁን እነሱ በሚሆኑት ነገር እያየሁ በስሜት አውሎ ንፋስ እንደሚነዳ አልነዳም ማለት ነው?

"በትክክል፡፡ እሩቅ ብትሆኝም እንደ እናት ትወጃቸዋለሽ፡፡ ነገር ግን በዚያን ጊዜ እኔ ለእነሱ ያለኝ በፍቅር የተሞላ ፈቃድ ምን እንደሆነ በደንብ ይገባሻል፡፡"

ክሌር፡- ስለዚህ በመከራው ወቅት ወደ ምድር አንመለስም ወይም ደግሞ በምድር ምን እየተከናወነ እንዳለ የማየት እድል የለንም ማለት ነው?

"የለም አትችሉም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለማበረታታ ብቻ ምድርን ትረግጡ ይሆናል እንጂ የነገሩ ተሳታፊ አትሆኑም፡፡ እንዳውም በድንገት በመገኘት የማበረታቻ ቃል ለመስጠት እንጂ የሚያመውን እውነታ ተካፋይ አትሆኑም፡፡

"አየሽ የአንቺ እውነታ በብዙ መልኩ ልዩ ነው የሚሆነው፡፡ ማለትም አሁን በሥጋ በምድር ላይ እንደ ሆነሽው ያህል ስሜታዊ በመሆን በነገሩ ላይ ተሳታፊ መሆን የማትችይበት ነው፡፡ ምክንያቱም አንቺ ወደፊት የምትኖሪበት እውነታና ዓለም ልዩ ስለሚሆን ነው፡፡"

"ምንም እንኳን ትንሽ ብርሃን በውስጥሽ እያለፈ  መሆኑን ባይም ፣ አውቃለሁ ለአንቺ ይህንን ፅንሰ ሐሳብ ለመረዳት ከባድ እንደሚሆን፡፡

"አየሽ በመንግስተ ሰማይ ነገሮች ሁሉ ልዩ ናቸው፡፡ እንኳን እዚህ ሆነሽ በሰማይ ስትሆኚ እንኳን እንዴት ምላሽ እንደምትሰጪ ወይም እንዴት ምድርን እንደምታዪ ማሰብና መገንዘብ አትችይም፡፡ እውነታው ይህ ነው፡፡ አሁን ያለሽበት ግን ጭጋግ ብቻ ነው፡፡ ከዛ ነገር ርቀሽ እያለሽ በምንም ዓይነት መልኩ ማስረዳት አልችልም፡፡ የኔ ፍቅር አንቺው ራስሽ ተገኝተሽ በተግባር ማየት አለብሽ፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ነገር የነገርኩሽን ቃል እንዳለ ውሰጂው፡፡ ይህንን ታደርጊያለሽ?

ክሌር፡- አዎ! ኢየሱስ ትልቅ ውስጣዊ ሰላም አግኝቻለሁ፣ የምትነግረኝ ነገር ሁሉ እውነት ነው፡፡ ደግሞም እንደተናገርከው እንደዛው ይሆናል፡፡

"እያወራሁ ስላለሁት ጉዳይ ብዙዎች ሊፈፀም ያለውን ታሪክ ተመልሰው ባለማየታቸውና ተሳታፊ ባለመሆናቸው በጣም ነው ቅር የሚሰኙት፡፡ ለእናንተ እንደዚህ እላለሁ፡፡ ይህንን ቃሌን ስሙ፡፡ ወደ መከራ እኮ ነው የምትገቡት፡፡ ለእናንተ ወዳልተዘጋጀውና በስርዓት ላልኖሩት ለተዘጋጀላቸው ስቃይ ነው የምትገቡት፡፡ እናንተ ለእኔ ያላችሁን ፍቅር አሳይታችኋል፡፡ ስለዚህም እኔን ንቀው ያልታዘዙት በሚያልፉበት በእነዚህ ነገሮች ውስጥ እንድታልፉ አልፈልግም፡፡

"ነገር ግን አብረን ወደዚህ በምንመለስ ጊዜ ያን ጊዜ እድሉን ታገኛላችሁ፡፡ በዚያን ጊዜ ሁሉ ነገር አዲስ ይሆናል፡፡ ያን ጊዜ የሚሰጣችሁ ሥራ ስለሚኖር እንዲሁም ብዙ  አጋጣሚዎችና አዲስ ነገሮች ስለሚኖሩ ያን ጊዜ የተሰጣችሁን ስጦታ ትጠቀሙበታላችሁ፡፡ የኔ ሙሽሮች ለእናንተ ያለኝ እቅድ በጣም የሚያስደስቱና በጣም ድንቅ  ናቸው፡፡ ደግሞም በልባችሁ ለመስራት ትመኙ የነበረውን ሁሉ ለመፈፀም የሚያስችል አስፈላጊ ነገር ሁሉ በሙላት ይሰጣችኋል፡፡

"አዎን ፍፁም በሆነ መልኩ ነው የሚሟላላችሁ፡፡ ሙዚቃችሁ ያብባል፣ የሞዚቃው ጨዋታ ፍፁም ከመሆን አንድም አይጎድልም፡፡ ቅባቱ ደግሞ ልቦችን ወደ እኔ በማምጣት እንድፈውሳቸውና መልሼ እንድገነባቸው ያደርጋል፡፡ አያችሁ ሁላችሁም የምትጠብቁት ይህንን ነው፡፡ ከእኔ ቀድማችሁ በመሄድ የምታስቡት ይህ በቅጣቱ ዘመኑ የሚካሄድ መስኳችሁ ነው፡፡

"ሁላችሁም በልባችሁ ውስጥ የተቀመጠውን፣ እንዲሁም እኔ በበለጠ ለእናንተ ያቀድኩትን ብዙ ብዙ ነገሮች እንድትሰሩ ብዙ አጋጣሚዎች ይኖራችኋል፡፡ ከአሁን ወዲያ ብዙ ደክማችሁ ከልበ ደንዳናነት የተነሳ ምንም ውጤት የማታዩበት አይሆንም፡፡ እንደዛ አይሆንም መስጠት ያለባችሁን ሁሉ ለመቀበል ልብ ሁሉ በደንብ ይከፈታል፡፡

"የኔ ሙሽሮች ሐሴት አድርጉ፡፡ ሐሴት አድርጉ ዋጋችሁ ትልቅ ነውና፡፡ ደግሞም የሚሰጣችሁ ሥራ ትልቅ ነውና ሐሴት አድርጉ፡፡ በፊታችሁ ይህንን ተመልከቱ፡፡ አዎ እውነት ነው በጥቁር ልብስ ትደንሳላችሁ፡፡ አንድ አይናችሁ መንግስተ ሰማይን አንድ አይናችሁ ደግሞ ምድርን ይቃኛል፡፡ እውነታው መሆን ያለበት ግን አመድ የተነሰነሰበት ማቅ ልብስ ሳይሆን በከንዴ ላይ መሆናችሁ ነው፡፡

"ጥሩ! የኔ ውድ አሁን ረካሽ?"

"አዎ ጌታዬ እኔ አምኛለሁ፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፡፡ አንተ የምትናገረው እውነቱን ብቻ እንደሆነና ቶሎ ሊሆን ስላለው  ነገር እያዘጋጀኸን እንደሆነ ገብቶኛል፡፡"

"የኔ ውድ የተናገርኩትን ስለተቀበልሽ አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻው በልብሽ የነበረውን ጥያቄ ምላሽ ተቀብለሽ ስለተረጋጋሽ በደስታ ልቤ ዘለለ፡፡ ደግሞም የእረኛሽን ድምፅ በእውነት ሰምተሻል፡፡

"ደግሞም ታማኙን ድምፄን በእውነት እስከታውቂው ድረስ በአንቺ ላይ መስራቴን እንደማላቆም ነግሬሽ ነበር፡፡ እነዚህን ነገሮች የምሰራው እኔ ነኝ፡፡ ከአንቺ የምፈልገው አሁን እንዳደረግሺው እንድታደርጊ ብቻ ነው፡፡"

"አመሰግናለሁ የኔ ፍቅር፡፡ እምነትሽን በእኔ ላይ ስለጣልሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ ክሌር አፈቅርሻለሁ፡፡ቃሌን በአንቺ መናገር እንደጀመርኩት ከእኔ ጋር ወደ ቤት እስከትመጪ ድረስ እንዲሁ እቀጥላለሁ፡፡"

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ስምንት - ማርች 12 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 8 - March 12, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . . ጌታዬ አንተ ከንጥቀት በፊት መጨረስ እንዳለብኝ የተናገርከኝን ሥራ ሁሉ እንዴት አድርጌ መጨረስ እንደምችል ምንም አልገባኝም፡፡

ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ . . . "ስለ ጉዳዩ እንነጋገር ?"

ክሌር ፡- አዎ ያ እኔን በጣም ይረዳኛል

"ይህንን በዚህ ጊዜ ስርተሽ መጨረስ አለብሽ ብዬ የሰጠሁሽ የጊዜ ገደብ የለም፡፡ እኔ ያልኩሽ የሰጠሁሽን ሁሉ ስርተሽ ትጨርሻለሽ ነው እንጂ መቼ እንደሆነ ግን አልተናገርኩም፡፡"

ጌታ አንተ ያመለከትከኝ ከንጥቀት በፊት እንደሚሆን ነው፡፡ ደግሞም ከሙሽራዬ ፊት የተቀመጠውን ደንቃራ ነገር ያነሳሁት የበለጠ ጊዜ እንዲኖራት ነው ብለህ ነበር፡፡ አሁን እኔ በጣም በጣም ግራ ገብቶኛል፡፡ ምክንያቱም አሁን ነገሮች ሁሉ የተመሰቃቀሉ እየመሰለኝ ነው፡፡

"የተመሰቃቀለውን እኔ ግልፅ ላድርግልሽ፡፡ በመጀመሪያ ሁሉም ነገር ተሰርቶ እንደሚያልቅ ቃል ገብቼልሻለሁ፡፡ አውቃለሁ አንቺ ያሰብሽው ከንጥቀት በፊት ሁሉም እንደሚያልቅ ነው፡፡ ነገር ግን ምንም የጊዜ ገደብ አልሰጠሁሽም፡፡"

ጌታ እባክህ እርዳኝ፡፡ ያለማመን ወጥመድ ውስጥ እየገባሁ ነው፡፡

"የኔ ውድ እንደ ወትሮው ፅንተሽ ቁሚ፡፡ ትዕግስተኛ መሆን አለብሽ፡፡ አንቺ ለመስራት ያሰብሽውን፣ ያም እኔ በልብሽ ያስቀመጥኩትን ሁሉ አከናውነሽ የምትጨርሽበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ይህም ከንጥቀት በኋላ ይሆናል፡፡"

ከንጥቀት በኋላ?

"አዎ ከንጥቀት በኋላ?"

ነገር ግን ለሙሽራህ ተጨማሪ ጊዜ እንደምትሰጣት ተናግረሃል፡፡

"አዎ ተጨማሪ ጊዜ ሰጥቼያታለሁ፡፡"

ነገር ግን እኔ የመሰለኝ ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ነበር፡፡

"እርሱን በግልፅ ስንት ዓመት እንደሆነ አልነገርኩሽም፡፡ ስለ እርሱ አሁንም አባቴ የሚለውን እየጠበቅሁ ነው፡፡ መቼ መሆን እንዳለበት ትክክለኛው ጊዜ እየተመረጠ ነው፡፡"

እሺ . . . እኔ ነገሮች በመሃከል ተቆርጠውብኝ ነው፡፡

"ያለማመን ደግሞ እንደገና መጣ፡፡"

ጥፋተኛ ሆኜ ተገኝቻለሁና ኢየሱስ እርዳኝ፡፡

በዚህ ሰዓት እሳት ለማቀጣጠልና ለህዝቅኤል እራቱን ለማሞቅ ፈለኩኝ፡፡ ደግሞም ይህ ጊዜ እርሱን እንኳን ደህና መጣህ የምልበት የዕረፍት ጊዜዬ ነው፡፡ እናም አውቃለሁ ወደ ህዝቅኤል ብሄድ ግራ ከገባኝ ነገር ይገላግለኛል፡፡ መጫወቻ ሆኛለሁ ወይንስ በእውነት የሚናገረኝ ኢየሱስ ነው?

(ህዝቅኤል) ተመልሻለሁ፡፡ አብሮሽ ያለው ኢየሱስ ነው፡፡

ኢየሱስም "አሁን ረክተሽ ሰላምን አገኘሽ?"

አዎን ጌታዬ፡፡

"የኔ ጣፋጭ ሙሽራ እንድረዳሽ ጠይቀሽኝ ነበር፡፡ እርሱ የኔ አፍና የአንቺ ደግሞ ሽፋን ነው፡፡"

ኢየሱስ እንደዚህ ብዙ ጥያቄ እየጠየኩህ እንዴት ጣፋጭ ትለኛለህ?

"ቅር አልተሰኘሁም እንዳውም የአንቺ ግልፍተኝነት የእኔን የዋህነትና ትህትና ለልጆቼ እንዳሳይ እድል ይሰጠኛል፡፡ በሌላ አነጋገር እኔ ለክሌር ትሁትና የዋህ ከሆንኩ እናንተ ደግሞ በእርግጠኝነት ለሌላው የዋህና ትሁት ትሆናላችሁ፡፡"

"እየሽ የአንቺን ግትር ባህርይ ለመልካም ነገር እጠቀምበታለሁ፡፡"

ጌታ በእውነት አንተ ለስላሳ፣ ደግና ይቅር ባይ ነህ፡፡ ከእኔ ጋር ባለህ ግንኙነት ትዕግስተኛ ስለሆንክ አመስግንሃለሁ፡፡

"ስለማፈቅርሽና ትግልሽ ስለሚገባኝ አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ በነገራችን ላይ ይህ በአለም ላሉ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሰራ ነው፡፡ ያንን እኮ ፈትተነዋል አሁን የምፈልገውን ልነግርሽ ነው፡፡"

እሺ ጌታ እየሰማሁ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ግንባሬን ሳመኝ

"ጊዜው አጭር ስለሆነ ሁለታችሁም እያላችሁ ይህንን መልዕክት ቶሎ ቶሎ ብዬ ላጠቃለውና ለዛ ቀን ራሳችሁን እንድታዘጋጁ ይሁን፡፡ በአሜሪካና በዓለም ሁሉ ሊመጣ ያለውን ማዕበል ማፈረካከስ የምትችሉት በፀሎትና ፀንቶ በመቆም ነው፡፡"

"ሁለታችሁም በእያንዳንዱ ቀን በማንኛውም ሰዓት ጠንካራና የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡"

መዘጋጀታችንን እንዴት እናውቃለን?

"እጅግ ውስጣዊ የሆነ ሰላም ይሰማችኋል፡፡ በሁለታችሁም ውስጥ የሚሰማችሁ የጥድፊያ ስሜት ነበር፡፡ የምታጠፉት ምንም ጊዜ እንደሌላችሁ በመረዳት በትኩረት ቀጥሉ፡፡ እባካችሁ ወገባችሁን ታጥቃችሁ የሰጠኋችሁን መልዕክት ጠንክራችሁ በመሥራት አቀናብሩትና እዚህ ለሚቀሩት ተዉላቸው፡፡"

"ክሌር እየሰማሽ ነው?"

ጌታ እኔ ድብዝዝ ብሎብኛል፡፡

"ያ የበላሽው ጣፋጭ ነው፡፡"

ነው እንዴ ?

"ከእኔ ጋር ለመቆየት ሞክሪ፡፡"

"መጠነኛ የሆነ የኒውክላር ልውውጥ ይኖራል፡፡ ይህም በዓለም ላይ ሽብርን ለመንዛት በቂ ሲሆን ኦባማ ሰላምን እንዲያመጣ በማለት ስልጣን ላይ እንዲወጣና ጀግና ሆኖ እንዲቆጠር ያደርገዋል፡፡"

"አሜሪካ በከፍተኛ ጩኸትና ሁካታ ትታወካለች፣ መገናኛ ዘዴዎች በጊዜያዊነት ይቋረጣሉ፡፡ ነገር ግን ማርሻል ሎው ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ መገናኛ ብዙሃን አስፈላጊ ናቸው፡፡ ደግሞስ አሸናፊው በመገናኛ ብዙሃን አሸናፊነቱን በዓለም ሁሉ ሳይናገር እንዴት ደስታውን ያጣጥማል፡፡ አሜሪካ ከዚህ አስደንጋጭ ሁኔታ ማንም ከሚጠብቀው በላይ ቶሎ ታገግማለች፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ነገር ወደፊት ምን እንደሚሆን በሙሉ እውቀት የተዘጋጀ ነውና ነው፡፡"

"አሜሪካ ከአሁን ወዲያ የዓለም ታላቋ ኃያል አገር አትሆንም፡፡ ይህች አገር መልሳ የምትገነባውና የተመረዘውን የምታስተካክልበት ብዙ ሥራዎች አሉባት፡፡ እንዳትሳሳቱ በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው ሲሻኮትና ሲታገል ከምድር በታች ያሉ ከተሞች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ይሸሽጋሉ፡፡ በዛን ጊዜ ህግና ስርዓት ይጠፋል፡፡ ወንጀለኞች ለመድፈርና ለመዝረፍ ዕድሉን ይጠቀሙበታል፣ ህይወት እጅግ የተዘበራረቀ ይሆናል፡፡"

"ቦንቡ በወደቀ በዚያው ቀን ነው እኔ ለእናንተ የምመጣላችሁ፡፡ ራሳችሁን ቀና አድርጉና ሰማዩን ተመልከቱ፡፡ በዚያኑ ቀን እኔ ለእናንተ እመጣላችኋለሁ፡፡

"እንደገና ልድገመው ራሳችሁን ቀና አድርጉ፡፡ በዚያኑ ቀን እኔ ለእናንተ እመጣላችኋለሁ፡፡ ተስፋ አትቁረጡ ደግሞም አትደንግጡ፡፡ ደግሜ ደጋግሜ ነግሬያችኋለሁ፣ የመዳን ቀናችሁ ቀርቧል፡፡ ይህ ነው ስትጠብቁት የነበረው ዘላለማዊ ዕለት፡፡"

ጌታዬ እኔ መናገር ተስኖኛል፡፡

"እኔ እርግጥ እንደሆንኩ የሚያሳየው ክስተት በእርግጥ እየመጣ ነው፡፡"

"አትፍሩ፣ የቆማችሁበትን አጠንክራችሁ ያዙ፣ አይናችሁን ደግሞ ወደ ሰማይ አቅንታችሁ ተመልከቱ፣ እኔ እመጣለሁ፡፡"

ጌታ እርዳን ፡፡

"እንዲረዷችሁ መላዕክቶቼን ቀድሜ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ሁሉም የተዘጋጀ ስለሆነ አትገዳገዱም፣ አትወድቁም፡፡"

ጌታ ተመስገን፣ እጅግ እናመሰግንሃለን፡፡

"አያችሁ ይህንን ለእናንተ ላረጋግጥላችሁ ፈልጌ ነበር፡፡ ነገር ግን የእኔና የእናንተ ግንኙነት የተጠበቀ መሆኑን እርግጠኛ እስክትሆኑ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ፡፡"

ክሌር - ኢየሱስ እኔ በእውነት ደንዝዣለሁ፡፡

"አውቃለሁ፡፡ ይህንን ለመቀበል ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን በደንብ አዘጋጅቻችኋለሁ፡፡ ስለዚህም ፈተናውን በደመቀ ሁኔታ ነው የምታልፉት፡፡"

ክሌር፡- ኢየሱስ በቃ ይኸው ነው?

"ለአሁን ይኸው ነው፡፡"

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት ዘጠኝ - ማርች 13 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 9 – March 13, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . ዛሬ በጣም የሚገርም ነገር ገጥሞን ነበር፡፡ ይህም በምን ምክንያት እንደሆነ አናውቅም ነገር ግን ቀኑን ሙሉ ኢንተርኔት የለም ነበር፡፡ ስልኩ ግን በእርግጠኝነት ከኢንተርኔቱ ጋር ተያይዟል፡፡ በዚህም ምክንያት ስልክም የለም ነበር፡፡ ምናልባት ገመዱ ተበጥሶ እንደሆነ አላወቅንም፡፡ ብዙ ጊዜ የህንፃ ግንባታ ሲካሄድ ገመዶች ይበጣጠሳሉ፡፡

ለወትሮው የማገኛቸውን ሰዎች ባለመገኘቴ ብቸኝነት ተሰምቶኝ መደናገጥ ፈጠረብኝ፡፡ እናም ሌሎችስ ኢንተርኔት ባለመኖሩ ምን ተሰምቷቸው ይሆን ብዬ አሰብኩ፡፡ ከሌሎች ጋር ባለመገናኘታቸው እነርሱም እንዴት ዓይነት መገለል፣ ፍርሃትና ግራ መጋባት ተሰምቷቸው ይሆን? ወደ ጌታ ፊት ለፀሎት ስቀርብ ከዚህ ሁኔታ የተነሳ ልቤ እጅግ ከብዶብኝ ነበር፡፡

ጌታም እንዲህ አለኝ . . . "ከንጥቀት ወደኋላ ለሚቀሩት ለምትወጃቸው የተዘጋጀ ጥቅል መተው አለብሽ፡፡ ክሌር ይህ ሐሳብ የአንቺ ሳይሆን የኔ ነው፡፡"

ክሌር፡- ቀኑን ሙሉ ይህንን ሐሳብ በልብ ውስጥ ሳሰላስለው ነበር፡፡ እናም የመገናኛ መስመሮች መቋረጣቸው ሁኔታውን በትክክል ገልፆታል፡፡

"ውድ ልጆቼ እነዚህ መልዕክቶች ጠቃሚዎችሁ ከሆነ ከሄዳችሁ በኋላ የምትወዷቸው እንዲያገኟቸው ኮፒ በማድረግ እነርሱ ሊያገኙአቸው በሚችሉበት ሥፍራ አስቀምጧቸው፡፡ ይህ ጥንቃቄ ብቻ ነው፡፡ ከንጥቀት በኋላ እነርሱ መልዕክቱን የሚያገኙበት ድህረ - ገፆች ላይኖሩ ይችላል፡፡

"ወደፊት በስልጣን ላይ የሚወጡ ሰዎች ለእነርሱ አጀንዳ ማን አደገኛ እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ አንድ ነገር አግኝታችሁ ልባችሁን የሚነካ ከሆነና የእናንተን ዕይታ የሚያሰፋና ሰላም የሚሰጣችሁ ከሆነ ዳውን ሎድ በማድረግ ሊገኝ በሚችል ሥፍራ አስቀምጡት፡፡

ክሌር፡- ሲዲና ዲቪዲም ማዘጋጀት አለብን?

"ለማስቀመጥ የሚመችና ሲፈለግ የበለጠ ሊገኝ የሚችል ማንኛውንም ነገር አስቀምጡ፡፡ ምናልባት አንዱ ኮፒ አንድ ነገር ቢሆን እንኳን ከእያንዳንዱ ሁለት ኮፒ ብታስቀምጡ ጥሩ ነው፡፡ ዲያቢሎሶች ማንኛውንም ቅዱስ የሆነ ነገርን ለማጥፋት እጅግ ይቸኩላሉ፡፡ ይህም በትዕዛዝ የሚሆንና ወደኋላ የሚቀሩት እንዲገለሉ ለማድረግ ነው፡፡"

ክሌር፡- መታተም የሚችሉ በፒዲኤፍ የተዘጋጁ ፅሑፎችም አሉን፡፡

"አዎን አትሞ /print/ ማስቀመጡ ምርጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ለማንበብ ቀላል ስለሆነ፣ በዛ ወቅት ኤሌክትሪክና ኢንተርኔት ስለሚቋረጥና እስኪጠገን ድረስ ትንሽ ስለሚቆይ ነው፡፡ አደራጅታችሁ የምታስቀምጡት ጥቅል ፍቅርን ከሚገልፅ ደብዳቤ ጋር አብራችሁ አስቀምጡ፡፡ ሰዎችን ከመክሰስ ተጠበቁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ያሳብዳቸዋል ወይም ተስፋ ያስቆርጣቸዋል፡፡ ንግግራችሁ የሚገነባ፣ ጨለምተኛ ያልሆነና ተስፋን የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ በዋናነት ግን ፍቅራችሁን የሚገልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ መልካሙ ነገር እንዳመለጣቸው በደንብ እያወቁ ቁስላቸውን መንካት አያስፈልግም፡፡ በጉልበታቸው እንኳን መቆም ስለማይችሉ ማድረግ ያለባችሁ ማበረታታት ነው፡፡

"ኑዛዜ የሚመስል ነገር ወይም ነገሮችን እንዴት እንደሚከፋፈሉ ዝርዝር ነገሮች ተዉላቸው፡፡ ይህም እርስ በርሳቸው እንዳይጨቃጨቁ ይረዳቸዋል፡፡ስታከፋፍሉ አታዳሉ፡፡ እንዳውም ለማይገባቸው በልዩ መልክ ደግ ሁኑላቸው፡፡

"አሁን ትኩረታችሁ ሁሉ መሆን ያለበት በነፍሳቸው መዳን ላይ ነው፡፡ እኔ አፍቃሪ አምላክ ነኝ፡፡ ነገር ግን በሰው ልጆች ላይ ቁጣዬ በተነሳ ጊዜ እነዚህን ሁሉ ማሳመን ከባድ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህንን አስታውሱ አስቀድሜ የወሰንኳቸውን አስቀድሜ አውቃቸዋለሁ፡፡

"ይቅርታ እንዳደረጋችሁላቸው በፅሑፋችሁ ግለፁላቸው፡፡ እናንተም በእነርሱ ላይ የሰራችሁትን ኃጢያት ምን ምን እንደሆነ ዘርዝራችሁ ይቅርታ በመጠይቅ እንዲተዋቸው ለማድረግ ይቅርታ ጠይቋቸው፡፡ ያለፈውን ለመተውና ወደፊት ለመዘርጋት ይህ ቅባት ያስፈልጋቸዋል፡፡ እመኑኝ ይህ ዘሎ መውጣት ይሆንላቸዋል፡፡ ማንም ሊያስበው የማይችለው አስቸጋሪው ሽግግር ከዚህ ወጥቶ መለወጥ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡

"የጌታ ማደሪያዎች የሚለውን ፀሎት እንዲፀልዩና እጄን እንዲይዙ አበረታቷቸው፡፡ በችሎታዬ እመራቸዋለሁ ደግሞም በፍቅሬ አፅናናቸዋለሁ፡፡ነገር ግን ለእኔ እንደሚገኙ ሆነው መፀለይ አለባቸው፡፡ አዎ በጉልበታቸው ተንበርክከው የሚፀልዩትና በትህትና የሚያቀርቡት ልመና እጅግ ተደማጭነት ያለው ነው፡፡ ከዚህ በበለጠ መልኩ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ቅርበት ያለውና እጄን ይዞ የመሄድ ግንኙነት መልካም ሲሆን የቀረው ሌላ ነገር ሁሉ እንዲሁ በራሱ ይቀጥላል፡፡

"እነርሱ ማወቅ ያለባቸው እንደምወዳቸው ነው፡፡ ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር ነኝ፡፡ ደግሞም ሊቀርቡኝ ይችላሉ፡፡ ለወደፊቱም ተስፋ ያላቸው ናቸው፡፡ አሁን ቢሞቱም ወይንም በመከራውን ዘመን ውስጥ ቢያልፉ ወደፊት ገና መልካም የሆነ ጊዜ ይጠብቃቸዋል፡፡ እንዲያውቁ የምፈልገው ሁሉም ነገር ያለቀና የተበላሸ አይደለም፡፡ እንዲህ አይደለም፣ እንዳውም

ህይወታቸው ገና መጀመሩ ነው፡፡ አዎ እርግጥ ነው መንገዳቸው በአደጋ የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ እኔ በጣም በተጠጉ ቁጥር ታምራቶቼንና የፍቅሬ ጥልቀት ምን ያህል እንደሆነ በመለማመድ ምላሹ እጅግ የጠለቀ ይሆናል፡፡

"ህይወታቸውን ሙሉ ለማግኘት ሲሸከረከሩ የነበሩት ነገር በአንፃሩ ግን ሲሸሹት የነበሩት ነገር ይህ ነበር፡፡ አሁን ግን እኔ እውነት እንደሆንኩ፣ እንደምወዳቸውና ከእነርሱ ጋር እንደሆንኩ የሚያውቁበት ጊዜ ነው፡፡

"ባለፉት አመታት ሁሉ ሊሰሯቸው የሚገቡ ነገሮች ነገር ግን ያልሰሯቸው ሁሉ የሚሰሩት አሁን በዚህ ወቅት ነው፡፡ ነፍሳቸውን የሚያጧት ያገኟታል፣ ነፍሳቸውን ግን አጥብቀው የሚይዟት ያጧታል፡፡ ይህ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የሚመስል፣ ነገር ግን ደግሞ በእምነትና በመተማመን ላይ የሚሸከረከር ነገር ነው፡፡ በቃሉ ውስጥ የተፃፉት ምልክቶችና ተስፋዎች በመፈፀማቸው ምክንያት መፅሐፍ ቅዱስ በ180 ዲግሪ እንደሚመልሳቸው ተስፋ አለ፡፡

"ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንዶች ምን እንደሚያስከትል ሙሉ እውቀት እያላቸው በራሳቸው መንገድ መጓዛቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በዚህም የሚማሩት ትምህርት አለ፡፡ አንድ ቀን ታዲያ የአመፃቸው ጥልቀት ምን ያህል እንደሆነና ውጤቱም ለምን አደገኛ እንደሚሆን በሙላት ታውቃላችሁ፡፡

ክሌር፡- ጌታ በታላቁ መከራ ወቅት ምን እንደሚፈፀም ማየት የምንችልበት አጋጣሚ አለ?

"ነገሮችን የምንከልስበት ወይም መልሰን የምናይበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር እናንተ ለማወቅ አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድታዩ ይደረጋል፡፡ ወደ መጨረሻው አካባቢና ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ወደ ምድር ከመመለሳችን በፊት ብዙ እንድታዩና ከእኔ ጋር ተመልሳችሁ ለመግዛት እንድትዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ከዛ ሁሉ በፊት ግን በምድር በተመደባችሁበት ሥፍራ ለመሥራት የሚያስችል ትልቅ የግንዛቤ ማስጨበት፣ የስልጠና፣ የመታጠቅና የዝግጅት ጊዜ ይኖራል፡፡

"አሁን እዚህ ሆናችሁ የማይቻል የሚመስል ነገር በመንግስተ ሰማይ አግባብ መሰረት ሲታይ የተለየ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ዳሩ ግን  የጫጉላ ጊዜ ስለሚኖር በምድር ያለውን የሰውን ልጆች መከራ በማምጣት ጊዜውን አላበላሽም፡፡

በዚህ ጊዜ ሁልጊዜ እንደማደርገው ሁሉ ብዙ ጥያቄዎች ይመጡብኝ ጀመር፡፡ እናም . . . ጌታ ይቅርታ አድርግልኝ አልኩት፡፡ ምክንያቱም ሐሳቤን ማንበብ እንደሚችል ስለማውቅ ነው፡፡

እርሱም "ቀጥዪ. . . በእያንዳንዱ ምሽት ሌላ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ይገባኛል፡፡" አለኝ

ቤተሰቦቻችንን ማየትና መርዳት አለመቻላችንን ሳስበው በጣም ከባድ ስለሆነብኝ ነው፡፡ ይህ በእውነት እኔን የማይለቅ ነገር ሆኖብኛል፡፡

"ምክንያቱም ከዛ ጋር በጣም ከመጣበቅሽ የተነሳ እያንዳንዱ ነፍስ ለመቀደስ መጓዝ ያለባትን መንገድ ስላልገባሽ ነው፡፡ ለዚህ ነው ትላንትና በመንገዳቸው ላይ ነው የምትቆሚው ያልኩሽ፡፡ በህይወታቸው ውስጥ ከእኔ መኖር ይልቅ የአንቺ መኖር የበለጠ የሚጠቅም ይመስልሻል?"

በፍፁም! ነገር ግን እንደማስበው የሁለታችንም . . . ጥሩ ይመስለኛል. . .

"አየሽ ያንን ለምን እንደማልፈቅድ?"

ዝም ብዬ ስገምተው አብሬያቸው ብሆን ምናልባት ትልቅ ችግር እሆንባቸዋለሁ፡፡

"ክሌር አንዳንድ ጊዜ እንድታበረታቻቸው ይፈቀድልሽ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ይህንን የምሰራው በራሴ መንገድ ነው፡፡"

ጌታ ያንተን መንገድ ተቀብያለሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ ሐሳብ ላይ የመጨረሻዬ እንዲሆን እባክህ እርዳኝ፡፡

"እርዳታሽ ዱሮ መጥቷል፡፡ በመንግስተ ሰማይ ደግሞ ትልቅ ሥራ የሚበዛብሽ ሴት ስለምትሆኚ ፍርሃትሽን ለማጥፋት ይህ ይረዳሻል፡፡"

ይህ ምናልባት የማይረባ ጥያቄ ሊሆን ይችላል ግን በመንግስተ ሰማይ ጠላት የምናስበውን ነገር ሊያቃውስ ይችላል?

"አይ ይህንን ለማድረግ አልተፈቀደለትም፡፡ እንዲህም በመሆኑ በመንግስተ ሰማያት የማሰብ ነፃነት ስለሚኖርሽ በምድር በነበርሽ ጊዜ ከጨለማ ኃይላት ሲሰነዘርብሽ የነበረው ጭቆና ምን ያህል ከባድ እንደነበር ትረጃለሽ፡፡"

ስለዚህም የትኛውም ስርዓት የሌለው አስተሳሰብ በመንግስተ ሰማይ እያለን ቢመጣ ሁሉም ከእኛ ነው ማለት ነው?

"ክሌር በመንግስተ ሰማይ ምንም ስርዓት የሌለው አስተሳሰብ የለም፡፡ እውነትና ግልፅነት ብቻ ነው ያለው፡፡ ካላየሽው በስተቀር ልታውቂው ስለማትችዪ ምን ዓይነት ይሆን ብለሽ ለማሰብ እንኳን እንዳትሞክሪ፡፡

እሺ፡፡

"እንድትበሳጩ ወይም እንድትሰጉ አልፈልግም፡፡ ሁሉም ነገር ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ የሚካሄድ ነገር ነው፡፡ ለዘላለም ህይወት የሚያስፈልጋችሁ ነገር ሁሉ ተዘጋጅቶ ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡

ጌታ ሌላ የምትለን ነገር አለ?

"አድማጮችሽን ብዙ የቀረ ጊዜ እንደሌለ ንገሪያቸው፡፡ ለሚወዷቸው ትተውላቸው የሚሄዱትን ጥቅል ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሚወዱት የሌላቸው ደግሞ በአካባቢያቸው ላሉት ጥቅሉን ያዘጋጁና ይተዉ፡፡ ለሌሎች በማሰብ ለሚመጣው መከራ እንዲዘጋጁ ማድረግ ብዙ ቅባት ይጨመራል፡፡ በዚህ ዓይነት ደግነት ብዙዎችን ተስፋ ከመቁረጥ ትታደጋላችሁ፡፡ በኋላም ከግራ መጋባት ስላወጣችኋቸው ያመሰግኗችኋል፡፡

"እባካችሁ ታማኝ በመሆን አዘጋጁ፡፡"

"ነገ የበለጠ እወዳችኋለሁ"

እኔም እወድሃለሁ፡፡ ጌታ በቅርቤ ሁን

"ቅርብሽ ነኝ"

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት አሥር - ማርች 15 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the rapture event 10 - March 15, 2015

ክሌር፡- ጌታ ፕሬዚዳንት ትራፕ የጥልቁን መንግስት ክፉ ተግባራት እንዲያጋልጥ በስልጣን ላይ አስቀምጦታል፡፡ እናም መፀለያችንን ብንቀጥል የሁለት አመት ሰላም በምድር ላይ ይሆናል፡፡ መንግስቱንም ለሁለት ዓመታት በምድር ላይ ይፈትናል፡፡ እነዚህንም መልዕክቶች ለማግኘት ከቪዲዮው መጨረሻ ላይ በተገለጡት ድህረ ገፆቹ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ አሁን ወደ መልዕክቱ እንሂድ፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "የውቅያኖስ ነውጥ "፡፡ አገራችሁ አሜሪካ እየተነጋገርን እያለን ወደ ውቅያኖስ ነውጥ ውስጥ እየገባች ነው፡፡ ይህም ነውጥ እንዲሳካ ሁሉ ነገር ተስተካክሎ ተቀምጧል፡፡ የሚቀረው ምድሪቷን በድንገት አጥቅቶ ተግባርያዊ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ቀጠሮ ተይዞለታል፡፡ ይህችን ምድር ለማንበርከክ ብዙ ክስተቶችን በአንድ ጊዜ ለመፈፀም ሁሉ ነገር በደንብ ተቀነባብሯል፡፡ ለዚህም ጉዳይ የሰለጠኑት ኑ ተብለው እስኪጠሩ ድረስ በየጥጋ ጥጉ እየጠበቁ ናቸው፡፡

"ምንም መጥፎ ወሬ መስማት የማይፈልጉ ብዙዎች ማየት በማይችሉትና ባልጠበቁት መንገድ ተይዘው ሊጠመዱ ነው፡፡ ብዙዎች መሪዎቻቸው ምን ያህል የተባላሹ እንደሆኑ ምንም እውቀት የላቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ በኒውዩርክ ገበያ ማዕከል የደረሰው ድንገተኛ አደጋ በአሜሪካ መንግስት በተደረገ ሴራ እንደሆነ የሚያምኑትን እንዴት የራሳችሁን መንግስት እንዲህ ትላላችሁ በማለት እንደ እብድና ያለተለመደ አስተሳሰብ ያላቸው አድርገው ቆጥረዋቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ህይወታቸው የሚያጠነጥነው በዙሪያቸው ባለው ምቾትና የኑሮ ደረጃ በመሆኑ ምን እየመጣ እንደሆነ ማየት ተስኗቸዋል፡፡ ስለዚህም በሚመጣው ነገር እጅግ ግራ የሚጋቡት እነሱ ናቸው፡፡ በእነርሱ ላይ እየተፈፀመ ያለው በሚሊዮን ዓመት ውስጥ እንኳን ይደረጋል ብለው በፍፁም አያምኑም ፡፡ በዛው አንፃር ግን ይፈፀማል ብለው ያላሰቡት በሚያሳስብ ደረጃ በእርግጥ እየተከናወነ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን እነሱ ምንም ትኩረት አልሰጡትም፡፡"

"ቦንቡ በወደቀ ጊዜ በህዝብ ላይ ግራ መጋባትና ድንጋጤ ይሆናል፡፡ የብዙ ሰዎች የቤተሰብ አባላት መጥፋት ድንገተኛ የልብ ድካም ሞትንና እራስን በራስ ማጥፋት ያስከትላል፡፡"

"እንዲህም ሆኖ ግን ከአደጋው የሚተርፉና አጥሩን ጥሰው በመውጣት ለነፃነታቸው ተነስተው የሚዋጉ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ እጅግ ዘግይተዋል፡፡ ነፃነታቸው ቀድሞ ተወስዷል፡፡ አሁን ማድረግ ያለባቸው የወደፊቱን ይህም የመንግስተ ሰማይ ህይወታቸውን ማረጋገጥ ነው ፡፡ ይህም ስለ መዳናቸው፣ ንስሐ ስለ መግባታቸውና በሁሉ ነገር በእኔ ላይ መደገፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ነገር ግን በእኔ እርዳታ ሳይሆን በራሳቸው አይምሮ በመመራት መሳሪያ አንስተው ለመዋጋት የሚያስቡ ይወድቃሉ፡፡ በዚህ ምድር ላይ የመጣውን ማንኛውንም ነገር ሊያሸንፉ የሚችሉት እኔን የሚያውቁኝና የእኔ የሆኑ፣ በዚህ ምድር ለትክክለኛው ነገር እንዲዋጉ በእኔ የተጠሩ ወንዶችና ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ብቻ ናቸው ማንኛውንም እንግዳ የሆነ ነገርን ሁሉ ሊያሸንፉ የሚችሉት፡፡"

"ስለዚህም ለብቻችሁ ይህንን ለመፈፀም ያሰባችሁ በሚያሳዝን ሁኔታ ተሳስታችኋል፡፡ እስካሁን ከተዘጋጁት ጋር በመሆን በሥልጣን ሥር ሆናችሁ ሥሩ፡፡"

"ጌታ አገሪቷን ለመመከት እነዚህ የተመረጡት የአንተ ከሆኑ ለምን ሳይነጠቁ ይቀራሉ?"

"ይህ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ የኔን ሙሽራ ባህርይ ታውቂያለሽ?"

የማውቅ ይመስለኛል፡፡

"ጠረኛ ነች?"

እንዳውም አይደለችም፡፡ እርሷ በፊልሙ እንዳየኋት አይነት ቄስ ነች፡፡ ሊገድል የተቀጠረው ወታደር በፊቱ ያገኘውን ሰው ሁሉ እየተኮሰ ሲገድል ቀጥ ብሎ ወደ ገዳዩ እንደሄደው፣ ከዚያም በጥይቱ ተበሳስቶ እንደተገደለው ሚሽነሪ ዓይነት ናት፡፡

"ትክክል ነው፡፡ እነዚህ ዓይነት ሙሽሮች ናቸው እኔን ሊገናኙኝ የሚመጡት፡፡ የኔ ሙሽራ ባህር ይህ ነው፡፡ እርሷ አፍቃሪ ነች እንጂ ተዋጊ አይደለችም፡፡ እርሷ የምትዋጋው ከራሷ ኃጢያት ጋር ብቻ ነው፡፡"

ነገር ግን ቀደም ባለው መልዕክትህ ለውጊያ የተመረጡ እንዳሉ ተናግረሃል፡፡

ይህ የአንዳንድ ነፍሶች ባህርይ ነው፡፡ እነዚህ ነፍሶች አፍቃሪ ለመሆን ተዋጊ ይሆናሉ፡፡ እነዚህንም እወስዳቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ነፍሶች ተፈጥሮአቸው እጅግ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ባህርያቸው መዋጋት ነው፡፡ እነዚህም በመንግስቴ ውስጥ ሥራና ሥፍራ አላቸው፡፡ በመጨረሻውም የፍቅር መንገድ ይገባቸዋል፡፡ መላዕክቶቼ የፍቅር መንገድ በደንብ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ክብሬንና መንግስቴን መጠበቅ ግዴታ ስለሆነባቸው ለመዋጋት ተነስተዋል፡፡ ጦርነቱ ሲያበቃ ግን ማለቴ ሁሉም ጦርነት ሲያበቃ መዋጋት ያቆማሉ፡፡ ምክንያቱም የሚዋጉት ምንም ስለማይኖር መዋጋት አያስፈልጋቸውም፡፡ ነገር ግን ያ ጊዜ ገና አልደረሰም፡፡

ጌታ አንድ ያልገባኝ ነገር አለ፡፡ በመጨረሻው የጥፋት ወቅት ጊዜ አትላንቲስን፣ ዳይናሶርንና ሌላውን ሁሉ ስታጠፋ አብረህ ሁሉን ለምን  አላጠፋኸውም?

"የኔ ፍቅር ይህ ለአንቺ አሁን አስፈላጊ መረጃ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመንግስተ ሰማይ ሁሉም ነገር ግልፅ ሆኖ ይገባሻል፡፡እሺ፡፡"

ጌታዬ አንተ በጣም የምትወደድ ነህ፡፡ ጥያቄ እንድጠይቅ ሁልጊዜ ትፈቅድልኛለህ፡፡

አንቺ እኮ የኔ ትንሿ ልጄ ነሽ፡፡ ደግሞም እያደግሽ ስለሆነ በምንም ዓይነት መልኩ ጥያቄሽን እንዳትጠይቂ በማድረግ ተስፋ አላስቆርጥሽም፡፡  እሺ አሁን ወደ እቅዱ እንመለስ፡፡

ወደ እቅዱ ?

"አዎ፡፡ ለመጉዳትና የራሳቸው የግል ፍላጎት ለማርካት ወደ ሰለጠኑት፣ አይምሮአቸው በስስት ተበልቶና ተደፍኖ ስለ ተበላሸው፣ ወደ ክፉና ወደ ገዳዮቹ እቅድ፡፡ የሚፈሩት ነገር እነሱ ላይ ይደርሳል፡፡ በምንም ዓይነት መልኩ ቢሆን ከሚመጣው የእሳት ቃጠሎ አያመልጡም፡፡"

"እውቀት በማጣታትና በራሳቸው ላይ በመታመን ሁኔታዎች ሁሉ እነሱ እንዳሰቡት የሚሆን መስሏቸዋል፡፡ ከእውነት ምን ያህል ርቀው እንዳሉ ምንም ፅንሰ ሐሳቡም የላቸውም፡፡ ከአንዱ እቅድ ወደሌላው እቅድ በተላለፉ ቁጥር ስግብግብ እቅዳቸው የሚያስከትለውን ከባድ አሉታዊ ውጤት ለማወቅ ምንም ፍንጭ የላቸውም፡፡ እነሱ የሚመለከቱት በአጭር የሚያገኙትን ነገር ነው፡፡ ነገር ግን በሰው ልጆች ላይ ያውም በራሴ ሐምሳል በፈጠርኩት ፍጥረት ላይ የሚፈፅሙትን አሰቃቂ ኃጢያት አልተገነዘቡም፡፡ ቀኑም እጅግ ሐዘን ይሆንባቸዋል፡፡"

"የኔ ፍቅር በተለይም የማስጠነቅቀው በመከራው ዘመን በዚህ የሚቀሩትና በራሳቸው መሳሪያን በማንሳት ሊዋጉ የሚፈልጉትን ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ከባድና አስቀያሚ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ለአሁኑ ግን መሆን ያለበት እርስ በርስ መያያዝ፣ መፀለይና በሁሉም ፊት ሊመጣ ስላለው ነገር አንዱ ሌላውን ማፅናናት ነው፡፡"

"ለተስፋ፣ ለፍቅርና ለደህንነት እርስ በርስ የመያያዝ ጊዜ ቢኖርም በመካከላቸው ግን ከዳተኞች ይኖራሉ፡፡ በመንፈስ ብቻ ነው አንዱ ሌላውን ነፍስ ሊያውቅ የሚገባው፡፡ ሥጋ ይዋሻል ደግሞም ያታልላል፡፡ ነገር ግን መንፈስ እውነት ለሆነው ምስክርነት ይሰጣል፡፡ ለዚህ ነው መፀለይና ከእኔ ጋር ህብረት ማድረግ ፍፁም አስፈላጊ የሚሆነው፡፡"

"እኔን መጀመሪያ ሳታማክሩ ምንም ነገር እንዳታደርጉ!"

"በመጀመሪያ እኔን ሳታማክሩ ማንንም ሰው እንዳትቀበሉ፡፡ ምክንያቱም በሰው ልብ ውስጥ የተደበቀውን የክፉ አጀንዳ እኔ እገልጣለሁ፡፡"

ክሌር፡- እዚህጋ መናገር የምፈልገው ለአንዳንድ ነገሮች ዕጣን እንዴት አድርገን እንደምንጠቀም ነው፡፡ ዕጣን መጠቀም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ለምሳሌ ጌታን የሸጠውን ይሁዳን ማን እንደሚተካው ለማወቅ ደቀመዛሙርት ዕጣ ተጠቅመዋል፡፡ እንዲሁም ዮናስ የነበረችበት መርከብ ስትናወጥ ችግሩ ማን ላይ እንደሆነ ለማወቅ ዕጣ በማውጣት ዕጣው ዮናስ ላይ ወድቀቋል፡፡ እኛም ይህንን ተከትለን በመፅሐፍ ቅዱስ ተስፋ የተገቡልንን ቃሎች በመፃፍ በመፀለይና መንፈስ ቅዱስን በመጠየቅ የትኛውን የቃሉን ክፍል እንደምናነብ ምሪትን እንጠይቃለን፡፡ ደግሞም ጌታን ጥያቄዎችን እንጠይቅና የመፅሐፉ ቅዱስ ቃሎችን ለምሳሌ ውሸት፣ የሥጋ ምኞት፣ ቅናት፣ ደስታ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ስናገኝ ይህም ያለንበትን ሁኔታ ወይም የእቅድን ተግባር ሊያሳየን ይችላል፡፡ በዚህም አሰራር ዕጣን አንድን ነገር ለመለየትም መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ለምሳሌ በምትሰሩት ሥራ ላይ ማን ተሳታፊ እንደሚሆን ማን ደግሞ ተሳታፊ እንደማይሆን ለማወቅ ስሞችን በቁራጭ ወረቀት በመፃፍና ዕጣውን በማውጣት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ይህንን መልዕክት ለማጠቃለል እርስ በርስ ተያያዙ፣ ለፀሎት ከፍተኛ ሥፍራ ስጡት፡፡ ምክንያቱም ከፀሎት ውጪ በጨለማ ውስጥ ያሉ ቡድኖች ብቻ ትሆናላችሁ፡፡ በሰው ጥበብ ላይ አትደገፉ፡፡ በእኔ ላይ ብቻ ተደገፉ፡፡ ደግሞም መንፈሴ መመሪያ ይሰጣችኋል፡፡ ይህም በትልቅ ንፋስ ሳይሆን በለሰለሰ ትንሽ ድምፅ፣ ረጋ ባለ ግፊት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ይመራችኋል፡፡

"ይህንን አስታውሱ፡፡ ሰውነታችሁን ብታጡ ጊዜያዊና የብልጭታ ክስተት ስለሆነ የሚያሳስብ አይደለም፡፡ ነገር ግን ወሳኝና ዘላለማዊ የሚሆነው የነፍሳችሁ ጉዳይ ነው፡፡ ከልጆቻችሁ ወይም ከወላጆቻችሁ ጋር እንዲሁም የምትወዷቸውን እንስሳቶች እንደገና ትገናኙ ይሆን የሚለው ነው፡፡ ዋናው ወሳኙ ነገር እኔ ለወደቁትና ለአመፀኞች መላዕክት ባዘጋጀሁት እሳት ውስጥ መጣል ወይስ ማርና ወተት ወደምታፈልቀው፣ የዘላለም ደስታ ተገባላችሁን  ወደተገባላችሁ የተስፋ ምድር ለዘላለም መውረስ? ነገር ግን በፍፁም እንዳትሳሳቱ፡፡ በምድር የኖራችሁት ኑሮ ለዘላለም ከምትኖሩበት የዘላለም መኖሪያችሁ ጋር በምንም ነገር ሊወዳደር የሚችል አይደለም፡፡"

"ምንም ነገር ቢሆን ፍፁም ምንም ነገር ነፍሳችሁን ለዘላለም ገሃነም አሳልፋችሁ እንድትሰጡ የሚያደርግ ነገር ሊኖር አይገባም፡፡"

## ከንጥቀት በኋላ የሚከናወን ክስተት አሥር አንድ - ማርች 16 ቀን 2015 ዓ.ም

## What is to come after the Rapture, event event 11 – March 16, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች.  . . ጌታዬ ምንድነው ነገሩ? አንዳንድ ቀን ቶሎ እንደምትመጣ በከባዱ ይሰማኝና በማንኛውም ደቂቃ የምትመጣ ይመስለኛል፡፡ አንዳንድ  ቀን ደግሞ የመምጣትህ ነገር ከውስጤ ይጠፋና ነገሮች እንደነበሩ የሚቀጥሉ ይመስለኛል፡፡

"ይህ የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡"

ነገር ግን እኔ አልወደድኩትም፡፡ መቼ እንደሆነ ያለማወቅ በጣም ያማል፡፡

"ምን መስራት እንዳለብኝ ማወቁ ለእኔም ህመም ነው፡፡ የራዕይ መፅሐፍ እንዲፈፀም አልፈልግም፡፡ ነገር ግን እኔ መጥቼ በምድር ለመግዛት ደግሞ በግዴታ መጀመሪያ መሆን ያለበት መፈፀም አለበት፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም መፈፀሙ አስፈላጊ ቢሆንም መፈፀም ያለበት ግን የኔ ፈቃድ ሳይሆን የአባቴ ፈቃድ ነው፡፡"

"እንዲህም ቢሆን ግን ይህ ነገር መሆኑ በጣም በጥልቀት ያማል፡፡ ነገር ግን የኔ ውድ ይህንን አንቺ እንድታዩው አልተፈቀደልሽም፡፡ አንቺ እንደሌላው አለም ይህንን በማየት ራስሽን መለወጥ አያስፈልግሽም፡፡ ሙሽሮቼ በእኔ ጎን ተሰባስበው መጥቼ እንድወስዳቸው የኔን መምጣት እየተጠባበቁ ነው፡፡ ነገር ግን ራዕዩ መፈፀም ያለበት ለማይበገሩት፣ በኩራት ለተሞሉት፣ ለዕብሪተኞች፣ በራሳቸው ለሚተማመኑና በራሳቸው ለረኩ፣ በተለያየ ምኞትና በከፍተኛ ፍላጎት አይናቸው ለታወረ ነው፡፡ በእነዚህ ላይ ነው ራዕዩ መፈፀም ያለበት፡፡"

እዚህጋ ትንሽ ጊዜ ልውሰድና አንድ ነገር ልበል፡፡ እኔ በግማሽ ጎኔ ከልጆቼ ጋር ባለ ጉዳይ ያለብኝን የአለም ነገር ላጫውታችሁ፡፡ ከመጀመሪያው ባሌ የወለድኳቸውን ልጆቼን እኔ ሳልሆን ያሳደጋቸው አባታቸው ነው፡፡ ጋብቻችን የተቀደሰ ጋብቻ አልነበረም፡፡  ትዳራችን ለሁለታችንም ቀንበር የሆነብን ነበር፡፡

በቀድሞ ባለቤቴ ላይና በልጆቼ ላይ ምናልባት ከአንዱ በስተቀር ኑሮ እጅግ ከባድ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ አሰቃቂ የሚባሉ ነገሮችን ለምሳሌ በአንድ ህብረተሰብ የሚገኙትን ወንዶች፣ ሴቶችና ህፃናት መግደል ለምን ይፈቅዳል ? ለሚለው

ጥያቄያቸው ማስረዳት ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ ሰዎች ኃጢያት ለመስራት ሰበብ ይሆንላቸዋል፡፡ 'እግዚአብሔር ይህንን አድርጓል፣ ያንን አድርጓል ስለዚህም በእርሱ አላምንም ፡፡ እርሱ ፍቅር ቢሆን ኖሮ፣ መልካም ቢሆን ኖሮ እንደዚህ አያደርግም ነበር' ይላሉ፡፡

ይህንን ነገር ስንት ጊዜ እሰማ እንደነበረ ልነግራችሁ አልችልም፡፡ ስመልስላቸው የነበረው ታዲያ ዛሬ ማታ ጌታ የተናገረውን የሚመስል ዓይነት መልስ ነበር፡፡ እስካሁን ጌታ ጨካኝ የሚመስላችሁና ወይም ደግሞ እርሱ ምድርን የማይቆጣጠር የሚመስላችሁ፣ አዎ ምናልባት በአንድ ነገር ልክ ናችሁ፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር 'አይቆጣጠርም'፡፡

እርሱ የሚፈቅደውና የማይፈቅደው ነገር አለ፡፡ በዚህ በኩል ልክ ነው፡፡ ነገር ግን ሰይጣንና የሰው ፈቃድ ነው ነገሮች እንዲከናወኑ የሚያደርጉት፡፡ ቁልፉን ለመጫን ወይም ላለመጫን የሰው ፈቃድ ነው የሚሰራው፡፡ ቦንብ ለመስራት ወይም ላለመስራት እንኳን ፈቃዱ የሰው ልጆች ነው፡፡

ጌታ በእኛ ነገር ጣልቃ ገብቶ ስንት ጊዜ ከአደጋ እንዳስመለጠን አውቃለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜም የሰውን ፈቃድ እንኳን በመጣስ ይህንን ያደርጋል፡፡ አሁን ግን የራዕይ መፅሐፍ ተፈፃሚ መሆን አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህም ጌታ ወደ ምድር መጥቶ መግዛት እንዲችል ነው፡፡ ዛሬ ስለዚህ ነገር ነው ትንሽ ሊነግረን የሚፈልገው፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔር ጨካኝ ነው ለምትሉና የእርሱ አካሄድ ላልገባችሁ ለእናንተ ምናልባት ይህ መረዳትን ይፈጥርላችሁ ይሆናል፡፡ ጌታ እዚህጋ የሚለው ሙሽሮቹ የራዕይ መፅሐፍ ተፈጻሚ ሲሆን በማየት ትኩረታቸውን ለመሳብ አያስፈልገውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በእርሱ ዘንድ በመገኘት ለመታዘዝ ተዘጋጅተዋል፡፡

ነገር ግን ቀሪው አለም፣ አለምን የሚቆጣጠሩ፣ ገዢ ምሁሮች፣ የማይበገሩ፣ ኩራት በውስጣቸው የሞላ፣ በራሳቸው የሚተማመኑና ራስ ወዳዶች የአስተሳሰባቸውን ውጤት ማየት አለባቸው፡፡ ከዚህም በላይ ብዙ ማለት እችላለሁ፡፡

ጌታ እጅግ ጠንካራ ሆነውብህ መሆን አለበት እነርሱን ለማሳመንና ለመቀየር ይህንን መንገድ የመረጥከው፡፡(ጌታ የሚያወራው የመከራውን ዘመን ነው)፡፡

ኢየሱስ እንዲ በማለት ቀጠለ. . ."ማንም ገዳይ የሆኑ እንስሳትን ከምድር በታች የሚያራባ፣ ወረርሽኝና ቸነፈርን በማምጣት አለምን ለመቆጣጠር የሚያስብ ሁሉ ጠንካራ የአመለካከት ማስተካከያ ያስፈልገዋል ! ይህም እኔ ካቀድኩት ያነሰ የትኛውም ነገር አይመልሰውም፡፡"

"አባቴና እኔ የተለያዩ አማራጮችን በማውጣት በማውረድ የመጨረሻ ትንሽ ጥፋት የሚያመጣውን የመረጥን አይመስላችሁም? ትንሽ የሚያስቆጣ? ትንሽ የሚጎዳ?"

ክሌር፡- አዎ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ይህ የአንተ ተፈጥሮ ስለሆነ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመሆንህ ነገሮችን ማውጣት ማውረድ ባይጠበቅብህም . . .

"አዎ እኛ (አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ተነጋግረንበታል፡፡ በእውነት ተነጋግረናል፡፡ ብዙ ነገሮችን በመውሰድ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡አንዱን እንኳን ወስደን ብናይ እኔ ከአስርት ዓመታት በፊት ንፁህ የሆነ ቴክኖሎጂ ሰጥቻቸው ነበር፡፡ ነገር ግን እነሱ እኔ ከሰጠኋቸው ይልቅ የሚጣሉበትን ቴክኖሎጂ መረጡ፡፡"

"በእነሱ ውስጥ ያለው የግል ፍላጎት እጅግ የላቀ ነው፡፡ አይናቸው በፍፁም ስለታወረ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው የሚበጀውን መልካም ነገር እንኳን መለየት አይችሉም፡፡ በአለም ሁሉ ላይ የሚነሳው ችግር የኃይል አቅርቦት ምንጭ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ነፃ ስጦታ የሆነውን የኃይል አቅርቦት ለመቀበል አልቻሉም፡፡ እነሱ ያንን በመጨቆን፣ የኃይሉን ምንጭ ለጦርነትና ለሰው ልጅ ጥፋት የሚውል የጦር መሳሪያ ግንባታ እንዲውል በማድረግ ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲውል የሰጠሁትን የኃይል ምንጭ አግደዋል፡፡ እንዴት የተጣመሙ እንደሆኑ ታያለሽ?"

አዎ ጌታዬ ተረድቻለሁ፡፡ ነገር ግን ምንም የማያውቁ ንፁህ የሰው ልጆች መሰቃየታቸው የሚያሳፍር ነው፡፡

"ነገር ግን የሰው ልጅ ሲባል ከላይ ጀምሮ እስከታች እስከዚህ ንፁህ የሚባል የለም፡፡ የወሲብ ድርጊቶችን ማየት፣ የባርያ ጉልበት፣ የወሲብ ሽያጭ፣ ከድሆች ላይ ከዚያችው ካለቻቸው መስረቅ፣ እንዲሁም ድሆች እርስ በርሳቸው መሰራረቅ፡፡ ከታች እስከላይ ያለው ሁሉም አንድ ላይ የተበላሸና የሸተተ ነው፡፡ ራስን የመውደድ የሰው ተፈጥሮ ነው በእግዚአብሔር ሊጠበቅ የሚያስፈልገው፡፡ ሰው ሰውን ሊጠብቀው ወይም ሊቆጣጠረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሰው ለመበላሸት ቅርብ፣ ደካማና ለራሱ ጥቅም ሲል ትክክል ያልሆነን ነገር ለመስራት ቀድሞ የሚስማማ ነው፡፡

"አየሽ ወደዚህ ደረጃ ዝቅ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም እኔ ተመልሼ ሰው ለራሱ የፈጠረውን የተበላሸ፣ የተበከለ፣ ዝቅ ያለውን ሁሉ በማጥፋት ምድርን እንደገና መሙላት አለብኝ፡፡ አሁን ጊዜው ሩቅ አይደለም፣ የኔ ትንሽዬ እባክሽ ጠብቂኝ፡፡ ሩቅ አይደለም፣ጠብቂኝ፡፡ ሩቅ አይሆንም፡፡

ዛሬ ማታስ የእርሱን መምጣትና ከእርሱ ጋር መሆንን እጅግ ፈልጌያለሁ፡፡ ይህንን መቀበል አለብኝ፡፡ ስለዚህም በትንሽ መሰዋዕ ሥፍራ ሆኜ አነባሁ፡፡ ምክንያቱም እጅግ ስለናፈቀኝና ከእርሱ ጋር መሆን በጣም ስለምፈልግ ነው፡፡ ይህም አለም እጅግ የተመሰቃቀለ ነው፡፡ ነገር ግን የመምጣቱ ነገር ሩቅ አለመሆኑን መናገሩ ትንሽ የሚያበረታታ ቃል ነው፡፡

ኢየሱስ ይህ ነገር ለዘላለም ይመስላል፡፡ ደግሞም በየቀኑ እያረጀሁና በየቦታው እያቆጠቆጠ ባለው ብክለት የበለጠ ከተሳሳተ ሐሳቤ እየተመለስኩ ነው፡፡

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ብርታት ሰጥቼሻለሁ፡፡ ስለዚህም እስካሁን ማለፍ እንደቻልሽው ሁሉ አሁንም እነዚህን ነገሮች ተቋቁመሽ ማለፍ ትችያለሽ፡፡ እንድትወድቂ ወይም ዝልፍልፍ እንድትዪ አልፈቅድም፡፡ የኔ ውድ ወደላይ አነሳሻለሁ፡፡ "

ዛሬ ታዲያ ስለምንድነው መናገር የፈለከው ?"

"የሚያስከትለውን የውጤት አስፈላጊነት ነው ለማውራት የምፈልገው፡፡"

"በሰውና በሰይጣንና የሚከናወኑ ድርጊቶች የኔንም ሥራዎች ወደ ፍፃሜ ያደርሳሉ፡፡"

ይህ አግባብ አይደለም!

"ያንን አውቃለሁ፣ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ብቻ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሊመጣ ያለው ነገር የእያንዳንዱ ሰው አስተዋፅዎ እንዳለበት ማየት አቅቷቸዋል፡፡ አንድ የመጠጥ ሱሰኛ ለእሱ መጠጣት ማንም ተጠያቂ መሆን ባይችልም እርሱ

ግን ሁልጊዜ ምክንያቶችን እየፈጠረ ሌሎችን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሚከሰው ዓይነት ማለት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ወንጀለኛውን ከመጠቆም ይልቅ እኔን መውቀስ ይቀላል፡፡"

ጌታ እነሱ ሁልጊዜ የሚያነሱት ለእስራኤሎች ቃል የገባህላቸውን ምድር ስታወርሳቸው እስራኤሎች ወንዶችን ፣ ሴቶችንና ልጆችን ሁሉ እንዲገድሉ ያደረከውን ነው፡፡

"አዎ ምክንያቱም አጋንንቶች ከሴቶቹ ጋር ወሲብ ሲፈፅሙ እነርሱ አልነበሩም፡፡ ለአምላካቸው ለሞሎክ ወይም ለሰይጣን መስዋዕት ለማቅረብ ልጆች ኃይለኛ ለሆነ እሳት ሲሰጡ እነርሱ አልነበሩም፡፡ እነዚህ ትንንሽ ህፃናት ከህመሙ የተነሳ አምርረው ሲያለቅሱ እነርሱ አልነበሩም፡፡ የነበራቸውን ሁሉ ለሰይጣን ስለት ሲሰጡ እነርሱ በዛን ጊዜ አልነበሩም፡፡

"በመንፈሳዊ አሰራር ካንሰርንና ሌሎች በሽታዎችን የሚያመጡ ነገሮች በወንዶች፣ በሴቶች፣ በህፃናትና በእንሰሳ ላይ ሲቀብሩ እነሱ አላዩም፡፡ ቢያንስ ህፃናቶቹ ከእኔ ጋር በሰማይ ናቸው፡፡ ቢያድጉ ኖሮ በእርግጠኝነት ሌሎች ምንም የማያውቁ ህፃናትን በማሰቃየትና በጭካኔ በመግደል በገሃነም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በተጣሉ ነበር፡፡"

"አለም የማያውቀውና የማያየው ብዙ ነገር አለ"

"ለሰዎች የሚቀለው ግን በሆነባቸው ነገር እግዚአብሔርን መውቀስና በለመዱት የኃጥያት የኑሮ ዘይቤ በመቀጠል ምርጫቸው ተገቢ እንደሆነ ለማሳመን እግዚአብሔርስ መቼ ትክክል ነው? ወይም እርሱን ሰምቶ መታዘዝ ዋጋ የለውም በማለት ምክንያት ያቀርባሉ፡፡"

"ሁሉም እንደዚህ ዓይነት አመለካከት የላቸውም ፡፡ አንዳንዶቹ በፅድቅ የሚኖሩና ነገር ግን በሃይማኖት ጦርነትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እኔን የሚወቅሱ ናቸው፡፡ ነገሩ በእውነት በማን እንደሚሰራ በትክክል ማየት አይችሉም፡፡

"ነገር ግን በእውነት የሚወዱኝ ያውቃሉ፡፡ እነሱ መልካም ይሁን ክፉ ለይተው ያውቃሉ፡፡ በሚገባ ያውቁኛል፡፡ በተወሰኑ ቡድኖች ላይ እንኳን ሰይፌን ብመዝ በእኔ ላይ እምነት አላቸው፡፡ እነዛ ሰዎች የአይምሮአቸው ዝንባሌ የገሃነም እንደሆነና ለሰይጣን እንደሚኖሩ፣ ደግሞም የሰይጣን የህይወት ዘይቤ እንደሚሰብኩ ያውቃሉ፡፡

"በዚያን ጊዜ እንኳን እስራኤሎች የማያምኑትን የአኗኗር ዘይቤ ስለተከተሉና እንዲሁም እነዚህን ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ ስላስገቡ መውደቂያቸው ሆኗል፡፡"

(ክሌር) ከዚህ ጋር የሚሄድ አንድ ነገር ብናገር፡፡ በሰለሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ ብዙ ሚስጥራዊ የሆኑ ክፍሎች ተገኝተዋል፡፡ አስከፊ ነገር እየተካሄደ እንደነበርም ነቢያቶች ተናግረዋል፡፡ ይህም አስከፊ የሆን አምልኮ በእነዚህ ሚስጥራዊ ክፍሎቹ ውስጥ ይካሄድ እንደነበረ ነው፡፡

"መልካምንና ክፉን በአንድ ላይ ማስኬድ አይቻልም፡፡ አንዱ ሌላውን ይሰርዘዋል፡፡ ፈሪሳውያኖቹ አጭበርባሪዎች ሆነዋል፡፡ ምክንያቱም በገንዘብና በመግባባት ምክንያት ሰለሞንና ሌሎቹ በቤተ መቅደስ ውስጥ "አምላካቸውን" ያስከበረ ሚስጥራዊ የሆነ ክፍሎችን እንዲገነቡ ፈቅደዋል፡፡ ይህም ሰለሞን ባገባት በመጀመሪያ አረማዊ ሴት ምክንያት ለጥፋት ምክንያት ሆነ፡፡

"አንድ የተበላሸ አፕል በርሜል ውስጥ ያለውን ሁሉ እንደሚያበላሸው ይህ ለእናንተ ትምህርት ይሁናችሁ፡፡ ለወንድ እንደ ሴት ውበትና ማፅናናት የመሰለ ነገር የለም፡፡ ይህም ታሪክን በብዙ መልኩ የቀየረና ለብዙ ስልጣኔ ውድቀት የሆነ ነገር ነው፡፡"

"ስለዚህ በአለም ለሚገኘው ክፉ እኔን መውቀስ ካለማወቅና ከኩራት የተነሳ ነው፡፡ ሰው በራሱ ላይ ምን እያደረገ እንደሆነ አላወቀም ወይም አልገባውም ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እቅዱ እንዲበላሽና ለመስተካከልም እንደማይፈልግ የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህም ዘንጉን በተቃራኒው በመግፋት የእርሱ የኃጢያት ህይወት ቀጣይነት እንዲኖረውና ትክክል እንደሆነ ለማሳመን እኔን ይወቅሳል፡፡ የኔ ውድ ለዚህ ነው በራዕይ መፅሐፍ የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ መፈፀም ያለባቸው፡፡ ሰው በራሱ ላይ ምን እንዳደረገና በመጨረሻም የት እንዳደረሰው ማየት አለበት፡፡

"የማደርገው ነገር ሁሉ ከቁጣ አይደለም፡፡ ማለትም ሰው ቁጣዬን ያየዋል፡፡ ነገር ግን ሰው እንደሚለው ይህንን የማደርገው ከበቀል የተነሳ ሳይሆን ለማስተማር ነው፡፡ ይህም በሚያም መንገድ ማስተማር ነው፡፡ ይህም ራሳቸው ባዘጋጁት አልጋ ላይ መተኛት አለባቸው፡፡ በዚያ ሁኔታ እንኳን ከምህረቴ የተነሳ ጣልቃ ገብቼ ብዙ ነገሮችን ባልከለክልላቸው ብዙ ዘግናኝ የሆኑ ነገሮች ይከሰቱ ነበር፡፡ በሰማይ ስትሆኚ ብዙ ነገር ግልፅ ይሆንልሻል፡፡ በዛ ብዙ ነገር እየገባሽ ይሄዳል፡፡"

"ስለዚህም ወደፊት ምን ሊመጣ እንዳለ ብቻ ተረጂ፡፡ ይህ የኔ ምርጫ ሳይሆን የእነርሱ ምርጫ ነው፡፡ ይህ የኔ በቀል ሳይሆን የእነሱ የሥራ ውጤት ነው፡፡ የሚሆነው ሁሉ ሰውን ከመጥላት የተነሳ ሳይሆን ሰውን ከማፍቀር የመጣና ስሜቱን ቀስቅሶ ለመመለስ ነው፡፡ እኔ የማደርገው እያንዳንዱ ነገር ምንጩ ፍቅር እንጂ ከሌላ ከምንም የመነጨ አይደለም፡፡

"ወደ ገሃነም የሚገቡት ነፍሳት እንኳን ያ እነሱ የፈለጉትና የመረጡት ቦታ ነው፡፡ ነፃ ፈቃዳቸውን የምሰርዝ እኔ ማነኝ? እነዚህ ሰዎች በመንግስተ ሰማይ ቢሆኑ በምንም ዓይነት መልኩ አይደሰቱም ነበር፡፡ ይህንን ነፃ ፈቃድ ለሰው የሰጠሁት መልካምን ወይም ክፉን በራሱ ምርጫ የፈለገውን መምረጥ እንዲችል ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ምን ማድረግ እችላለሁ?"

ክሌር፡- ምንም፣ ፍፁም ምንም ልታደርግ አትችልም፡፡ ሰዎች አይነሰውሮች ስለሆኑና ስለማያዩ የሚያሳዝን ነው፡፡ ችግራቸውን የፈጠርከው አንተ አይደለህም ፡፡ እነሱ በራሳቸውና በሰይጣንም እርዳታ ነው፡፡

"ስለዚህ አሁን ዋነኛውና ወሳኝ ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህም አዲስ ምዕራፍ ሁሉም ነገር እንደገና ትክክል የሚሆንበት፣ ኩራትና ዕብሪት የሚጋለጥበት፣ ብክለት የሚወገድበትና ሰው መልካሙን ከክፉ መምረጥ የሚችልበት ሌላ ዕድል የሚፈጥርለት ነው፡፡"

"እኔ እየመጣሁ ነው፡፡ ይህ ጊዜው ነው"

## በእምነት ላይ ተቃውሞ እየመጣ ነው - ማርች 30 ቀን 2015 ዓ.ም

## Attacks against faith are on the way – March 30, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . ዛሬ ምሽት በፀሎት ጊዜ ጌታ በመስቀሉ ላይ ነበር፡፡ ሰውነቱ ሁሉ በደም ተጨማልቋል፡፡ እኔም ከእርሱ ጎን በግራው በኩል በመስቀል ላይ ተሰቅዬ ነበር፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ያለው በቀኜ በኩል ነው፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ መሬቱ ላይ ቆሞ አየሁት፡፡ እኔንም በእጆቹ ይዞኝ ነበር፡፡ ሁለታችንም የሾህ አክሊል ደፍተን ነበር፡፡ እርሱም እጅግ እያለቀሰ ነበር፡፡

ኢሱስ እንዲህ አለ . . . "መራራ፣ መራራ፣ ማድረግ ያለብኝ ነገር እጅግ መራራ ነው ፡፡ ክሌር አፅናኚኝ፡፡ ዛሬ በእውነት ከእኔ ጋር እንድትቆዪ እፈልጋለሁ፡፡"

ጌታ እጅግ በጣም አዝኛለሁ፡፡ የበለጠ ታዛዥ እንደሆን እባክህ እርዳኝ፡፡

"አሁን እዚህ ከእኔ ጋር ነሽ፡፡ እናም ደስ ብሎኛል ከእኔ ጋር ቆዪ፡፡"

ጌታ ነገ እችላለሁ? እንዴት ከባድ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡

"ከእኔ አትራቂ በተለይም አሁን፡፡"

ጌታ መልዕክቱን እንዲህ በማለት ማስተላለፍ ጀመረ . . . ጊዜው እየቀረበ ሲሄድ በእምነትና በተስፋ ላይ ያለው ተቃውሞ እየበረታና እየተያያዘ ይሄዳል፡፡ በልሳን ስለመናገር እስካሁን የተነገረው ውሸት ሰይጣን አመንጭቶ ከለቀቀው ጋር ሲወዳደር ትንሽ ጉርምርምታ ብቻ ነው፡፡ በእምነት ላይ የሚነሳው ተቃውሞ አስፈሪ ነው የሚሆነው፡፡ ሁላችሁም ተዘጋጅታችሁ እንድትቆሙ እፈልጋለሁ፡፡ አምላካችሁ ትክክል እንደሆነ ሙጭጭ ያለ አቋም ያዙ፡፡ አምላካችሁ ትክክል መሆኑን አምናችሁ ችክ በማለት ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡

"ይህንን ስል ምን ማለቴ መሰላችሁ፣ የሚመጣውን ተቃውሞ ሁሉ ሰብስባችሁ በውሸት ግድግዳ ላይ በምስማር አጣብቁት፡፡ ወደ አይምሯችሁ አስገብታችሁ አታስላስሉት፡፡ የሚወረወሩትን ሐሳቦች ሁሉ አታስተናግዱ፡፡ ነገር ግን ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር አመሳክሩት፡፡

በእናንተ ላይ የሚወረወር የትኛውም መሳሪያ አይከናወንም፡፡ ለሚከሳችሁ ሁሉ መልስ ይኖራችኋል፡፡ ይህ ለጌታ አገልጋዮች ሁሉ የተሰጠ ውርስ ነው፡፡ ማሸነፋቸው ከእኔ የተነሳ ነው፡፡ ጌታ እንዲህ ብሎ አወጀ "ከእኔ የተነሳ አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡ 54፡17 ኢሳያስ የጌታ ቃል ትርጉም "

"በአንቺ ላይ የተሠራ ማንኛውም መሣሪያ አይከናወንም በፍርድም በሚነሣብሽ ምላስ ሁሉ ትፈርጂበታለሽ። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስታችሁ ይህ ነው፥ ጽድቃቸውም ከእኔ ዘንድ ነው፥ ይላል እግዚአብሔር፡-"

የኔ ሙሽሮች ክብሬን አስከብሩ፡፡ በከሳሼ ፊት ተከላከሉ፡፡ ምን ሊሆን እንዳለ ይህም ወደ እኔ እንደምወስዳችሁ ነግሬያችኋለሁ፡፡ ጠላት በእኔ ላይ ያላችሁን እምነት ለማስጣልና ነፍሳችሁን ከእኔ ለመንጠቅ ተስፋ በማድረግ የመጨረሻ አንድ ተከታታይ ሙከራ ያደርጋል፡፡

ስለ እኔና ስለ ክብሬ የቆማችሁ አገልጋዮቼ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ሐሜት የሚፍጥር ነገር መስማት የለባችሁም፡፡ በትልቅ ፍርሃትና ግራ መጋባት ወቅት ነው ጠላት መንገድ በማግኘት እምነታችሁን ለማጥፋት የሚሞክረው፡፡ እነዚህ ነገሮች እየተሰማችሁ ከሆነ ከኢጋንንት ጋር ተጋጥማችኋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ስሜት ውስጥ ወጥታችሁ የሚጨቁናችሁን ለመጣል እንዴት ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው እኔን ለእርዳታ ጥሩ እያልኩ የማስጠነቅቃችሁ፡፡ ይህንን ሁኔታ ለብቻችሁ ለመጋፈጥ እንዳትሞክሩ፡፡ እነርሱ በኃይል በርትተው ሊያሸንፏችሁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም እኔን መጥራት አለባችሁ፡፡

"ክብሬን አስከብሩ፡፡ የተገለጠላችሁን እውነት አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ እውነት ሆኖ ያወቃችሁትን ሊያስጥላችሁ የሚያሳድዳችሁን ጠላት አትፍቀዱለት፡፡ የብልጦችን ክርክርና ምክንያት አትስሙ፡፡ እኔ የሰጠኋችሁ እውነታ ጥቃት እንደተቃጣበት ሲሰማችሁ ተነስታችሁ ተሟገቱ እንጂ ወደ አይምሮአችሁና ወደ ልባችሁ እንዲገባ አትፍቀዱ፡፡

"ያለነው በጦርነት ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጠላት እስረኛ አድርጎ ለመውሰድ ያለው የመጨረሻ እድሉ ነው፡፡ ቀድሞ ያወቀ ቀድሞ ይዘጋጃል፡፡ ሁልጊዜ 'ጌታ ከክፉ አድነን' እያላችሁ ፀልዩ፡፡ በዚህ ጊዜ ህዝቄኤል አንድ ነገር ለመጨመር ፈለገ፡፡ ጌታም "ትክክል ነው አለኝ"፡፡

"ሰላምንና ደስታን የሚረብሽ የትኛውም ነገር የኢጋንንት ሥራ ነው፡፡ ፍርሃት ሲሰማችሁ አቁሙ፡፡ ቃሌን ተጠቅማችሁ ያንን ውሸት አጥፉት፡፡ ፍርሃት፣ ስጋት፣ ደህንነት ያለመሰማት፣ ጥርጣሬና መርበትበት፣ እነዚህ ሁሉ እናንተን ሽባ አድርጎ ለማጥፋት ጠላት የሚጠቀምባቸው የጦር መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ግራ መጋባት የኢጋንንትን ጣልቃ ገብነት የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው፡፡ ለእግራቸው ጠንካራ መርገጫ ሥፍራ ከማግኘታቸው በፊት ሰይፋችሁን ያዙና አጥፏቸው፡፡

"ወደ እናንተ ለመምጣት ይሞክራሉ፣ ነገር ግን በአንድ አቅጣጫ ሲመጡባችሁ በሰባት አቅጣጫ እመልሳቸዋለሁ፡፡ ተዋግታችሁ በሰባት መንገድ እንዲመለሱ ለማድረግ እረዳችኋለሁ፡፡ እንዲሮጡና እንዲበተኑ አደርጋቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን የእናንተን ትብብር እፈልጋለሁ፡፡

ክሌር በእኔ ላይ ለማረፍ ሞክሪ፡፡ የምናገረው ነገር በእርግጥ ለአንቺ እንደሆነ እውቅና ለመስጠት ሞክሪ፡፡ እባክሽ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አይምሮሽን ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዲዋልል አትፍቀጅለት፡፡ እሺ?

አዎን ጌታ የሚናገረውን እየሰማሁ እያለ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ፡፡ እንዲህም አልኩ "ጌታ እርዳኝ፡፡"

"እረዳሻለሁ፣ እየረዳሁሽም ነው፡፡ ይህ መልዕክት ሰላምን ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ አንድ ላይ ሆነን የሰራነውን መልካም ነገር ጠላት እንዴት አድርጎ ሊመልሰው እንደሞከረ ተመልክተሻል፡፡ የአንቺንና በዚህ ጊዜ ጥበብ የሰጠኋችሁን የነቢያቶቼን ደስታ ሊሰርቅ፣ የውሸት ወሬ ሊነዛና ስም ሊያጠፋ እንደነበረ ተመልክተሻል፡፡ ውጤታማ እንዲሆኑ አትፍቀጅላቸው፡፡ ታማኝ መሆኔንና ሙሽራዬን በሐሴት ፣ በሙላትና በደስታ ወደ መንግስቴ ላስገባት የገባሁትን ቃል እንደምፈፅም ተሟገቺ፡፡ ክብሬንም አስከብሪ፡፡

እንደማስበው ከሆነ "ኢየሱስ በአንተ እታመናለሁ" ብለን በኃይል መጮህ አለብን፡፡

"እነዚህ ነገሮች የመጨረሻውን መልዕክቴን አስቀድመው አጉድፈውታል፡፡ የኔ ሙሽሮች  በእናንተ ላይ ያመጣውን ውጤት በማየት በጥቃት ላይ እንደሆናችሁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመንፈሳችሁ ዕረፍት የሚነሳ ምንም ነገር ሲገጥማችሁ በጥቃት ላይ ናችሁ፡፡ ጠላት ደስታችሁንና ሰላማችሁን ሰርቋችሁ እንዲሄድ አትፍቀዱለት፡፡ ሰይፋችሁን አንሱና ተዋጉ፡፡ ይህ ጊዜ ብዙ አይቆይም ነገር ግን ከባድ ይሆናል፡፡ ቀድሞ ያወቀ ቀድሞ ይዘጋጃል፡፡"

ጌታ . . .? (ጥያቄውን ገና ሳልጠይቀው መለሰልኝ)

"የመገናኛ አውታሮችን እጠብቃቸዋለሁ ብዬ አልነገርኩሽም?"

ነገር ግን እነርሱ ከሁሉ እንቅስቃሴ በፊት የመገናኛ አውታሮችን እናጠቃለን ብለው የለም? (በኤሌክትሪክ የሚደረጉ ማንኛውንም የመገናኛ ዘዴዎችን እንደ ኢንተርነት፣ ኮምፒተሮችንና የመሳሰሉትን በኤልክትሮ ማግኔቲክ ፐልስ ማጥቃት)፡፡

"የኔ ውድ እነሱ እናደርጋለን የሚሉትና የኔ ችሎታ ለውድድር አይቀርብም፡፡ እኔ ከእነርሱ መንገድ በላይ ነኝ፡፡ እናም እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ልጆቼን በኢንተርኔት መገናኘት አስባለሁ፡፡ አዎ ለጥቂት ጊዜ መገናኘትን የሚያቃውስ የኃይል መቋረጥ ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ ሊያጠፉ የሚችለውን አልፈቅድም፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ክሌር አታምኚኝም? አየሽ እንደገና ኩራትሽ መጣ፡፡ ልትሚገቺለት ስለማትችይ አትቀበዪውም፡፡ ታሳፍሪያለሽ፡፡"

አዝናሁ፡፡ ጠላት እዚህ ደርሶ እንዳልሆነ እርግጠኛ ለመሆን ብቻ ነው፡፡

"ለዛ ደግሞ ትዕዛዝ ሰጥቼሽ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚያ የበለጠ ነው እያየሁ ያለሁት፡፡ በእውነቱ ከሆነ አንዳንዱ ሰዋዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ስለምወድሽ አምላክሽን እንኳን ጥያቄ ውስጥ ብታስገቢም አልተውሽም፡፡ እያልሽ ያለሽው እኮ 'ጌታ እርግጠኛ ነህ? እነርሱ በመጀመሪያ የሚያጠፉት ያንን ነው፡፡ ስለዚህም ያንን አያደርጉም ብሎ ለማመን ያስቸግራል፣ እርግጠኛ ነህ?' እያልሽ እኮ ነው ያለሽው? ምክንያቶችሽ ምን ያህል መሳለቂያ እንደሆኑ ታያለሽ?

አዎ ጌታዬ ፍርድ የሚገባኝ ጥፋተኛ ነኝ፡፡ በጣም አዝናለሁ፡፡ እባክህ እርዳኝ፡፡

"አሁን እያደረግሁ ያለሁት ያንን አይደለም?"

አዎ ማለቴ ገና ይህ ነገር መታየት ሲጀምር እባክህ ኩራቴን አስታውሰኝ፡፡ እባክህ?

"አዎ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ኩራትሽ ሁልጊዜ የሚመጣ ከሆነ መቼ ነው የማስታውስሽ? እንዲህ ከሆነ ነገሮችን መስራት እጅግ ያስቸግረናል፡፡ እንችላለን?

ኢየሱስ አንተ ካልክ . . .

"አዎ ብያለሁ፡፡ በይ አሁን ትንሽ የሳቅ ጊዜ ይኑረን፡፡ ከአንቺ ጋር መጫወትና የማይጠበቀውን ነገር መናገር ደስ  ይለኛል፡፡ በአይምሮሽ ስታመላልሽው ማየት ለእኔ ዝም ብሎ ጨዋታ ነው፡፡ በተጨማሪም በአንቺ አይምሮ ውስጥ የምሰራው ይህ ሥራ

በሌሎችም በሚያዳምጡሽ ውስጥ በምንም መልኩ ይኖራል፡፡ እናም እምነታቸውን የሚሸረሽረው ምን እንደሆነ እነርሱም ያያሉ፡፡"

ይህንን ስትል በዚህ ጉዳይ ብቻዬን አይደለሁም ማለት ነው?

"ዝንጀሮዎች በዛፎች ላይ ይጠላጠላሉ?"

እንደሚመስለኝ ሥራቸው ሁልጊዜ መንጠላጠል ነው፡፡

"ትክክል፡፡ ከእስራኤል ጋር ስንት መቶ ዓመታት ተቋቋምኳቸው? እናም እስካሁን እነርሱ ችክ ያሉ  የማያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስለ ሰው ፍጥረት አንድ ነገር ወይም ሁለት ነገር አውቃለሁ፡፡ አንቺስ ስለዚህ የምትይው የለሽም?

ያለኝ ይመስለኛል!

"በጣም ጥሩ አሁን እንቀጥል፡፡"

ጌታ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ትንሽ የሚያሳፍር ነበር፡፡

"የኔ ውድ የአንቺ ስህተት የሰው ልጆች ሁሉ ስህተት ነው፡፡ ይህንን ቀድሜ አልነገርኩሽም? እኔ እንዲያገለግለኝ ስፈልግ የነበረው የመጨረሻ ትንሽ ብቃት ያለውን ሰው ነበር፡፡ በዚህም ደረጃ አንቺን አግኝቻለሁ፡፡ ታዲያ አሁን ምኑ ነው የሚያሳፍረው? አንቺ ብቸኛዋ ልዩ ሰው እንደሆንሽ ይታይሻል?

ሳቅ፣ ጌታ አመሰግንሃለሁ፡፡ አዎ በእውነትም በራሴ ልዩ ነገር ተባርኬያለሁ፡፡

"በዚህ ምክንያት ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ያነሰ እንደሆነ ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዳታስቢ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አንቺና እንደ አንቺ ያሉት ሙሽሮቼ ሁሉ ታናሽነታችሁ በእኔ ተወዳጅ አድርጓችኋል፡፡ ይህ ሪክ ጆይነር የትህትና ካባ ብሎ የተናገረው ነው፡፡ እንዲሁም ጳውሎስ በድካሜ እመካለሁ ያለው ነው፡፡ ይህም ገና ሳትወለዱ ጀምሮ ባዶ፣ ደሃና ደካማ ሆናችሁ እንድትወለዱ የተወሰነና ውጤታማ ለመሆንም የኔን ቅባት እንደሚያስፈልጋችሁ ምልክት ነው፡፡ በመንግስተ ሰማይ ይህ እጅግ ክብር ያለውና ምርጥ ነገር ነው፡፡ ሁሉም ሙሽሮቼ ነገሮችን በዛ መንገድ ቢመለከቷቸው እመኛለሁ፡፡

"ይህ መሆኑ በእናንተ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሚያስችለውን ዋነኛውን በር እንዲዘጋ ያደርጋል፡፡ አየሽ ጠላት ሁልጊዜ 'አንቺ ደደብ ነሽ፣ ምን ታውቂያለሽ፤ ማን የሆንሽ መሰለሽ? እግዚአብሔር ለአንቺ ይናገራል? ያስቃል፣ እየቀለድሽ መሆን አለበት፣ አንቺ እኮ የማትረቢ ነሽ፣ ለምንም ነገር የማትበጂ ነሽ' እያለ ያንኳስሳል ደግሞም ይዋሻል፡፡ እጅግ የሚወደው ነገር ደግሞ 'እንትናንና እንትናን አየሻቸው? እነርሱ አሁን አንድ ነገር ላይ ደርሰዋል፡፡ ብልሆችና ችሎታ ያላቸው ናቸው፡፡ አንቺ ግን ? ያስቃል ለምንም የምትበጂ አይደለሽም፡፡ የሆነ ሆኖ ያመንሽው ሁሉ ውሸት ነው! ታያለሽ' በማለት ነገሮችን በመበጥበጥ ቀንተሽ ኃጢያት እንድትሰሪ ማድረግ ነው፡፡"

"ስለዚህ ሙሽሮቼ ደህንነት እንዳይሰማችሁ የሚያደርገው ይህ በር እንዴት በሰፊው እንደተከፈተ ታያላችሁ? ልትዘጉት ትፈልጋላችሁ? እንዲህ በሉ 'አዎ ይህ ሁሉ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን በሚያበረታኝ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን እችላለሁ፡፡' ይህ

ክርክሩን ሁሉ የሚዘጋ ቃል ስለሆነ የሚጮሁትን ድምፆች ሁሉ በዚህ ዝጉ! እናም 'አምላኬ እኔን ሊጠብቀኝና መመሪያ ሊሰጠኝ የታመነ ነው' በሉ፡፡

"የኔ ውዶች አሁን የሆነ ድምፅ ስለ እኔ ባህርይ ሥም ለማጥፋት ቢሞክር ትክክለኛውን መልስ ትሰጡታላችሁ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ተነሱና ክብሬን አስከብሩ፡፡ እንደዛ አድርጋችሁ አፋቸውን ስትዘጉ እንዴት ተባርኬያለሁ! አያችሁ ጨቋኙ እናንተን ሊያጠቃ እያቀደ ያለውን እንዴት መመከት እንዳለባችሁ ጥቂት ትምህርቶች እየሰጠኋችሁ ነው፡፡ እባካችሁ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

"ሙሽራዬ (ህዝቄል) አንድ ነገር ሊነግርሽ እየፈለገ ነበር ፡፡ ክሌር አይደለም እንዴ?"

እምም?

ምንድነው ቅድም የነገርከኝ?

ረሳሁት፡፡

"ስለ ብዙ አስተማሪዎችና ስለ ብዙ ድምፆች?"

ትክክል በዚህ ጉዳይ ላይ ቀደም ብዬ አንድ ቪዲዮ ሰርተን ነበር፡፡ እናም ይህንን ቪዲዮ እንድትመለከቱት የዩቲዩብ አድራሻውን በስተመጨረሻ እፅፍላችኋለሁ፡፡ ይህም በውሸት መልዕክቶች በመናወጥና አንነጠቅ ይሆን ? ብለው በመስጋት ከጌታ ሙሽሮች ብዙ ደብዳቤዎች ደርሰውናል፡፡ እኔ ለማለት የምፈልገው ተጠነቀቁ ነው፡፡ አንድን ነገር ለማወቅ መጓጓት እንዴት ኃይል እንዳለሁ አውቃለሁ፡፡ እናም እየሰማችሁት ያለው ነገሮችን የመቆፈር መጥፎ ምግባር ያለውን ሰው ነው፡፡ ጌታ ግን ነገሩን በቁጥጥር ሥር ያደርገዋል፡፡ ሁላችንም ብንሆን ጌታ መልካም እንደሆነና የንጥቀቱ ተካፋይ እንደሚያደርገን ማረጋገጫ እንፈልጋለን፡፡ ሁላችንም ብንሆን አሁን በዚህ ሰዓት እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ ሁላችንም ስለ ንጥቀት ብዙ ነገሮችን ማረጋገጫ እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን ይህ ደግሞ መንፈሳዊ አለመብላላትንና ግራ መጋባትን ይፈጥራል፡፡ ብዙ ሰዎችን በምትሰሙበት ጊዜ እነርሱ ያሉትን ሁሉ በየመልኩ ማስቀመጥ አለባችሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ለማግኘት ብዙ የምንፈልገው ከደህንነት እጦት የተነሳ ነው፡፡ ጌታ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲህ ብሎኛል፡፡ "ስለ አንድ ነገር እውነት እንደተሰጠሽና ቅባት እንዳለው መንፈስሽ ከመሰከረልሽ በመፈለግ ዝም ብለሽ አትባክኚ፡፡" ይህ የሚያሳየው ደካማ እምነትንና አለማመንን ነው፡፡ ይልቁንም የተሰጣችሁን አሰላስሉት፣ አጥብቃችሁ ያዙት እንጂ የማወቅ ጉጉት ወጥመድ ውስጥ አያስገባችሁ፡፡ በእርግጥም ደግሞ ወጥመድ ውስጥ ያስገባችኋል፡፡

ጠላት እንድትፈፅሙ ለሚፈልገው ለእያንዳንዱ ኃጢያት ሁሉ የማወቅ ጉጉትን ይጠቀማል፡፡ መልካም ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንደማይሰሙ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ለማወቅ ትልቅ ጉጉት እንዲኖራችሁ ካደረገ ብዙ ምንጮችን እንድትፈትሹና ግራ እንድትጋቡ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ያለማመንን በመፍጠር በእምነታችሁ ላይ ቀውስን ይፈጥራል፡፡ በተለይም ጠላት የእምነታችንን አቅጣጫ ሊያስቀይር እቅድ እንዳደረገ ጌታ እያስጠነቀቀን ባለንበት በዚህ ጊዜ መጠንቀቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም ማንን እንደምንሰማ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡

ካገኘናቸው ምንጮች ሁሉ አንዱ ለእኛ ተስማሚ ነው ብለን ካሰብንና ለመረዳታችንም አስተዋፅዎ ካደረገ በጥያቄ ውስጥ ከሚገቡ ከሌሎች ምንጮች ላለመጠጣት መጠንቀቅ አለብን፡፡ ለማወቅ በመጓጓት ያለማቋረጥ አንድን ነገር ስፈልግ ጌታ ከዚህ ድርጊቴ ሊያስጠነቅቀኝ በተደጋጋሚ ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚሰጠኝ ክፍል አለ፡፡

"ከጉድጓድህ ውኃ፥ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ" ምሳሌ 5፡15፡፡ ይህ ክፍል ምንም እንኳን የሚያወራው ስለ ሞራል ውድቀት ቢሆንም ለአስተማሪዎችና ግንዛቤ ለማግኘት ለምንጠቀምባቸው ምንጮችም የሚሰራ ነው፡፡ በተለይም ባለ ድርሻ አካላት በበዙበት በዚህ ዘመን በትል የተበከለ ውኃን ከመጠጣት መጠንቀቅ አለብን፡፡

እኔ እንደማስበው ዕረፍት የሚያሳጣችሁ ነገር ካለ የተቀደሰ ጥሩ ፊልም እዩ፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር አልሞትም የሚለውን ፊልም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ወይም ስለ ኢየሱስ የተዘጋጀውን የምትወዱትን የትኛውንም ፊልም፣ ወይም የልዕልቷ ማስታወሻ 2 የሚለውን ዓይነት እንኳን ማየት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ፊልም የሚያሳየው አንዲት ተራ ሴት እንዴት ልዕልት ከዚያም ንግስት ልትሆን እንደቻለች የሚያሳይ ነው፡፡ ታዲያ እኛስ ብንሆን በመጨረሻው እንደዛ ለመሆን አይደለም እየሰራን ያለነው? ይህ አሁን የተነጋገርነው ትንሽ እንድናስብ የሚያደርገን ይመስለኛል፡፡

(ኢየሱስ) "የኔ ሙሽሮች በዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው አንድ ነገር ይህንን የሰጧችሁን ቃል በልባችሁ ብትይዙትና ለመታዘዝም ታማኝ ብትሆኑ እኔም ጠላት እንድትፈሩ ከሚያደርጋችሁን ወጥመድ ለመጠበቅ ታማኝ እሆናለሁ፡፡"

"ምንም የሚያስፈራችሁና የሚረብሻችሁ ነገር እንዳይኖር አሁን በረከቴን በእናንተ ላይ አደረግሁ፡፡ እኔ አምላካችሁ ነኝ እናንተም ሙሽሮቼ ናችሁ፡፡

https://youtu.be/Cj-7MR2BruA Confusion-Listening To Too Many Prophets on the Rapture

## ሁሉ ነገር እንዳለ የሚቀጥል ይመስላል - አፕሪል 7 ቀን 2015 ዓ.ም

## Everything Seems Business As Usual, April 7, 2015

*ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች "ኦ ጌታዬ ተጨማሪ ጊዜ ቢኖር እንዴት ተመኘሁ፡፡ ብዙ የጠፉና ግራ የተጋቡ ነፍሳት አሉ፡፡ ስለዚህም ብዙ ሰዎችን ለመንካትና ለመድረስ ፈለግሁ፡፡"*

*ኢየሱስ እንዲህ በማለት መለሰ . . . "አውቃለሁ"*

*ተጨማሪ ጊዜ እንዲኖረን ተመኘሁ*

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የለንም"

*"ጌታ ግን ታውቃለህ . . . ሁሉ ነገር እንደተለመደው ይመስላል"*

"መግዛትና መሸጥ፣ ማግባትና ለጋብቻ መስጠት ነው?"

*አዎ አለም የተረጋጋና እስከ መጨረሻው እንዲሁ የሚቀጥል ይመስላል፡፡*

"አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን አይቀጥልም፡፡ ያታልላል፡፡ ያለው ሁኔታ እስካልተናጋ ድረስ ከበስተጀርባ ብዙ ነገር እየተከናወነ ቢሆንም እንኳን ለማውቅ ግድ የሚላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡"

*ሰዎች ምላሽ እየሰጡ ነው፡፡*

"ስለፈሩ ነው ምላሽ እየሰጡ ያሉት"

*ቢሆንም ምላሽ እየሰጡ ነው፡፡ ተጨማሪ ጊዜ አይኖረንም?*

"እኔ የማውቀውን ብታውቂ ኖሮ፣ ይህንን ጥያቄ አትጠይቂም ነበር፡፡"

*ጌታ ስለዚህ ጉዳይ በየቀኑ ነው ከራሴ ጋር የምታገለው፡፡ አለም እጅግ የተረጋጋና እስከመጨረሻው በተለመደው መልኩ የሚቀጥል ይመስላል፡፡ አንተ ባትሆንና መገለጥ ባይኖር ኖሮ እንዲሁ ይቀጥላል ብዬ አስብ ነበር፡፡*

"ታዲያ እኔን በማግኘትሽ ደስ አይልሽም?"

*ጌታ ምን ጥርጥር አለው! ህይወት ከአንተ ውጪ የቁም ቅዠት እንጂ ህይወት አይሆንም ነበር፡፡*

*"አውቃለሁ እንዴት እንደሚሰማሽ፡፡ እንዴት እንደሚሰማሽ አውቃለሁ ምክንያቱም እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ እኔም ሽክምሽ ስለሚሰማኝ ነው፡፡ ነገር ግን ምን እየተከናወነ እንዳለ እኛ ስለምናውቅና አንቺ ግን ስለማታውቂ ነው፡፡ ነገሩ የነበረው እንዳለ እንዲቀጥል የመፈለግ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም 'የኔ የሆነ ነገር ምንም አይነካ፣ ሥራዬን አሰራለሁ፣ ትርፍ አገኛለሁ፣ የምፈልገውን እገዛለሁ፣ ስለዚህም ኑሮዬን በሰላም ልኑርበት የሚል ነው፡፡"*

"ብዙዎች ያሉት በዚህ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ሌሎች ደግሞ በስውር እቅድ በማውጣት ለማጥቃት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ እቅዳቸው እንደሚሰራም ተማምነዋል፡፡ ምክንያቱም ሌላው የተለመደውን ማትረፉንና ሸቀጥ መሰብሰቡን ተያይዞታል፡፡ ደግሞ ይህ በሰላም እስከቀጠለ ድረስ ደስተኞች ናቸው፡፡"

"ሌሎች ደግሞ ስለ ሃይማኖትና ስለ መናገር ነፃነት፤ ስለ ትክክለኛ ፍርድና ስለ ደህንነት እሴት ያላቸውና ስለሚመጣው ነገር የማስጠንቀቂያ ደውል ስለሰሙ በድንጋጤ በመሞላት በጨረፍታ ካዩት ነገር ለማምለጥ እቅድ እያወጡ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ወደላይ አሻቅበው እየተመለከቱ ከዚህ እንዳድናቸው የኔን መምጣት እየተጠባበቁ ናቸው፡፡"

"ክሌር ሁሉ ነገር በአይናችሁ ፊት እየሆነ ነው ያለው፡፡ ነገር ግን በፊታችሁ እየታየ ያለው ህይወት በሁሉም ዓይነት መልኩ የቀረበ ነው፡፡ በአንድ መልኩ የተለመደውን ሸቀጡን የሚሞላው ሲሆን በሌላው ወገን ደግሞ የበላይነትን፣ ተቆጣጣሪነትን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በሌላው የህይወት ክፍል ደግሞ በነፃነት መኖር ሲሆን በሌላኛው ደግሞ መንግስተ ሰማይ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የህይወት ነፀብራቅ ክፍል በፊታችሁ ይገኛል፡፡ ስለዚህም በእያንዳንዱ ቀን የትኛውን የህይወት ዓይነት እንደምትመርጡ መወሰን አለባችሁ፡፡ የትኛው የኑሮ አቅጣጫ ነው የእናንተ ትክክለኛው ህይወት? እናም የትኛው ነው የእናንተ ጌታ? ማንን ነው የምታገለግሉት? አንደኛው የህይወት ክፍል ፈንድቶ በማሸነፍ የሌላውን ነፃነት ሁሉ ሊጨፈልቅ፣

ምድር ከውስጥ ወደ ውጪ ልትገለበጥ እንዲሁም ከላይ ወደታች ልትሆን ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሰዎች ወደ ኋላቸው መለስ ብለው ይመለከቱና ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ይላሉ፡፡"

"ይህማ የሆነባችሁ ምክንያት የሚያስፈልጋችሁን ብቻ የምታገኙበትን የህይወት አቅጣጫ መርጣችሁና ከሌላው ነገር ሁሉ ባይተዋር በመሆን ተለይታችሁ መኖር ስለመረጣችሁ ነው፡፡ ከዚህ የህይወት አቅጣጫ ሌላ ምንም የሚታያችሁ ነገር አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በመረጣችሁት የህይወት አቅጣጫ ስኬታማ ለመሆን ለሌላው ጊዜ ስለሌላችሁ ነው፡፡ እናም አንድ ቀን . . . ሁሉም አበቃ፡፡ ስለዚህም ግራ በመጋባት ቆማችኋል፡፡ እድለኞች ሆናችሁ እስካሁን ቆማችሁ ከሆነ ይህ ነው ነገሩ፡፡"

"የመሬት መራድ  በተከሰተ ጊዜ የመሬቱ ውፍረት ምን ያህል እንደነበረ የሚያስታውሰው አይኖርም፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ የሚታወሰው በተከሰተው ርደት የደረሰው መራራ ችግርና እጦት ነው፡፡ ይህም በሆነ ጊዜ በፍርስራሹ ላይ ሆነው ይፈልጉኛል፡፡ አለምን ማፍቀር እንዴት ራቁታቸውንና ምስኪን አድርጎ እንዳስቀራቸው ይገባቸዋል፡፡ ሲያገኙኝም አቅፋቸዋለሁ፣ በቁስላቸውም ላይ ዘይትን አፈሳለሁ፣ ለቅድስናም አነሳቸዋለሁ፡፡"

"እያልኩ ያለሁት ነገር ሳይነጠቁ ለቀሩ ሰዎች አትዘኑ ነው፡፡ ይህ የእነሱ እጣ ፋንታ ነው፡፡ ምክንቱም እነሱ የመረጡት በዛ የህይወት መንገድ ብቻቸውን ተለይተው፣ በራሳቸው እጅ የሚያስፈልጋቸውን በማግኘትና ህይወታቸውን ሁሉ ትኩረት ሲያደርጉ የነበሩት ስኬት በማግኘት ላይ ስለነበር ነው፡፡ አዎን ይህንን መርጠዋል፡፡ አለምም እንዲህ በመሆኑ የማያዩ አድርጎ ራቁታቸውን አስቀርቶአቸዋል፡፡ ይህም ሲሆን ለነፍሳቸው መዳን ምክንያት ይፈጠራል፡፡ ነገር ግን ይህ ባይሆን ኖሮ ገሃነም በእነሱ በተሞላ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ሁሉም መጥፎ ሆነው አይደለም፡፡ ነገር ግን በወቅቱ አምላክ የለሾችና የማያስፈልጋቸው ስለነበሩ እንጂ ፡፡ የኔ ምህረት ግን የእነሱ አለም እንዲደቅና እንዲያበቃ ያደርጋል፡፡ ለእነሱ ያለኝ ፍቅር ነው ይህንን መቅሰፍት እንዲመጣ ያደረገው፡፡ ምክንያቱም ራቁታቸውን ሲቀሩ ብቻ ነው ወደ እኔ ሊመጡ የሚችሉት እንዲሁም እውነትን ለማወቅና ከእኔ ለመፅናናት ረሃብ የሚይዛቸው፡፡"

"አያችሁ ሰው ቤቱን አንድ ጊዜ በአሸዋ ላይ ከሰራና ዝናብ መጥቶ ጎርፍ ቤቱን ጠራርጎ ከወሰደው፣ ያን ጊዜ ነው ያ ሰው ቤቱን በአለት ላይ መገንባት አስፈላጊ መሆኑን የሚረዳው፡፡ በወቅቱ ታዲያ በአጠገቡ በመገኘት እንዴት እንደሚገነባው አስተምረዋለሁ፡፡ ስለዚህም በይደር ላይ የሚገኘውና የማይቀረው አቅርቦቴ ልጆቼን በመንፈስና በእውነት ወደ እኔ ለመመለስ ነው፡፡"

"አዎን አስጨናቂ ነው፣ አዎን ጭካኔ ያለበት ነው፡፡ አዎን ለአይን ሲታይ ሚዛኑን ያልጠበቀ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ለታዳጊ ልጁ መኪና ለመግዛትና የቅንጦት ቤት ለመስራት በጣም ደሃ የሆኑትን የሦስተኛ አለም አገሮችን ሲበዘብዝ የነበረ ሰው ግን ምንም አልተባለም፡፡ በእንደዚህ ዓይንት አመለካከት የተጠመዱ ሰዎች በምንም ዓይነት መልኩ ይሁን እነሱ የሚፈልጉት ብቻ እንዲገኝ ነው ፍላጎታቸው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ሰዎች ሌሎች አገሮች የሚኖሩትን የመጨረሻውን ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እንዲቀምሱት ይደረጋሉ፡፡ እናንተ በመበልፀግ ስትቀጥሉ እነዚህ አገራት ግን እናንተ እንደ ኑሮ ዘይቤ የምትቆጥሩት ኑሮአቸው እነርሱ ግን ተስፋ በሚያስቆርጥና እስረኛ በመሆን ተቅለስልሰው እንዲኖሩ በሚያደርጋቸው ባህልና ኢኮኖሚ ውስጥ እየኖሩ ናቸው፡፡

"ክሌር ይህ በጣም በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ እናንተ የማታዩት ነገር እነዚህ ሰዎች እንዴት እንደሚበዘበዙ ነው፡፡ እኔ ለዘሪ ዘርን አልሰሰጠሁምን? ነገር ግን አሁን ስግብግብና ክፉ ሰዎች ዶለተው ደሃው የእነርሱን ዘር እንዲገዛ ለማስገደድ ዘዴ ፈጥረዋል፡፡ ይህንን ለስንት ጊዜ ነው የምፈቅደው? የደሃው ጩኸት በየዕለቱ ወደ ጆሮዬ ይደርሳል፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ጥቂት የህክምና አገልግሎት እንኳን ለማግኘት ይቸገራሉ፡፡ በአንፃሩ እናንተ አገር መካከለኛ ገቢ ያላቸው እንኳን ተጠቃሚ የሚያደርግ የህክምና መዋቅር እያለም ሌላውን ለመቆጣጠርና ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት በየጊዜው አዲስና የተሸሻለ መንገድን በመቀየስና ምንም በማያውቁት ላይ በመረማመድ እናንተ ታብባላችሁ፡፡"

"ኦ በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን እጅግ የተበላሸ ነው፡፡ ይህ ነገር ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዲቀጥል አባቴ ለምን ይፍቀድ?" እኛ የሰዎችን ልብ ለመቀየር ብዙ ጥረናል፡፡ ነገር ግን እነሱ ቀዳሚነት ባለው ኑሮ፣ ለምቾትና ለመደላቀቅ ካላቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ትክክለኛ ባልሆነ የአኗኗር ዘዴ አይናቸው ታውሯል፡፡

"እነዚህን ነገሮች ለእናንተ መናገር ለእኔ የተለመደ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንዲገባችሁ የምፈልገው በየቀኑ የምመለከታቸው የብልሹነት ገፅታዎች እንዴት የሚገርም እንደሆነና በአንፃሩም ለፍትህ የሚጮኸውን ጩኸት ነው፡፡ በጣም የባሰው ደግሞ ይህ ድሆችን እስከ መጨረሻው ጠብታ ገንዘባቸውን ለመጭመቅ የተለመደ ወንጀላቸውን የሚያቀነባብሩ ሰዎች የራሳቸውን ህይወት አደጋ ላይ መጣላቸውን ያለማወቃቸው ነው፡፡"

"አዎ ይህ አንዱ ገፅታ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥላቻን ያለመረጋጋትንና ተስፋ መቁረጥን ያነሳሳል፡፡ ሙስሊሞች ለእምነታቸው እራሳቸውን መስዋዕት ሲያደርጉ በደስታ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ተስፋ በሌለው፣ በተበላሸና ውስብስብ በሆነ አለም ውስጥ ደስታን የሚሰጣቸው አንድ እድል ይኸው ስለሆነ ነው፡፡ ሰው ለመኖር ምክንያት ሲኖረው የነበረውን ህመም በመሸፈን ወደ ክብር ለመመለስ ስሜት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን የመኖሩ ሚስጢር ከጠፋበት በክብር መሞትን ይመርጣል፡፡ ስለዚህም ሰይጣን በዚህ ፍትህ በሌለበት ምድር ላይ ሰው ሊያገኝ የማይችለውን ነገር ራሱን ነፃ በማውጣት 'በገነት' እንዲኖር እድልን ፈጠረለት፡፡ ታዲያ እነዚያን ድሆችን የሚያሳድዱትን፣ በአብዛኛው አይሁድ የሆኑትን የባንክ ባለቤቶችና /Bankers/ የአለም መሪዎችን መጥላት የለባቸውም? ደግሞ ሌላው ውጤታማ የመሆን ስሜት 'ሴተኛ አዳሪዋን ማጥፋት' የሚል ስሜት ነው፡፡ ይህ ራሱ አስከፊ ነው፡፡ ስለዚህ አያችሁ? ይህ ችግር ተስፋ የሌለው የተወሳሰበ ነገር ነው፡፡ እኔ ግን ለመንገስና ለመግዛት ወደ ምድር ተመልሼ ስመጣ የብረት ዘንጉ የሚሰርቀውንና ዝቅ ማለት ያለበትን ጀርባ ሁሉ ይሰበራል፡፡ ከሰው ሁሉ በታች የተናቀውን እንኳን፡፡"

"ፍትህና  አክብሮት ለሚፈልጉት ሁሉ ይሰጣቸዋል፡፡ ሁሉም የሚያስከብር እውነተኛ ሥራ፣ እንዲሁም የሚያስፈልገውን ትምህርት ለማግኘት የሚያስችላቸው እድል ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ከእግዚአብሔር ውጪ አንድም ሰው አይበለፅግም፡፡ ገና ከመጀመሪያው አንድም ሰው ከእግዚአብሔር ውጪ፣ ራሱን ለእኔ ፍፁም በመስጠት እንዲሁም እኔን ለማገልገል ፍላጎት ከሌለው ህይወት ሊኖረው አይችልም፡፡ ህሊናቸው መረዳት ከማይችሉት በቀር እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ውስጥ መኖር አስፈላጊነቱን ያያል፡፡"

"አየሽ ክሌር ከታች ወደላይ እንደገና መጀመር አለብን፡፡ ሌላ አማራጭ ስለሌለ ተስፋ አትቁረጪ፡፡ ሁሉንም ነገር ለማቃናት እመጣለሁ፡፡ ቃል እገባልሻለሁ፣ ሁሉንም ነገር እናቃናዋለን፡፡ ይህ እስኪሆን ድረስ ግን በሰማይ የዕረፍት ጊዜ እንዲኖርሽ ለማሰብ ሞክሪ፡፡ ይህንን የምልሽ ግማሽ ማንነትሽ ሰዎችን ለመርዳት ተጨማሪ ጊዜ እንደምትፈልጊ ስለማውቅ ነው፡፡"

"ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ፡፡ ይህም ፍቅር በአምላካችሁ ዘንድ ብቻ የሚገኝና ራስን አሳልፎ የሚያሰጥ ፍቅር ነው፡፡ ይህም ፍቅር አንድ ነፍስን ወደ እኔ ለማምጣት የሚናፍቅ ፍቅር ነው፡፡ እባርካችኋለሁ ደግሞም የምጠይቃችሁ በህይወታችሁ ለእኔ ቦታ እንዲኖር ለማድረግ  የምታደርጉትን ጥረት እየጨመራችሁ እንድትሄዱ ነው፡፡  እናም አንድ ቀን ለስቃያችሁ፣ ለፀሎታችሁና ለልፋታችሁ ዋጋ ይከፈላችኋል፡፡"

## ሥፍራን ላዘጋጅላችሁ ሄጀለሁ - ኤፕሪል 26 ቀን 2015 ዓ.ም

## I've gone to prepare a place for you, April 26, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . " በመንግስተ ሰማይ ለሙሽሮቼ ለእያንዳንዳችሁ   የተሰራላችሁ ቤት በፍላጎታችሁ መሰረት ፍፁም የተለየ ተደርጎ ነው የተሰራው ፡፡ የእያንዳንዱ ቤት ቀለም፤ የአሰራር ህብር፣ የስነ ህንፃ፤ የአትክልት ቦታ፣ የእንስሳት መገኛትና የተፈጥሮ አካባቢዎች ሁሉ የእያንዳንዱን ፍላጎትና ምርጫ ያካተተ ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ የምትመርጡት የጋራ መኖሪያዎችን ነው፡፡ እናም ለእናንተ ያዘጋጀሁላችሁን መኖሪያዎችን ትወዷቸዋላችሁ፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ በረሃ ትወዳላችሁ፡፡ ለእናንተ ያሳደኩትን ቁልቋል እስክታዩ ጠብቁ፡፡ ደግሞም የምትወዱት ቀለም ያለውና ሁልጊዜ እምቡጥ የማይጠፋውን አበባ ትመለከታላችሁ፡፡ የውኃ ጅረትና ገደላማ ሸለቆ፤ ከሰማይ በላይ ሰማያዊ ቀለም ያለው ውሃ፣ በአረንጓዴ የተሸፈነና  በውኃ ላይ  የመንቀሳቀስ ትዕይንት ያለው ተደርጎ የተዘጋጀላችሁን ቤተ መንግስት ትወዱታላችሁ፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ ደግሞ የባህር ዳርቻን ትወዳላችሁ፡፡ ለእናንተ የምትወዱትን የቀንድ አውጣ ሼል፤ በቅርጽ፤ በቀለም እና በአንፀባራቂነቱ በተለያየ መልኩ መርጬላችኋለሁ፡፡ በጣም ረጃጅምና ቀጫጭን ቅጠል ያላቸው ተክሎች፤ ሰፋፊ ቅጠል ያላቸው ተክሎች፣ እንዲሁም የከበሩ የቴምር ዛፎችና ትኩስ ኮኮናት አዘጋጅቼላችኋለሁ፡፡ ከመጠን በላይ የተዘጋጀውን መኖሪያችሁን  አይታችሁ አትጠግቡትም፡፡"

«ተራራና ጫካ ለምትወዱ ደግሞ ክሌርን መጠየቅ ወይም የፃፋትን መፅሐፍ ማንበብ ይጠቅማችኋል፡፡ እጅግ ትገረማላችሁ፡፡ ልብ ቅርፅ ያላቸው ኃይቆች፤ አብሮነትን የሚፈልጉ ብዙ ቀለማት ያላቸው አሣዎች፣ በጀርባቸው በማዘል የውኃውን ጥልቀት የሚያስጎበኟችሁ የውኃ ውስጥ ኤሊዎች፣  በሞገስ ከጎናችሁ የሚራመዱ የዱር እንስሳቶች ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም የምትወዷቸው እንስሳቶች እየጠበቋችሁ ነው፡፡ እነርሱም እንዴት እየጠበቁ እንዳሉ ልትረዱ አትችሉም፡፡ አመናችሁም አላመናችሁም ቃሉ እንደሚል እንስሳቶቹም የእናንተን ጓደኝነት በናፍቆት እየጠበቁ ነው፡፡"

ሮሜ 8-19-21 "<u>የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።"</u>

«ስማቸውንና ማን መሆናችሁን ያውቃሉ፡፡ ከእናንተ ጋር መግባባትን በመፍጠር ልክ እንደተፃፈው እንደዛው የፍጥረትን አንድነት ለማምጣትና ንፁህ የሆነ ብፅዕናን ለመፍጠር ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን ያስረዳሉ ፡፡ ሁሉም ነገር የተሞላው በፍቅር እንደሆነ ሁሉ ሁሉም ያንኑ የተሞላውን ፍቅር ያፈሳል፡፡"

«ሙሽሮቼ ለእናንተ አዘጋጅቼ የምጠብቃችሁ ነገር ከመደነቃችሁ ብዛት ትወድቃላችሁ፡፡ እያንዳንዱን ለእናንተ የፈጠርኩትን ነገር ቀን በቀን ማየት ስትጀምሩ ለብዙ ቀናት ያህል(ምንም እንኳን ጊዜ ከምድር የተለየ አግባብ ቢኖረውም) ከመደነቃችሁ ብዛት ግራ ይገባችኋል፡፡ ቢራቢሮዎች በምትወዱት ቀለማት፤ የምትወዷቸው ወፎች፤ የሚዘምሩና ማራቸውን በለጋስነት የሚያካፍሉ፣ በእኔ ፍቅር መሞላታቸውን ለመግለፅ ልብ ቅርፅ ሰርተው የሚበሩ ንቦችን ታያላችሁ፡፡"

«ሰዎች የክፉ ምሳሌ አድርገው የተጠቀሙባቸው እንሰሳት እንደ በረዶ ጉጉት፣ ጭልፊትና የመሳሰሉት እንስሳት እኔ በፈጠርኳቸው በቀደመው ማንነታቸው የፍጥረታቱ አባልና ስብስብ በመሆን ይገለጣሉ፡፡

«በመንግስተ ሰማያት ሞት የለም ውልደት ግን አለ፡፡»

*ጌታ ሆይ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?*

«ይህ ሚስጥር ነው፡፡ አሁን ለአንቺ የምገልጥልሽ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንን ጉዳይ ወደፊት አንቺን ላስደንቅበት አስቀምጩዋለሁ፡፡ እሺ ምክንያታዊ ላድርገውና ለምሳሌ ቅሪት የሆነች አንድ እንስሳ ሞተች እንበል፡፡ በእርግጥም ይህች እንሰሳ ከህፃን ልጇ ጋ እንደገና እንድትኖር ትደረጋለች፡፡

«ይህ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎችም መንገዶች አሉ፡፡ መኳኳቷን ከማታቋርጥ ሙሽራዬ ጋር ነው እየተጓዝኩ ያለሁት . . .»

"በምድር የምትወዱትን ምግብ የሚተካ የምግብ ዓይነት ነገር ግን ከሥጋ ውጪ የሆነ በመንግስተ ሰማይ አዘጋጅቼላችኋለሁ፡፡ በመንግስተ ሰማይ እንሰሳትን አሣዎችን ቢሆን ወፎችን ወይም ጡት አጥቢዎችንም ቢሆን መግደል የለም፡፡ እንደምትገምቱት መንግስተ ሰማይ በጣም ሰፊ ነው! በአንድ ሜዳ ውስጥ ሜዳ እንደገና በዛ ሜዳ ውስጥ ሌላ ሜዳ ይገኛል፡፡ ህዝቅኤል በትልቅ ዛጎላማ ሼል ውስጥ እንዳየው ዓይነት በአንድ ወርድና ስፋት /Dimensions/ ውስጥ ሌላ ወርድና ስፋት ይገኛል፡፡ »

*አዎ ህዝቅኤል ከጌታ ጋር እየዋኘ እያለ በሐይቁ ታችኛው ክፍል በአሻዋው ላይ በጣም ትልቅ የሆነ የዛጎል ሼል ያያል፡፡ እየዋኘና ወደ ሼሉ እየቀረበ ሲመጣ ህፃናትና የእንስሳት ልጆች እየተጫወቱበት ወደአለ ወደ ትልቅ አረንጎዴ ሜዳ ውስጥ ይገባል፡፡ በጣም ደስታ የተሞላበት ቦታ ነበር ይህም ለህፃናት የተሰራ ቦታ ነበር፡፡ በቃላት ሊገለጥ የማይችል ደስታን ለህፃናቶች ተብሎ የተዘጋጀ ሥፍራ ነው፡፡*

«በመንግስ ሰማያት ውስጥ በአቫተር ፊልም ላይ እንዳያችሁት ዓይነት መጎጎዣ መኪናዎች፣ ፈረሶችና ትላልቅ ወፎች አሉ፡፡ በአየር ላይም በነፃነት መንቀሳቀስ ብትችሉም በምታራመዱ ጊዜ እንኳን ሸክም የሚሆንባችው ነገር አይኖርም፡፡ ሁሉም ነገር

የእናንተን ጥረት የማይጠይቅ ወይም ህመም የሌለው ነው፡፡  ይህ ለአንዳንዶቻችሁ መገለጥ ይሆናል፡፡ ምክንያቱ አሁን በዚህ ምድር ላይ ህይወት ሁሉ ለእናንተ ህመም ስለሆነ ነው፡፡

ጌታ ጥያቄ አለኝ፡፡ ኪቦርድስ . . . ይኖራል? ታውቃለህ እኔ ምን ያህል ኪቦርዴን እንደምወድ፡፡

ጌታም እንዲህ አለ . . . «በመንግስተ ሰማያት ውስጥ የሚኖረው መሳሪያ እንደ ላባ በጣም የቀለሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ልክ አሁን እንዳለሽ ዓይነት ብዙ ስራዎች ይኖሩሻል፡፡ ቢሆንም ከመሳሪያዎቹ ጋር መላክቶች ይመደቡልሻል፡፡ እናም ማንኛውንም የወደድሽውን ዓይነት የሙዚቃ ድምጽ ወዲያው በቅፅበት ያወጡልሻል፡፡ በአይምሮሽ ያለውን ማድመጥና ያለ ምንም ስህተት ተግባርያዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ተግባቦት ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ነው የሚከናወነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ከተፈጥሮ በላይ ነው የሚከናወነው፡፡»

*ኦ! በጣም የሚደንቅ ነው! ይህ የምድርን ሁለት ሰስተኛውን ጭንቀት ይቀንሳል፡፡*

«እንደ እውነቱ ከሆነ በመንንግስተ ሰማያት ውስጥ ሁሉ ነገር ያለ ልፋት የሚገኘው ነው፡፡»

*ጌታ ታዲያ ይህንን ኑሮ ለምደነው ወደ መሰልቸት እንመጣ ይሆን?*

«ኦ በፍፁም! በጣም ብዙ ብዙ ስጦታዎችን መለዋወጥ፣ ተግባቦቶች፣ መዝሙሮችና ፊልሞች ይኖራሉ ......»

*ቆይ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ፊልም መሥራት አለ?*

«አዎ ብዙ የሚነገሩ የታሪክ ትርክታዎችና የፈጠራ ስራዎች ከምድር ካሉት ሙሉ ለሙሉ የሚሻል ነገር ይኖራል፡፡ ቀላሉ ነገር ደግሞ እነዚህ ስራዎች በመንግስተ ሰማያት በቴፕ ተቀርፀው ለዘላለም መቀመጣቸው ነው፡፡»

*በመንግስተ ሰማያት ውስጥ መቅረጫ  አለ?*

«አዎ የመቅረፅ መሳሪያዎች አሉ፡፡ ልክ በመንግስተ ሰማያት መፅሐፍት ቤት ውስጥ መፅሐፍት እንዳለ ሁሉ ምስልና  ድምፅ መቅረጫም አለ፡፡ ነገር ግን በመላዕክቶች ቀጥታ የሚቀርቡ ብዙ ፕሮግራሞችም ይኖራሉ፡፡ እነርሱም በአጠቃላይ ሂደቱ ውስጥ በተዋናይነትና በረዳትነት ያገለግላሉ፡፡ ክሌር እኔ ለናንተ ያዘጋጀውትን ነገር ለማሰብ መጀመር እንኳን አትችሉም፡፡»

*ኦ! ይህን ስሰማ ብዙ ለመስማት እጓጓለሁ፡፡ በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ ሁልግዜ ፊልም መስራት እፈልግ ነበር፡፡ ህዝቅኤልም እንደዛው፡፡*

«እድል ታገኛላችሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን ልናገር፣ አምልኮውን ፍፁም ስለምትወጂው ወደዛ ትሳቢና የዛ አካል ትሆኛለሽ፡፡ ከዚያ በኋላ ከአምልኮ ላይ አንቺን ማስነሳት ከባድ ነው የሚሆነው፡፡»

*ኦ ጌታ! ይህ ልቤን በበረከት ይሞላዋል፡፡ በምድር ላይ በጣም የምንፈልገውን አምልኮ የመምራት ኢድል አግኝተን እንደማናውቅ ታውቃለህ፡፡ ደግሞ የኔ ችሎታ መሻሻል ያስፈልገዋል፡፡*

«ይህ ነገር ከአሁን በኋላ ምንም ችግር ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በአይምሮአችሁ የሆነ ነገር ትሰማላችሁ፣ ከዚያም ወዲያውኑ ፍፁም በሆነ መልኩ ትጫወቱታላችሁ፡፡»

*"ኦ ጌታ ሆይ ይህ ለእኛ እጅግ ብዙ ነው፡፡*

«አውቃለሁ የእኔ ፍቅር፡፡ ነገር ግን ለሙሽሮቼ ሁሉ በቅርብ የት እንደምወስዳቸው ትንሽ ሐሳቡ እንዲኖራቸው ፈልጌ ነው፡፡ ይህም ለጉዞዋቸው የመጨረሻ እርምጃ ብርታት እንዲሆናቸው ነው፡፡የአሁኑ ስቃይ ከሚጠብቃቸው ክብር አንፃር ምንም ሊወዳደር የማይችል እንደሆነ እንዲያዩ ነው ፡፡ በእርግጥም ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል ይፈፀማል፡፡

«እንግዲህ ተስፋ አደርጋለሁ ሁላችሁም ቃሌን ጠጥታችሁ የሚጠብቃችሁን መንግስተ ሰማያት አትኩራችሁ እንደምታዩ፡፡ ክሌር ደግሞ ማታ ስለነበረን የፀሎት ጊዜ ንገሪያቸው፡፡»

እና በሚወዛወዘው ወንበር ላይ በገነት አትክልት ሥፍራ ውስጥ የነገረኝን ይህንን ነው የማካፍላችሁ ፡፡ በጣም በሚያምርና የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የተዋቡና ሽታቸው የሚያውድ ዕፅዋዕት ያሉበት፣ ደግሞም እፅዋት የሚያዜሙ የሚመስልበት ሥፍራ፣ ፍፁም ሰላምና ደስታ ያለበት ቦታ፡፡ ብቻ ምን ልበላችሁ በቃ በጣም የሚያምር አካባቢ ነው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የምወዳቸውን አንዳንድ ክርስቲያኖች ማየት ጀመርኩ፡፡ ሐዋሪያቶች፣ ነብያቶች፣ታማኝ ሰዎችና የእግዚአብሔር ሴቶችን፡፡ በተጨማሪም ታማኝና እጅግ ውብ የሆኑ የዩቲዩብ ቤተሰቦችንም በዛ ለማየት ጓጉቼ ነበር፡፡ እንዲህም እያልኩ አሰብኩ ምነው እነሱም ነፍሳቸው እንደዚ ባማረ ቦታና በክርስቶስ ልብ ውስጥ እንዳለ ማየት ቢችሉ፡፡

እናም ጌታ እንዲህ አለኝ. . . «አንድ ቀን ይህ ራዕይ እነሱንም ያጠቃልልና ሁላችንም አብረን እንደሰታለን፡፡ ነገር ግን ለአሁን የእኔ ጣፋጭ ወንድና ሴት ሙሽሮቼ ሁላችሁም እውነተኛውን ፍፁም ህይወት አንዳንችን ከአንዳችን ጋር በህብረት የምንኖርበት ሥፍራ ለእናንተ እያዘጋጀሁላችሁ ስለሆነ ተፅናኑ፡፡ ተበረታቱ እናም ጠንክሩ በቅርብ እመጣለሁ፡፡»

### ሁሉን ነገር ለመተው አሁን ጊዜው ነው - እ.አ.አ. ሜይ 8 ቀን 2015 ዓ.ም - በካሮል ጂንጊስ
### It is time to let it go, May 8, 2015 by Carol Jennings

"በሚመጡት ቀናቶች ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ለእናንተ እጅግ አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት ነው፡፡ ይህም መቼ እንደምትበሉ፣ የት እንደምትሄዱና እንዴት እንደምትኖሩ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ነገሮች እጅግ እየፈጠኑ ስለሚሄዱ ጊዜያቶችን እንደተለመደው መጠቀም አይቻልም፡፡ብዙ ነገሮችን ወደኋላ እየተዋችሁ ወደፊት ብቻ መሄድ አለባችሁ፡፡ ለእናንተ የሚጠቅም ወይም መያዝ ያለባችሁ የሚመስላችሁን ነገር ሁሉ እየተዋችሁ መሄድ ያለባችሁ ጊዜ ነው፡፡"

"አሁን ሁሉን ነገር ትታችሁ መሄድ ያለባችሁ ጊዜ ነው፡፡ አሁን ያላችሁ ኃብት ወይም ንብረት በምርጫ ወቅት ከህይወታችሁ ወይም ከቤተሰቦቻችሁ ህይወት ጋር ሲነፃፀር እጅግ ትንሽ ወይም ምንም ነው፡፡ ስለዚህም በማንኛውም ጊዜ ከአንዱ ቤት

ወደ ሌላው ቤት፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፣ ከአንዱ አገር ወደ ሌላ አገር ወይም ከአንዱ ከተማ ወደሚቀጥለው ከተማ ለመንቀሳቀስ የተዘጋጃችሁ እንድትሆኑ አሁን እያስጠነቀቅኋችሁ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በአስተሳሰባችሁ ብልህ ሁኑ፣ ለእናንተና ከእናንተ ጋር ላሉት በህይወት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ብቻ አዘጋጁ፡፡ ይህም መፅሐፍ ቅዱስ፣ ጥቂት ቅያሪ ልብሶች፣ የሚጠጣ ውኃ፣ ደረቅ ምግቦች ወይም የጣሳ ምግቦች እንዲሁም አንድ ወይም ሁለት ብርድ ልብሶችን አዘጋጁ በጀርባ በሚታዘል ሻንጣ በማዘጋጀት ደቂቃ ባልሞላው የማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ አንስታችሁ እንድትሄዱ በቅርባችሁ አስቀምጡ፡፡"

"በጥቂቱ የሚያስፈልጓችሁ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ለምሳሌ እንደ ኮፕዩተር/ከተቻለ/ ፣ ባትሪዎች፣ የባትሪ ድንጋዮችና ጥቂት ፍላሾች ቅርብ በሆነ ቦታ በሚቀመጥ ሻንጣ ውስጥ አስቀምጧቸው፡፡ ለመጓዝ እራሳችሁን በሸክም ማስጨነቅ የለባችሁም፡፡ የምትይዟቸው ነገሮች ቀላል መሆን አለባቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ደግሞ ህይወታችሁን ቀላል ያደርጉላችኋል፡፡"

"በምድር ላይ በቅርቡ ሊከናወኑ ያሉ ክስተቶች እጅግ አስደንጋጭና ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ነው፡፡ በዛ ውስጥ ለማለፍና በጠላት ተይዞ ላለመገደል በእኔ ላይ ትልቅ እምነት መጣልን ይጠይቃል፡፡"

"የኔ ፍላጎት በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎች እንዲከተሉኝ፣ እንዲሰሙኝ፣ እንዲታዘዙኝና በህይወት እንዲኖሩ ነው፡፡ በዚህም ወደ ሚሊንየሙ መንግስት ተሻግረው እኔ መልሼ አዲስና ንፁህ ባደረኩት ምድር ተዋልደውና ተባዝተው ምድርን እንዲሞሏት ነው፡፡"

"እርግጥ ነው በሰባቱ ዓመታት ውስጥ ብዙዎች ይሞታሉ፡፡ ነገር ግን ለእኔ ታማኝና በመሆን በፍጥነት የምትታዘዙ ከሆነ ከእነሱ መካከል አትሆኑም፡፡ እኔ እጠብቃችኋለሁ፣ ደግሞም በራሴ ጊዜና ቦታ እመራችኋለሁ፡፡ እኔ እረዳችኋለሁ፡፡ ነገር ግን እናንተ ደግሞ ሁል ጊዜ እኔን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች መሆን አለባችሁ፡፡ እናንተን ለመርዳት እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ መላዕክቶቼም በዙሪያችሁ ይሆናሉ፡፡ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ጥያቄ ሲገጥማችሁ፣ ከፈራችሁ፣ ግራ ከተጋባችሁ እኔ ምላሽ አሰጣለሁ፡፡"

"በዚህ ጊዜ ቅዱሱን መንፈሴን በጆሯችሁ በግልፅ መስማት ግዴታ ይሆናል፡፡ ለነፍሳችሁ መዳን እንደጠየቃችሁኝ ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ጠይቁኝ፡፡ እነዚህም በመንፈስ ቅዱስ እሳት መጠመቅ፣ በመንፈስ ለመፀለይ የልሳን ስጦታ፣ የፈውስ ፀጋ፣ እንዲሁም የእወቀትና የትንቢት ስጦታዎች ናቸው፡፡"

"በዚህ ወቅት ላይ ሆናችሁ ስለ ኢንተርኔት አታስቡ፡፡ መጠበቅ ያለብኝን በደንብ እጠብቃለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን በዚህ ደረጃ ኢንተርኔት ብታጡም እኔ እራሴ ላስተምራችሁና እነዚህን ስጦታዎች ላካፍላችሁ በአጠገባችሁ እሆናለሁ፡፡"

"የተወደዳችሁ ይህንን ከልባችሁ ውሰዱት፡፡ እምነት ይኑራችሁ፡፡ በቅርብ ጊዜ የሰማይ አባት ይህንን አለም ታይቶ በማይታወቅ በፍርድ ዓይነት ትርምስምስ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን ለእናንተ ቀድሞ የተዘረጋ እንከን የለሽ እቅድ አለኝ፡፡ "

"ዛሬ ምሽት በእምነትና እኔን በማመን በረከት እየባረኳችሁ በፍቅር እሰናበታችኋለሁ፡፡

"የእናንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡"

**በክርስቶስ የሚገኘውን ህይወት ፈልጉ - ሜይ 8 ቀን 2015 ዓ.ም. - ካሮል ጄንጊስ**

**Seek Life in Jesus, May 8, 2015 - Carol Jennings**

*ካሮል እንዲህ በማለት ጀመረች . . . የኔ ኢየሱስ በዚህ ማለዳ ትናገረኛለህ ?*

"አዎ የኔ ውድ "

"አሁን ይህንን ቃል እተውልሻለሁ፡፡ ጎበዝ ሁኚ ደግሞም እምነት ይኑርሽ፡፡ እኔ ሁልጊዜ ከአንቺ ጎን ሆኜ ስለምጓዝ ዛሬም ቢሆን ወይም በፊትሽ ባሉ በየትኛውም ቀናቶች በምድር ላይ ስለሚሆነው ነገር አትፍሪ፡፡  ይህ ፅሑፍ ለምን እንዲፃፍ እንደማደርግ እንደማታውቂ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ ፅሑፍ ወደፊት ለሚያነቡት ሰዎች ጥቅም የሚውል ነው፡፡"

"የኔ አገልጋይ የሆነችው ካሮል ትግሉን ለብዙ ዘመን በከባድ ሁኔታ ታግላለች ደግሞም በእኔ ድልን አግኝታለች፡፡ እናንተም እንደሷ እንድታደርጉ ከልብ ትመኛለች፡፡ እርሷ ከዚህ እስከትሄድ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን ለእሷ የምናገረውን በደንብ አድምጡ፡፡ ለእናንተ ብርታት፣ጥንካሬና ጥበብ የሚሰጣችሁ ማቴሪያል አለላችሁ፡፡ እርሷ በራሷ አይምሮ በጣም ትንሽ ናት፡፡ ነገር ግን በእርሷ የሚያልፈው የኔ ኃይል የሰው ልብን ለመንግስቱ ለመቀየር ኃይል አለው፡፡"

"ይህንን መፅሔት የምታነቡ ፈልጉኝ፡፡(እነዚህ ቃላቶች ከእኔ የግል መፅሔት ተወስደው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ እንዲካተቱ ተድርገው ነው)፡፡ ፈልጉኝ እናም እገኝላችኋለሁ፡፡ ለከሌር የሰጠዋትን ደብዳቤዎች አንብቡ፡፡ እነዚያ ደብዳቤዎች ለእናንተ የህይወት መመሪያዎችና የቅድስና መንገዶች ናቸው፡፡ የሰጠኋችሁን ቃሎች ተከታተሏቸው፡፡ ትዕዛዛቶቹንም ፈፅሟቸው፡፡ እኔ እነዚህን የሰጠኋችሁ በህይወት እንድትኖሩባቸው ነው፡፡

"በዚህ ጊዜ የጠራኋችሁ ለመንግስቴ ነው፡፡ በእናንተም አማካኝነት ሌሎችን ብዙዎችን እደርሳለሁ፡፡ ለሌሎች ለብዙዎች ሲባል በዚህ ወቅት እንድትገኙና የእኔ ጥሪ እንዲደርሳችሁ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለዚህ የተመረጣችሁ ናችሁ፡፡"

"ኑ የኔ ጓደኞች ፣ ለእኔ ታማኝ ሁኑ፡፡ እናም የመንግስተ ሰማይን ቁልፍ እሰጣችኋለሁ፡፡ አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፡፡"

"ንጉሡ ኢየሱስ"

**ከንጥቀት ተካፋይ ለማይሆኑት መልዕክት - በሥጋ ላይ አትደገፉ - ሜይ 9 ቀን 2015 ዓ.ም**

**For the left behind: put no confidence in the flesh, May 9, 2015**

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . ጌታ ዛሬ የተናገረኝ መሰረታዊው ነገር ለአገልግሎት ወደኋላ ስለሚቀሩና በዚህም የንጥቀቱ ተካፋይ ስለማይሆኑ ሰዎች ነው፡፡

ኢየሱስ ኢንዲህ አለ. . ."በማንኛው ምክንያት ይሁን የንጥቀቱ ተካፋይ ያልሆናችሁና እዚህ የቀራችሁ ሁሉ እባካችሁ በሥጋ አትደገፉ፡፡ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ቢሆን እኔ ጣልቃ ሳልገባ እንዳውም በትክክለኛው አገላለፅ ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ለራሳችሁ የሚያስፈልጋችሁን ለማግኘትና እራሳችሁን ለመጠበቅ አታስቡ፡፡ በሥጋችሁ በታመናችሁ ቁጥር፣ ራሳችሁን ለማሸነፍ ችሎታችሁን በተጠቀማችሁ ቁጥር፣ ለሚያስፈልጋችሁ ነገር ለራሳችሁ ብቁ ለመሆን በጣራችሁ ቁጥር ለውድቀት ራሳችሁን እያዘጋጃችሁት እንደሆነ እወቁ፡፡ ሌሎች ደግሞ አሉ ኪሳቸው ባዶ የሆነ፣ የሚሄዱበት የሌላቸው፣ የሚበላ የሌላቸውና ምንም ዝግጅት ሳያደርጉ ወደ ታላቁ መከራ የሚገቡ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን በየደረጃውና በደረሱበት ሁሉ የሚያስፈልጋቸው ይቀርብላቸዋል፡፡

"አንድ ነፍስ እምነቱን በእኔ ላይ ሲጥል የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ ነፃ ነኝ፡፡ ለመኖር የሚያስፈልገውን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ጉዳያችሁ ሁሉ የእኔ ሲሆን ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ደህንነት ያለመሰማት፣ መርበትበትና ቶሎ ውሳኔ ለመስጠት መቸኮል ያለጊዜው ወደ ዲያቢሎስ ገስግሳችሁ በእጁ እንድትወድቁ ከማድረግ በቀር ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ ነገር ግን ነፍሳትን ወደ እኔ በማምጣት ላይ ብታተኩሩ እኔ የሚያስፈልጋችሁን ለማድረግ ነፃ ነኝ፡፡ የኔ ታማኝነት ይሸፍናችኋል ደግሞም ደጀናችሁ ይሆናችኋል፡፡ እኔን የማያውቁ ሰዎች ናቸው ለራሳቸው የሚስፈልጋቸውን ነገር ለማሟላት የሚሯሯጡት፡፡ እኔን ካወቃችሁኝ ግን ለዚህ ሁሉ መውጫ መንገድ እንዳለኝ ትገነዘባላችሁ፡፡ ይህም ሙሉ የምግብና የመድኃኒት አቅርቦት፣ እንዲሁም ጠላት እንዳያያችሁ መሸፈንን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

"ክሌር ይህ አሁን እየነገርኩሽ ያለሁት የሚመለከተው ሳይነጠቁ እዚህ የሚቀሩትን ነው፡፡ ከአሁን ወዲያ አብረን የምናሳልፋቸውን አብዛኛዎቹን ጊዜያት እነሱን የማዘጋጅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

""በዚህ ጊዜ በአይምሮዬ ከመሬት መንቀጥቀጥ ጋር ተያይዞ ዛሬ ስለቀረበው ስለ የሎው እስቶን ቻርት ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እነዚህም እጅግ በጣም ትልልቅ፣ ጠንካራና ጠፍጣፋ ከለር ያላቸው ዘንጎች ሲሆኑ፣ ከተለመደው ወጣ ያሉ ናቸው፡፡ እናም እንዲህ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ 'ኒብሩ የምትባለው ፕላኔት ናት ማለት ነው ይህንን ሁሉ ለውጥ በምድር ላይ የምታመጣው፡፡ እነርሱ ደግሞ ይህ እንደሚሆን ቀድመው ያውቁ ነበር፡፡'

ጌታም . . . "አዎ ሁሉንም ያውቃሉ፡፡ ይህንንመ ለህዝቡ መናገር ሲገባቸው እነርሱ ግን ግማሹን የሰው ልጅ ሊጠርግ የሚችለውን ይህንን ትልቅ ጉዳት ምንና ምን ሊሆን እነደሚችል ያሰላሉ፡፡

"የኔ ውድ አስፈላጊ ወደሆነው ወደ ዋናው ጭብጥ ነገር እንመለስ፡፡ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነገር እኔ መልካምነትንና ደግነትን እንደማደርግ ማመንና መተማመን ላይ ነው፡፡ ከእነዚህ አመለካከቶች ውጪ አሸናፊ መሆን አይቻልም፡፡ የኔ ጥበቃ ከሚፈልጓቸውና ከሚያሳድዷቸው ሽፋን በማድረግ ለእነርሱ እንዳይታዩ ያደርጋል፡፡ የኔ ጥበቃ የዱር አውሬዎችን

ያባርርላቸዋል፡፡ የኔ ጥበቃ ምድር ከፍታ እንድትውጣቸውና ከጠላቶቻችሁ እንዲሸሽጉ ያደርጋል፡፡ የኔ ጥበቃ ውኃና ምግብ በሌለበት አቅርቦትን ያደርጋል፡፡ እኔ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው አጀንዳቸውን በመንግስቴ ላይ ባደረጉና ነፍሶችን ለመሰብሰብ በተሰማሩት ላይ ነው፡፡ እንዲሁም ይህንን  የማደርገው ከራስ ወዳድነት አልፈው ራሳቸውን ለሌሎች በመስጠት ለሚመሩና ሌሎችን ለመንከባከብ ታማኝ ለሆኑት ነው፡፡ ለእነዚህ ነው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥበቃና አቅርቦት የማደርገው፡፡

"ድነት የሚያስፈልጋቸውን ብዙዎችን ወደ እናንተ እጨምራለሁ፡፡ ዘላለማቸው በእናንተ ላይ ተንጠልጥሏል፡፡ ስለዚህም ስለ እነርሱ የዘላለም ጉዳይ ቅድሚያ የምትሰጡ ከሆነ እኔ ደግሞ እናንተን እሸፍናለሁ፡፡ በምድር ላይ ከሚመጣው ፈተና የተነሳ ነፍሳት ግራ ይጋባሉ፣ በፍርሃት ይዋጣሉ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ወደላይና ወደታች ይራወጣሉ፡፡ ስለ ሁኔታው ግራ ከመጋባታቸውና ግንዛቤ ከማጣታቸው የተነሳ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ፀጋ በስተቀር ይህም እጃችሁን ራሳቸው ላይ በመጫን፣ ፍፁም ሰላም የሚሰጣቸውንና  የሚፈውሳቸው የኔን ፀጋ ካልተቀበሉ በቀር ሊያረጋጋቸው የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡

"እናንተ ለፈወስ የተጠራችሁ፣ እኔ በእናንተ ውስጥ ስለምኖር የኔ እጅ ከልባችሁ ወጥቶ በእናንተ በኩል እንደሚቀሳቀስ በማሰብ በታመሙትና በስቃይ ባሉት ነፍሶች ላይ እጃችሁን ጫኑ፡፡ ሌላውን እኔ እጨርሰዋለሁ፡፡ ማመን ያለባችሁ እኔ በእናንተ ውስጥ እንደምኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ ብቻ ነው ለየትኛውም ከባድ ለሚባል በሽታ ፈወስ ምክንያት የሚሆነው፡፡

"በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፣ በልሳን ተናገሩ፣ በልሳናችሁም ዘምሩ፡፡ መናገር የያዛችሁት የኔን ቋንቋ ነው፡፡ እኔም በእናንተ ውስጥ አልፌ ፍፁም የሆነውን ፀሎት እፀልያለሁ፡፡ በልሳን ለመፀለይ ማንም ተስፋ እንዲያስቆርጣችሁ አትፍቀዱ፡፡ ዲያቢሎስ የሚያፍሩ፣ በራሳቸው የማይተማመኑና ምንም ያልገባቸውን ነፍሶችን በመጠቀም ይህንን ኃይል ያለውን ስጦታችሁን ሊያስቆማችሁ ይሞክራል፡፡ እናንተ ግን አትፍቀዱ፡፡ እንዳውም ከምንግዜውም የበለጠ በልሳን መፀለይ ያለባችሁ አሁን ነው፡፡ በምትፀልዩበት ጊዜ ለአንዳንዶቻችሁ የልሳኑን ትርጉም ይሰጣችኋል፡፡ ይህም የሚቃወማችሁ ሰው ወይም አውሬ ወይም ራሳችሁ እንደሆናችሁ ግልፅ እንዲሆንላችሁ ነው፡፡

"ብዙ የተለያዩ ተቃዋሚዎች ወደፊት ስለሚኖራችሁ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥበብ ያስፈልጋችኋል፡፡ ፀሎትን ከሁሉ ነገር ፍፁም ቀዳሚ ተግባር ካደረጋችሁ የሚሆነውን ነገር በቅድሚያ አስጠነቅቃችኋለሁ፡፡ ከራሳችሁ ህይወት እንኳን በበለጠ ከእኔ ጋር በፀሎት ለማሳለፍ ትኩረት ልትሰጡት ይገባል፡፡

"ከህብረታችሁ አንድም ሰው ቢሆን ካለ ፀሎት መንቀሳቀስ የለበትም፡፡ ሳይፀልይ ከእናንተ ጋር የሚንቀሳቀስ ሰው ህብረታችሁን ለማዳከም ዋናው ምክንያት ነው፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በኋላ ከዳተኛ ይሆኑና ጫናን በመፍጠር ህብረቱ ያልተገባ ምርጫ እንዲያደርግ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም ለዚህ መፍትሄው እያንዳንዱ ሰው ሁልጊዜ በፀሎት እንዲቆይ ማድረግና የማይፀልዩትን ግን ወደሌላ ሥፍራ እንዲሄዱ መፍቀድ ነው፡፡ ይህንንም የምታደርጉት ወደ እኔ እንዲመጡና እኔ በምፈልገው ደረጃ እንዲኖሩ ለማድረግ በራሳችሁ የምትችሉትን ሁሉ ካደረጋችሁና መሻሻል ካላሳዩ ነው፡፡

"በመጨረሻውም ነገሮች እየተባባሱ ሲሄዱ፣ ከእኔ ጋር በሙሉ ልባችሁ መጣበቅና በራሳችሁ እውቀትና አካሄድ ያለመደገፍ ግድ እየሆነባችሁ ይሄዳል፡፡ እኔም በትክክለኛው አካሄድ መሄድ እንድትችሉ አነሳሳችኋለሁ፡፡ በህልማችሁ እንኳን እየመጣሁ

መመሪያ አሰጣችኋለሁ፡፡ ወደ ክስተቶች መጨረሻ እየሄዳችሁ በመጣችሁ ቁጥር ነገሮች የበለጠ እየተደበላለቁና የእናንተም ነፃ መውጣት እየቀረበ መምጣቱን በደንብ ተረዱ፡፡

"ሁሉም ነገር የሚሆነው በእኔ ላይ ባላችሁ እምነትና መተማመን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ለጥንካሬ፣ ለብርታት፣ ለጥበብ፣ ለርህራሄና ለሰላም ፀልዩ፡፡ የምትድኑት በእምነታችሁ ስለሆነ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፡፡

"ሰዎች ሁኔታዎችን ማለፍ አቅቷቸው ፍፁም ሲሰበሩና መቀጠል ሳይችሉ በአይናችሁ ትመለከታላችሁ፡፡ ያስጥለናል ብለው የገመቱት እንደማያስጥላቸው ሲያውቁ ውስጣቸው ተስፋ ሲቆርጥ ትመለከታላችሁ፡፡ ያን ጊዜ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ መፀለይና ርህራሄን ማሳየት ነው፡፡ የኔ ፀጋ ይሸከማቸዋል፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዳንዶች ታማሚዎች ወይም አካል ጉዳተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለእነዚህም በሚቻላችሁ ሁሉ የሚያስፈልገውን አድርጉላቸው፡፡ በእነሱ ምክንያት ትዕግስታችሁን አትጣሉ ወይም አታባርሯቸው፡፡ ምናልባት እነዚህ ሰዎች ከእኔ ፀጋን ለመቀበል ምክንያት ይሆኑላችኋል፡፡ እነርሱን ስለተከባከባችሁ እኔ ደግሞ እናንተን እንከባከባችኋለሁ፡፡

"ነገር ግን ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አንድን ሰው ወደኋላ ትታችሁ መሄድ ካለባችሁ ምግብና መጠጥ አብራችሁ በመተውና በመፀለይ ለእኔ የምህረት እጆች አሳልፋችሁ በመስጠት ሂዱ እንጂ እራሳችሁን በመክሰስ አትጨነቁ፡፡

"የምትፈተኑት በምትችሉት ልክ ብቻ ስለሆነ እናንተ ማድረግ ያለባችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ ደግሞ ተራው የኔ ይሆናል፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ በደረሳችሁ ጊዜ ፊታችሁን ወደ እኔ መልሱና እንዲህ በሉ፡፡ 'ጌታ ሆይ እኛ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል ከአሁን ወዲያ ያለውን አንተ ተረከበን፡፡' በዚያን ጊዜ እኔ የምትቀጥሉበትን ብርታት እሰጣችኋለሁ፡፡

"ይህንን አስታውሱ የኔ ኃይል ፍፁም የሚሆነው በእናንተ ድካም ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ነው እናንተ ለእኔ ምን ያህል ውድ እንደሆናችሁና በእውነትም ደግሞ እኔ በእናንተ ውስጥ ማን እንደሆንኩ የማሳየው፡፡ አሁን መረዳትን ሁሉ በሚያልፍ ሰላም፣ ብርታት፣ ፅናት እባርካችኋለሁ፡፡ ሩጫውን ፈጽሙ፡፡ እናም ይህንን አስታውሱ በሁኔታዎች ሁሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ምንም ነገር ቢያጋጥማችሁ አልተዋችሁም፡፡ ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡

## የቀረው እጅግ ጥቂት ጊዜ ስለሆነ ወደ እኔ ኑ - ሜይ 11 ቀን 2015 ዓ.ም - ካሮል ጄኒንጊስ

## There is very little time – come to Me, May 11, 2015 - Carol Jennings

"ዛሬ በዚህ ማለዳ በተለመደው አጠራራ ጓደኞቻችን ብለን ለምንጠራቸው የማስተላልፈው መልዕክት አለኝ፡፡ የምናገረውም ስለ ጊዜ ነው፡፡ ስለ ጊዜ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ብሎ ተናግረንበታል፡፡ ነገር ግን ስለ ጊዜ ስናነሳ ብዙ ገፅታዎች አሉት፡፡ ዛሬ ግን የማነሳው የጊዜ ገፅታ ነፍሳችሁን የሚመለከተውን ነው፡፡"

"አሁን የቀራችሁን ቀሪ ጊዜ መቁጠር ያለባችሁ ለትንሽ ጊዜ ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ከእኔ በቀጥታ ለእናንተ የተሰጠ እጅግ ውድ ዕቃ አድርጋችሁ ነው፡፡ ይህ የተሰጣችሁም ጊዜ እናንተ እንደፈለጋችሁ ልትጠቀሙበት፣ ለመደሰቻ ጊዜ ወይም ደግሞ ሸቀጦችን ከገበያ ቦታዎች ያለአግባብ እንድታግበሰብሱበት አይደለም፡፡ ይህ ያለፈ ታሪካችሁ መሆን አለበት፡፡ አሁን

ሁላችሁንም የምላችሁ ሙሽሮቼ ወደቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት ቅድስናንና ፅድቅን ጨምሩ እንዳልኳቸው አሁን ደግሞ እናንተን ለዛ ህይወት እጠራችኋለሁ፡፡"

"እኔን በህይወታችሁ ላይ በመሾም ታዘዙኝ፡፡ እንዲሁም በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያስቀመጥኩላችሁን እውነት ታዘዙ፡፡ በምድር ላይ ለመጨራሻ ጊዜ ያመጣሁትን የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃትን አይታችኋል፡፡ እናንተ ለዛ ምስክሮች ናችሁ፡፡ በዛ ወቅት የተላለፈውንና ለውጪ አገራት እንኳን ሳይቀር የተሰራጨውን ይህንን ትምህርት ሳትቀበሉ እንዳትቀሩ፡፡ የሰማችሁትን የእውነትንና የመዳንን ቃል በቀላሉ አትመልከቱት፡፡ እነዚህ የሰማችኋቸው ቃሎችና እውነቶች ህይወታችሁን ከአደጋ ለመታደግ ወሳኝ ናቸው፡፡"

"ይህ አሁን ያላችሁበት ወቅት ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሲቆጠር ለሰባት ዓመታት ብቻ የሚቆይ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ምናልባት ይህንን ፅሑፍ ያገኛችሁት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከሆነ ነው፡፡ ይህንን መልዕክት ስታገኙ ለህይወታችሁ ትልቅና እጅግ አስፈላጊ ነገር አግኝታችኋል፡፡ ምናልባት ይህንን ስታገኙ ወዲያው ከንጥቀት በኋላ ከሆነ እኔን ለመስማት የመጀመሪያዎቹ ዕድለኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ምናልባትም በምድር የቀሩትንና የኔ የሆኑትን ለመሰብሰብ በሚደረገው የመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በመንፈሴ ከምትሞሉት መካከል የመጀመሪያዎቹ ከሆናችሁ በእርግጥም የተባረካችሁ ናችሁ፡፡

"ነገር ግን ይህንን እውነት እነግራችኋለሁ፡፡ ይህንን መልዕክት የምታገኙት የቅጣቱ ዘመን ከጀመረ 1ኛ ወይም 2ኛ ወይም 3ኛ ዓመት ካለፈ በኋላ ከሆነ ይህንን የሰማችሁትን ቃል ለመቀበል ወቅቱ ነው፡፡ አሁን እኔን ለመፈለግና በእኔ ለመገኘት ጊዜው ነው፡፡ ምክንያቱም እዚህ ደረጃ ከደረሳችሁ በኋላ ጊዜ ማጥፋት ውሳኔ ለመስጠት ጊዜው እያለፈባችሁ ነው፡፡

"በሰባተኛው ዓመት አጋማሽ ላይ በህይወታችሁ ላይ እንደገና ሌላ መነዋወጥ ይሆናል፡፡ ይህም ነውጥ በሚታየው አለም ላይ ብቻ ሳይሆን በማይታየውም አለም ትልቅ መናወጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የክፉ ኃይላት በከባድ ሁኔታ ለጦርነት ይሰለፋሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ በምንም አይነት መልኩ ቢሆን የተለመደውን ዓይነት ህይወት መኖር እጅግ የማይቻልበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆነው እስካሁን ድረስ ለገዢው አባማና ከበታቹ ለሚያስተዳድሩት ክፉዎች ካልተንበረከካችሁ ነው፡፡"

"አዎን ለእናንተ የክርስቶስ ተቃዋሚው ማን እንደሆነ እየጠቆምኳችሁ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ (ከ3 1/2 ዓመት በኋላ ማለት ነው) ይህ ሰው ለመቃወም ለሚሞክሩት ሁሉ እንዴት የክፉዎች ተምሳሌት እንደሆነ ሳታውቁ አልቀራችሁም፡፡ በሚቃወሙት ላይ ብዙ ሞትን፣ ብዙ ጥፋትን፣ ብዙ በሽታዎችንና ጉዳቶችን በማምጣት በብዙ ሚሊዮኖች ላይ ከባድ ጥፋትን አድርሷል፡፡ ብዙዎችም እርሱን በመቃወም ህይወታቸው አልፏል፡፡"

"ይህንን መልእክቴን ያገኛችሁት ካሮልና ክሌር ከሚባሉ አገልጋዮቼ ሲሆን እነርሱም እኔ መጥቼ ወደ መንግስተ ሰማይ ከእኔ ጋር እንዲኖሩ ከመውሰዴ በፊት ይህንን መልዕክት በአለም ላይ ተበትነው ያሰራጩ ከነበሩት ከብዙዎቹ መካከል ናቸው፡፡ ነገር ግን እናንተ የመጨረሻችሁን ውሳኔ ለማስተላለፍ የቀራችሁ በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፡፡ እናንተን በዛ ጊዜ ጠላት ሁሉ ነገር ደህና እንደሆነ እንዲያሳምናችሁ በመፍቀድ ከእውነተኛ ሰዎች እውነቱን እንዳትረዱ ወደ ጎን ዞር ብላችሁ ነበር፡፡"

"አሁን ግን እነግራችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ውሸትና የነፍሳችሁ አጥፊ ሴራ ናቸው:: ከዚህ በኋላ ግን ይህንን ውሸት መቀበል የለባችሁም:: ምክንያቱም ጊዜው በጥድፊያ እያመለጣችሁ ነው:: የኔ የሆኑትን ህዝብ በአስተማማኝ ሥፍራዎች ፣በህይወት እንዲኖሩ አሰባስቤ፣ በጤንነትና በምግብ አበልፅጌና የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ አድርጌ በአለም ዙሪያ ሁሉ በየቦታው አስቀምጫለሁ:: አሁን አጄን ያዙና ወደ እነርሱ እንድመራችሁ ፍቀዱልኝ:: ልባችሁን በሙሉ ለእኔ አሳልፋችሁ ስጡኝና ወደ እነርሱ ልምራችሁ:: በመራኋችሁም በዛ ቦታ አስከፊውን ጊዜ በሰላም፣ በእውነትና አይታችሁ በማታውቁት ወይም እጅግ በረሳችሁት በእውነተኛ ፍቅር ትጨርሱት ይሆናል:: "

"ልጆቼ አሁን የእናንተ ጠላት ጊዜ ነው:: አሁን ይህ ለእናንተ በደንብ ላይገባችሁ ይችላል:: ነገር ግን ወደፊት ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባችኋል:: አሁን በዚህ መልዕክት ላይ የተፃፈውን የእኔን ቃል ብቻ ተቀበሉኝ:: እንደዚህ ግልፅ የሆነ ብዙ የማስጠንቀቂያ መልዕክቶች አታገኙም:: አሁን እንኳን በነፍሳችሁና በመንፈሳችሁ ላይ እነዚህ ቃሎች እውነትና ታማኝ እንደሆኑ እንድታምኑ እየሰራሁ ነው ምክንያቱም እነዚህ ቃሎች የተነገሩት በእውነተኛውና በታማኙ ነው:: "

"እባካችሁ ወደ ልባችሁ አስገቡኝና ላግኛችሁ፣ ላድናችሁና ደህንነታችሁና መዳናችሁ አስተማማኝ ወደሆነው ወደ በረሃ ተሸከሜ ልውሰዳችሁ:: ምክንያቱም በመንግስቴ ከእኔ ጋር እንድትገናኙ ልቤ እጅግ ይናፍቃል::"

"ኑ! የኔ ውድ ጓደኞች ኑ! እናንተን እየጠበኩ ነው፣ ኑ!

ለነፍሳችሁ መዳን በመስቀል ላይ የሞትኩት ኢየሱሰስ ክርስቶስ፣ አሁንም በማያልቀው ፍቅሬ ወደ እኔ እንድትመጡ እየጠበኳችሁ ነው::

## አለም ፍርክስክሱ ሲወጣ እናንተስ ትቆሙ ይሆን? ሜይ 11 ቀን 2015 ዓ.ም

## Will you stand when the world crumbles? May 11, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . የተወደዳችሁ የዩ-ቲዩብ ቤተሰቦች ጌታ ከገበያ ማዕከላት፣ ከኢንተርኔት መረቦች፣ ፊልሞችን ከማየትና ከሌሎችም የመዝናኛ ዓይነቶች እንድትርቁ የጠየቃችሁን ጉዳይ አንዳንዶቻችሁ ግራ እንደተጋባችሁ ነው የገለፃችሁት:: ለእናንተ በምፀልይ ጊዜ ሁሉ ነገር ፍንትው ብሎ ታየኝ:: በአሜሪካና በሌሎች ቦታዎች የምንገኝ ሁሉ በዳንኤል መፅሐፍ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተገለፀው ጭኖቹ ብረት፥ እግሮቹ ግማሹ ብረት ግማሹም ሸክላ የሆነውና በምድር ሁሉ ላይ በመነሳት ምድርን የሚበላው ምስል ጉዳይ ሲፈፀም ልናይ ነው:: የጀርመኑ ሂትለር እንዳደረገው እንደዛው ብዙዎች ግንዛቤው ሳይኖራቸውና ሳያውቁ ሊጠመዱ ነው::

ግንዛቤው ሳይኖራቸው የሚጠመዱት ደግሞ ጊዜያቸውንና እሴቶቻቸውን በዚህ አለም ጉዳዮች ላይ ያደረጉ ሲሆኑ እነዚህም ገንዘብ፣ ገበያ ማዕከላት፣ ግብይቶች፣ ለተለያዩ ነገሮች መጓጓት፣ ከበረ በአላት፣የተለያዩ ግብዣዎች፣ ጊዜን የምናጠፋባቸው ሁኔታዎችና የመሳሰሉት ናቸው:: ነገር ግን ጊዜያቸውን በቋሚነት ከጌታ ጋር የሚያደርጉና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ዋጋ የሚሰጡ ሰዎች ስለሁኔታው በቅድሚያ በደንብ ስለሚያውቁ ፀንተው የሚቆሙት እነዚህ ናቸው:: በአንፃሩ ግን

በዙሪያችን የሚንኮታኮቱትና በሚመጣው ኃይል እግር ሥር እንደ አቧራ ብናኝ የሚሆኑት ሁላችንም ነፃ ሰዎች እንደሆኑ የምናውቃቸው ሰዎች ናቸው።

በአንድ ቀን አለም ይቀያየራል። ጊዜያቸውን በኢንተርኔት፣ በዜና፣ በቲውተር፣ በፌስ ቡክ፣ በዩቲብ፣ በስልክን በመሳሰሉት የመገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች ጊዜያቸውን የሚያጠፉ ሰዎች እነርሱ የሚያውቁት አለም ሲቆም በአንድ አፍታ አንዱ ከሌላው በመለየት ፍሬ አልባና ባዶ ይሆናሉ።

በዚያን ወቅት እውነታችን እግዚአብሔር ብቻ ይሆናል። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት አሁን ካልኮተኮትነው በስተቀረ ባለስልጣኖች በጭፍን ወደ እሥራት ከሚመሩን እግዚአብሔራዊ ካልሆነው ከሚመጣው መንግስት እውነታ ውጪ ምንም እውነታ ሊኖረን አይችልም። ለገንዘብ ከኖራችሁ በገንዘብ ትወድቃላችሁ። ዋጋ ቢስ በሆነ መዝናናቶች፣ አለማዊ በሆነ መንገድ ኖራችሁ ከሆነ፣ እላይ በተጠቀሱት የመገናኛ መንገዶችና በከፍተኛ መጓጓት ኖራችሁ ከሆነ እናንተ እውነት ብላችሁ የያዛችሁት መንገድ ሲወሰድባችሁ እነዚህ የተወሰዱባችሁ ምቾቶቻችሁ እንዲመለሱላችሁና የደህንነት ስሜት እንዲሰማችሁ ለማድረግ የሚጠይቃችሁን መስዋዕት ሁሉ ትከፍላላችሁ።

ነገር ግን በምን ዋጋ መጠን ነው ይህንን የምታደርጉት? ሰው አለምን ሁሉ ቢያተርፍና ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? በዚያን ሰዓት ብዙዎች ነፍሳቸውን ያጣሉ። ምቾቶቻቸው እንዲመለሱላቸው ለማድረግ ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ። መፅሐፍ ቅዱሳቸውንና የባንክ ደብተራቸውን ጎን ለጎን ያስቀምጣሉ። አይታያችሁም? ኢየሱስ ለእነዚህ ጊዜያቶች እያዘጋጀን ነው። በዚህም በእርሱ ላይ ፀንተን እንድንቆምና ነገሮችን ሳናውቅ ግራ በመጋባት እንዳንደነግጥ እያዘጋጀን ነው። ለዚህ ጊዜ ልባችንን አዘጋጅተናል። ጥንካሬያችንን ከእኛ ውጪ በሆነ በመገናኛ ብዙኃን ላይ ሳይሆን በውስጣችን በሚኖረው በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን ኮትኩተናል። የእኛ ጥንካሬ ሊሆን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው። የቀረው አለም በተፈጠረው ትርምስምስ ግራ ተጋብቶት እያለ እኛ ግን አይምሮን የሚያልፍ ሰላም ይኖረናል።

እርሱ የመርከባችን መሪ በመሆን አቅጣጫን ያሳየናል፣ ይመራናል። ሞገዱ በኃይል ቢናወጥም የመርከቡ መሪ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ስለሆነ ኢየሱስ በማዕበሉ ውስጥ እንደተኛ እኛም በሰላም እንተኛለን። ስለዚህም እኔ የምጠይቃችሁ ህይወታችሁን በመቀየር ጌታን እንዳታስቀኑት ነው። ይህንን እንድታደርጉ የጠየቃችሁ ለሠርጋችን ቀን ብቻ ሳይሆን ለሚያስፈልግና እውነተኛ ለሆነ ዓላማ ነው። ይህም ሌላው አለም በትርምስ ውስጥ ሲወድቅ እናንተ ፀንታችሁ እንድትቆሙ ነው። መልካም አድናቂዎች በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥሉ። እሴቶቻችሁንና በህይወት የምታደርጉት አትኩሮት ሁሉ በእርሱ ላይ አድርጉት። በዚህም አለም ሁሉ ሲበታተን እናንተ ግን እግዚአብሔር በገባላችሁ ቃል ላይ በመተማመን ትቆማላችሁ።

## ለእናንተ ያለኝ ፍቅር እጅግ ትልቅ ነው - ሜይ 12 ቀን 2015 ዓ.ም - በካሮል ጄንጊስ

## How is great is My love for you, May 12, 2015, by Carol Jennings

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "የተወደዳችሁ ዛሬ ማለዳ ለመናገር የምፈልገው ስለ ፍቅር ነው።"

"ስለ እኔ ፍቅር"

"የኛ ውድ ጓደኞች በካርሎስ መፅሔት ላይ የተላለፈውን እስካሁን ስታነቡ ነበር፡፡ እርግጠኛ ነኝ እስካሁን ለእኔ ያላትን ፍቅር በመፅሔቷ በሁሉም ስፍራ በፃፈችው ፅሑፍ በማየት ተረድታችኋል፡፡ ይህንን ፍቅር ልዩ ሆኖ አግኝታችሁታል? የእርሷ ፍቅር እንዴት ጥልቅና ጠንካራ እንደሆነ በትንሹ እንኳን ብልጭ ብሎ ታይቷችኋል? በከፍተኛ ደረጃ እንኳን ከእርሱ ጋር ብትጓዝ በደበዘዘ ሁኔታ እንጂ ማየት ያልቻለችውን፣ እንዲሁም በጣም በጥቂቱ ቆንጠር አድርጋ ያገኘችውን አምላክ ማፍቀሯ ለምን እንደሆነ ገብታችኋል? በዚህ ምድር ላይ የኖረችው ለ61 ዓመታት ሲሆን ስለ እኔ የተረዳችውና እንደምወዳት ያወቀችው ለ58 ዓመታት ነው፡፡ ተገረማችሁ? ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?" እናንተ እንደምታስቡት የማይታየውን፣ እጅግ በርቀት የሚገኘውን መውደድ ?

"የኔ ውድ፣ ውድ ጓደኞች ይህንን እወቁ፡፡ ከመወለዳችሁ በፊት፣ አለምን እንደምታዩት አድርጌ ከመፍጠሬ በፊት፣ እናንተ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ እንደ ጭላንጭል የተቀመጣችሁ ፍጥረት ነበራችሁ፡፡ እግዚአብሔር አብ ፀነሳችሁ - እናንተን፣ አይምሯችሁን፣ ልባችሁን፣ ነፍሳችሁን፣ ሰውነታችሁን፣ ሁለንተናችሁን፣ መንገዳችሁን ሁሉ፡፡ እንዲሁም እንደዚህ ባለ ጊዜ እንድትወለዱ ተደርጋችሁ፡፡ እናንተ በአጋጣሚ በተደረገ ወሲባዊ ግንኙነት ወደዚህ አለም የመጣችሁ  አይደላችሁም፣ በፍፁም፡፡

"ስለ እናንተ እያንዳንዱን የወሰነው እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ ይህም የት አገር ፣ ከየትኛው ቤተሰብ፣ መቼ እንደምትወለዱ ሁሉ በእርሱ የተወሰነ ነው፡፡ የት መማር እንዳለባችሁ ትዕዛዝን የሰጠው፣ አብራችሁ የተጫወታችሁትንና የተደባደባችሁትን ሁሉ የወሰነው፣ ጥሩ የምትሉት ወይም የማትሉት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያለውን እያንዳንዱን የህይወታችሁን ታሪክ የወሰነው እርሱ ነው፡፡

"ኃጢያት ብዙ ሙከራዎችን፣ ፈተናዎችንና ከባድ ነገሮችን ወደ ህይወታችሁ ይዞ መጣ፡፡ ከእነዚህም አብዛኛዎቹ  ምናልባት የመጡት በጠላታችሁ በሰይጣን ነው፡፡ ከተወለዳችሁ ጀምሮ ስለ እኔ መጥፎ እንድታስቡ ያደረገው እርሱ ነው፡፡ እኔ ግን እዛው ከእናንተ ጋር ነበርኩ፡፡ ከዛች ጊዜ ጀምሮ መላዕክቶቼ  እየጠበቋችሁ ነበር፡፡

"እናንተ ብቻዬን ነኝ ብላችሁ ባሰባችሁት ወቅት፣ ህይወት እጅግ ከብዷችሁ ከዚያ በኋላ መቀጠል የማትችሉ በመሰላችሁ ጊዜና ከዚያ የበለጠ ከባድ ነገር ሊመጣ እንደማይችል በመገመታችሁ ጊዜ ሁሉ ወደ እኔ እየሳብኳችሁ፣ በነፍሳችሁ ውስጥ ፍቅሬን እያፈሰስኩና እኔን ቀና ብላችሁ ተመልክታችሁ የኔን ልብና የኔን መንገድ እንድትመለከቱ በመፈለግ ከእናንተ ጋር ነበርኩ፡፡

"ቆንጆ ቢራቢሮ ባያችሁ ቁጥር፣ ወይም ህፃን ድመት አይታችሁ በህይወታችሁ ደስታን ስታመጣ እኔ ነኝ ይህንን ሁሉ ወደ እናንተ የላኩላችሁ፡፡ እውነተኛ የፍቅር ቃል ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከእህቶቻችሁ ወይም ከወንድሞቻችሁ፣ ከአስተማሪዎቻችሁ፣ ወይም ከጓደኞቻችሁ የሰማችሁት እነሱ አወቁትም አላወቁትም እኔ ነበርኩ በእነርሱ ውስጥ አልፌ እጄን ይዛችሁ እንድትከተሉኝ በመፈለግ ስናገራችሁ የነበረው፡፡ አያችሁ? እኔ በመልካሙም በመጥፎውም ነገር ሁሉ አብሬያችሁ ነበርኩ፡፡

"ታዲያ ይህንን ያህል ከወደደኝ ለምን ይህ ወይም ያ ነገር ደረሰብኝ' ለምን ይህ ያ ሆነ?' በማለት ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ 'ደግሞስ ፍቅር ሲል ምን ማለቱ ነው? እስቲ በአካባቢያችንን ያለውን ተመልከቱ፣ እስቲ አሁን ያለሁበትን እንኳን ተመልከቱ ??? ልትሉ ትችላላችሁ፡፡' አዎ እነዚህ ነገሮች ሊገቡን አይችሉም፡፡ ነገር ግን እስቲ ራሳችሁን ለደቂቃ ያህል ከዚህ ውስጥ አውጡ፣ ንዴታችሁንና መራራነታችሁን ወደ ጎን አድርጉና ለጥቂት ጊዜ ከእኔ ጋር በመሆን ስለ ምክንያት እንነጋገር፡፡

"ለመሆኑ አንድ አፕል የሚበቅለው አጠገቡ ካሉት ዛፎች በተመሳሳይ ሁኔታ ነውን? በእያንዳንዱ ላይ የተበላሸና ያልተበላሸ ፍሬ አይኖረውምን? ፍሬዎቹ አጠገብ ለአጠገብ ተንጠልጥለው እያሉ አንዱ የሚያብረቀርቅ ቀይ ሌላው ደግሞ ደብዘዝ ያለና በትንሹ የሚምር አይሆንምን? እንዲሁም አንዱ ፍሬ በነፍሳት ተወግቶ እዛው በዛፉ ላይ እያለ መበስበስ ይጀምር የለምን? ሌላውስ ደግሞ ተቀጥፎ በመበላት ደስታን ይሰጥ የለምን? ቀጥፎ ለወሰደው ደስታን ይሰጥ የለምን? ሌላው ደግሞ እዛው በዛፉ ላይ በመቆየት ሲበስል መሬት ወድቆ በእግር ይረገጥ የለምን?

"እወነቱን ልንገራችሁ እነዚህ ሁሉ እኔ የፈጠርኳቸው ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው እኔ ማን እንደሆንኩ ክብሬን፣ ግርማዊነቴንና በመፍጠር ኃይሌ ለምድር የሰጠሁትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለሌሎች ፍጥረታቶቼ ግድ እንደሚለኝ ሁሉ ለእነዚህም ግድ ይለኛል፡፡

"ሁለት አዲስ የተወለዱ ቡችሎችን እንውሰድ፡፡ አንዱ ቡችላ አሰልጥነው በቤት ውስጥ ክብካቤ ወደሚያደርጉለትና ደስተኛ ህይወት ወደሚሰጡት ቤት ተወሰደ፡፡ አንዱ ደግሞ ልቡ ክፉና ጨለምተኛ ወደሆነ ቤት፣ ሁልጊዜ ወደሚመታው፣ ወደሚያሰቃየውና መጨረሻም ወደ ገደለው ሰው ቤት ተወሰደ፡፡ ሁለቱም የተወደዱ አይደሉምን? ሁለቱስ የኔ ፍጥረታት አይደሉምን? ሁለቱስ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አይደሉምን? በመጨረሻስ መላዕክቶቼን ልኬ እኔ ወዳለሁበት አቅፈው እንዲያመጡትና በደስታ እንዲኖር አላደርግምን?

"ልያችሁ ሰዎች አይኖቼ ድንቢጦችን እንኳን እንደሚያይና አንዷ እንኳን እኔ ሳላውቅ እንደማትወድቅ ስነግራቸው አያምኑኝም፡፡ ደግሞም እያንዳንዱ በፍጥረቴ ውስጥ ያለ ነገር እንዴት የልቤ ክፍል እንደሆነ አይገባቸውም፡፡

"አሁን ምናልባት ታሾፉብኝ ይሆናል፡፡ ካሮል እንኳን በዚህ ጊዜ ተነስታ ማሰብ ጀመረች፡፡ ስለዚህም አሁን እየተናገርኩት ያለ ሐሳብ በእውነት ከእኔ የወጡ ቃሎች ወይስ ከእርሷ የመነጨ እንደሆኑ ጠየቀችኝ፡፡ ነገር ግን ምን እንዲገባችሁ እየሞከርኩ እንዳለ ልብ ብላችሁ አድምጡኝ፡፡"

*ጌታ መናገር እችላለሁ?*

"አዎ ትችያለሽ"

ስለ አፕሉ ፍሬ ሲያስረዳ ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝም ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ እውነት ይህንን ነገር እየተናገረኝ ያለው ኢየሱስ ነው በማለት እየተደነቅሁ ነበር፡፡ እርሱ መሆኑን ሳረጋግጥ ግን የተናገረው እንዲገባኝ ትንሽ አይምሮዬን ከፈተልኝ፡፡

እኔ ራሴ ሰዓሊ ስለሆንኩ በእያንዳንዱ የስዕል ፈጠራዬ ውስጥ የኔ የሆነ ነገር ይኖራል፡፡ እናም በእነዚህ ስዕሎቼ ውስጥ የእናትነት ስሜት አለበት፡፡ ሳላውቀውም እነዚህ የስዕል ፈጠራዎቼ ሁሉ ይህ እንዲሰማቸው እፈልጋለሁ፡፡ ስለዚህ የገባኝ ነገር የምናያቸው ነገሮች ሁሉ የእርሱ ድንቅ የፈጠራ ሥራዎች ናቸው፡፡ በዚህም አንፃር በአለም ላይ በአይናችን የምናየው እያንዳንዱ ነገር አፕልን ጨምሮ አንድም ሳይቀር የእርሱ ክፍል ነው ማለት ነው፡፡ ይህ በደንብ እንዲገባን ለማድረግ ትላንትና ማታ ጌታ ስለ ሰማያዊ ቤታችን ለክሌር የነገራትን እጠቅሳለሁ፡፡

"ፍቅር የሰራውን ለውጥ ታያላችሁ፡፡ አንበሳና ኢጋዘን ጎን ለጎን ተኝተው በመተቃቀፍ አብረው ያንቀላፋሉ፡፡ ኦተሮች በውኃ ላይ በመንሳፈፍና ቆንጆ የሆኑ ሼሎችን በእግራችሁ ሥር በመጣል እንድታሻሿቸው ይጋብዟችኋል፡፡ ንቦች የልብ ቅርፅን በመፍጠር ወደላይ እየበረሩ ማራቸውን እንድትካፈሉ ይጋብዟችኋል፡፡

"በስራችሁ የሚገኘው አሸዋ እናንተ እንዲመቻችሁ ለማድረግ በመስተካከል ቅርፁን ይቀይራል፡፡ ገደላማ ሸለቆው እግር መርገጫና እጅ መያዣ ስላለው በቀላሉ ለመውጣትና ለመውረድ ያመቻል፡፡ ወደላይም ስትወጡ በጣም የሚያስደስት በእምነበረድና በክርስታል ያጌጡ ትንንሽ ዋሻ የሚመስሉ ታገኛላችሁ፡፡ ንስር አሞራ ወደ ጎጇቸው ገባታችሁ ጫጩታቸውን እንድትዳስሱ ይጋብዟችኋል፡፡ የዛፍ ቅጠሎች በአጠገባችሁ ስታልፉ በደስታ ይዘላሉ፡፡ በላዩ ላይ ስትሄዱ ሳሩም  በፍቅር እየኮረኮራችሁ፣ ቅርፅ ባለው መልክ እያነፀባረቀ ሰላምታ ይሰጣችኋል፡፡

"በመንግስተ ሰማይ የሚገኙ ድንቅ ነገሮች ማለቂያ የላቸውም!  ይህ ሁሉ ለእናንተ የተቀመጠ ነው፡፡ ምክንያቱም እናንተ በምድር የኖራችሁት ለእኔ ነው፡፡ ስለዚህም አሁን በዘላለሙ መኖሪያችሁ መገመት በማትችሉት ነገሮች! ነገር ግን በምድር ሲመስጣችሁ በነበረው ነገር አስደስታችኋለሁ፡፡

*እዚህ ላይ ጌታ የነገረን ነገር አሸዋው፣ ዛፎቹና ሳሩ ሳይቀር ለእርሱ ፍቅር ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ ለእኛ ነው፡፡ እኛ እንዲገባንና በውስጡ እንድንጠቃለል ነው፡፡*

"አመሰግናለሁ የኔ ውድ ፡፡ በደንብ አድርገሽ ነው የገለፅሽው፡፡

"ጓደኞቼ ምንም የማይታሰበውን አፕልን እንኳን ቦታ ሰጥቼው በእኔ ንድፍ የተሰራና ክብሬን የሚገልጥ ከሆነ፣ እንዲሁም አጠገባችሁ የሚገኘውን ውሻ ክብካቤ የማደርግለት ከሆነ ስለ እናንተስ ምን ያህል ግድ የሚለኝ ይመስላችኋል? ለእናንተስ ያለኝ ፍቅር ምን ያህል የበለጠ ይመስላችኋል?

"የተወደዳችሁ ውድ ጓደኞቼ! ስለእያንዳንዳችሁ በልቤ ያለው ፍቅር ልትገምቱት ከምትችሉት በላይና የሰው ልጅ ከሚረዳው በላይ ነው፡፡ እናንተ እኮ ከፈጠርኳቸው ፍጥረታት ከፍተኛውን ደረጃ የያዛችሁ ፍጥረታቶቼ ናችሁ፡፡ አዳምን ከምድር አፈር ከማበጀቴና ህይወቴን በእርሱ ውስጥ እፍ ከማለቴ በፊት በአይምሮዬ ውስጥ የተፀነሳችሁ ናችሁ፡፡

አያችሁ? አሁን እንኳን ምን ያህል ነፍሳችሁ ወደ እኔና ወደ መንግስቴ መጥታ ከእኔ ጋር ለዘላለም እንድትኖሩ እንደምጓጓ ትንሽ ገባችሁ?

"እንድታስቡበት እለምናችኋለሁ፡፡ አለም በአሁን ሰዓት ምን ያህል ውበት እንዳላት ዙሪያችሁን ተመልከቱ፡፡ ውልብ የሚል ማብለጭለጭ ነው የሚታይባት፡፡ ከአሁን ጀምሮ ትንሿን ትንኝ፣ ቢራቢሮና እያንዳንዱን እንስሳት ተመልከቱ፡፡ እንዲሁም ገና በማደግ ላይ ያለውን እያንዳንዱን ዕፅዋት በማየት አስተውሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የእኔን ማንነት የሚገልፁና ለእናንተ የፈጠርኩት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

"የዚህ ሁሉ ፈጣሪ የሆንኩት እኔ እወዳችኋለሁ፡፡

"ጓደኞቼ ወደ እኔ ኑ! አለም ለእናንተ እጅግ አስቀያሚ፣ ሸካራና አደገኛ ናት፡፡ ነገር ግን እንዲህም ቢሆን ለሚያስፈልጋችሁ ነገር፣ ለመፅናናትና ለእርዳታ ብላችሁ ወደ ጠላት እቅፍ ውስጥ እንዳትገቡ፡፡ እውነቱን ልንገራችሁ እዛ የምታገኙት በሽታ፣ሞት፣ ጥላቻና ጥፋት ብቻ ነው፡፡

"ጓደኞቼ ወደ እኔ ኑ፡፡ እኔ በክብር የተሞላ፣ መሰረታዊና ድንቅ የሆነ ህይወት አሰጣችኋለሁ፡፡

ወደ እኔ ኑ ጓደኞቼ! ወደእኔ ኑ!

የሁሉም ምንጭ የሆነው !!

## "አሁን ምረጡ ገንዘብንና በራስ መተማመንን ወይስ እኔን?" - ሜይ 12 ቀን 2015 ዓ.ም - ካሮል ጄንጊስ
## Money, self reliance or Me, you must decide, May 12, 2015 - Carol Jennings

*ጌታ ዛሬ ምሽት ለጓደኞቻችን መልዕክት አለህ?*

"አዎ አለኝ መፃፍ ጀምሪ፡፡"

"የዛሬው ምሽት ርዕሳችን ገንዘብ የሚል ነው፡፡"

"አሁን ያላችሁ ብር ብዙ ቢሆን ትንሽ በመከራው ጊዜ ገንዘብ በፍጥነት ነው ያለፈ ታሪክ የሚሆነው፡፡ አንድ ደረጃ ላይ ስትደርሱ ውሳኔ ልታስተላልፉ ግድ ይሆናል፡፡ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚውን የኦባማንና የአስተዳደሩን ምልክት ለመብላት፣ ለመትረፍና ለመኖር ልወሰድ? ወይስ ሌላ ጥሩ አማራጩን? በሚለው ላይ ይሆናል፡፡

"ከእነዚህ ሁለት አማራጮች አንዱን መምረጥ ምን እንደሚያስከትል እንመልከት፡፡ የአለም ኢኮኖሚ ሲወድቅ፣ ሁሉም የገንዘብ መዋቅሮች ሲፈራርሱ፣ በአለም ላይ ያሉ ሳንቲሞች፣ የገንዘብ ምንዛሬዎች ሲተረማመሱ፣ ምልክቱን መወስድ ተገቢ የሚመስልበት፣ ትልቅ ነገር የማይመስልበት፣ እንዳውም አርቆ ማሰብና ብልህነት የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ደግሞም እስካሁንም ሲሰራበት የነበረና ሐሳቡ አዲስ የማይመስልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ስለዚህ ትንሽ የኮምፒዩተር ቺፕ እጃችሁ ወይም ግንባራችሁ ላይ ብታደርጉ ምናለበት? በቃ ይኸው ነው፡፡ ነገሩን አታካብዱ፣ የምትፈልጉትን ገዝታችሁ እጃችሁን በማወዛወዝ ክፍያውን መፈፀም ብቻ ነው በቃ ሌላ ጣጣ የለውም የሚባልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ አጋንንት በሰዎች ውስጥ አንዴ ከተደበቁና የወደቁ መላዕክቶች ከመጡ፣ ያን ጊዜ ለበላይ አለቆቻቸው የመታዘዝ ግዴታ ይመጣል፡፡ ስለዚህም አነዚህ ሰዎች እነሱ ትክክል ሌሎቹ ሰዎች ግን የተሳሳቱ አድርገው በአይምሯቸው እንዲቀበሉ በዚህም ውሸትን እውነት እውነትን ውሸት አድርገው እንዲቀበሉ ይደረጋሉ፡፡

"ብቻ በዚያም አለ በዚህ፣ በምንም መልኩ ተቀነባብሮ ቢቀርብ የመጨረሻው ውጤት እኔን መከተል ወይም ሰይጣንን መከተል ነው፡፡

"ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት ቺፑን በሰውነታችሁ ውስጥ ማስገባት የወደፊት ህይወታችሁ ላይ የማይፈታ ማህተም ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ቺፑ የአጋንንት "ዘር" ስላለበት አንዴ በሰውነታችሁ ውስጥ ከተቀበረ ሌላ ዘረ መለመል /DNA/ ወደ ደማችሁ ውስጥ ይልካል፡፡ ይህም የእናንተን ዘረ መለመል /DNA/ ለዘለቄታው በማጥፋት በድሮው ዘመን ኔፍሊም የሚባሉትን ዘረመለመል እንዲኖራችሁ ያደርጋል /ዘፍጥረት 6፡1/፡፡ ይህ ከሆነ ወዲያ ወደ ነበረበት እንደገና መመለስ አይቻልም፣ ደግሞም ይቅር አይባልም፡፡

"ለዚህ ነው አሁን ከመርፈዱ በፊት ወደ እኔ እንድትመለሱና ህይወታችሁን ለእኔ አሳልፋችሁ እንድትሰጡ የምጮኸው፡፡ በቺፑ ትንሽ ድርቆሽ ገዝታችሁ ለጥቂት ቀናት ከምትቆዩ ይልቅ ራሳችሁን ለሞት አሳልፋችሁ በመስጠት ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ ብትገናኙና ለዘላለም ብትኖሩ ይሻላችኋል፡፡ በዚያም ቢሆን በዚያ መሞታችሁ እንደሆነ የማይቀር ነው፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ ስልጣን የሚይዙት እንደሆነ ብትኖሩ ወይም ብትሞቱ ትንሽም ግድ የሌላቸው ናቸው፡፡

"እነሱ ሁሉንም ነገር የሚያደርጉት አንድ ግባቸውን ወይም ፍላጎታቸውን ለመፈፀም ብቻ ነው፡፡ ይህም የሰውን ልጅ ሁሉ በመስረቅ፣ በመዝረፍ፣ በመግደልና በማጥፋት ሁሉንም በቋሚነት የገሃነም ዜጎች ማድረግ ነው፡፡ የፈለገውን ያህል ታማኝነታችሁን ለእነርሱ ብትገልፁ የእናንተ ህይወት ለእነሱ ምንም ዋጋ የለውም፡፡

"በሌላው አንፃር ግን ለእኔ የእናንተ ህይወት ከሁሉ ነገር እጅግ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ወደ ምድር የመጣሁት ለእናንተ ብዬ ነው፡፡ በመስቀል ላይ ህይወቴን የሰጠሁት ትንሹን እርምጃ እንድትራመዱ ነው፡፡

**ኢየሱስን ተከተሉ እንጂ የአውሬውን ምልክት አትቀበሉ! - ሜይ 9 ቀን 2015 ዓ.ም - ካሮል ጄንጊስ**

**Follow Jesus - do not take the mark of the beast, May 9, 2015 – Carol Jennings**

ካሮል . . . ጌታ እውደሃለሁ፡፡ አሁን በጣም እየቀረብን መምጣታችንን ባሰብኩ ቁጥር አይምሮዬ ባዶ እየሆነና እያዞረኝ ነው፡፡ ታውቃለህ ስንጠብቅ በጣም ብዙ ጊዜ ነው፡፡ ህይወቴን ሙሉ ስጠብቅ ነበር! እንዲህም ሆኖ ወደ ኋላ መለስ ብዬ አመታቶቹን ስቃኛቸው እንደ ጥቂት ደቂቃዎች ነው የምቆጥራቸው፡፡

"ዋናው ነጥብ ይህ ነው፡፡ ውዴ ዛሬ ምሽት በአይምሮሽ ላይ ያስቀመጥኩት ሐሳብ ይህንን ነው፡፡ ህይወት እጅግ አጭር ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ዘላለም በጣም እጅግ በጣም ረዥም ነው፡፡ በዚህ ምድር ወደኋላ ለሚቀሩት ግልፅ ሊሆንላቸው የሚገባው ዋናው ሐሳብ ይህ ነው፡፡ የቀረው ህይወት የመጨረሻውንና አስፈላጊውን ውሳኔ የምትወስኑበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም በሚመጡት ቀናቶች እኔን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የምትወስኑበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

"መንግስት፣ ጓደኞቻችሁ፣ አለቆቻችሁ፣ ቤተሰቦቻችሁ ወይም ሌላ ማንም ሰው ምንም ይበል ምን ሊያሳምናችሁ ቢሞክር በፊታችሁ ያለው ምርጫ ሁለትና ሁለት ብቻ ነው፡፡ እኔን ወይም ሰይጣንን መምረጥ፡፡"

"ከእኔ ጋር ህይወት መቆሚያ የሌለው ነው፡፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም በክብርና በህይወት መኖር፣ እንዲሁም ልትገምቱት ከምትችሉት በላይ ንፁህ ፍቅር የሚገኝበት ህይወት ነው፡፡"

"ከሰይጣን የምታገኙት ግን ህመም፣ ሞት፣ መከራ፣ የማያልቅ ስቃይና በእሳት ውስጥ መጣል ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሞት በሥጋ መሞት ሲሆን ሁለተኛው ሞት ደግሞ በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ ከፈጠርኳችሁ፣ እስትንፋስ ለነፍሳችሁ ከሰጠኋችሁና እናንተ ሊገባችሁ ከሚችለው በላይ ከምወዳችሁ ከእኔ መለየታችሁ ነው፡፡"*(ይህም ሁለተኛ ሞት ለዘላለም ወደ እሳት ባህር መጣል ነው)*

"ዛሬ ማታ ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ፡፡ የቱን ትመርጣላችሁ? የነፍሳችሁን ጠላት የሆነውንና አለምን ሁሉ በሚችለው ዘዴና ውሸት በመጠቀም እናንተንና የሰውን ዘር ለመስረቅ፣ ለመግደልና ለማጥፋት የተዘጋጀውን? እናንተን ሊያሳምናችሁ በፈጠረው ደስታን በሚመስል ጊዚያው እርካታ የዘላለምን ህይወት መሸጥ ዋጋ ያለው ነገር አይደለም፡፡"

"ይህ ከያዕቆብና ከኤሳው ታሪክ ጋር አንድ ነው፡፡ ባርኮትንና ቃብትን በጥቂት ሥጋዊ ደስታ ለመለወጥ አንዴ ውሳኔ ከወሰኑ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ ያጡትን ማግኘት የማይቻል ነው፡፡"

ዛሬ ምሽት እነግራችኋለሁ፣ የአውሬውን ምልክት ተጠንቀቁ፡፡

"ሰው በነገሩ ይስቃል፣ መንግስት ስለነገሩ ይዋሻል፡፡ እኔ ግን እውነቱን እነግራችኋለሁ፡፡ ከተቀበላችሁት የዘረ መለመልን /DNA/ በመቀየር የሰይጣን ልጅ እንድትሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ነፃ ለማውጣትና ለማዳን የሚቻልበት

መንገድ የለም፡፡ ልጆቼ ብልህ ሁኑ፡፡ አሁን በጣም ብልህ ሁኑ፡፡ እኔን ስሙኝ፡፡ እንድረዳችሁና በፊታችሁ የመጡባችሁን ቀናቶች እንድታመልጡ ድምፄን ስሙ፡፡ ድምፄን በመስማት ብቻ ነው በህይወት የምትኖሩት፡፡ ድምፄን በመስማት ብቻ ነው ሰይጣን ያቀደባችሁን ሞት የምታመልጡት፡፡ ምንም እንኳን ጊዜው ከባድና የስቃይ ጊዜ ቢሆንም የሚቆየው ግን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አድናችኋለሁ፡፡ እዛው ከእናንተ አጠገብ እሆናለሁ፡፡ መጀመሪያ ለደህንነት እኔን ጥሩኝ /ንስሐ ገብታችሁ ነፍሳችሁ እንዲድን/፡፡ ከዚያም ጠላት እንዳይገድላችሁና የመከራውን ዘመን በህይወት እንድትኖሩ እኔን ጥሩኝ፡፡"

የሚወዳችሁ አባታችሁ፣ አባ ኢየሱስ፡፡

## የገሃነም መንጎች ወደ ምድር ተለቀዋል - ጁን 20 ቀን 2015ዓ.ም

## The Hordes of Hell Have Been Released, June 20, 2015

"የገሃነም መንጎች ወደ ምድር ተለቀዋል፡፡ አመፅን ለመቀስቀስ ካሉበት ወጥተዋል፡፡ ሰው በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ይህንን አድርጓል፡፡ በዚህም ሥራ የሰርን እጅ አለበት፡፡ እነዚህ ሰዎች ፍፁም እውሮች ናቸው፡፡ ይህ ነገር በእነሱ ላይ ምን ረብሻ እንደሚያመጣ አልገባቸውም፡፡ ምን እንዳደረጉ ባወቁ ጊዜ ግን ነገሩን ለማቆም የማይችሉበት ደረጃ ደርሷል፡፡ እነሱ በነቁ ጊዜ ያደረጉት ምድር ደርሶ የምድርን ግማሽ አጥፍቷል፡፡"

(ክሌር) እዚህጋ አንድ ነገር ለመጨመር እፈልጋለሁ፡፡ በሰርን ግቢ ውስጥ የሺቫን ሃውልት በመትከል ማታ ማታ ሙብራቱ እንዲበራ ይደረጋል፡፡ ሺቫ የምትባለው ጣኦት የምትወክለው የጥፋትንና የትርምስን ህይወት ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ የሚለው ገና ከሥር መሰረቱ እነዚህ ሳይንቲስቶች ዕውር ከመሆናቸው የተነሳ ምን ዓይነት ትርምስን እንደሚፈጥሩና በእነሱ ላይ ምን ነገር እንደሚያመጣባቸው አያውቁም፡፡

(ክሌር) ጌታዬ እኔ እኮ የመሰለኝ ሰርን በብዛት እየጎዳ ያለው የመሬትን የላይኛውን ክፍል፣ እንደገናም ፍጥረታቶቹም የሚመጡት ከሆነ ከኢጋንንቶች ፕላኔት ነበር፡፡

"ገሃነም የሚገኘው ከምድር ታችኛው ክፍል ነው፡፡ በአጋንንት የተለከፉ ፍጥረታት ወደ ምድር በመውጣት ምድርን እንዳይበክሉ መከላከያ የተደርገበትን የተለየ ዳይናሚክ ስበት ሽፋኑን ወደ ጎን በማድረግ አንስቶታል፡፡"

(ክሌር) ጌታ እያወራ እያለ አንድ ነገር ተመለከትኩ፤ ብርሃን የሚያስተላልፍ ትልቅ የአሣ መለኪያ ሳህን የሚመስል በመሬት ዙሪያ ያለና ነገር ግን በአክስለሬተሩ የተነሳ አየሁ፡፡

"ክሌር በእውነት ከሆነ በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ እነዚህን ልጆች የማይገባቸውን ነገር እያዘበራረቁ በሆነ መልኩ ከእኔ በልጠው ለመገኘት ወይም እኔ የፈጠርኩትን በማባዛት ከእኔ ጋር ለመስተካከል የሚፈልጉ አድርጌ ነው የማያቸው፡፡ ይህ በአብዛኛው የምሑርነት ኩራት ነው፡፡ በዚህም የእነዚህ ወንዶችና ሴቶች ቡድን ከፍ ወዳለው የፕሮፌሽን ጣራ ላይ ወጥቶ ቁጢጥ በማለት ኀብዝናቸውን ለአለም በማወጅ ብሎም ከእኔ ጋር እኩል እንደሆኑ ለማሳይት እየፈለጉ ነው፡፡"

"ነገር ግን አንድ ጉልህ የሆነ የጎደላቸው ነገር አለ፡፡ እና እኔንስ ማን ፈጠረኝ? አያችሁ እኔ በሰጠኋችሁ ህንፃ ብሎኬት ላይ መጫወት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ብሎኬቶቹ እርስ በርስ የተያያዙት በእኔ ፍቅርና ኃይል ነው፡፡ ትክክል ነው እነሱን በማንቀሳቀስ የተለያዩ ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችል ህግ አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የተፈጠሩት በእኔ ነው፡፡"

"የተሰራበትን ብሎኬት ባነሳው እነርሱ እዛው ውስጥ ሆነው አለም ያበቃለታል ነበር፡፡ እነርሱ በባዶ ሥፍራ ከሚንሳፈፉ የሉሎች ኃይል /globs of energy/ውጪ ምንም አይደሉም፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ግብ የሰይጣን ነው፡፡ የእነርሱን ከፍተኛ ፍላጎት በመጠቀም ሊያጠፋቸው ነው፡፡ አሁን ግን ዓይናቸው ማየት ስለማይችል ተሰውሮባቸዋል፡፡ እንደተናገርኩት ግን ምን እየሆነ እንዳለ መረዳት ሲጀምሩ ያን ጊዜ ደግሞ ወደኋላ ለመመለስ ጊዜው ያልፍበታል፡፡ ነገር ግን አለም የባህር ኃይል እንደተባበረባት ፊኛ ሳትነፋፋ እኔ ጣልቃ እገባለሁ፡፡"

"ለስንት ጊዜ ነው ከፈጠርኳቸው፣ የህይወትን እስትንፋስን እፍ ካልኩባቸውና ትልልቅ ጭንቅላት ካላቸው ከአንዳንዶቹ ጋር የመማሪያ እርዳታ አድራጊ የምሆነው? አይሆንም ይህ የሥራ ህይወታቸውን ያበላሻል፡፡ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ በውስጣቸው ለእውነተኛው የሳይንስ አለም የተጠሩ መሆናቸውን ቢያውቁም እንደ ጲላጦስ ጥሪያቸውን በመከተል ስራቸውን ማበላሸት የለባቸውም፡፡ ጲላጦስ እኔን መስቀል እንደሌለበት ቢያውቅም የተነሳበትን ተቋውሞና ቄሳር ከስልጣኔ ያባርረኛል ብሎ በመፍራት ብቻ አደረገው፡፡ እናም አሁን ተመልከቱ የማያጓጓውን የገሃነም ህይወቱን፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር፡፡ እነዚህም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን ለሥልጣንና ታዋቂ ለመሆን ያላቸው ከፍተኛ ጉጉት ስለበለጠባቸው ታምራት ካልመጣ በስተቀር የሚያስቆማቸው ነገር የለም፡፡"

"ስለዚህም ይህውና የጥፋት አፋፍ ላይ ደርሰናል፡፡ የገሃነም መንጋዎች ወደ ምድር ክልል ወጥተዋል፡፡ እነዚህም መንጋዎች የሚያውቁት የሰው ዘርንና የፈጠርኩትን ፍጥረት ሁሉ መጥላትና ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ እናም አሁን ማንም ሊገምተው ከሚችለው በላይ ሊገለጡ ነው፡፡ ይህም በሰዎች በኩል ምድሪቱን ማጥፋት ነው፡፡ ክሌር እነሱ የራሳቸው መንገድ አላቸው፣ እኔም በእጃቸው ሰጥቻቸዋለሁ፡፡"

(ክሌር) ነገር ግን፣ ጌታ ሆይ 'መጨረሻ የሌለው አለም' የሚለውስ ፀሎትስ?"

"ምድር ትወድማለች፣ ነገር ግን አትጠፋም፡፡ አዲስ የፀደይ ጊዜን ከእኔ ጋር ይዤ እመጣለሁ፡፡ በአዲስ የተፈጠረች ውብ ምድር፣ ሁሉንም መልሼ አስተካክላለሁ፡፡ በአክስለሬተሩ ፕሮጀክት ላይ የሚሰሩት አብዛኛዎቹ ክፉ አይደሉም፡፡ እንዲሁ ትልቅ ምኞት ያላቸውና መሰረታዊ የማሰብ ችሎታ የጎደላቸው ናቸው፡፡ እጅግ መሰረታዊ የሆነውን ህይወት መከተል ሲገባቸው ባለማስተዋል ዝናንና ክብርን የሚያስገኝላቸውን የምሑርነት ግባቸውን መርጠዋል፡፡ ብልህ የሆነ ድክ ድክ የሚል ህፃን ልጅ ሊቆጣጠሩት ከማይችሉት እሳት ጋር እየተጫወጡ እንደሆነ ሊያረጋግጥላቸው ይችላል፡፡"

"የዚህም መሰረታዊ ጉዳይ እነዚህ የገሃነም መንጋዎች ወንድና ሴቶችን በሁሉም አቅጣጫ በማነሳሳት ለመጨረሻው ጥፋት ይዳርጓቸዋል፡፡ በሰዎች ትከሻ ላይ በመቀመጥ ንፁህ የሚመስል ሐሳብ ነገር ግን ማዕበላዊ ጥፋት በምድር ላይ የሚያመጣ ፣ በስነ ምህዳሩ በኩል፣ በብዙዎች አይምሮ በኩል፣ አስተሳሰባቸውንና ስነ-ልቦናቸውን በመቆጣጠር ለማይረባ መጨረሻ ህይወት ይዳርጓቸዋል፡፡ እነዚህም መሰረታዊ ጥበብና የማሰብ ችሎታ የጎደላቸው ናቸው፡፡"

"እግዚአብሔርን ያለማወቅና ሞራል ማጣት፣ ለጤናማ ህይወት መሰረታዊ የሆነውን ህይወት ባለመማራቸው እግዚአብሔርን መፍራት እንዲሁም ነገሮች እንዴት ተጠብቀው መቆየት እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ እነሱ ባጠቃላይ ስለ እምነትና ስለ

ሃይማኖት፣ ስለ ሞራል አስፈላጊነት እንዲሁም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን የህይወት ዘይቤ ከውስጣቸው ፍፁም አሽቀንጥረው ጥለውታል፡፡ እውነትን፣ እውነትን ብቻ ቢከተሉ ኖሮ መሰረታዊ የሆነው የቱ እንደሆነ በመረዳት በቅዱስ ፍርሃት እኔ በስርዓት የፈጠርኳቸውን ነገሮች ባላተረማመሱት ነበር፡፡"

"የኔ ውድ እንዲገባሽ እፈልጋለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ክፉ ሥራው እየጨመረ ይሄዳል፡፡ አዎን ክፉ የሰው ልጆችን ለመንከስ፣ ለመበከልና ለማጥፋት እየተቃረበ ነው፡፡ ቀስ ብሎ ይጀምርና እየጨመረ በመሄድ በሚመጡት ጊዜያት ድልን ይቀዳጃል፡፡"

## ከንጥቀት ለሚቀሩት መልዕክት

## Message for the left behind

"አሁን ጊዜው የሞት ንፋስ የሚነፍስበት ጊዜ ነው፡፡ እናም እኔ በዚህ ሥራ ውስጥ ተሳታፊ ነኝ፡፡ ይህም ንፋስ ሰዎች ወደ ህሊናቸው ተመልሰው እንዲነቁና አገራቸው በእውነት አስፈላጊ መሆኑን እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ሲነቁ፣ በቁጥርና በትጥቅ ከበለጠ ጋር ሲጋጠሙ ድጋፉ የታል? ጦርነቱ መሰረተ ቢስና ጉዳቱም እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ቢሆንም በዚህ አገር ላይ ብርሃን ፍፁም የጠፋ ሲመስል እኔ የነገሮችን አዝማሚያ እቀይራለሁ፡፡

በትንሽ የተሰፋ ጭላንጭል ብቻ ንፋሱን በማርገብገብ ወደ እሳት እቀይረዋለሁ፡፡ በዚህም ብዙዎች የተወሰደውን ለማስመለስ ይነሳሉ፡፡ እነዚህም እንደ ጌዲዮን 300 ጦረኞች የሚጋጠሙት እግዚአብሔር ከሌላቸው ከብዙ ሠራዊት የአውሬ ኃይላት ጋር ነው፡፡ እነዚህም አንዳንዶቹ ሰውን የሚመስሉ ነገር ግን የሰው ባህርይ የሌላቸው ናቸው፡፡

ይህ ጦርነት ታሪካዊና እኔ ከዚች አገር ጋር አብሬ እንዳለሁ የሚያሳይ እንዲሁም 'በምናምነው በእግዚአብሔር' በሚለው ቃል ላይ እንደገና የምትመሰረት ትሆናች ፡፡ "

"እስከዚያው ድረስ ኪሳራው እጅግ የሚዘገንን ይሆናል፡፡ ይህም በራሃብ፣ በኒውክላር ፍንዳታ እንዲሁም ዘርን ለማጥፋት በሚደረግ ተግባር የአገሩን ህዝብ ቁጥር እጅግ ይቀንሳል፡፡ ይህም ሌላ ዘር መጥቶ አገሪቷን ለመውሰድ የተደረገ ጥረት ነው፡፡

እኔ ከእርሷ ጎን ስላልነበርኩ አሜሪካ እንደነበረች እንደዚህ አትቀጥልም፡፡ ልክ እስራኤልን እንደቀጣሁ ይህንንም ህዝብ እቀጣለሁ፡፡ ነገር ግን የአሜሪካ ቅጣት እንደ እስራኤል ስደት ሳይሆን ሞት ነው፡፡

እንዲህም ቢሆን ግን ቅሬታዎች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህም ቅሬታዎች ውስጥ ቆራጥ የሆኑ ሰዎች የእኔን መርሆ መሰረት በማድረግ አገሪቷን እንደገና ይመሰርቷታል፡፡  የቀድሞው መንግስት ከፋት ሁሉ ፈፅሞ መጥፋት አለበት፡፡ የዚህን ክፉ መንግስትና በሁለት በኩል የሚያስቡትን የእነዚህን ሰዎች ሥር መሰረት ጨለማው እንዲውጣቸው ስለማደርግ ይህ መንግስት የተገነባበት አንድ ጡብ እንኳን መቅረት የለበትም፡፡"

"ሰይጣን የአሜሪካን ጉዳይ ጨርሻለሁ ብሎ ደምድሞ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከአመድ ውስጥ ያለፍርሃት  ራሳቸውን ለእኔ አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ይነሳሉ፡፡ ከእነዚህም ከተረፉት ውስጥ እንግዲህ ምን ቀረን? ሲሉ እኔ ግን አሜሪካን እንደገና በህዝብ እሞላታለሁ፡፡"

ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገድል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል። የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው። (ራዕይ 13፡10)

"እንዲህም ቢሆን ግን ለእኔ ታማኝ የሆኑትን አልጥላቸውም፡፡ ስለዚህም በዚህ ምድር ላይ ሊመጣ ካለው መቅሰፍት ነፃ አወጣቸዋለሁ፡፡ በመንግስተ ሰማያትም ያመልኩኛል፡፡ ደግሞም ከእኔ ጋር ተመልሰው በመምጣት በአገራት ውስጥ ፅድቅን መልሰው ያሰፍናሉ፡፡ ለምህረት ጩኹ፡፡ በምህረቴ ቅሬታዎችንና የወደቀውን አገር አፅናናለሁ፡፡"

እኔ እንደሚመስለኝ ጌታ መሃሪ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ እናም ይህንን አገር አይጥልም፡፡ ነገር ግን መስተካከል ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ ይህ ደግሞ ለአሜሪካ ብቻ ሳይሆን ለአለም ሁሉ ነው፡፡ ስለዚህም ምህረት እንዲያደርግ እንፀልይ፡፡ ደግሞ ጌታ ለህዝቅኤል አሁን ይህንን ቃል ሰጠው፡-

"በጽድቅ የሚሄድ ቅን ነገርንም የሚናገር፥ በሽንገላ የሚገኝ ትርፍን የሚንቅ፥ መማለጃን ከመጨበጥ እጁን የሚያራግፍ፥ ደም ማፍሰስን ከመስማት ጆሮቹን የሚያደነቍር፥ ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚጨፍን ነው። እርሱ ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣል ጠንካራ አምባ መጠጊያው ይሆናል እንጀራም ይሰጠዋል፥ ውኃውም የታመነች ትሆናለች።"(ኢሳያስ 33፡15-16)

ይህ የሚያመለክተው ከቅሬታዎቹ ውስጥ እንዲህ ዓይነት የባህርይ ሞራል ያላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ሥፍራ አላቸው፡፡ እናም የእነርሱ መኖሪያ ማንም ሊወስደው የማይችል ድንጋይ ነው፡፡ በድንጋዩ ላይ ይጣበቃሉ፡፡ ይህንን መልዕክት የምትሰሙ ሰዎች ይህ በጣም የሚያበረታታ መልዕክት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ፃድቅ የሆኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ሥፍራ አላቸው፡፡

## ከንጥቀት ወደ ኋላ ለሚቀሩት የአቅርቦት መመሪያ - ኤፐሪል 22 ቀን 2015 ዓ.ም

## Provision and Instruction ForThoseLeft Behind, April 22, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ዛሬ ምሽት ለእናንተ መናገር የምፈልገው ስለ መንፈሳዊ እድገት ነው፡፡ እስካሁን ከእናንተ ጋር አብዛኛውን ጊዜዬን ሳደርግ የነበረው ስለ መንፈሳዊ እድገት ጉዳይ ነበር፡፡ ይህም በቁመት መጨመር፣ መሞላት፣ የተረጋጋ ህይወት፣ በጥሩ መሰረት ላይ መመመስረትና ለሁሉም ነገር ዝግጁ መሆንን ያጠቃልላል፡፡ ምክንያቱም የእናንተ ጭብጥ ህይወት ያለው በመንፈሳዊው አለም ከእኔ ጋር እንጂ በቅርብ ሊተረማመስ ካለው ከምድራዊ ህይወት ልክ አይደለም፡፡

"ሰዎች ምን ሊመጣ እንዳለ ካለማወቃቸው የተነሳ ህይወት በዚሁ መልኩ ለሁልጊዜው እንደሚቀጥል በመቁጠር ገና ብዙ እያቀዱ ናቸው፡፡ ለዛ ነው ስለሚመጣው ነገር አይናቸው የታወረው፡፡ ክሌር እኔ ከአንቺ የምፈልገው የምትችይውን ያህል ሰዎችን ከዚህ ከትርምስ ሁኔታ ሊያነሳቸው የሚችል ነገር ትተሽ እንድትሄጂ ነው፡፡ ለነፍሶች ላደርግ የምችለው ያንን ነው፡፡

"አያችሁ! ሰርን፣ ከሎኖችና ምሁራን መደበቂያ ሥፍራቸውን በድንጋዮች ውስጥ ለማድረግ እጅግ ከባድና አደገኛ ስህተት እየፈፀሙ ነው፡፡ በዚህም ድርጊታቸው ኃይለኛ የውኃ ነውጥና እሳተ ጎሞራ በእነርሱ ላይ ይከፈትባቸዋል፡፡ ይህም ትልቅ ጥፋትን ያስከትላል፡፡ በዛን ጊዜ ይህንን እንዲሰሩ ላቀናበሩት ጩኸታቸውን ያሰማሉ፡፡

(ክሌር) ይህ በፍፁም አይሆንም ያልከኝ መስሎኝ ነበር!!!

"ነገር ግን ሁሉም ዋጋ ቢስና በጥልቁ የሚዋጥ ይሆናል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ለእነሱ የሚገባና ትክክለኛ ነገር ይሆናል፡፡ እናም ለሁሉም ይህ ከምድር በታች የሚሰሩት ሰፈር ለእነርሱ አስተማማኝ እንዳልሆነ ምክር ሰጥቼያቸዋለሁ፡፡

"እንዲህም ሆኖ ግን በበረሃው ውስጥ አስተማማኝ ስፍራን አዘጋጅቻለሁ፡፡ የተፈጥሮ ዋሻ፣ ውኃ እንደልብ ያለበትና በቂ ምግብ የሚያገኙበት፡፡ ልክ መላዕክቶች ለእስራኤላውያን በበረሃ መና እንዳቀረቡላቸው ለመኖር የሚያበቃቸው በቂ ነገር ይለቀቅላቸዋል፡፡

(ክሌር) እዚህጋ ትንሽ እረፍት ልውሰድና፣ ይህ ለእኔ በጣም የሚደንቅ ነገር ነው!!! መላዕክቶች ነበሩ ማለት ነው በበረሃ ለህዝቡ መናውን ሲያከፋፍሉ የነበሩት፡፡ ይህ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው፡፡

"ብዙዎቹ የምግብ ማከማቻዎች ባዶ አይሆኑም፡፡ የህክምና አቅርቦትና ፈውስ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሁኔታ እስከ መጨረሻው በእኔ ይቀጥላል፡፡ ብዙዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ለፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የታመሙትን ክብካቤ በማድረግ፣ በፍርሃት ላይ የወደቁትንና  በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙትን ደግሞ በማበረታታትና በማፅናናት ይሰማራሉ፡፡ አንዳንዶች ህይወታቸው በምድር ሊያበቃ ሲል ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገቡ ይረዷቸዋል፡፡

"በዚህ ዘግናኝ ወቅት ግን እኔ አጅግ የሚደንቅ እቅድ አለኝ፡፡ በፀሎት ምክንያት ብዙ የጠላት ግድግዳዎች ይፈራርሳሉ፡፡ ቅዱሳንን ለመጠበቅ ከተፈጥሮ በላይና ቃል በቃል ሰማይና ምድርን አነቃንቃለሁ፡፡ አንዳንዶች መስዋዕት ይሆናሉ፣ አንዳንዶች በህይወት ይኖራሉ፡፡ ለሁሉም ግን የሚያስፈልገው ሁሉ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለጠላቶቻቸው ፈቃድ አሳልፌ አልሰጣቸውም፡፡ አዎን በጣም ትልቅ ስቃይ የሚይታበት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአንፃሩ ትልቅ ክብርና የእምነት አሸናፊነት የሚታይበት ነው፡፡ ከመንግስተ ሰማይ ብዙዎች ለማፅናናትና የሚያስፈልገውን ለማቅረብ ጉብኝት ለማድረግ ይላካሉ፡፡ መላእክቶቼ ወደኋላ ለቀሩትና ከኃይለኛው ቁጣዬ ለምሸፍናቸው ለደህንነታቸው ዋና ተጨናቂዎች ናቸው፡፡

"የማካፍላችሁን መመሪያ በትክክል ስሙኝ፡፡ ትልቁ መሳሪያችሁ ፀሎት ነው፡፡ እንዴት እንደምትፀልዩም አስተምራችኋለሁ፡፡ ምንም ሳትደክሙ ከውስጣችሁ ወደ ውጪ እንዲሁ ይፈሳል፡፡ ስለዚህም ፀጋዬ በእናንተ መካከል ጠንካራ ይሆናል፡፡ በፍርሃትና በአደጋ ጊዜ ፀሎት ከውስጣችሁ ይመነጭና በደቂቃዎች ውስጥ ሁለንተናችሁን ይወርሳል፡፡ እናም በአስተማማኝ ቦታ ውስጥ ትደበቃላችሁ፣ ሰላሜም ይበዛላችኋል፡፡

"ብዙዎች ይከዳዳሉ፡፡ ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስ መለየት ብቻ ነው ጥንቃቄ መውሰድና ከማይታመኑ ሰዎች ጋር ህብረት እንዳታደርጉ የሚያደርጋችሁ፡፡ በውጫዊ ሁኔታ ለምሳሌ በሚናገሩት፣ በሚመስሉት፣ በሚያደርጉት ድርጊትና በተለመደው በሰው ደረጃ ዓይነት ፍርድ የምትሰጡ ከሆነ ትሞኛላችሁ፡፡ በእኔ ላይ በመደገፍ ብቻ ነው ደካማ  ወይም እናንተን እንዲያገኙ የላኳቸውን ነፍሶች መለየት ያለባችሁ፡፡

ይህንን በድጋሜ እናገራለሁ፡፡ ይህ የምሰጠው መመሪያ ወደ ኋላ ለሚቀሩት እነጂ ለሚነጠቁት አይደለም፡፡ እነዚህን መመሪያዎች በወረቀት አትሞ በቀላሉ ሊገኝ በሚችል ሥፍራ መቀመጥ አለበት፡፡

"በብሉይ ኪዳን ዘመን ህዝቤን እስራኤልን ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ጥበቃ እንደጠበኩት እንደዚሁ ከንጥቀት ወደ ኋላ መቅረት ላለባቸው ጥበቃ አደርጋለሁ፡፡ ከእነሱ ውስጥ አንዱ መሪ ሆኖ ይሾማል፡፡ ለተሾመው ለእርሱ ወይም ለእርሷ ከተፈጥሮ በላይ

የሆነ እውቀትና ጥበብን አሰጣለሁ፡፡ ከመካከላችሁ የተሾመውን ወይም የተሾመችውን ለተልዕኳችሁ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ በደንብ ጠብቋቸው፡፡

በእናንተ መካከል ዳያቢሎስ መከፋፈልን፣ አለመግባባትን፣ ማጉረምረምንና ቅናትን እንዳያመጣ ተጠንቀቁ፡፡ ይህ መርዝ በመካከላችሁ እንዳይሰራ ጠብቁ፡፡ እናንተን ለመከፋፈልና ለመበታተን ይህንን ይጠቀማሉ፡፡ አንድ ላይ በመሆን ሁኔታውን ማለፍ ትችላላችሁ፡፡ ከተለያይችሁ ግን ደጀን የሚሆን ዲጋፊ ስለምታጡ ብዙ አደጋ ይገጥማችኋል፡፡ ስለዚህም ለያይተው እንዳያሸንፏችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ከጠላት በልጣችሁ ብልህ ሁኑ፡፡ በመልካምነትና በትህትና ከተመላለሳችሁ ችግር አይገጥማችሁም፡፡ በራስ ፍላጎት መንቀሳቀስ፣ ራስን መውደድ፣ ተጠራጣሪነትና መራራነት ገዳዮቻችሁ ናቸው፡፡

"በቡድን ውስጥ ብዙ ፈተናዎች ሊገጥማችሁ ይችላል፡፡ አዎ ብዙ ፈተናዎች፡፡ የሚያሙ ውሳኔዎችን መወሰን፣ የሞትና የህይወት ውሳኔዎች ማድረግ ሊኖርባችሁ ይችላል፡፡ የምትወስኑት ውሳኔ እጅግ ከባድ በሚሆን ጊዜ ሰላሜን አሰጣችኋለሁ፡፡ ውሳኔን ለመወሰን እንዲያስችላችሁ ዕጣ በማውጣት ልትጠቀሙ ትችላላችሁ፡፡

(ክሌር) እዚህጋ ጣልቃ ለመግባት፣ ዕጣ ለማውጣት ማንኛውንም ነገር መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ ለምሳሌ ልምጭ፣ በጫካ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ፍሬዎችን ድንጋዮችን . . . ወዘተ፡፡ ዕጣ ማውጣትን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲጠቀሙ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ዮናስ ከታዘዘበት በመሸሽ በመርከብ ሲኮበልልና መርከቢቷ ስትናወጥ ይህ በማን ምክንያት እንደሆነ የሆነባቸው በመርከቢቱ ውስጥ ያሉት ዕጣ በማውጣት ነው የተጠቀሙት፡፡ እንዲሁም ጌታን የከዳው ይሁዳን ለመተካት የጌታ ሐዋርያት የተጠቀሙት ዕጣ ነበር፡፡

"በበርሃ ጉዟቸው ከእስኤላውያን ጋር እንደነበርኩ ከእናንተም ጋር እሆናለሁ፡፡ የፍቅሬን ምልክት፣ የአደጋን ምልክት፣ የምትሄዱበት መንገድ ትክክል አለመሆኑን ምልክት፣ በትክክለኛ መንገድ እየሄዳችሁ እንዳላችሁ ምልክት አሰጣችኋለሁ፡፡ እናንተ ግን ሁልጊዜ የምሰጣችሁን ምልክት በቅርበት ተከታተሉ፣ በጥንቃቄና በማስተዋል ተንቀሳቀሱ፡፡

(ክሌር) ታውቃላችሁ ሁልጊዜ ስለ ምልክቶች ሳስብ የልብ ቅርስ ያለው ድንጋይ፣ የኢየሱስ ፊት በዛፎች ግንድ ላይ ይታየኛል፡፡ እኔ አላውቅም ነገሩ ልዩ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በደንብ ከተከታተለ ምልክቶቹን ልታዩ ትችላላችሁ፡፡

"ምናልባት ትክክለኛ ውሳኔ ማድረጋችሁን ከተጠራጠራችሁ፣ ቆም በሉና ፀልዩ፡፡ እየተጠራጠራችሁ ጉዞ ከመቀጠልና ወጥመድ ውስጥ ከመግባት እኔን ብትጠብቁ ይሻላል፡፡ ውሳኔን ተግባርያዊ ለማድረግም ሆነ ለመጠበቅ ጊዜ አለው፡፡ ፈተናው እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው በጥበቃ ወቅት ላይ ነው፡፡ ሁልጊዜ ፀልዩ፣ አምልኩ፡፡ ጠላቶችቻሁን በከበባችሁ ጊዜ ሁሉ እስከዚያ ድረስ በእያንዳንዱ ጉዟችሁ ስለተደረገላችሁ ጥበቃና አቅርቦት አመስግኑ፡፡ የኔን ሥም እንደ ጦር መሳሪያ ተጠቀሙበት፡፡ ምክንያቱም እየተዋጋችሁ ያላችሁት ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም፡፡ ነገር ግን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።(ኤፈሶን 6፡ 12)

"አሁን ሁላችሁም እንድታስታውሱ የምፈልገው፣ እምነት በማጣት ወጥመድ ውስጥ መውደቅ እንዴት ቀላል እንደሆነ ነው፡፡ ያለማመን፣ ጥርጣሬና ፍርሃት እናንተን ለማጥቃት ጠላት የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ቀድሞ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ለሚመጣ አደጋ ቀድሞ ጥንቃቄ ይወስዳል፡፡

"የኔ ውዶች የሰጠኋችሁን መመሪያዎች አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ ምክንያቱም መመሪያዎቹ የህይወትና የሞት ጉዳይ ስለሆኑ ነው፡፡ ሰው በእናንተ ሰውነት ላይ ለሚያደርገው ነገር አትፍሩ፡፡ ግድ ሊላችሁ የሚገባው የዘላለም ነፍሳችሁ ጉዳይ ነው፡፡ ለሰውነታችሁ፣ ለልጆቻችሁ፣ለሚስታችሁ ወይም ለማንኛውም ምክንያት ብላችሁ አታመቻምቹ፡፡ ከክፉ ነፃ ላወጣችሁ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ ከክፉ አድነን ብላችሁ ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ ይህ አጅግ ኃይል ያለው ፀሎት ነው፡፡

## ሊመጣ ያለውን የታላቁን የመከራ ዘመን እንዴት ማለፍ እንደሚቻል - ኖቬምበር 7 ቀን 2015 ዓ.ም

## Surviving the Coming Tribulation, November 7, 2015

በጌታ ልብ ውስጥ የምትኖሩ ውዶች ጌታ ይባርካችሁ!

ዛሬ ማታ ጌታ መልዕክቱን ለማተኮር የፈለገው ስለሚመጣው የመከራ ዘመን ነው፡፡

"በየትኛውም ታሪክ ውስጥ ሆኖ የማያውቅ ወደፊትም ሊሆን የማይችል ወቅት ሊመጣ ነው፡፡ አሁን ምን ላደርግ ነው ብሎ ሰው ሁሉ የመጨረሻ ሊያስብ የሚችለውን ሐሳብ የሚያስብበት ጊዜ ነው፡፡ ለእነሱ ምንም ነገር ስሜት የማይሰጥና ሁሉም ነገር መላ ቅጡ የጠፋ ነው የሚሆንባቸው፡፡ ነገር ግን እኔ በዛ ወቅት በምድር ለሚቀሩት አሁን እያዘጋጀኋቸው ነው፡፡"

"ኃብት ማከማቸት፣ በስልጣን ላይ መሆን ወይም በትልቅ የክብር ስፍራ መቀመጥ ምንም ዋጋ የለውም፡፡ ምክንያቱም በዛን ጊዜ ሁሉም ነገር ፍርስርሱ ስለሚወጣና የሚሆነው ነገር ሁሉ የሚታየው ለአዲሱ አለም አቀፍ ስርዓት ታዛዥ ከመሆናችሁ ጋር ነው፡፡ በአሁን ጊዜ ትልቅ ስልጣንን የሚፈልግ ማንኛውም ክርስቲያን ከንጥቀት በኋላ በንዴት ግድግዳውን ይመታል፡፡ በዚህም መደንገጥ አያስፈልግም የሚያስፈልገው ግንዛቤ መጨበጥ ብቻ ነው፡፡ በመከራው ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ገንዘብ የሚስፈልጋቸው ለማካበት ሳይሆን ለመኖር ነው፡፡ ይህንን ስናገር በአካል ለመኖር ብቻ ማለቴ አይደለም፡፡ መኖር መንፈሳዊ ህይወታቸውንም  ያጠቃልላል፡፡ ለዚህም የመንፈሴን እንቅስቃሴ መረዳትና ንቁ መሆንን ይመለከታል፡፡"

"በመከራው ውስጥ ለሚያልፉት ጥበቃ የሚያገኙት ከመንፈሴ ብቻ ነው፡፡ በየትኛውም አይምሮ የሚደረግ እቅድ ለቤተስብ ሰላምን አያመጣም፡፡ የኔ ችሎታና ጥበቃ ብቻ ነው በብቃት ሊያድናችሁ የሚችለው፡፡ ለዚህም ጥሩ ምስክር የሚሆነው ራቢ ራዲጅ የሚባለው የህይወት ምስክርነት ነው፡፡ በመከራው ዘመን ለማለፍ ወደኋላ የቀራችሁ የኔ ውዶች የትኛውም የጦር መሳሪያ ያድነናል ብላችሁ አታስቡ፡፡ በሙሉ ልባችሁ ወደ እኔ ተመልሳችሁ  ለጥበቃ እኔን ጠይቁኝ፡፡ እኔን ብቻ የምትደገፉ ከሆነ ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ ጥበቃ እጠብቃችኋለሁ፡፡ ሰይፍን የሚያነሱ ግን በሰይፍ ይጠፋሉ፡፡"

(ክሌር) እዚህጋ ጣልቃ ገብቼ "ሚሽን" የሚለውን ፊልም ያያችሁትን ሰዎች ላስታውሳችሁ ፈልግሁ፡፡ ፊልሙን ላላያችሁት ደግሞ ቆንጆ ፊልም እንደሆነ እነግራችኋለሁ፡፡ የመጨረሻው የፊልሙ ክፍል የሚያሳየው ቅጥረኛ ወታደሮቹ /the mercenaries/ የአገሪቱን ተወላጆች ሁሉ ለመግደል ወደ ጫካው ይመጣሉ፡፡ የአገሪቱ ተወላጆችም በሁለት ቡድን በመከፈል ሁለት ዓይነት የተለያየ አመለካከት ነበራቸው፡፡ አንዱ ቡድን ጀስዊት ተብለው በሚታወቁት አንድ ሰው የሚመራ ቡድን ሲሆን ይህ ቡድን የሚፈልገው መዋጋት ነው፡፡ ሌላኛው ቡድን ደግሞ የሚፈልገው መፀለይ ነው፡፡ ታዲያ ልነግራችሁ የፈለግሁት በመጨረሻው በውጊያ ብቻ ለማሸነፍ ከፈለጉት ቡድኖች ይልቅ የፀለዩት ጥሩ ውጤት እንዳገኙ ነው፡፡

"ይህች አገር/አሜሪካ/ ከጠላት እጅ ለመታደግ የሚዋጉ ወንዶችና ሴቶች ወታደሮችን አዘጋጅቻለሁ፡፡ እነዚህም ወደ ተግባር በመግባት ከሚመጣው ስርዓት ምድሪቱን ለመንጠቅ የነቃ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡ የሚመጣው ዘመን ከስተት ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ ያልታየ ሲሆን የኔም ጥበቃ በሰው ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ጠንካራው ጥበቃ ይሆናል፡፡"

"ይህም ቢሆን ግን መከተል ያለባችሁ የተወሰኑ ህጎች አሉ፡፡ ታማኝነት ከሁሉም የላቀና አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላው መቆጣጠር ያለባችሁ ለሌላው መጥፎ ምሳሌ ላለመሆን የራሳችሁን ኃጢያት ነው፡፡ ሰይጣን እጅግ ብልጥ ስለሆነ አንድን ነፍስ እንዴት አድርጎ ኃጢያት እንደሚያሰራው ያውቃል፡፡ ሌላው የኔን ጥበቃ ለማግኘት ከፍተኛ ነጥብ የሚያስጡት የበጎ አድራጎት ሥራ፣ ትህትናና ትዕግስት ናቸው፡፡"

"በኃጢያት በወደቃችሁ ጊዜ ምንም ጊዜ ሳታጠፉ ወዲያውኑ ወደ እኔ ቅርቡ፡፡ በእውነት ንስሐ በመግባት ያንን ኃጢያት ተቃወሙት፡፡ እኔም ወዲያውኑ እሸፍናችኋለሁ ጥበቃዬንም አጠናክራሉ፡፡ ያንንም ኃጢያት ደግማችሁ እንዳትሰሩት ፀጋዬን እሰጣችኋለሁ፡፡ በሌሎች ላይ እንዳትፈርዱ አስተምሬያችኋለሁ፡፡ የኔን ሽፋን ወዲያው የሚያሳጣችሁ ኃጢያቶች ኃሜት፣ አሉባልታ፣ ስም ማጥፋትና ወሬ ናቸው፡፡ ጠላት ይህንን በመካከላችሁ የሚፈጥረው ከፋፍሎ ለማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ለጥቃት ተጋላጭ እንድትሆኑ መንገድን ለመክፈት ነው፡፡ የበለጠ ቁልፍ ሥፍራ እየተሰጣችሁ በሄደ ቁጥር የልባችሁም ዝንባሌ የተስተካከለ እንዲሆን መጣር አለባችሁ፡፡"

"የታመሙ ወይም የደከሙ ሰዎችን አታንኳሱ፡፡ የእነሱ ፀሎት አስፈላጊና እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡"

(ክሌር) ይህ በእኛም ተልዕኮ ውስጥ እውነት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሸማግሌዎችና የደካሞች ፀሎት የሚደንቅ ውጤት ሲያመጣ ተመልክተናል፡፡

"ስሜቶቻችሁ የእናንተ የመጨረሻ ጠላቶቻችሁ ይሆናሉ፡፡ በቂ እንቅልፍ ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የምታሳልፉት የጭንቀት ጊዜ የማሰብ ችሎታችሁንና ጉልበታችሁን ያደክማል፡፡ ይህ የዕረፍት ጊዜ የመትረፍ ስልት ይሆንላችኋል፡፡ በተለይም መንፈሳዊ የመትረፍ ስልት፡፡ ፀሎትና የበጎ አድራጎት ተግባር የመትረፍ አጋጣሚያችሁን ይጨምራል፡፡ ፀሎት ግን ከሁሉም ኃይል ያለው አንደኛ መሳሪያችሁ ይሆናል፡፡"

"ጠላት እጅግ ተንኮለኛ ስለሆነ በስሜታችሁ ላይ የተለያዩ ጫናዎችን በመፍጠር አንዱ በአንዱ ላይ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡ ይህ ወንድሙን በወንድሙ ላይ የሚያስነሳውን የጠላትን ሙከራ ማከሸፍ የሚቻለው ቁጭ ብሎ ሁሉን ነገር በግልፅና በእውነት በመነጋገር ነው፡፡"

(ክሌር) እዚህ ላይ ንስሐ ስለ መግባት አስፈላጊነት መጨመር እፈልጋለሁ፡፡ አንድ ጊዜ የማን አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑን ካወቃችሁ፣ ትክክለኛ ምርጫ ያላደረገው፣ ወይም ትክክል ባልሆነ መንገድ የከሰሰው ሰው ንስሐ መግባትና ሌላኛውን ሰው ይቅርታ መጠየቅ አለበት፡፡

"እጅግ በጣም አስፈላጊው ነገር ደግሞ ትዕግስትና ንዴትን ማሳለፍ ነው፡፡ ውድቀት ከበስተኋላው ሁልጊዜ ምክንያት አለው፡፡ እናም ይህንን ለመወጣት በጎ በማድረግና በወንድማማች ፍቅር መኖር ለእናንተ የሚቀርብ የሁልጊዜ ፈተና ነው፡፡"

"አስታውሱ አንዱ ሌላውን በፈረደበት ፍርድ ይፈረድበታል፡፡ ስለዚህ ይቅርታ እንዲደረግላችሁ ከፈለጋችሁ እናንተ መጀመሪያ ይቅርታ ማድረግ አለባችሁ፡፡ ራሳችሁን ከሌላው አስበልጣችሁ ታዩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ ይህንን ገና ስታስቡ የእናንተ የመውደቂያ ጊዜ ነው፡፡"

"የኔ ውዶች እርስ በርሳችሁ በከፍተኛ ደረጃ ለመከባበር እራሳችሁን ማስለመድ አለባችሁ፡፡ ምናልባት ሌላው በእናንተ ፊት የተናቀ መስሎ ሊታያችሁ ይችላል፡፡ እኔ ግን የማየው ልብን ነው፡፡ ስለዚህም በኔ ዕይታ ብዙ ፍቅር ያለው የበላይ ነው፡፡ እናንተ በብዙ ነገር ልትበልጡ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን በበጎ ተግባር ላይ ካልተሰማራችሁ ለማያስፈልግ ኩራትና ራስን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይዳርጋችኋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በውስጣቸው ቅን ለመሆን ፈቃደኛ ከመሆናቸው የተነሳ በጣም ጎበዝ፣ ብልህና ስኬታማ ቢሆኑም ከእነርሱ በትልቅ ልዩነት ዝቅ ላሉት እነርሱ ዝቅ ይላሉ፡፡"

"አሁን የእናንተ ጉዳይ የአለም ጉዳይ ሳይሆን መንፈሳዊና መለኪያውም ሰማያዊ ሚዛን ነው፡፡ ስለዚህም በአለም ሲለካ ትክክክል የመሰለ ነገር በሰማያዊ ልኬት ግን ተቀባይነት የሌለው ይሆናል፡፡ ሪክ ጆይነር በመፅሐፉ በጎ ተግባርና መንፈሳዊ ዕይታ ግንባር ቀደም እንደሆነ ገልፆታል፡፡ ይህንን አስታውሱ ማናችሁም ብትሆኑ ፍፁም የሆነ መፅሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ መረዳት የላችሁም፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ለህብረቱ የሚጨምረው ስጦታ ይኖረዋል፡፡ ለዚህም የእናንተ ኃላፊነት የተሰጣችሁን ማወቅና ኮትኮቶ በማሳደግ ለህብረቱ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህም እውነተኛው የቡድን ተግባራዊ ሙከራና እያንዳንዱ በልዩነቱ በማፍራት ለሌላው ማስተላለፍን ያመለክታል፡፡ በዚህም ስኬታችሁ ወይም ውድቀታችሁ የሚለካው ለደካማው ባደረጋችሁት ጥንቃቄ መጠን ነው፡፡"

"ስጋት ወይም ፍርሃት ባደረባችሁ በየትኛውም ጊዜ መሆን ያለበት የመጀመሪያው እርምጃ መፀለይ ነው፡፡ የመጀመሪያ ምላሻችሁ መሆን ያለበት ፀሎት ነው፡፡ በማንኛውም የጦርነት ወቅት እንደሚደረገው ሁሉ በጣም አስፈላጊና ዋና ከሆነው ነገር የሰውን ትኩረት ለመስረቅ ብዙ ሐሰተኛ የወሬ ዘመቻዎች እንደሚኖሩ ነው፡፡ መረጃ ለማግኘት በእኔ ላይ ብቻ የምትተማመኑ ከሆነ ከእንደዚህ ዓይነቱ ወጥመድ ታመልጣላችሁ፡፡"

"በተጨማሪም አማኞችን ጠራርጎ ለማውጣት የሚደረግ ሙከራ አለ፡፡ ስለዚህም ከእናንተ ጋር ህብረት እናደርጋለን የሚሉትን ሁሉ አትመኑ፡፡ ተልዕኳቸው ምን እንደምታደርጉ አጀንዳችሁን ለማወቅና ሪፖርት ለማድረግ ነው፡፡"

"በእናንተ ውስጥ እያንዳንዱ ልዩ የሆነ ዓላማ አለው፡፡ ስለዚህም በእያንዳንዱ ውስጥ ያለውን ልዩ ነገር በማወቅ አዳብሩት ደግሞም አክብሩት፡፡ ከመካከላችሁ አንድ ሰው ለማገልገል ቢፈልግ በምንም ዓይነት ሁኔታ አትከልክሉት፡፡ ለእንደዚህ ላሉት የሚሰሩት ሥራ ስጧቸው እንጂ ሥራ ፈት አታድርጓቸው፡፡ ይህ በኋላ በእናንተ ላይ መጥፎ ምላሽ ያስከትላል፡፡ ሰላምን በቡድኑ ውስጥ ለመጠበቅ የቡድኑ አባል እያንዳንዱ ተፈላጊ፣ ዋጋ ያለውና ጠቃሚ መሆኑን እንዲሰማው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም በቅንጅት ሲሰራ ሁሉም እርካታ ያገኛል፡፡ በቡድኑ ውስጥ የመከፋፈል አዝማሚያ ሲታይ የሚከፋፍል መንፈስን በመቃወም ፀልዩ፡፡ ይህ ሁልጊዜ ጠላት የሚጠቀምበት መንገድ ነው፡፡"

"በዚህ ጉዳይ ላይ የምናገረው ነገር አለ፡፡ ቡድኑን ለመከፋፈል አብሮ የሚሰራ መንፈስ የውሸት መንፈስ፣ አታላይ መንፈስ፣ ያለመግባባትን የሚፈጥር መንፈስ፣ እንዲሁም ንግግርን የሚያጣምም መንፈስ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ በቡድን ውስጥ መከፋፈልን የሚያመጡ መናፍስቶች ናቸው፡፡"

"ይህ ጠላት ያለማቋረጥ የሚፈፅመው ተግባር ነው፡፡ ይህም ከፋፍሎ ማሸነፍ ወይም አንዱን ከውስጣቸው ለውድቀት ማስነሳትና ማሸነፍ በሚለው መርህ መሰረት ነው፡፡ ከእናንተ ውስጥ አንዱ በወደቀ ጊዜ አግዙት፡፡ የወደቀውን ሰው ሞቅ ባለ ሁኔታ፣ ዋስትና በተላበሰ መልክና በሙሉ ይቅርታ አንሱት፡፡ በመናደድ ምላሽ መስጠት መናፍስቶችን ኃይል በመስጠት አለመስማማትንና እርካታ ማጣትን ያመጣል፡፡ ይህ ደግሞ በአንዳንዶች ልብ ውስጥ መከንከንን በመፍጠር ቆይቶ ከባድ አመፅንና መከፋፈልን የሚያመጣ ይሆናል፡፡"

"ምንም ነገር ቢሆን ጥሩ ነው ወይም ጥሩ ኢጋጣሚ ተፈጥሮልናል አትበሉ፡፡ የምታደርጉት እያንዳንዱን ነገር መጀመሪያ ፀልዩና ከእኔ መልሱን አግኙ፡፡ የትሮጃኑን ፈረስ ታሪክ ሁልጊዜ አስታውሱ፡፡ በዛን ጊዜ ሁሉም ከጠላቶቻቸው በጣም የሚገርም ምርኮ ያገኙ ነበር የመሰላቸው፡፡ ነገር ግን ፈረሱን ሲስቡትና በውስጡ የመሸገው የጦር ኃይል ወጥቶ ከተማውን ሲቆጣጠር ነበር እውነቱ የተገለጠው፡፡"

"ነገሩን ሲጠቃለል በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ስኬት ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን እንዲገባችሁ የምፈልገው ስኬትን የምለካው በህይወት መኖራችሁ ወይም በውጊያ ችሎታችሁ አይደለም፡፡ የከፍታ መለኪያዬ ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህም ለእኔ መሞት ማትረፍ ነው፡፡"

"ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ። ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።"(ማቴዎስ 10፡28-29)

## የመጨረሻው መጨረሻ ከፋች ክስተት - ዲሴምበር 6 ቀን 2015 ዓ.ም

## The Turn-key event - Decembere 6, 2015

ኢየሱስ እንዲህ ይላል . . . በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሞስሊሞች መስኪድ ሲፈርስ በጉልበታችሁ ተበርከኩ፡፡ ያ የመጨረሻው መጀመሪያ ክስተት ነው፡፡"

"የኔ ውድ ወደ ሩጫው መጨረሻ እየደረስሽ ነው፡፡ ቀጥ ብለሽ ፊት ለፊትሽን ብቻ በትኩረት ተመልከቺ፡፡ ጊዜው እያለቀና መሆን ያለባቸው ለመሆን እየፈጠኑ ነው፡፡ ስለዚህም ጠላት ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት እየቀረበ ነው፡፡ ታስታውሻለሽ ባለፈው ስለ ነገርኩሽ ከፋች ክስተት? በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሞስሊሞች መስኪድ መውደም?"

"አዎን ጌታ አስታውሳለሁ፡፡"

"ያንን ባየሽ ጊዜ፣ በጉልበትሽ ተንበርከኪ፡፡ ያን ጊዜ የፈተናው ጅማሬና እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች አይተውት የማያውቁትና በህልማቸው እንኳን ይሆናል ብለው ያልገመቱት ይሆናል፡፡ መስኪዱ እንዲፈርስ እቅዱን ያወጡት እንኳን ያስከተለውን ውጤት ሲመለከቱ በድንጋጤ ይዋጣሉ፡፡ ከሌር አትፍሪ በቅድሚያ ነገሬሻለሁና አትፍሪ፡፡ ተበርከኪና መዳንሽ እንደቀረበ አውቀሽ አመስግኚ፡፡

"ክስተቱ ከተፈፀመ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ችግሩ ሳይጎላ ቢቆይም ወዲያው እጅግ እየከፋ ይመጣል፡፡ አገሮች ሁሉ ሲፈራርሱ በዓይኖቻችሁ ፊት ትመለከታላችሁ፡፡ እናም አይኖች ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ያርፋሉ፡፡ ለመዘጋጀት ምንም ጊዜ የለም፡፡ ምንም ጊዜ፡፡ ስለዚህም በፀሎት ብቻ ቆዩ፡፡ ወደ ውጪ አትውጡ፤ ቤታችሁን አትልቀቁ፡፡ በጉልበታችሁ ወድቃችሁ ፀልዩ፡፡ መለኮታዊ የምህረት ፀሎት/The divine Mercy prayer/ መፀለይ ያለበት በመንፈሴ በተደገፈ ፀሎት ነው።

"የመጨረሻው የምህረት ጠብታ ከተሰጠው የተስፋ ዋንጫ ውስጥ ይለቀቃል፡፡ አዎን የመጨረሻው ጠብታ፡፡ ያን ጊዜ ወደ እኔ የሚመለሱ እንደሚድኑ ሁሉ አንዳንዶች ደግሞ በእሳቱ ውስጥ ያልፋሉ፡፡

"ነገር ግን እናንተ ብርቅዬ ሙሽራዎቼ፣ እናንተና ቤተሰባችሁ ይህም  እውነተኛ ቤተሰባችሁ በእናንተ ጥላ ሥር ይሆናሉ፡፡ ሁላችሁም ጥንቃቄ ይደረግላችኋል፡፡ መፍራት ምንም አይጠቅምም፡፡ የሚጠቅመው መፀለይና መታመን ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፣ ኢየሱስ አምንሃለሁ በማለት አሁንም አሁንም እየደጋገማችሁ ፀልዩ፡፡ "ለመሃፀን ፍሬዎቻችሁ እኔ ጥንቃቄ አደርጋለሁ፡፡ ኃጢያታቸውን እያመኑና ንስሐ እየገቡ አንድ በአንድ ወደ እኔ ይመለሳሉ፡፡ ክሌር በዚህ ምድር እስካለሽ ድረስ የምትችይውን አድርጊ፡፡ በኢየሩሳሌም ያለው መስኪድ በወደመ ጊዜ በጉለበቶችሽ ተንበርክኪ፡፡

"ክሌር ለእኔ ያዘጋጀሻቸው ስጦታዎች አሉ?"

ጌታ አዝናለሁ፡፡ እኔ በጣም ገብጋባ ሆኛለሁ፡፡

"ደህና ለእኔ ስትዪ አድርጊው፡፡ የምግብና የተፈጥሮ ፍላጎትሽን የበለጠ በመቆጣጠር የምትገልጫቸውን እነዚህን ትንንሽ የፍቅር ምልክቶችን ማየት እፈልጋለሁ። እባክሽ ክሌር ትንሽ ትሞክሬያለሽ? እኔ ፀጋውን እሰጥሻለሁ፡፡"
እሺ ጌታ እሞክራለሁ፡፡ ለመሞከር የምችልብትን ፀጋ አገኛለሁ?

"አዎ ይሰጥሻል፡፡ አገልግሎትሽን ከሁሉ በፊት አስቀድሚ ፡፡ ሌላውን ሁሉ ወደጎን አድርጊው፡፡

"ለእናንተም ለሙሽሮቼ የምለው ይህንኑ ነው፡፡ ስለ እኔ የምትሰጡት ምስክርነት ለእኔ እንደ ትንንሽ የሠርግ ስጦታ አድርጋችሁ አቅርቡልኝ፡፡ ስለ እምነታችሁ ንቀትንና ውርደትን ችላችሁ የኖራችሁ አሁን በቅርብ ጊዜ፣ በጣም በቅርብ ጊዜ ደስታን ትጎናፀፋላችሁ፡፡ ህይወታቸውን ሙሉ መርከቡን ሲሰሩ ንቀት እንደደረሰባቸው እንደ ኖህና ቤተሰቡ እናንተም ይህ ቢደርስባችሁ አሁን ግን ነፃ የምትወጡበት ጊዜ ደርሷል፡፡ በጥፋት ውኃ ዘመን የመርከቡን በር ዘግቼ  የታላቁ ምንጮች ተነድለው ውኃው ምድሪቱን ሲያጥለቀልቅ በግድግዳው እያለፈ ይሰማ የነበረው የፌዝ ሳቅ ትንሽም ሳይቆይ በጩኸት ተተከቶ ነበር፡፡

"በዚያን ጊዜ ታዲያ ኖህና ቤተሰቡ በጣም በጥልቅ ሐዘን ላይ ነበሩ፡፡ ነገር ግን እነርሱ የድርሻቸውን እንደተወጡና የጠፉትን ለማዳን ሰው ሊያደርግ የሚችለውን ጥረት ሁሉ እንዳደረጉ ስነግራቸው ከመረዳት በላይ የሆነ ሰላምን አገኙ፡፡ በእውነቱ ከሆነ እኔ ውጪ የቀሩት ሰዎች ወደ መርከቢቱ እንዲገቡ ፈቃዴ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የእነሱ ህይወት በኃጢያትና በኔፍሊሞች እጅግ ተመርዞ ስለነበረ ነው፡፡

"ታዲያ ያን ጊዜ ብዙ ምህረት ተደርጎ ነበር፡፡ የኔ ተፈጥሮ ከሰው ሊወዳደርና የሰው ልጅ ሊረዳውና ሊገባው ከሚችለው በላይ ስሜቴ አግባብነት ባለው መልኩ ቶሎ የሚነካ ነው፡፡ የእናንተ የባህል ችግር ደግሞ አስተሳሰባችሁን የተዛባ ማድረጉ ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህም ቢሆን በኖህ ዘመን ከነበሩት ከኔፍሊም ወንዶችና ሴቶች ጋር ሲወዳደር ገና የእነሱን ያህል ድርጊታችሁ አስከፊ አልሆነም፡፡ ነገር ግን እንደዚያ ሊሆን እያኮበኮበ ነው፡፡

"እግዚአብሔርን መፍራት የለም፡፡ ይህንን ስል በእውነት እግዚአብሔርን መፍራት የለም ማለቴ ነው፡፡ ነገር ግን ወደፊት ይህ መሆኑ አይቀርም፡፡ እኔ ግን እያወራሁ ያለሁት ሰዎች ከፍራቻና መጥፎ ነገር ይደርስብናል ብለው ከመስጋት የሚመጣውን እግዚአብሔርን መፍራት አይደለም፡፡ እኔ እያወራሁ ያለሁት በፍፁም ጥልቅ በሆነ ፍቅር ላይ የተመሰረተውን እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ እግዚአብሔርን መፍራት ይገባል፡፡ ይህም እኔ እንደ ሰው ኃጢያትን እንደማላፀድቅ ወይም ከኃጢያት ጋር እንደማልተባበር ፣ እንዲሁም እኔ ስለ ፅድቅ ያለኝ ሐሳብና የሰው ልጅ ስለ ፅድቅ ያለው ሐሳብ የተለየ መሆኑን በመረዳት በእውቀት ላይ የተመሰረተ እግዚአብሔርን መፍራት ይገባል ማለቴ ነው፡፡

"ያ ወጣት ትልቅ ፀጋ የተሰጠው፣ ህዝቤ የኔን መምጣት ተገንዝቦና ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ለማድረግ ነው፡፡ ከሌር ወጣቱ ምን እንደተማረ ስታጠኚ ስለ ፅድቅ ምንነት እየገባሽ ይመጣል፡፡ እናም የሰው ልጅ እንዴት እንደተበላሸ ይገባሻል፡፡ ይህም እናንተ ስለ ኃጢያታችሁ ዕዳ መክፈል እንደማትችሉ፣ ስለዚህም እኔ ለእናንተ ኃጢያት በመስቀል ላይ መሞት እንደነበረብኝና እናንተ እዳችሁን መክፈል በፍፁም እንደማትችሉ ነው፡፡ በፍፁም መክፈል አትችሉም ነበር፡፡

"የኔ ውድ አሁን ግን ከእኔ ጋር ልትሆኚ እንደምትፈልጊ ልብሽን አይቻለሁ፡፡ ለዚህም ለዘላለም ከእኔ አጠገብ እንድትሆኚ እንደገና መልሼ እራሴን ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡

"የኔ ሙሽሮች ይህ እናንተንም የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ነው አንድ ኃጢያት ስትሰሩ፣ በጣም ትንሿን ኃጢያት እንኳን ስትሰሩ በአባቴ ፊት እያለቀስኩ የምማልደው፡፡ ደግሞ ከሁሉም በጣም የሚጎዳው እያወቃችሁ ሳትታዘዙ ስትቀሩ ነው፡፡ እመኑኝ ሙሽሮቼ እኔ የምጠይቃችሁ ለእናንተ እጅግ መልካም የሆነውን ብቻ ነው፡፡ ታምኑኛላችሁ?

"አሁን ወደ እኔ ቅረቡ ምክንያቱም የምንሰራው ሥራ አለ፡፡ ነፍሳት ነፃ እንዳወጣቸው ወደ እኔ እየጮሁ ነው፡፡ የእውነትና የፍቅር አምባሳደሮቼ በመሆን ለጩኸታቸው መልስ ስጡልኝ፡፡ ይህንን ለማድረግ ጥረት ስታደርጉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ስታገኙ እርዱ እንጂ ምን ላድርግ ብላችሁ አትጨነቁ፡፡ በዚህም ኃሳብ ላይ ልባችሁን አሳርፉ፡፡ እኔ ማድረግ ያለባችሁን እንድታደርጉ ልባችሁን አፈጥናለሁ፡፡ እኔ እመጣለሁ!!! ቶሎ እመጣለሁ፡፡ ደግሞ የኔን መምጣት እያሰባችሁ ልባችሁን በዚህ ተስፋ ላይ አሳርፉ፡፡"

**በቅርብ ሊሆኑ ያሉ የክስተቶች ቅደም ተከተል - ኤፕሪል 8 ቀን 2016 ዓ.ም**

**Order of Events / April 8, 2016**

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . .ኸርት ዱዌለርስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርታትና ጥበብ ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡

ዛሬ ማታ አንድ መልዕክት ትኩረቴን ስቦት ነበር፡፡ ይህም ስለ አስተሮይድ የተነገረ አንድ ትንቢት ሰምቼ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ስለዚህ ጉዳይ ዘርዘር ባለ መልኩ የተናገረኝ ነገር አልነበረም፡፡ እንዲሁም በቅርብ ሊፈፀሙ ያሉ ነገሮችን መቼ እንደሚሆኑ ጊዜውን አልነገረኝም ነበር፡፡ ስለዚህም ባልተገባ መልኩ ትንሽ ግራ ተጋብቼ ነበር፡፡

እናም ወደ ጌታ ቀርቤ እንዲህ አልኩት፡፡ ጌታ ሆይ ስለዚህ ጉዳይ እንዴት እንደማደርግ አላውቅም፣ ግራ ገብቶኛል፡፡ይህ መልዕክት እኛ ለማወቅ በመጓጓት ፈልገነው የሰማነው ጉዳይ ሳይሆን መልዕክቱ እኛ እንድንሰማው የተደርገ ነው፡፡ ደግሞም አንተ ልታስተላልፍ የፈለከውን መልዕክት ሁሉንም በአንድ ሰው በኩል ሳይሆን በተለያዩ ነቢያቶችህ በኩል እንደምታስተላልፍ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም ምን ማሰብ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡

ጌታም ለዚህ ነገር ቶሎ ነው መልስ የሰጠኝ፡፡ እንዲህ በማለት "ይህንን ነገር ላብራራልሽ ትፈልጊያለሽ? ይህ ለማውራት የማልፈልገው ርዕስ ቢሆንም ህዝቤ ግን ግራ ተጋብቶት ማየት አልፈልግም፡፡"

"እርግጥ ነው ኮሜት ፖርት ሪኮን ይመታል፡፡ በዚህም አደጋ ሚሊዮኖች ይገደላሉ፡፡ ለዚህም ልቤ በጥልቅ ኃዘን ውስጥ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ከንጥቀት በፊት ነው፡፡"

(ክሌር) ከንጥቀት በፊት?

(ኢየሱስ) "አዎን ያንን ህልም ለምን የላኩብሽ ይመስልሻል?"

(ክሌር)- ጌታ የሚናገረው ከዓመት በፊት አንድ ሰው ያየውን ህልም ነው፡፡ ይህንን ህልምና ሌሎችንም ጌታ የገለጠልኝን መልዕክቶች ለማገናዘብና ለማቀናበር ተስኖኝ ስለነበር ነው ጌታ ቅደም ተከተሉን እስኪነግረኝ እየጠበኩ ያለሁት፡፡

የህልሙ ይዘት ይህንን ይመስላል፡፡ እኔ ከቤተሰቤ ጋር በሰሜን ካሊፎርኒያ እቤታችን ውስጥ ነበርን፡፡ በጊዜውም በጣም ጭንቀት ላይ ነበርን፡፡ በጣም ብዙ የሚያስፈሩና ብዙ የአደጋ ጊዜዎችን አገራችን (አሜሪካ) አሳልፋለች፡፡ እናም እነዚህን ጊዚያቶችን ተቋቁመን አሳልፈናል፡፡ ነገር ግን አሁን እየተከሰተ ያለው ነገር አንድ ነገር ከምስራቅ አቅጣጫ ወደ እኛ እየመጣ

ያለ ሲሆን ይህም ከአቅማችን በላይ በመሆኑ በህይወት ለመኖር የማንችልበት ደረጃ ላይ ስለደርሰን በህይወት ለመኖር የቀረን ጊዜ በጣም ጥቂት ሴኮንዶች ብቻ ነበሩ፡፡

ባለቤቴንና ሁለት ታዳጊ ህፃናቶቼን አየኋቸውና ኢየሱስ ወደ እርሱ ለመሄድ ዝግጁ እንዲያደርገን እንፀልይ አልኳቸው፡፡ ሁላችንም አንገቶቻችንን ዝቅ አደረግንና እኔ መፀለይ ጀመርኩ፣ "ኢየሱስ እባክህ ከአንተን ጋር እንድንገናኝ ዝግጁ አድርገን"፡፡ በዚህም ጊዜ ትልቅ የፍንዳታ ኃይል በእኛ ውስጥ ተፈጠረ፡፡ በዚያው ቅፅበት ሁላችንም ማብራት ጀመርን፡፡ በዚያ ወቅት በሰውነታችን ላይ ምን የተለየ ሁኔታ እንዳለ እንኳን ለማየት አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ሁላችንም እንደ ብርሃን የሚያበራ ነጭ ኮከብ መስለን ነበር!!!

እስቲ ፀሐይን ለመመልከት ሞክሩ፡፡ ልክ እንደዛ አብርተን ነበር፡፡ አዎ አውቃለሁ ያ የሆነው በውስጣችን ካለው ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ነው፡፡ ፍፁም የቀየረን ከሙታን የተነሳው የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በኛ ውስጥ ስለፈነዳ ነው፡፡

ይህም ፍንዳታ ትልቅ የመብረቅ ድምፅን በመፍጠር በመካከላችንም ሰማያዊ ብልጭታን ሲፈጥር ተመለከትኩ፡፡ በዚህ ቅፅበትም ሁላችንም በብርሃን ፍጥነት ወደ ሰማይ እንደ ሮኬት ተተኮስን፡፡

እኛ ብርሃን ነበርን በብርሃንም ፍጥነት እየተጓዝን ነበር፡፡ በዚህ ሂደት አይኔን ለመክፈት ባልችልም፣ አይኔን ብከፍት ግን እራሴን በገነት እንደማገኘው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ በቅፅበታዊ ሁኔታ ኢየሱስ ተመስገን በማለት ጮሁኩ፡፡ እርሱን ማመስገን ማቆም አልቻልኩም፡፡ ከእንቅልፌ ስነቃ በጣም በትልቅ ደስታ፣ በሰላምና በትልቅ የመደነቅ ስሜት ነበር፡፡

(ክሌር) እና ይህንን ህልም ያሳየኸኝ እንዲገባኝ ነበር?

(ኢየሱስ) "በትክክል ነገሩ እንዲገባሽ ለማድረግ ነበር፡፡ አየሽ ፖርቶ ሪኮ ላይ የሚወረወረው ኮሜት ምድርን ከዛቢያዋ ይወርውራታል፡፡ እንደ ሰከረ ሰውም ያደርጋታል፡፡ ሞኞች ሆይ ልጆቻችሁ ከዚህ ክስተት የሚያመልጡ ይመስላችኋል? ይህ ኮሜት ምድርን ከመታት በኋላ ምድር በጣም ለመኖርያ እጅግ የተለየች ትሆናለች፡፡ ነገር ግን እናንተ ይህንን ለማየት እዚህ አትገኙም/የሚነጠቁት/፡፡ ህልሙን እንደነገረቻችሁ ሴት ተለወጣችሁ ከምድር ትወሰዳላችሁ፡፡ ከዚህ ግዙፍና አስቀያሚ ክስተት በፊት ህዝቅኤል በህልሙ እንዳየው እናንተም ድንገት አወጣችኋለሁ፡፡"

(ክሌር) ህዝቅኤል በፈረንጆች አቆጣጠር ዲሴምበር 6 ቀን 2015 ዓ.ም ያየው ህልም ይህ ነው፡፡ በመኪና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እየሄድን ነበር፡፡ በቅፅበት በጣም ከባድ ንፋስ ከበስተጀርባችን ከምስራቅ አቅጣጫ የሚመጣ ንፋስ ይነፍስ ጀመረ፡፡ እኔም ምን እንደሆነ ለማየት ወደ ኋላ ዞሬ ብዬ ስመለከት በሰማይ ላይ ጥቁር ዳመና እየተከባለለና እየተሽከረከረ አየሁ፡፡

በመጀመሪያ ግራጫና ዳመናማ ሲሆን በኋላ ግን ጥቁርና ጨለማ እንዲሁም የሚያጉረመርም ማዕበል በመሆን እያደገ አየሩን ሁሉ ተቆጣጠረው፡፡ ድምፁ እጅግ ከፍ ያለና የሚያስጠላ እንዲሁም በራሱ ህይወት ያለው ይመስል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡ ጨለማው በመንገዱ ላይ የሚገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ይሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን ከእኛ በላይና ከፊታችን የሚገኘው ሰማይ ንፁህና ፀሐያማ ቀን ይመስል ነበር፡፡

ዳመናው መናጥና መሽከርከር በመቀጠል እንግዳ የሆነ ቅርፅን ፈጠረ፡፡ቅርፁም በደንብ ሲለይ የመቅዘፊያ ቅርስ ሆኖ ወጣ፡፡ በደመናው የሚታየው ምስል እኛን ለመውሰድ እንደሚጣደፍ በጣም በትልቅ ፍጥነት እየተጓዘ ነበር፡፡ ይህ በፍጥነት የሚጓዘው ነገር በደረሰባቸው ጊዜ በጨለማ ውስጥ ስለሚከታቸው ከበስተኋላችን ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ እኛም ከሌሎች ብዙ ሌሎች መኪናዎች ጋር ከዚህ ነገር ለማምለጥ ፍጥነታችንን እጅግ በመጨመር ለማምለጥ እየሞከርን ነበር፡፡ በቅፅበት ከሰሜን ምስራቅ ነጭ ፈረስ በአየሩ ላይ እየጋለበ ታየን፡፡ እኔም ግልፅ በሆነ ሁኔታ ስመለከት ከኋላው ሰረገላና ሌሎች በዛ ያሉ ፈረሶችና ፈረሰኞች አየሁ፡፡ እየቀረበ ሲሄድ ኢየሱስ ነጭ ልብስ ለብሶና በራሱ ላይ ዘውድ ጭኖ በሰረገላው ላይ ተቀምጦ በግልፅ ይታያል፡፡ ኢየሱስ ዳመናውንና መቅዘፍያውን በመቅደም ከኋላችን ሆነ፡፡ እርሱም እጁን እያውለበለበልን ልክ በነችን እንደሚጠብቅ በቡድን በቡድን በማድረግ ወደፊት ወሰደን፡፡ ከኋላችን ከጌታ ሠራዊት ጀርባ ጨለማው እየወሰዳቸው ስለሆነ አሁንም የሚሰቀጥጥ ጩኸትና ድምፅ ይሰማ ነበር፡፡

ጌታና የእርሱ ሠራዊት ከዚህ አስደንጋጭና አውዳሚ ሁኔታ በመካከላችን በመግባት ከለላ ወይም ሽፋን ሆኑን፡፡ በጣም በፍጥነትም እየተጓዝን ከአስደንጋጩ ነገር እየራቅን ሄድን፡፡ እኔ በዛ ጊዜ የሚመስለኝ በዓየር ላይ ነን ወይም ደግሞ ወደ ላይ ወደ ዓየር ልንወሰድ ነው፡፡ ህልሙ እዚህ ላይ ያበቃል፡፡"

ኢየሱስም . . . "ደህና አሁን አንዳንድ ዝርዝር ሐሳብ አግኝተሻል፡፡ አሁን ተረጋጋሽ?"

ክሌርም እንዲህ አለች . . . ስለዚህ የክስተቶቹ ቅደም ተከተል በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሙስሊሞች መስኪድ መውደም፣ የ3ኛው የዓለም ጦርነት፣ የሰላም ስምምነት/በእስራኤልና በክርስቶስ ተቃዋሚው መካከል/ መደረግ፣ የኮሜት መውደቅ ከዚያም መነጠቅ ነው?

(ኢየሱስ) "የሰላሙ ስምምነት ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በፊት አይከናወንም፡፡ የሰላም ስምምነቱን ለማድረግ ጊዜ የለም ያ የሚከናወነው ከንጥቀት በኋላ ነው፡፡ ጦርነቱ ምድርን ለኮሜት ዝግጁ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡ የማያሚ መመታትና የኮሜት መውደቅ በአንድ ቀን የሚከናወን ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ጨለማውና ንፋሱ ሲከሰት እናንተ በዚህ የላችሁም /የሚነጠቁትን

ይመለከታል/፡፡ በዚያም ክስተት የምድር ስርዓት ይለወጣል፡፡ ይህም ለውጥ በፊዚካል፣ በኤሌክትሪክ ማግኔቲክ፣ በአየር ንብረትና በቅርፅ ጭምር ነው፡፡ ክሌር ይህንን ያመጣው ሰው ነው፡፡ እኔ ይህቺ ፕላኔት ምድርን እንድትመታ አላደረኩም፡፡ ይህ የሚፈፀመው ያላዋቂ ሰዎች ኢጋንንትን በመስማት ህሊናቸውን ለክብርና ለስግብግብ ዓላማ በማዋላቸው ነው፡፡ ይህም በምድር ከሚኖሩት ሰዎች ሦስት አራተኛው ቢጠፉ ምድሪቱ ለመኖሪያ የተመቸች ትሆናለች ብለው በማሰብ ነው (ይህም በኒውክላር ጦርነቱ ነው)፡፡ ነገር ግን ገሃነምን በሰው ስትሞላ ምድር እንደምትለጠጥና በምድር ሥር ያሉ ከተሞቻቸው የእነሱ መቀበሪያ እንደሚሆኑ ያላቸው እውቀት በጣም ትቂት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ይህች ኮሜት መሬትን ትጭርና ዝም ብላ ትጓዛለች፡፡"

(ክሌር) ዝም ብላ ትጓዛለች?

(ኢየሱስ) "በትክክል፣ ይህ ክስተት መፈንከት ስለሚያስከትል በውጪኛው ጠፍር ጉዞ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ በዚህም አያበቃም፡፡ የተፈጠረው ፍንክት በጣም ትልቅ ነው፡፡ ይህም ሁለት ማይልስ ዲያሜትር(የክብ ኢጋማሽ ስፋት) ያለው ነው፡፡ በተጨማሪም እንዲገባሽ  የሚያስፈልገው የምድር ፍርስራሽና ጋዞች አብረው ከምድር ጋር እንደሚጓዙ ነው፡፡ ይህ ነው የከፋና የባሰ ጥፋት የሚያደርሰው፡፡

"ይህ ፍርሃትን ለማምጣት የተነገረ አይደለም፡፡ የኔ ውድ እውነታው ይህ ነው፡፡ይህም ሰው አግባብ በሌለው መንገድ ምድርን ለመነካካት ባደረገው ነገር የመጣ ውጤት ነው፡፡ እንዲሁም የአውሮፓ የኒኩላር ጥናት ድርጅት/CERN/ በዚህ ሥራ ላይ እጁ አለበት ፡፡

"ጠላትም በሚፈጠረው በዚህ ክስተት በመፈንጠዝ ላይ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ክስተት ብዙ ሰዎች ህይወታቸው ስለሚያልፍና ገሃነም በፍጥነት በሰው ስለሚሞላ ነው፡፡ ይህም ክስተት የሃጉራት የመሬት ይዞታ ይለውጣል፣ ግዙፍ የመሬት እንቅስቃሴዎችን ወይም መንሸራተትን፣ የመሬት ርዕደቶችንና አጥፊ ሱናሜዎችን ይፈጥራል፡፡

(ክሌር) ጌታ ለዚህ ክስተት እንዴት ነው የምንዘጋጀው?

(ኢየሱስ) "እምነታችሁን በእኔ ላይ ጣሉ፣ ኃጢያታችሁን ተናዘዙ፣ ጠላታችሁን ይቅር በሉ፣ ደግሞም በየቀኑ በንስሐ ህይወት ቆዩ፡፡ የምህረት እጆቻችሁን በዙሪያችሁ ላሉና ለተቸገሩ ሁሉ አድርጉ፣ በየትኛውም ጊዜ ጎረቤቶቻችሁን ለመርዳት ወደኋላ አትበሉ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ለምህረት ፀልዩ፡፡"

"በምድር ላይ የሠራችሁት ትክክለኛ ሥራ ለመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ስዎችን ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ሥራቸውን ለማውገዝ፣ ወይም የሰው ልጅ በምድር በኖረበት ዘመን ሥራውን ለመመዘን ትክክለኛው መለኪያ እናንተ ናችሁ፡፡ አዎን የህይወት መፅሐፍ ይከፈታል፣ መዝገባትም ይቀርባሉ፡፡ ምንም እንኳን ለነፍሳችሁ ሙሉ መስዋዕት ብከፍልም በህይወት ዘመናችሁ የፈፀማችሁት መልካም ሥራ ከሰራችሁት ኃጢያት ጋር ሚዛን ላይ ይቀርባል፡፡

"ይህ ሁለተኛው ፍርድ ሲሆን ይህም የፍርድ የተዘጋጀው ለሙሽራዬ ሳይሆን በመሬት ውስጥ ለሚገኙና እኔን ተቀብለው ለእኔ ላልኖሩት ሙታኖች ነው፡፡ ይህ የፍርድ ጊዜ ለብዙዎች እጅግ ትልቅ ሐዘን የሚፈጥር ነው፡፡ እነዚህም ፍርድ የሚጠብቃቸው ነፍሳት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ማስጠንቀቂያዬን በመንፈሳቸው ያደመጡ ነገር ግን ያልተስተካከሉ ወይም የፍርዱን ማስጠንቀቂያ በህሊናቸው ቢረዱም ትክክለኛ የሆነውን ላለማድረግ በህሊናቸው እንዳይወቀሱ ህሊናቸውን የዘጉ ናቸው፡፡

"በምድር የምትኖሩና እኔን ያልተቀበላችሁ ወደ ልባችሁ እንድገባ ፍቀዱልኝ፡፡ ለመሆኑ አንድ ቀን በሰማይና በምድር ፊት ለፍርድ እንደምትቆሙ አታውቁም? በህይወት ዘመናችሁ ሁሉ ህሊናችሁ በውስጣችሁ አንድ ነገር እንደሚያስፈልጋችሁ ወይም አንድ ነገር እንደጎደላችሁ ሲወቅሳችሁ እንደነበረ አታውቁም? እኔን ችላ ማለትና የምለውን ያለመስማት የሚያስከትለውን ነገር አታውቁም? እኔ ሁልጊዜ ልባችሁን ሳንኳኳ፣ ሳንኳኳ ነበር፡፡ ነገር ግን እናንተ ልባችሁን አልከፍት አላችሁኝ፡፡ አሁን ግን በዓለም ላይ /በምድሪቱ ላይ/ ሊመጣ ያለውን አስደንጋጭና ትልቅ ስቃይ ልትቀበሉ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ብዙዎቻችሁ አሁንም ግትር በመሆን እኔን ችላ በማለት ልባችሁን ጥርቅም አድርጋችኋል፡፡

"በዚህ ሁኔታ ሆናችሁ ከሞታችሁ እኔን የተቀበሉ ዘመዶቻችሁን ከአሁን ወዲያ በፍፁም አታይዋቸውም፡፡ በሐዘናችሁ ጊዜ እንዲያጫውቷችሁና እንዲያዝናኗችሁ የሰጠኋችሁን የምትወዷቸውን ለማዳ እንስሳቶቻችሁን ከአሁን ወዲያ አታዮአቸውም፡፡ የልጅ ልጆቻችሁን ከአሁን ወዲያ አታይዋቸውም፡፡ መኖርያችሁም ለዘላለም ሰይጣንና መላዕክቱ በሚኖሩበት በእሳት ባህር ውስጥ ይሆናል፡፡ በእሳቱ ውስጥም የምትጣሉት ለአንድ ሰዓት፣ ለአንድ ቀን፣ ለአንድ ሳምንት ወይም ለዓመታት አይደለም፣ ነገር ግን ለዘላለም ነው፡፡ እንግዲህ ምርጫው የእናንተ ነው፡፡ ከእኔ ጋር ያላችሁን ግንኙነት የተስተካከለ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፡፡ እኔ እንደምወዳችሁ ባለቤቶቻችሁ ወይም ልጆቻችሁ ወይም ቤተሰቦቻችሁ በተደጋጋሚ ነግረዋችኋል፡፡ ነገር ግን አሁንም እንዳቋሸሻችሁኝና እንደገፋችሁኝ ነው፡፡

"ስለዚህም በችግራችሁ ጊዜ ልደርስላችሁ አልችልም፡፡ ምክንያቱም በምድር የሚከሰተው ነገር ሲገለጥ በሚሆነው ነገር ስለምትደነግጡ በድን ትሆናላችሁ፡፡ ነገሩ ሲፈፀም የሚቀራችሁ ጊዜ እጅግ ጥቂት በመሆኑ ለሁሉም ነገር የዘገያችሁ

ትሆናላችሁ፡፡ለማምለጥ ብትፈልጉም እንኳን ማምለጥ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ነገሩ ሁሉ በጣም በፍጥነት ስለሚሆን አይምሯችሁ በብዙ ነገር ስለሚያዝ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እንኳን መወሰን ያቅታችኋል፡፡ ስለዚህም በዛ ወቅት ንስሐ ልትገቡም ሆነ እኔን ለመቀበል ጊዜ አይኖራችሁም፡፡ በተቃራኒው ወዲያው ለዘላለም ወደምትሰቃዩበት ወደ ገሃነም በኢጋንንት ተጎትታችሁ ትወሰዳላችሁ፡፡ ይህም ሥፍራ ስጋችሁ በትል እየተበላና እንደገናም እየተተካ ባለማቋረጥ በትሎች የሚበላበት፣ እንዲሁም ሥጋችሁ ባለማቋረጥ በእሳት የሚቃጠልበትና የተቃጠለው እየዳነ እንደገና ለእሳት ስቃይ ለዘላለም የሚዳረግበት ሥፍራ ነው፡፡

"ስለዚህም ይህንን የመጨረሻ ጥሪዬን ለእናንተ አቀርባለሁ፡፡ በእውነት በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ በህይወታችሁ የሆነው መልካም ነገር ሁሉ ከልቤ በመነጨ ለጋስነት የተደረገ ነው፡፡በሰዎች ላይ የፈጸማችሁትን በደል ሁሉ ይቅር እላችኋለሁ፡፡ ከእናንተ የሚጠበቀው ስህተታችሁንና ያደረጋችሁትን ጥፋት አውቃችሁ ንስሐ ለመግባት ፀጋ እንድትቀበሉ እኔን መጠየቅ ብቻ ነው፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ በህይወት ዘመናችሁ በፈፀማችሁት ክፉ ድርጊት ከክፉው ሽልማት አግኝታችሁበታል፡፡ ከድሆች ሰርቃችኋል፣ ንፁሃንን ገድላችኋል፣ ጥፋተኛ ያልሆኑትን አስራችኋል፣ በአጠቃላይ ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጥቅም ስትሉ ማንኛውንም ነገር አድርጋችኋል፡፡ ቢሆንም ለዚህ ሁሉ ላደረጋችሁት ሥራ እኔ ለመስቀል ሞት እራሴን መስዋዕት አድርጌ አቅርቤያለሁ፡፡ አሁን እኔ የምጠራችሁ ንስሐ እንድትገቡ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ በአለም ሁሉ ላይ በቅርብ ሊመጣ ያለው መቅሰፍት ሲገለጥ ንስሐ ለመግባት ጊዜ የላችሁም፡፡ አንዳንዶቻችሁማ ይህ መቅሰፍት እንዲመጣ በእቅዱ ውስጥ ተሳትፋችኋል፡፡"

"እናም አሁን የምጠይቃችሁ እኔ እየሰማኋችሁ ስለሆነ ለእኔ እንዲህ ብላችሁ ተናገሩ፡፡ "ኢየሱስ እኔ ኃጢያተኛ እንደሆንኩ አውቃለሁ፡፡ እስካሁን የሠራሁትን ለመጋፈጥ አልቻልኩም ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን የቀረኝ ጊዜ ጥቂት እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም ይቅር በለኝ፣ ምህረትን አድርግልኝና በመንግስትህ ተቀበለኝ፡፡ አንተ ለእኔ ኃጢያት እንደሞትክ አምናለሁ፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ከኃጢያት መንገዴ ተመልሻለሁ፡፡ በአንተ እርዳታ ለአንተ ለመኖር ወስኛለሁ አሜን፡፡"

## ከሰማያት እሳት ስለሚወድቅ ተዘጋጁ እንጂ አትፍሩ - ሜይ 12 ቀን 2020 ዓ.ም

## Fire will fall from heaven, May 12, 2020

(ክሌር) ውድ ቤተሰቦች አሁን ያለነው ወደ ምድር ሊመጣ ባለ ከባድ የፍርድ ወቅት ላይ ነው፡፡ ጌታ ይህንን ከዋና አባላቶቻችን በአንዱ አማካኝነት አረጋግጦልናል፡፡ ይህም ሰው ደግሞ በአለም ላይ ሊከሰቱ ያሉ አደጋዎችን በትክክለኛው ሁኔታ በማስጠንቀቅ የታወቀ ሰው ነው፡፡ ስሙም ማይክ ይባላል የሚታወቀውም ማይክ ፍሮም አራውንድ ዘ ዎርልድ (Mike from around the world) በመባል ነው፡፡ መልዕክቱንም ካውንስልነአርክ (Council1arch)በሚል መጠሪያ በሳውንድ ክላውድ( Sound Cloud) ላይ ይተላለፋል፡፡

ይህ አባላችን ላለፉት ስምንት አመታት የአለም መጨረሻን የሚመስል የዳመና ፍርስራሽ ይከሰታል ብሎ ሲያስጠነቅቀን ነበር፡፡ ይህም ደግሞ እ.አ.አ. በሜይ 12 ቀን 2020 ዓ.ም ከመሬት ጋር ይጋጠማል ብሎን ነበር፡፡ የዚህ ዳምናም ስፋት ከ3-4 ሚሊየን ማይልስ ሲሆን ይህም ዳመና የሚያያዘው ጨለማ ከምትባለው ፕላኔት ኒብሩና ፕላኔቶቿ ወደ መሬት መቅረብ ጋር ነው፡፡ የኛ ፀሐይና ፕላኖቶቿ(our solar system) በአሁን ወቅት በዚህ ሁኔታ እያለፉ ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ በምድር ላይ ምን ያህል አደጋ ሊያመጣ እንደሚችል ማንም የሚያውቅ የለም፡፡ ነገር ግን ከእኛ ዋና አባሎች ራዕይ አንፃር እሳት ከሰማያት ወደ ምድር በመውደቅ ብዙ አገራት በእሳቱ ሲቀጣጠሉ ተመልክተዋል፡፡ ከዚህ መልክት መጨረሻ ላይ ማዘር ኤሊሻ ወይም ናና ከጌታ የተሰጣትን ትንቢታዊ ቃል አካፍላችኋለሁ፡፡

ተወርዋሪ ኮከብ ምን ሊያደርስ እንደሚችል ሐሳብ እንዲኖራችሁ እንደ ምሳሌ አንድ ክስተት ላጫውታችሁ፡፡ እ.አ.አ. በሰምቴምበር 15 ቀን 2007 ዓ.ም. በፔይሩ 12,500 ጫማ በሚገኘው ካርካስ መንደር, እንዲሁም በቦሊቪያን ዳር ድንበርና በቲቲካከ ሐይቅ አጠገብ አንድ ተወርዋሪ ኮከብ በመውደቁ ምክንያት 15 ጫማ ጥልቀትና 43 ጫማ ስፋት ያለው የእሳተ ጎሞራ ጉድጓድ ፈጥሯል፡፡ ይህም በአካባቢው ጎልቶ የሚታይና ምድሪቱንና አፈሩን በእጅጉ የጎዳ ክስተት ነው፡፡ የአካባቢው ባለስልጣን እንዲህ ብሏል "የፈላ ውኃ ከእሳተ ጎሞራው መውጣት ጀምሯል፡፡ ደግሞም የድንጋይና የተቃጠሉ የከሰል ቅንጣቶች በአጠገቡ ተገኝተዋል፡፡" ከእሳተ ጎሞራው የሚያስጠላና የሚያቅለሸልሽ ጭስ ተወርውሮ በኃይል ይወጣል፡፡ በጣም የሚሸት፣ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ነገር፣ ድኝ ከውስጡ ይወጣል፡፡

ከዚህ ነገር በኋላ ወደዚህ ሥፍራ ለመጠጋት የሞከሩ በአካባቢ ያሉ የመንደሩ ነዋሪዎች በተለያዩ ምልክቶች የታጀበ፣ ነገር ግን በውል ምን እንደሆነ ባልታወቀ በሽታ ታመዋል፡፡ የአካባቢው ባለስልጣን እንደገለፀውም ይህ የሆነው ከእሳተ ጎሞራው ከሚወጣው ነገሮች ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለፁት በጣም የሚያበራ የእሳት ኳስ፣ ጭራው የሚጨስ ከመሬት 3,300 ጫማ ከፍ በማለት ይቀሳቀስ ነበር፡፡ ይህም ኳስ መሰል ነገር የተጓዘው ወደ ሰሜን ምስራቅ ሲሆን ይህም በሚሆን ጊዜ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ አይነት ነገር በመፍጠሩ በግማሽ ማይልስ የሚገኝ ጤና ጣቢያን መስኮት ብትንትኑን አውጥቶታል፡፡ በእሳተ ጎሞራው ውስጥ የጋዝ አረፋ ሲወጣና ለብዙ ጊዜ የቆየ የቁም ዳመና ታይቷል፡፡

ክስተቱ ከተፈጠረ ወዲያ ከ600 የሚበልጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ለጉብኝት ወደ ቦታው ሄደው ነበር፡፡ እናም እነዚህ ጎብኚዎች ሊገለጡ የማይችሉ ብዙ ምልክቶችን አስተናግደዋል፡፡ ለምሳሌ የቆዳ መጎዳት፣ ማቅለሽለሽ፣ ራስ ምታት፣ ተቅማጥና ተውከት የመሳሰሉትን፡፡ በፈረንጆች ስብቴምበር 20 ቀን 2020 ዓ.ም የፔይሩ ሳይንቲስቶች በራራ ኮከብ

መውደቁን አረጋግጠዋል፡፡ በጣም የሚገርመው ይህ ከመከሰቱ አንድ ሳምንት በፊት ከእኛ አንድ የህብረተሰብ አባል ለሳምንት ያህል በየቀኑ "እሳት ከሰማይ ይወድቃል" የሚል በሌላው ሳምንት ደግሞ "መስዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ደም" የሚል መልዕክት ትሰማ ነበር፡፡ ከዚህ ራዕይ ጋር በተያያዘ የሚሰጣት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል "በሰማይ ላይ እሳት" የሚለውን በካቶሊክ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኘው መፅሐፈ ባሮክ 6፡ 62 ላይ የሚገኝ ነበር፡፡ ይህም ክፍል እንዲህ ይላል "ከሰማይ የተላከ እሳት ተራሮችንና ጫካዎችን በማቃጠል ተልዕኮውን ይፈፅማል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የውሸት አማልዕክቶች በአቋምም ይሆን በኃይል አይወዳደሩትም፡፡"

(ክሌር)-- ጌታ ለኸርት ድዌለርስ ስለዚህ ጉዳይ ልትነግራቸው የምትፈልገው ነገር ምንድነው?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ከሰማያት ስለሚወድቀው እሳት እንዳይፈሩ ንገሪያቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ መፍራት ያለባቸው ለዘላለም በሚያቃጥለው ገሃነም ውስጥ መጣልን ሊሆን ይገባል፡፡ እኔ ወደገሃነም ሊጣሉ ያሉትን ከዛ ለመውጣት ወደ እኔ የሚጮኹትን ለማዳን በተጠንቀቅ ቆሜያለሁ፡፡ በምድር የምትኖሩ ሁሉ ገዢዎቻችሁ አታለዋችኋል፣ እንድትስቱ አድርገዋችኋል፡፡ ነገር ግን ክፉዎቹ እጅግ በትልቅ ሥልጣን ላይ የሚገኙት ናቸው፡፡

"እነርሱ ፍፁም ክፉ እየሰሩ መልካም እንደሰሩ እንድታምኑ በማድረግ ከትክክለኛው መንገድ አውጥተዋችኋል፡፡ እናንተ ወጣቶች የአለምን መንገድ እንድትከተሉ ተደርጋችሁ የሰለጠናችሁ፣ እናንተ ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ አድርገው ለምን በዚህ መንገድ እንዳሰለጠኗችሁ ከበስተጀርባ ያለውን አጀንዳ ምን እንደሆነ እውነቱን መግለጥ እንድትችሉ ብዙ የምትማሩት ነገር አለ፡፡

"ይህችን ቆንጆ ፕላኔት የፈጠርኳትና ያቆየኋት እኔ ነኝ፡፡ በውሸት እኔን የሚከሱኝ እነዚያ፣ እነርሱ ናቸው ለውድቀቷ ምክንያት የሆኑት፡፡ የሰይጣን አጠቃላይ አጀንዳ እናንተንና ምድሪቱን እጅግ በሚያም ሁኔታ ማጥፋት ነው፡፡ እርሱ እናንተንና በዚች ቆንጆ ፕላኔት ያለውን ሁሉ እጅግ ይጠላል፡፡ እናም የእርሱ ብቸኛ አጀንዳ ስቃይን፣ ጥፋትንና ሞትን ማምጣት ነው፡፡

"ይህንን የምነግራችሁ እናንተን ለማጥፋት ማጭበርበርና ያነጣጠረውን ጥፋት ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ ስለማታውቁ ነው፡፡ ይህ አገር አሁን ያለው መንገዱ በመጨረሻ ላይ የተዘጋ መንገድ ላይ ነው፡፡ ወደኋላ ለመመለስ የማይቻልበት ነጥብ ላይ ደርሷል፡፡ አሁን እየገባችሁ ያላችሁት ወደር የሌለው ስቃይና ጥፋት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም ሁላችሁንም የምጠይቃችሁ ከአሁን ቀደም ፀልያችሁ ያማታውቁትን ያህል እንድትፀልዩ ነው፡፡ ምክንያቱም በህይወት መኖራችሁ የሚወሰነው በዚህ ስለሆነ ነው፡፡ የሚመጣውን ማመን አትችሉም፡፡ ነገር ግን የተባላችሁትን በደንብ ያከናወናችሁና የተዘጋጃችሁ ሌሎችን መርዳት እንድትችሉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡"

(ክሌር) ጌታ ምን መጠበቅ እንዳለብን እባክህ ንገረን፡፡

ኢየሱስም . . . "ጥፋትና ሞትን ጠብቁ፡፡ በዚህ ወቅት ትኩረት ማድረግ ያለባችሁ ሥራ ላይ ሳይሆን የሚያስፈልገው ፀሎት፣ ፀሎትና የበለጠ ፀሎት ነው፡፡ በፀሎት ቀጥሉ፡፡ ህይወት የሚቀጥለው በታማኝነት በመፀለያችሁና ንቁ በመሆናችሁ ነው፡፡ ብዙ ነፍሶች፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሶች በሥጋ መሞታቸው ብቻ ሳይሆን ከሞቱ በኋላ መገኛቸው የት እንደሚሆን

የሚወስነው በፀሎታችሁ ነው:: በመጀመሪያ እንደነገርኳችሁ በመሬት ላይ ስለሚወድቀው እሳት አትጨነቁ:: መጨነቅ ያለባችሁ በገሃነም መጣላችሁና የዘላለም ህይወት ማጣታችሁ ነው::

"የእግዚአብሔር አገዛዝ ማንም እንደሚጠብቀው አይመጣም:: እኔ የምመጣው በመብረቅ፣ በብልጭታና በሰማይ ላይ በሚታዩ ምልክቶች ነው:: እስካሁን አብዛኞች ስለመምጣቴ ዝግጁ አይደሉም:: ለአባቴና ለእኔ የሚያሳስበን ይህ ጉዳይ ነው:: ክሌር እኛ የምንፈልገው የበለጠ ብዙዎች እንዲድኑ ነው::  ከዚህ በበለጠ ብዙዎች እንዲድኑ ነው:: ሙሽራዬ እንደተዘጋጀች በማሰብ በጭንቀት የኔን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ብትሆንም፣ እኔ ግን የምመለከተው መንግስቴ እንዲመጣና ፈቃዴ በምድር ላይ እንዲፈፀም መኖር ያልያዙትን፣ ለራሳቸው ብቻ የሚኖሩትንና ራስ ወዳዶችን ነው:: በዚህ ሁሉ ታዲያ ይህ ስጋዊነት ይቀጥላል:: ነፍሳት ምግብ፣ አልባሳት፣ መጠለያና ፍቅር ከማጣት ይሞታሉ:: በዚህም እኔ ምን ያህል እንደምወዳቸው እውቀት ሳይኖራቸው ያንቀላፋሉ:: ክሌር ሙሽራዬ ከዚህ ምድር ከመወሰዱ በፊት ብዙዎች እጅግ ገና ብዙዎች መዳን ያለባቸው አሉ:: እያንዳንዱ ራሱን ያጠመደው በንጥቀት ላይ ሲሆን አንቺ ግን ይህንን ጥበብ ወደ እኔ ቀርበሽ በመጠየቅሽ አዋቂ ነሽ:: እኔ ደግሞ የተጠመድኩት በእርሻው ላይ የሚሰራልኝን ሰራተኛ በመፈለግ ላይ ነው:: በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ያገኘሁት እጅግ ጥቂት ነው::

"የኔ ውድ ይህ ምን ማለት ነው? እኔ ከመምጣት መዘግየት አለብኝ ማለት ነው:: ሙሽራዬ እስካሁን በራሱ ጉዳይ ላይ ተይዛለች:: እርሷ በስቃይ ላይ ካሉት ጋር አይደለችም:: ከሁሉ በላይ ደግሞ እኔ በፍቅር እንደምወዳቸው ባለማወቃቸው ከሚሰቃዩት ጋር አይደለችም:: ወንጌሉ በአለም ሁሉ መሰበክ አለበት:: የኔ መምጣት በማንኛውም ሰዓት ሊከናወን እንደሚችል ግልፅ ቢሆንም እኔ ግን እርሷ የደረሰውን መከር ለመሰብሰብ በታዛዥነት በእርሻው ላይ ትሰራለች ብዬ እየጠበቅኋት ነው::

በዚህም ምክንያት ነው ንጥቀት አሁን የማይሆነው:: ይህ በመንግስተ ሰማያት የተወሰነ ጉዳይ ነው:: ለዚህ ሰዓቱ አልደረሰም:: ነገር ግን አንዳንድ ፍንጮችን እየሰጠሁ በቅርብ የመምጣቴን እሳት ማቀጣጠል አለብኝ:: ይህንንም የማደርገው ውዷ ሙሽራዬ ህይወቷን በመመርመር እኔን አለመምሰሏን የምታገኝበት ይሆናል:: ይህ የማጣሪያ ነጥብ ነው:: ሙሽራዬ እኔን መምሰል አለባት:: ስለዚህም በአለም አይን ጥቃት ሊደርስባት፣ ተቀባይነት ልታጣና ልትናቅ ይገባታል:: ይህም የሚሆነው ደግሞ በእኔ ጉዳይ ላይ፣ በእርሻው ሥራ ላይ የደረሰውን መከር በመሰብሰብ ላይ ስትጠመድ ነው::"

(ክሌር) ጌታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መፆም አቅቶኛል:: ይህ ደግሞ አንተ ከሰጠኸኝ ሥራ ይልቅ ራሴን ወዳድ መሆኔን የሚያሳይ ሲሆን እኔ ግን እጅግ ደካማ ሆኛለሁ::

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ እንድትረጂ የምፈልገው ለሁሉም ነፍስ በከባድ ሁኔታ እንዲፆም አልተሰጠውም:: አይንሽን ከፆም ላይ አንሺና በፍቅርና በአገልግሎት ላይ አተኩሪ:: ጠላት ሁኔታሽን እየተከታተለ ድካምሽ ላይ እንድታተኩሪ በማድረግ ተስፋ እያስቆረጠሽ ነው:: ይህ ለእያንዳንዳችሁ ኸርት ድዌልርስም የሚሰራ እውነት ነው:: ሰይጣን ክርስቲያኖችን በመክሰስ፣ የጥፋተኝነት ስሜትና ሃፍረት እንዲሰማችሁ በማድረግ ከእኔ ለመነጠል የሚያደርገው ጥረት ነው:: አንዳንዶች ፆም ጣዖት ሆኖባቸዋል:: እርግጥ ነው ፆም በህይወታችሁ ብርታት እንደሚሰጣችሁና አስፈላጊ እንደሆነ ጥርጥር የለውም:: ነገር ግን ጣዖት አይሁንባችሁ:: አልፎ አልፎ የሚፆም ጥብቅ የሆነ ፆም ካልሆነ በቀር ከእኔ ልትሰሙ ብቁ አይደላችሁም:: ፆምን ጣዖት በማድረግ እኔን ለመስማት መሞከር ፍፁም ውሸት ነው:: እኔን እንድትሰሙ ከመረጥኳችሁ ትሰሙኛላችሁ:: ራስን መካድ አከብራለሁ፣ ነገር ግን አምላካችሁ አታድርጉት::

ብዙ መብላትና ብዙ መዝናናት ስሜቶችን ስለሚያደነዝዝ በተወሰነ መልኩ መስማትን ይከለክላል፡፡ ስለዚህም ለእኔ ጥሪ ንቁ፣ ዝግጁና ትጉ እንድትሆኑ እነዚህን ነገሮች በመጠኑ አድርጓቸው፡፡ ክሌር እነዚያ የሚፆሙ ሰዎች በአይምሮአቸው ውስጥ ምን እንደሚመላለስ ብታዪ ኖሮ እጅግ ትደነግጪ ነበር፡፡ ብዙዎች  የሚፆሙት ንፁህ ባልሆነ የውስጥ ፍላጎት ነው፡፡ እነርሱ የሚፈልጉት እንደ ቅዱስ እከሌ ለመሆን ነው፡፡ ስለዚህም እንደ ቅዱስ እከሌ መፆም ስለምንችል እኛም ቅዱስ እንሆናለን በሚል እሳቤ ነው የሚፆሙት፡፡ ነገር ግን ይህ  አይሰራም፡፡ ከውጪ በሚታይ ምልከታ ሳይሆን ይህ ሊመጣ የሚችለው ልብን በሚያዘጋጅ ፍቅር፣ መታዘዝና ትህትና ነው ፡፡

"አሁን አንድን ነፍስ ከምግብ እንዲፆም ባዘው ያንን የማደርገው ለአንድ መልካም ምክንያት ሲሆን መታዘዙ ደግሞ ያስደስተኛል፡፡ መንፈሳዊ ህይወት ቅዱስ በሚመስል መልክ በተቆለለ ድፍረት የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ወጥመድ ነው፡፡ ለዚህ ነው እኔ ከእነዚህ ሁሉ የሚበልጠው ፍቅር ነው ብዬ የማስተምረው፡፡ አንድ ሰው በሁሉ ነገር ብቁ፣ ስኬታማ፣ የሚፆም፣ የሚፀልይ፣ ለሌሎች የሚያነባ፣ የእውቀት ቃልን የሚናገር ሆኖ ነገር ግን የወንድማማች ፍቅር ከሌላው፣ ይህ ሰው ዋናውን ነገር አጥቷል፡፡

"ብዙ ተብሏል ነገር ግን ግልፅ ላደርግላችሁ የምፈልገው በመንግስተ ሰማያት ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ተወስኗል፡፡ ቢሆንም ሙሽራዬ ተነስታ በእርሻው ላይ እንድትሰማራና መከሩን እንድትሰበስብ በምድር ላይ ብዙ መቅሰፍቶች ይኖራሉ፡፡ ይህ የማንቂያ ደውል እንጂ የመጨረሻው መለከት መነፋቱ አይደለም፡፡ እባካችሁ በዚህ እንዳትጠራጠሩኝ፡፡ ስለዚህ የምላችሁ ይህንን ነው "እየሄደች እያለችም ትጠንቀቅ"፡፡ በተሰጣችሁ ሥልጣን መሰረት ወደ ሥራ ግቡ፡፡ ለመንግስቴ መከረን ለመሰብሰብ ወደ እርሻው ተሰማሩ፡፡ የጠወለጉትንና ለእነርሱ ያለኝን ትልቅ ፍቅር የማያውቁትን ነፍሳት ወደ እኔ በማምጣት የበኩላችሁን አስተዋፅዎ አድርጉ፡፡

"እኔ ባላሰቀመጥኩላችሁ ሚዛን እየመዘነ ሁልጊዜ የሚከሳችሁን ጠላት በመፍራት ራሳችሁን አታሸማቁ፡፡ እንዲህ አይሁን፣ እናንተ በመታዘዝ እኔን ብቻ ተከተሉ፡፡ መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈፀምም ለራሳችሁ ጣዖትን አታዘጋጁ፡፡  በፆማችሁ ጊዜ የኔን መመሪያ ብቻ ተከተሉና ያንን ፍፅሙ፡፡ እኔ ብቻ ነኝ አቅማችሁን መተመን የምችለውና ለእናንተ መልካም ያልሆነውን የማውቅ፡፡ ይህንን አድርጉና በዚህ በእናንተ በደንብ ደስተኛ እሆናለሁ፡፡

"በተጨማሪ በደንብ ማየት ያለባችሁ ነገር በእናንተ አይን "የበለጠ ቅዱስ" ሥራ ነው ብላችሁ በማሰብ መሥራት የያዛችሁትን በመተው በጎን የሚመጣላችሁን ሥራ ለመስራት እንዳትሸወዱ፡፡ በቀደመው ዘመን በቀላሉ ያሸነፏችሁን ወጥመዶች፣ ትህትናና መታዘዝ በቀላሉ ያሸንፏቸዋል፡፡ የኔ አጋሮች አሁን ከእኔ ፅድቅ በተወለደ በጉንጉን አበባ ፀጋና ሰላም እባርካችኋለሁ፡፡ ይህም ከእኔ ጋር ያላችሁን ልዩ ግንኙነት እጅግ እንድትተማመኑበትና በትከሻችሁ እንድታርፉ የሚያስችላችሁ ነው፡፡" የጌታ መልዕክት በዚህ ላይ ያበቃል፡፡

አሁን ደግሞ ማዘር ኤሊሻ የተቀበለችውን መልዕክት በስተመጨረሻ አካፍላችኋለሁ ያልኳችሁን  አካፍላችኋለሁ፡፡

ማዘር ኤሊሻ መፅሐፍ ቅደሱን ስትከፍት ጣቷ ያረፈበት መልዕክት መፅሐፈ ባሮክ ምዕራፍ 6 ቁጥር 62 በሚለው ላይ ነበር፡፡ " እና እሳት የታዘዘውን ለመፈፀም፣ ተራሮችንና ጫካዎችን ለማቃጠል እሳት ከበላይ ይላካል፡፡" ነገር ግን እነዚህ የውሸት አማልክቶች በአቋምም ይሁን በኃይል በምንም አይስተካከሉትም፡፡" እዚህጋ የሚናገረው እየተካሄደ ስላለው ጣዖትና  እሳት ከበላይ ተራሮችንና ጫካዎችን ለማቃጠል ለምን እንደተላከ ነው፡፡

መፅሐፈ ሲራቅ 17፡24- 30 (የካቶሊክ መፅሐፍ ቅዱስ) <u>"ነገር ግን ንስሐ የሚገቡትን ምክንያት ሰጣቸው፣ ተስፋቸውን ያጡ ሰዎችንም ደስ ያሰኛቸዋል፡፡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ ኃጢያትህንም ተዋት፣ ከኃጢያትህ ተመልሰህ በፊቱ ተለማመጥ፡፡ ፊፅምህ ከኃጢያትህ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፣ ኃጢያትን ሁሉ ጥላ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈፅም፡፡ በህይወት ሳሉ እንደሚገዙለት ሰዎች እግዚአብሔርን በመቃብር የሚያመሰግነው ማነው? የሞተ ሰውን ግን ንስሐ እንደ ኢሚንት አለፈው፡፡ በህይወት ሳለህ ደስ እያለህ እግዚአብሔርን አመስግነው፡፡ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ብዙ ነውና የሚገዙለትን ሰዎች ይቅር ይላቸዋል፡፡ ሰው ሚች ስለሆነ ሰው ሁሉ በህይወት ፀንቶ መኖርን አይችልምና ይቅር ይላቸዋል፡፡"</u>

ይህ ሁሉ የሚያነጣጥረው ስለ አገራችን(ስለ አሜሪካ) ንስሐ መግባት ጉዳይ ነው፡፡ ኒውዮርክ ከተማ ከሁሉም ከተሞች በኮሮና ቫይረስ በከፍተኛ ደረጃ መጣቃቷ ሚስጥር አይደለም፡፡ የዚህም ምክንያት በውርጃ ስለገደሏቸውና ከእናታቸው ማህፀን ሲወጡ ስለቆራረጧቸው ልጆች ነው፡፡ ይህ እጅግ አስከፊ ነገር ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ከሆነ ኒውዮርክ ከሌሎቹ ከተሞቻችን በሚመጣው ፍርድ በከበደ መልኩ ትመታለች ብለን መጠበቅ እንችላለን፡፡

ማዘር ኤሊሺያ . . .  ጌታ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ ነገር ግን ማሰብ የምችለው የበለጡ ከባድ አደጋዎች እየመጡ እንደሆነና  ይህንንም በተመለከተ ብዙ ሰዎችን ማስጠንቀቅ እንዳለብኝ ነው የምትፈልገው፡፡

 ኢየሱስም . . . "የተወደድሽ  ሆይ የሚመጡ ነገሮች እጅግ አውዳሚና አጥፊ ናቸው፡፡ ብዙዎች ምን  እየተካሄደ እንዳለና ለምን ይህ ነገር እየሆነ እንዳለ ሊገባቸው አይችልም፡፡ የተወደድሽ ይህም የሚፈፀመው ደግሞ አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረበ ነው፡፡ የተኙትን ከእንቅልፋቸው የምቀሰቅሳቸው አለምን ሁሉ ያዳረሰው ወረርሺኝ ሲያበቃ ደግሞ ሌላውን በእግሩ በመተካት ነው፡፡ እስካሁን ሆኖ የማያውቅ አሜሪካን ሁሉ የሚያካልል እሳት ደግሞ በበጋው ወቅት ይከሰታል፡፡ ይህም እሳት ሰብልን እርሻዎችንና ቤቶችን የሚያጠፋ ነው፡፡ መተዳሪያቸውንም በእነዚህ ላይ ያደረጉ ትልቅ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ እንዲሁም የእሳት አደጋ ሰራተኞችና ብዛት ያላቸው አራዊቶቼ በእሳቱ ተቃጥለው ህይወታቸው ያልፋል፡፡

"በዚህ ጊዜም ብዙዎች 'ይህ ሁሉ ሲሆን ጌታ የታለ'? ብለው ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡' እናም ህዝቤ ለእናንተ የምመልሰው ይህንን ነው፡፡እኔ እዚሁ ነኝ፡፡ ሁልጊዜ እዚሁ እንደነበርኩ እናንተ ምላሽ እስክትሰጡኝ ድረስ እዚሁ እየጠበቅሁ ነው፡፡ አሁን ምድር እያለቀላት ነው፡፡ እናም በውስጧ የቀረ መልካም ነገር የለም፡፡ ህይወታችሁ እንደ እንፋሎት የሚበን መሆኑን ስለተረዳችሁ፣ አሁን ለእኔና ለፈቃዴ ሁሉን አሳልፋችሁ ትሰጡኛላችሁ? የታመናችሁበት፣ ተስፋችሁ ፣ኃብታችሁ፣ እንዲሁም ጤናችሁ እንኳን ሊያድናችሁ እንደማይችልና እኔ ብቻ እንደምችል አሁን ተረድታችኋል፡፡

"ህዝቤ ወደ እኔ ጩኽ፡፡ ለእኔ ውድ የሆኑት በታላቅ ትህትናና ፀፀት እኔን ቢጠሩና ከኃጢያት መንገዳቸው ቢመለሱ ምድራቸውን እፈውስ ይሆናል ብዬ እየጠበቋቸው ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎቻችሁ እኔ እንዴት ነው ኃጢያት የሰራሁት እኔ የእግዚአብሔር ሰው ነኝ፣ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ፣ አሥራቴን እሰጣለሁ ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ የኔ ውዶች ድነታችሁን መፈፀም ከዚያ የሚበልጥ ነው፡፡ ድነት ከኃጢያት ፍፁም ነፃ በመሆን የመኖር ፍላጎት ነው፡፡ የጠራኋችሁ እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱስ እንድትሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት ህሊናችሁን በጥልቅ በመመርመር ወይኑን የሚያጠፉትን ትንንሽ ቀበሮዎችን መቃወምና በዚህም አንፃር ህይወታችሁን መምራታችሁን የሚያመለክት ነው፡፡ በእርግጥ እኔን እየተከተላችሁኝ ነው? ጎረቤቶቻችሁን እንደ ራሳችሁ ትወዳላችሁ? የታመሙትን፣ ድሆችን የተራቡትን ትረዳላችሁ? ይህንን ስል ዝም ብሎ ገንዘብ እዚም እዛም መስጠትን ማለቴ አይደለም፡፡ በእውነት ከልባችሁ ለሌሎችና ለመንግስቴ  እየኖራችሁ ነው ወይ እያልኩ ነው፡፡ ወይንስ የምትኖሩት ለራሳችሁና ለቤተሰባችሁ ብቻ ነው? የኔ ውዶች እባካችሁ ንቁ፡፡ ከእንቅልፋችሁ ንቁና ከአሁን

ወዲያ አትተኙ፡፡ በአለም ላይ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት  አለምን አንድ ጊዜ አናውጣታለሁ፡፡ በእርግጥም መከሩ ብዙ ነው ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡

"ደግሞ አሉ ለእኔ ታማኝ በመሆን በልባቸው በእውነት የሚፈልጉኝና ለጥያቄያቸው መልስ ከእኔ የሚጠብቁ፣ ለእናንተ መልስ አለኝ፡፡ ይህ ጊዜ የኔን ፍቅር፣ የኔን ተስፋና እምነትን በዙሪያችሁ ለሚገኙት ለማካፈል ትልቅ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን በፊታችሁ ያቀረብኩትን ተቆጥሮ የማያልቅ አጋጣሚ ከሃፍረት የተነሳ እንዳያመልጣችሁ፡፡ የኔ ውድ ሙሽሮች ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡ አብዛኛዎቻችሁ እንደደከማችሁ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡ ታላቅ መከርን የመሰብሰቢያ ወቅት ደርሷል፡፡ እንዲያውም ጀምሯል፡፡

ማዘር ኢሌሻ  . . . ጌታ እባክህ እርዳን፡፡ እኔን እርዳኝ ምክንያቱም በእውነቱ ከሆነ የአንተ ሆነው እጅግ ከደከማቸው አንዷ ነኝ፡፡ በእምነትና በትልቅ ተስፋ ተነስተን ለመቆም እንድንችል አጠንክረን፡፡ ይህንንም የምንጠይቀው ለእኛ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያችንም ላሉ ጭምር ነው፡፡

ኢየሱስም . . . "አዎ የኔ ውድ በዚህ ጊዜ በትልቅ ብርታትና እምነት መነሳት ላለባቸው በእርግጥም ፀጋን እየለቀቅሁላቸው ነው፡፡ የልብሽን ጭንቀትና ስጋት እየሰማሁት ነው፡፡ የተወደድሽ ሆይ ቃል የገባሁልሽ ሁሉ በትርምሱ ጊዜ እንኳን ቢሆን ይፈፀማል፡፡ ከአመድ ውበትን እንደማወጣና ከተበላሸ ነገር ድንቅ ነገርን መፍጠር እንደምችል አስታውሺ፡፡ ስለዚህ በትርምሱ መካከል የምሰራውን ሥራ የሚመለከት ሰው ሁሉ ታማኝነቴን ይመሰክራል፡፡" ማዘር ኤሊሻ ከጌታ የተቀበለችው መልዕክት እዚህ ላይ ያበቃል፡፡

ተመሳሳይ መልዕክት የተቀበለ አንድ ወጣት አለ፡፡ ይህ ወጣት ወደ እኛ እንዲመጣ ጋብቻው ሁሉ ነገሩን እርግፍ አድርጎ ትቶ ከእኛ ጋር የተቀላቀለና እጅግ የሚደንቅ ሥራ እየሰራ ያለ ልጅ ነው፡፡ ጌታም በዚህ ወጣት በኩል እየተናገረን ነው፡፡ ጊዜ ካለ የእርሱን መልዕክት ደግሞ በሌላ ጊዜ አካፍላችኋለሁ፡፡

አሁን ግን የምላችሁ እባካችሁ ፀልዩ፡፡ በራዕይ መፅሐፍ እሳት ከሰማይ እንደሚወድቅ ልታውቁ ይገባል፡፡ ይህም ደግሞ አሁን ሊጀምር ነው፡፡ እንዳውም በአንዳንድ ቦታዎች መውደቅ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን እንደዚህ አይነት ዜና ከመገናኛ ብዙሃን አታገኙም፡፡ እስካሁን ብዙ አልወደቀም ነገር ግን ከአሁን ወዲያ እየጨመረና እየፈጠነ ሊመጣ ነው፡፡ ስለዚህ በቤታችሁ ሆናችሁ ፀልዩ፡፡ የንስሐ ህይወት ይኑራችሁ፡፡ የህይወት አቅጣጫችሁን አስተካክሉ፡፡

ዛሬ የጌታ ራት ቀን ነው፡፡ ለማንበብ ሬማ የተሰጠን ቃል ሁሉም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የሚናገሩ ናቸው፡፡ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ንስሐ ግቡ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ የሚል ነው፡፡

ኸርት ድዌለርስ ሁላችሁንመ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡ እስካሁን እኛንና መጠለያውን እየተከባከባችሁን ስላላችሁ እናመሰግናለን፡፡ በዚህ አንዳንድ መልካም ነገሮች እየተከናወኑ ናቸው፡፡ ወደፊት እነዚህን አካፍላችኋለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ለአሁን ግን ጌታ ፊቱን ያብራላችሁ፣ በክንዱ ደግፎ አቅርቦ ይያዛችሁ፣ ሰላሙን ይስጣችሁ፡፡ ደግሞም ለሚመጣው ነገር ልባችሁን አዘጋጁ፡፡ ይህም በእርሻው ላይ ተሰማርታችሁ ለተራቡት ፣ለተጠሙት፣ ለተጎዱትና አስተዋሽ ላጡት ተነስታችሁ እንድትሰሩ ነው፡፡

ሌላ ልነግራችሁ የምፈልገው ማይክ ፍሮም አራውንድ ዘ ወርልድ የሚለውን በሚቀጥለው አድራሻ ልታገኙት ትችላላችሁ፡፡ Mike from around the world - https://soundcloud.com/council1arch.

**የፍርስራሾች ደመና - ሜይ 19 ቀን 2020 ዓ.ም**

**Debris from the sky, May 19, 2020**

ውድ ቤተሰቦች ጌታ ይባርካችሁ እንዲሁም ይጠብቃችሁ፡፡ ቻነናላችንና ምሽጋችንን በደግነታችሁ ስለደገፋችሁ ለማመስገን እፈልጋለሁ። እኛ በየዕለቱ አንዳችን ከአንዳችን ብዙ ነገሮችን እየተማርን እንገኛለን፡፡ እናም ለማመን በሚከብድ መጠን እጅግ አፍቃሪና ደጋፊ በሆኑ ሰዎች ተባርከናል። ብዙዎችም በአገልግሎታቸው ወደፊት እየተጓዙ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዩኒቨርሲቲ በተጀመረ ቀን ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ ወደ እኛ የመጣው ወጣት ይገኝበታል፡፡ ይህም ወጣት በሕብረተሰቡ ውስጥ ቃል በመግባት የራሱን አገልግሎት  በመጀመር ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማበብ መጀመር ነው።  እኛ ጌታ እዚህ እያደረገ ባለው ነገር እጅግ ተደስተናል፡፡ ለዚህ ደግሞ እናንተም ተካፋዮች ስለሆናችሁ እናመሰግናለን።

አሁን ሕዝቅኤል ያየውን ህልም ለእናንተ ለማካፈል እፈልጋለሁ ፡፡ ከመጀመሬ በፊት ከሰማይ የሚወረወሩት የእሳት ኳሶች የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ከፍርስራሹ ደመና በፊት መጀመሪያ መሆኑን መናገር እፈልጋለሁ። የሥነ ከዋክብት ተመራማሪዎች (astronomers) የመጀመሪያዎቹን ደረጃዎች በመመልከት ይህ ደመና በምድር ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለማስላት አሁንም እየሞከሩ ነው። እነርሱ እንደሚሉት ከባዱ ተጽዕኖ የሚጀምረው ከ 30 እስከ 60 ቀናት በኋላ ነው፡፡  ስለዚህም ይህ የሚሆነው ከሰኔና ከሐምሌ በኋላ ይመስለኛል፡፡ እስካሁን በምድር ላይ ካረፉት ጥቂት የእሳት ኳሶች በመነሳት በፊት ከተጠበቀው በላይ ትንሽ ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን ከአሁን በኋላ የሚሆነው ነገር እጅግ ሰፊ ስለሚሆን ምን እንደሚያስከትል  አናውቅም።

ነገር ግን ሕዝቅኤል ስለዚህ ጉዳይ ከመንፈስ ቅዱስ መልዕክት ተቀብሏል፡፡ በህልሙም ከተራራው በታች በታኦስ ውስጥ የሚያገለግላቸውን ነፍሶች በመፈለግ ላይ ነበር፡፡ እነዚህም ነፍሶች በደቡብ በኩል በከተማይቱ መጨረሻ በሚገኝ ክሊኒክ ውጭ ተሰልፈው ነበር፡፡ እናም ደግሞ ሰዎች በየቦታው መንገዱን ሞልተውት ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች አብዛኞዎቹ ግራ የተጋቡ፣ ምን እየሆነ እንዳለና ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የማያውቁ ነበሩ፡፡ ከተለመደው በላይ በመንገዱ ላይ የሚጓዙና ወደ ክሊኒኩ ለመግባት  ተሰልፈው ተራ የሚጠብቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከመጠለያው  የመጣን አንዳንዶቻችን ደግሞ ምግብ በመስጠትና  ልዩ ልዩ መገልገያዎችን ለተለያዩ የከተማው ክፍሎች በማሰራጨት እየረዳን ነበር ።

በተጨማሪም ሕዝቅኤል የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያውን ጎብኝቶ በማንኛውም መልኩ ሊረዳቸው የሚችለው ነገር ካለ ሲጠይቃቸው በፍጥነት ተቀበሉትና የእሳት አደጋ ሰራተኞች የሚለብሱትን ጃኬትና ቦቲ ጫማ ሰጡት፡፡ ነገር ግን ልብሱ ምንም ምቾት አልሰጠውም ነበር። ሕዝቅኤልና የእሳት አደጋ ሰራተኞቹም በእሳት አደጋ መኪናው ወደ ታኦስ ሰሜናዊ ዳርቻ ሄዱ፡፡ በመንገዳቸውም ላይ ሊያቃልሉት የማይችሉት ከባድ ሁኔታ ገጠማቸው፡፡ አብረውት የነበሩትም ሰዎች እየተፈጠረ ያለው ነገር ምን እንደሆነ አልገባቸውም ነበር፡፡ የመንገዱ ጉዳት ሲታይ፣ የተቃጠሉት ቤቶች ሁኔታ እንዲሁም አጠቃላይ

የጥፋቱ ሁኔታ ሁሉ የወደቁት የእሳት ኳሶች በከባድ ሁኔታ መዝነባቸውን ግልጽ አድርጎታል። ታኦስ በጭራሽ እንደድሮዋ አልነበረችም ፡፡

ህዝቂኤልም ከእሳት አደጋ መኪናው በመውጣት አገልግሎት ከሚፈልጉት ሰዎች ጋር መሆን እንዳለበት ስለተገነዘበ ከመኪናው ወረደ። ሰዎች በክሊኒኩ በር ላይ በሰልፍ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ሁለት ጊዜ በኮቪድ የሞቱ ሰዎች አስከሬን ወደ አምቡላንስ ሲያስገቡ አዩ፡፡ በዚህም ምክንያት አካባቢው ሁሉ በተስፋ መቁረጥና ግራ በመጋባት ድባብ ተሞላ፡፡ ሕዝቅኤልም በመንገድ ላይ የነበሩ ከጠፉና ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ከማያውቁ፣ እግዚአብሔር ምን እያደረገ እንደሆነና ለምን ይህን ሁሉ እንደፈቀደ ፍንጭ ከሌላቸው ብዙ ሰዎች ጋር አብሮ በመሆን ሲያፅናናቸው ነበር። ህልሙ እዚህ ላይ ያበቃል፡፡

የተወደዳችሁ ጌታ በንጥቀት እኛን ለመውሰድ ከመምጣቱ በፊት የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ/Revival/ የሚኖረን ከሆነ፣ ሰዎች "እግዚአብሔር ለምንድን ነው ይህንን እያደረገብን ያለው?" የሚል ጥያቄ ጠይቀው መልስ ለማግኘት ይራቡ ዘንድ እኛ ከምቾቶቻችን መውጣት አለብን። በዘመኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተሰራፋው የሊብራሎች አጀንዳ ትክክል እና ስህተት የቱ እንደሆነ የማይለዩ በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሶችን አፍርቷል። በተለምዶ ተቀባይነት ያለው የሥነ ምግባር ጉድለት መለኪያ እግዚአብሔር ለምን እንደሚቀጣቸው እንኳን ለማወቅ ግራ አጋብቷቸዋል። እናም እንዲህ ይላሉ 'እኛ ጥሩ ሰዎች ነን፣ ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፣ አሥራትም እናወጣለን፡፡ ይህ በእኛ ላይ የሆነው ለምንድን ነው?'፡፡ እግዚአብሔር ሆይ በአገልግሎታችን ኃጢያትን ኃጢያት ብለን ካልጠራን፣ ነገር ግን ሕዝቡን ለማስደሰትና ከእነርሱ የምንፈልገውን ገንዘብ ለመቀበል ብቻ አገልግለን ከሆነ እባክህ እርዳን፡፡

ክሌር ፦ ጌታ ሆይ የምትነግረን ነገር አለ?

ኢየሱስም እንዲህ አለ "የተወደዳችሁ ኽረት ድዌለርስ፣ የልቤ ሰዎች ይህ እየተፈቀደ ያለው ነገር "ሁሉም እንደተለመደው ይቀጥላል" የሚሉትን ሰዎች ወደ ውስጥ ሰብሮ ለመግባት ነው፡፡ ከሰማያት ከተለቀቁት ከእነዚህ ከእያንዳንዳቸው ምልክቶች እንኳን ነገሮች በፍፁም ልክ አይደሉም፡፡ እኛ እየሞከርን ያለነው ህሊና ያጡ ሰዎች ከክርስቲያኒያዊ ስነ ምግባር ይልቅ የተማሩትን የአሜሪካን ባህላዊ ስነ ምግባር በማስቀደማቸው የእነርሱን ትኩረት ለመሳብ ነው። ሰዎች ባህላቸውን ሃይማኖት አድርገውታል።

"በአሁን ጊዜ በዓለም ዙሪያ እየተከናወነ ያለው ነገር ምድር በቆሻሻና በኃጢያት ውስጥ እንድትዋኝ የተደረገችበት የላላ የሥነ ምግባር ውጤት ነው፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በሰማይ ያለው አባቴ እየሆነ ያለውን ነገር ካልፈቀደ፣ ትዕይንተ አለሙ ራሱ/ the cosmos/ ሁከት ያስከትላል፡፡ ይህም ሥነ ምግባር የጎደላቸው ሰዎች መንገድ እጅግ መጥፎ መሆኑን ያሳያል፡፡

"ህዝቤ ሆይ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር መቼም አትጠራጠሩ ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ለምን መከናወን እንዳለባቸው ባትረዱም እንዲሆኑ መፈቀዳቸው ግን ለላቀ ዓላማ እንደሆነ አትጠራጠሩ። ከንጥቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንደሚኖር ነግሬያችኋለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁበት ምክንያት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችሁን ትታችሁ ከእርሻው ቦታ መከርን ለመሰብሰብ የተሻለ ጊዜ እንድትሰጡ ስለምፈልግ ነው።

“የተለመዱ የዕለት ተዕለት ተግባሮች ሲታገዱ ወንድምና እህቶቻችሁን ስለ እኔ ታላቅ ፍቅር ለመንገር ብዙ ጊዜ ታገኛላችሁ፡፡ ለዚህ ዝግጁ ናችሁ? በሕይወታችሁ ውስጥ የሚገኙ ነገር ግን መንግሥቴን ወደ ምድር ከማምጣትና ነፍሶችን ከማዳን ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ብዙ ነገሮችን ትተዋላችሁ? እያንዳንዳችሁ ልባችሁን እንድትመረምሩና መንፈስ ቅዱስ በፊታችሁ የሚያስቀምጣቸውን ዕድሎች ለማየት እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ጠይቁ፡፡ ነገሮች እየተጋጋሉ ሲሄዱ እነዚህም በብዛት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

“አሁን ሂዱና የኔን ጥያቄዎች በማሰላሰል በእያንዳንዱ ጊዜ ፍቅሬን ለነፍሶች ለማካፈል እድሉን እንድታገኙ በፀሎት አቅርቡ። ወደ ውጪ ስትወጡ “ጌታ ዛሬ የአንድን ሰው ህይወት ማሻሻል እንድችል እርዳኝ” በማለት ፀልያችሁ ውጡ። ይህ ደግሞ በእርግጥ የምፈፅመው ጥያቄ ነው፡፡ በመንግሥተ ሰማይ የትኛው ዘላለማዊ ሽልማት እንደሚያስገኝና የትኛው ፍፁም ሥጋዊና ዋጋ ቢስ እንደሆነ መለየት በሚያስችላችሁ በረከት አሁን ባረኳችሁ፡፡

“የምወዳችሁ ይህንን እውቀት ተግባርያዊ አድርጉት፡፡ ነገር ግን የአባታቸውን ቃል ሰምተው በመከር ወቅት ለመሰብሰብ ወደ እርሻው እንደማይወጡት አትሁኑ፡፡ እነርሱ “አዎ” ይላሉ ነገር ግን አይሄዱም፡፡ እናንተ ግን እንደዚህ መሆን የለባችሁም፡፡ ልባችሁን አዘጋጁ፣ ለነፍሶች ጊዜ ስጡ፣ ቅዱሳን መፅሐፍትን አጥኑ፡፡ ደግሞም ከእኔ ጋር ብዙ ጊዜ አሳልፉ፣ በፍቅሬ ለመሞላት ፍቀዱ፡፡ ይህንን ስታደርጉ ከእኔ የተካፈላችሁትን በሌሎች ላይ ማፍሰስ ትችላላችሁ።”

## ጥፋት እየመጣ ስለሆነ ጩኹ ንስሐም ግቡ - ስፕቴምበር 12 ቀን 2020 ዓ.ም
## Cry out devastation is coming, September 12, 2020

የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ በአሜሪካና በአለም ላይ እየመጣ ያለው ስቃይ እጅግ ከባድ ስለሆነ ጌታ ልባችሁን ያዘጋጅ፡፡ ዛሬ ጠዋቱን ሙሉ ስሰማው ያረፈድኩት የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ በሙሉ ድምፃችሁ አሰሙ፣ በመካከላችሁ የሚገኘውን ኃጢያት ሃቁን አትደብቁ፣ በሰዎች ስለሚደረገው ኃጢያት በግልፅ ተናገሩ !!! የሚለውን መዝሙር ነበር፡፡

በጌታ ፊት ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ተቀምጬ እያለሁ ትልቅ ጥቅልል ጥቁር ደመና፣ ወደ ውስጥ እየጠረገና ብዙ ቦታዎችን እየሸፈነ ከሰሜን ክፍል ሲመጣ አየሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ. . . "ከባድ ጊዜ እየመጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝቤ እስካሁን ጣኦት ከሆነበት ከተደላቀቀና ግዴለሽ ከሆነ የአኗኗር ዘይቤው ንስሐ አልገባም፡፡ ይህንን የአኗኗር ዘይቤ በቀላሉ የሜሪካኖች ጣዖተ አምልኮ ማለት ይቻላል፡፡ የሚማሩትም ጣዖት የሆነባቸውን ይህንን የአኗኗር ዘይቤ ለማግኘት ነው፡፡

"እያልኩ ያለሁት ከስግብግብነት፣ ከንፉግነት፣ ከማህበራዊ ሁኔታና ከፍትህ አልባነት የመነጨና በእውነት ላይ ያልተመረኮዘ የአኗኗር ዘይቤ በአመለካከቱ ላይ ተቀምጧል፡፡ ፕሬዜዳንታችሁ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እጅግ እየለፋ እያለ ዛፎቹን ብቻ በመመልከት ጫካውን ረስቷል፡፡ ይኸውም እድሜውን ሙሉ ስለ ህይወት የእሴት ደንብ ያለው ግንዛቤ በቢዝነስ ስኬታማ መሆን እና የተንደላቀቀ የአኗኗር ዘይቤ መከተል በሚለው ላይ ነው፡፡

"አንዳንድ የሞራል ልኮች ቢኖሩትም በማመቻመች ብዙ ነገሮችን አጥቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ ህሊናው በትክክለ አልተቀረፀም፡፡ ኃብት ስላካበቱ ብቻ መልካም ኑሮ አይኖርም፡፡ እንዳውም ብዙ ጊዜ መልካም ኑሮ የሚኖሩት ያላቸው ሳይሆኑ ድሆቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ህሊናቸው የሚከሳቸው ምንም ነገር ስለሌለ ነው፡፡ ሃብታሞቹ ግን ሌሊት በመነሳት ኃብታቸውን እንዴት አድርገው እንደሚያከማቹ ሲያቅዱ እንቅልፍ በማጣት ያድራሉ፡፡ ነገር ግን አንዳንደ ኃብታሞች ትክክለኛው የህይወት የእሴት ደንብ አላቸው፡፡

(ከሌር)፡- የተወደዳችሁ ኽርት ዱዌለርስ እዚህጋ እንድታውቁት የምፈልገው አንድ ነገር በምንም አይነት መልኩ ፕሬዚዳንት ዶላንድ ትራንፐ ካለን አመለካከት እንድንቀንስበት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እላይ ከተጠቀሰው፣ ነገር ግን ለእርሱ ከተሸፈነበት ከዚህ ነገር ውጪ ድንቅ ሰውና ለአገራችን ትክክለኛ ራዕይ ያለው ሰው ሲሆን ይህንን አገር ከብዙ ጥልቅ ችግሮች እያወጣ ያለ እጅግ ትልቅ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ለአገራችን ትልቅ ግርዘት ሊሆን ነው፡፡ ይህም ፕሬዚዳንታችንን የሚመለከት ሳይሆን ኃላፊነት ያለብንን እኛን በግል የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ሰው መልካም እንደሆነና ድንቅ ሥራ እየሰራ እንደሆነ፣ ነገር ግን ለእርሱ ያልታየው አንድ ነጥብ እንዳለ ይህንን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡

ጌታ እየተናገረ ወዳለው እንመለስ፡፡ ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ. . . " መልካም የሆኑት የዚህ አገር ባለፀጎች የተሰጣቸውን ለአለም የማካፈል ኃላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤው አላቸው፡፡ አዎን ያልኩት  በትክክል "የተሰጣቸውን" ነው፡፡ አንዳንዶች ሰርተን ያገኘነው ነው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን ለሌሎች ያልተሰጠ አጋጣሚና ተሰጥዎ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህም ለእነርሱ የማሰብ ችሎታ፣ ዕድልና የገቢ ምንጭ በማቅረብ እንዴት መልካም እንደሆንኩ ይገነዘቡ ይሆናል በማለት እየጠበኩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ለመረዳትና የገሃነም ቅጣት በራሳቸውና በዘራቸው ላይ ሳይመጣ ስጦታዎቹን ለመጠቀም ትልቅ የሞራልና የባህርይ ፅናት ይፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር አንዳንዶች ኃብታቸውን ለመንግስቱ የሚያውሉ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ለጥፋታቸው እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ዝም ብለው የሚያካብቱ አሉ፡፡

"ሃብታም መሆን ትልቅ ታማኝነትን ይጠይቃል፡፡ ኃብትን በአግባቡ መጠቀም ፀጋ ነው፡፡ ማንም ሰው ሰርቶ ገንዘብ ማግኘትና ያሰበውን እየገዛ ሊያጠፋ ይችላል፡፡ ነገር ግን የቅርብ ጎረቤቱን ወይም ራቅ ያለ ቦታ የሚኖርን ሰው ለመርዳት እጅግ ሃቀኛ መሆንን ይጠይቃል፡፡ በሌላ አባባል የማያውቃቸውንና ከእነርሱ ምንም የሚጠብቀው ነገር ሳይኖረው የሚያደርገውን ማለት ነው፡፡ የተወደዳችሁ ጌታ የሚናገረው ስለ እነዚህ ነው፡፡

"ሰውን ማዕከል ያደረገው የአለም አስተሳሰብ /Secular Humanism/ የሰይጣን ፍልስፍና ሌላው ስሙ ሲሆን የአለም የሞራል ደንብ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም እናንተ ገንዘብ ለማካበት ስትሯሯጡ የዲያቢሎስ ወኪሎች የራሳቸውን የህይወት ዘይቤ አሾልከው በማስገባት የሰውን ልጅ መርዳት በሚል የውሸት ሽፋን የክርስቲያኑን የህይወት ዘይቤ እንዲተካ አድርገዋል፡፡ የሰይጣን ቤተክርስቲያንን መሰረታዊ የእምነት መመሪያ ስትመለከቱ ሰውን ማዕከል ካደረገው የአለም አስተሳሰብ /Secular Humanism/ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይና ግንኙነት ያለው ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ አሁን በመሪነት፣ ወይንም ገና ወደ መሪነት እየመጡ ላሉ መሪዎች ዘመናዊው የእሴት ደንብ ሆኗል፡፡ ይህ አልገባችሁም? እነዚህ ሰዎች አለምን ለመግዛት ከሌሎች እጅ መውሰዳቸውን መልካም እንዳደረጉ አድርገው ነው የሚያምኑት፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን የሚመለከቱት እንደ አዳኝ አድርገው ነው፡፡ ይኸውም እነርሱ የተወለዱት የፍጥረትን ህግጋትና ጤናማውን ህሊና በመቆጣጠርና በማንቀሳቀስ እንዲሁም ግዙፍና አስቀያሚ ፍጥረታትን በላቦራቶሪ በመፍጠር አለምን ማስተካከል ነው፡፡ በተጓዳኝ ደግሞ የክርስቲያኖችን እውነት በማንቋሸሽ፣ የእነርሱን አስበልጦ ለሁሉም በማስተማርና አሹልኮ በማስገባት በህዝቡ ውስጥ ማስረፅ ነው፡፡ ይህ

ደግሞ በውጪ ሲመለከቱት ምንም ችግር የሌለበት ይመስላል፡፡ እውነቱ ግን በውጪ ታጥቦ ነጭ የሚመስል ነገር ግን አለምንና በውስጧ ያለውን ለማጥፋት የተዘጋጀውን የሰይጣንን ሥራ ለመሸፈን የተደረገ ድርጊት ነው፡፡ በዚህ ላይ እኔ የምለው ነገር እነዚህ ሰዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ አያውቁትም ነው፡፡ በእውነት ለአለም መልካም እየሰሩ ይመስላቸዋል? በስህተት እየተመሩና እየተታለሉ እንደሆነ በፍፁም ማየት አልቻሉም፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . . እነርሱ የሚያምኑት ከሁሉ ዘር የበላይ እንደሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ውጪ አለምን ለማስተካከልና ለመቆጣጠር ልዩ መብት እንዳላቸው ነው፡፡ በእርግጥ ከሆነ እነርሱ ራሳቸውን የሚያዩት በምድር ላይ ለሚገኝ የሰው ዘር ሐሳብን ለማስፋፊት ኃላፊነት ያለባቸው አማልክት አድርገው ነው፡፡

"በአሜሪካ ያላችሁ ህዝቦቼ! አንዳንዶቻችሁ ባገኛችሁት ገንዘብ የሚያበረታታ ነገር አድርጋችኋል፡፡ ሌሎቻችሁ ግን ለሚያሳፈር፣ ለስስትና ሃብት ለማጋበስ ንግስናን በመስጠት የገሃነምን ህመም  ለራሳቸው አከማችተዋል፡፡ ክሌር እያልኩ ያለሁት ፕሬዚዳንታችሁ ህሊናው በትክክሉ መንገድ ያልተቀረፀ እጅግ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ በእርግጥ ነው የፕሬዚዳንትነቱን ቢሮ ከያዘ ጀምሮ እየተሻሻለ ይገኛል፡፡ ቢሆንም ግን አሁንም ፍትህን የሚያዛቡ ሁኔታዎች ምሽግ እንደያዙ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እርሱ የድሆች አባት ስላልሆነ ነው፡፡ አገራችሁ በሞራል ጉዳዮች ላይ ትልቅ ስጦታ ያለውን ሰው መርጣለች፡፡ ነገር ግን እውነተኛ የህይወት እሴቶችን በጠለቀ መልኩ እና እስካሁን በማያውቀው ሁኔታ መማር አለበት፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ከእርሱ ጋር ስለሆንኩ ይማራል፡፡ እርሱ ለስኬታማ አሜሪካዊ ሞዴል ለመሆን ተመራጭ ሰው ነው፡፡ ለዚህ ነው ለእርሱና ለአሜሪካ እውነተኛ ትህትና የሚያስፈልገው፡፡ እርሱ የአሜሪካን ህልም እየኖርን ነው ብለው ለሚሰማቸው ለብዙዎች የስኬት መስታወት ነው፡፡ ነገር ግን በቅርብ ሲነቁ ይህ የሚያስቡት የአሜሪካ ቅዠት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡

"በአለም ላይ ላላችሁት ህዝቤ ሁሉ በተለይም ደግሞ በአሜሪካ ላለችሁት የምመኘው ነገር እጅግ በተትረፈረፈ ኃብት ውስጥ ኖራችሁ ያላከፈላችሁ ንስሐ እንድትገቡና የማካፈል ህይወት ምን እንደሆነ እንድትማሩ ነው፡፡ ወላጆቻችሁ ራሳቸውን ብቻ እያገለገሉ በመኖራቸውና ይህንንም የህይወት ዘይቤ ለእናንተ እንደ ምሳሌ ስለተዉላችሁ መልካምና ክፉ የቱ እንደሆነ ተገለባብጦባችኋል፡፡ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የህይወት ጥሪያቸውን ይኸውም እኔን ማስቀደምና ለድሆች ማካፈልን ረስተዋል፡፡

"ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች እጅግ ብዙ ኃብትን ሲያግበሰብሱ በአንፃሩ ደግሞ በአለም ላይ ያሉ ድሆች ፍትህ በማጣት ወደ ሰማያት የጮኹትን ጩኸት እኔ የእናንተ አምላክ ሰምቼዋለሁ፡፡ በሰማያት ያለው የፍትህ ምክር ቤት የተጠራቀመውን አቤቱታና የተሰራውን መልካም ሥራ መዝኖ አይቷል፡፡ በዚህም አንፃር በአሜሪካ መሰረታዊ የሆነ ችግር ተገኝቷል፡፡ ይህም ከኢኮኖሚው ማንሰራራቱ ጋር ምንም የሚያያይዘው ነገር የለም፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ በአንድ በኩል በቢሮ ለመቆየት በማሰብ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ የሚያስችል መመሪያ አውጥቷል፡፡

"ነገር ግን እኔ አሁንም የማየው በዚህ አገር ያለውን ስግብግብነት፣ አሰቃቂ የሆነውን የአኗኗር ዘይቤ ለመኖር ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት፣ በአንፃሩ ደግሞ ድሆች በመበዝበዛቸው ወደ ሰማያት የጩኹትን ጩኸት ነው፡፡ ይህ ፕሬዜዳንት ብዙ መልካም ነገሮችን አከናውኗል፡፡ ነገር ግን ስለ ገንዘብ ያለው መሰረታዊ አመለካከት የተጣመመ ስለሆነ እኔ ስለ ገንዘብ ያለኝ ደረጃ ከሚታየው የገንዘብ ደረጃ ጋር ተቃራኒ እንደሆነ መገንዘብ አይችልም፡፡ ይህንን ኃጢያት በአጠቃላይ ህዝቡም ሊገነዘበው አይችልም፡፡ ይህም ኃጢያት በዚህ አገር ላይ በተለይ መልኩ ለሚመጣው ቅጣት በር ከፋች ሆኗል፡፡

"አሜሪካ ተነሱ! ተነሱ! ፍርድ በእናንተ ላይ ሊሆን ደርሷል፡፡ ከአሁን ወዲያ በመካከላችሁና በአለም ያለውን የድሆችን ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት አትችሉም፡፡ ከአሁን ወዲያ በምድር ላይ ለራሳችሁ ብዙ ኃብት ልታጠራቅሙ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ከልባችሁ ምት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተቃጥሎ ያልቃልና ነው፡፡ የኔን ጥበቃ ከፈለጋችሁ በእኔ ደንብ መኖር ብቻ ሳይሆን ለአገራት አባት መሆን አለባችሁ፡፡ ይህም ፍትህንና እኩልነትን በማምጣት የድሆችን ብዝበዛ እንዲቆም ማድረግ አለባችሁ፡፡

"በተጨማሪም እነዚህ ነገሮች በአገራችሁ ህጋዊ መሆን የለባቸውም፡-

1. የዘር እህሎች በተፈጥሮ ተመልሰው መራባት የሚችሉበትን ከውስጣቸው በማጥፋት ከድሆች ላይ መስረቅን፡፡ እኔ ዘሮች ሁሉ በራሳቸው እንዲባዙና እንዲያድጉ አላደረኩምን? ታዲያ ለምንድነው ይህንን አስፈላጊ ስጦታ ከደሃው ላይ የሰረቃችሁት? በድሆች ላይ ካቅማቸው በላይ ህይወት እንዲከብድባቸው ለፈፀማችሁት ለዚህና ለሌሎች ወንጀሎች ሁሉ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡

2. ወንዶችና ሴቶችን አዋርዶ እንደ እንሰሳት የሚያደርገውን የወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችንና ፊልሞችን /pornography/ በህግ መፈቀድ የለበትም ፡፡ ይህም ለአጋንንቶች ሥፍራን በመስጠት በሰው ልጆች ላይ ሊነገር የማይችል ጥፋትን የሚያመጣና በውስጣቸው በመኖር ትልቅ ወንጀልን እንዲፈፅሙ የሚያደርጋቸው ነው፡፡ አሜሪካ! የወሲብ ድርጊቶችን በግላጭ ማየት/pornography/ የሚፈቅደው ይህ ህግ በአገራችሁ መፈቀድ የለበትም፡፡ ተነሱ! የኃጢያታችሁ ጩኸት ወደ ሰማያት ደርሶ የጥፋት መዶሻው ሊመታ ነው፡፡

3. ምንም የማያውቁ ህፃናትን በውርጃ/abortion/ እየጨረሳችሁ እንደሆነ በደንብ ታውቁታላችሁ፡፡ የዚህን ኃጢያት ውጤት ምን እንደሆነ ለማየት የኒውዮርክ ከተማን ማየት ብቻ ይበቃችኋል፡፡ ለዚህ ከተማ እኔ እስካሁን ምህረትን አድርጌያለሁ፡፡ ነገር ግን ፍትህ እየጮኸ ስለሆነ የፍትህ ሚዛኑ ወደ አንድ በኩል እያመዘነ ነው፡፡ ሚዛኑም ያጋደለው ከተማዋን በመደገፍ አይደለም፡፡

4. ለወሲብ ሰዎችን ማጓጓዝ/ Sex trafficking/ ይህንን ወንጀል ለመከላከልና በመካከላችሁ ያሉትን የወደቁ መላዕክት/alien demons/ ጦርነት በመክፈት መልካም ሥራ ሰርታችኋል፡፡ ነገር ግን ለምንድነው አንድ ላይ የተደራጁ ላቦራቶሪዎች/corporate laboratories/ ሰዎችንና እንሰሳትን እያዳቀሉ እንዲፈጥሩ፣ እንዲሁም ምንም ክፉ ትዕዛዝ ቢታዘዙ እንዲፈፅሙ የተደረጉ ነፍስ የሌላቸው ሰዎችን እንዲፈጥሩና ሊነገር የማይችል ጥፋት እንዲያመጡ ነፃነት የሰጣችኋቸው? እነዚህ ኮርፖሬሽኖች ሳይንቲስቶች ሳይሆኑ ስግብግብ ወንጀለኞች ናቸው፡፡ እኔ በዚህ ምድር ላይ ለህይወት የሚያስፈልጋቸውን፣ ደስታን እንዲያገኙና እንዲያብቡ የፈጠርኳቸውን ነፍሶች ሊጠገን በማይችል ጥፋት ያጠፉ ናቸው፡፡

5. የጥንቆላ ሥራ በአገራችሁ በፍፁም ህጋዊ መሆን የለበትም፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡ የሰይጣን አምልኮና ጥንቆላ ህጋዊ መሆን የለበትም፡፡ እነዚህ ሁለቱ፣ ሰዎች በሚስጥራዊ ጥበብ የበለጠ እንዲደሰቱ በማድረግ የሰውን ልጆችንና ምድርን የሚያጠፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ትዕዛዙን የሚቀበሉት ብቸኛው አጀንዳ ሊነገር የማይቻለውን ህመምና ሞት

ከሚያመጣው፣ ለማብዛት የተፈጠረችውን ምድርን ከሚያጠፋው፣ እንዲሁም እስትንፋስ የተሰጣቸውን ወንዶችና ሴቶችን ከሚያጠፋው ከሰይጣን ዘንድ ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮችና ሌቦች ሆነው ሳለ እናንተ ግን በሃይማኖት እኩልነት ሰበብ በመካከላችሁ እንዲሆኑ ፈቀዳችሁላቸው??? ምንም የማያውቁትን ለመስረቅ፣ ለመግደልና ለማጥፋት፣ እንዲሁም የማያልቅ ኃይል ታገኛላችሁ በሚል ውሸትና የተስፋ ቃል የሰውን ልጅ ለማበላሸት ፈቀዳችሁላቸው? አሜሪካ ይህንን በመካከላችሁ ለምን ፈቀዳችሁ? እኔ የምህረት አምላክ ስለሆንኩና የሰራሁትን ሁሉ የምወድ ስለሆነ በእናንተ ላይ ያለውን ኃጢያት ለመንብኘት አልመጣሁም፡፡ ነገር ግን እናንተ የሰይጣንን እና የጥንቆላን አምልኮ እንዲቀጥል ስለፈቀዳችሁ ይህ ጥፋት እንዲመጣ ችላ ብላችኋል፡፡ ለመሆኑ በአደገኛ ሱስ የተያዘ ወጣት እንዲሁም ህፃናት የሚደርስባቸው ወሲባዊ የሞራል ውድቀት ከጥንቆላ ጋር ያለውን ግንኙነት አታስተውሉምን? ለዚህ ከፉ ጉዳይ መፍትሔ ስላልፈለጋችሁ በራሳችሁ ላይ ይህንን እንዳመጣ አይታያችሁምን?

6. ወሲብና ብጥብጥ በፊልሙ ኢንዱስትሪ፡- አሜሪካ! ለመሆኑ ህሊናችሁ የት ነው የተቀበረው? በታረዱት ሰውነት በታች? እነዚህ የተገደሉት እኮ ምንም የማያውቁ፣ መልካም ነገር እንዳለ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው የተደረጉና ለከፉ ምሳሌ ለመሆን አይምሯቸው በፕሮግራም እንዲቀረፅ የተደረጉ ናቸው፡፡ ለእንደዚህ አይነቱ አፀያፊ መዝናኛ አይኖቻችሁን ስትጨፍኑ ልጆቻችሁ ዘማዊ ጉዳዮች ለመሆን እየተቀረፁ እንደሆነ አታውቁም? ታዳጊዎች በቪዲዮ ጨዋታና በፊልም ደም ለማፍሰስ እንዲጠሙ፣ መልካምና ምንም የማያውቁትን ለመግደል እየሰለጠኑ እንደሆነ አታውቁምን??? እንዴት ነው ይህንን ብልሹ ሁኔታን በመፍቀድ እውቀት ያጣችሁትና የሚቀጥለውን ትውልድ ገዳይና ደፋሪ አድርጋችሁ የምታሳድጉት?? ለዚህም መልሱ ስስትና ለገንዘብ መስገብገብ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ይሸጡና ለሰው ልጆች ጠላት ለሆኑት ለጭራቆች ገንዘብ ያስገኛሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ከእናንተ እውቀት ውጪ በራሳችሁ ጣራ ሥር እነዚህ ነገሮች እየተካሄዱ ናቸው፡፡

7. የፆታ ግራ መጋባት፡- ይህ ትምህርት እየተካሄደ ያለው የሞራል ባሕርይን ለመፋቅና የሰውን ዘር ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ነው፡፡ እንዲሁም ምንም የተሻለ እውቀት የሌላቸውን የልጆችን ህሊና ለማበላሸት ነው፡፡ እናንተ ይህንን ፈቀዳችሁ??? አሜሪካ የት ናችሁ??? የት ናችሁ??? ለህይወት ዘይቤያችሁ/Life style/ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ተጨማሪ ሥራ ስትሰሩ ልጆቻችሁ ግን እንዴት ሰውን እንደሚያሰቃዩ፣ እንደሚደፍሩና እንደሚገድሉ እናንተ በከፈላችሁት የቪዲዮ ጨዋታዎች እየተማሩ ነው፡፡ በዚያም የቤተሰብን እሴቶች በማጥፋት ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን እየተማሩ ነው፡፡ የት ናችሁ?

8. ሌሎች ብዙ ፍትህ ያጡ ጉዳዮች ቢኖሩም ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ጎልተው ከወጡት ጥቂቶቹ ናቸው፡- ሌሎች አገራትን በወታደር፣ ሽብርና ረብሻን በማስነሳት መቆጣጠር፣ በትክክለኛው መንገድ የተመረጠውን መንግስት እንዲወርድ በማድረግ፣ አካባቢ የሚበክሉና የሚያጠፉ፤ እንዲሁም የሰው ልጆችን ህይወት የሚጎዱ ሙከራዎች በመሞከር ሊቆጠር የማይችል ኃዘን በሰው ልጆች መካከል እንዲሁም በራሳቸው ህዝብ ላይ አምጥታችኋል፡፡ እንዲሁም የአሜሪካን ህይወት በመካድ በዙሪያችሁ ስለ ተፈፀመው ኃጢያትና በዚህም ምክንያት በህዝቡ ላይ ስለተፈጠረው ኃዘን ግድ የለሾች መሆናችሁ ነው፡፡

አሜሪካ ኃጢያታችሁ! ኃጢያታችሁ! ኃጢያታችሁ! ለፍትህ ወደ ሰማያት ጮኹ፡፡ ከተኛችሁበት ንቁ፣ ህይወታችሁን መርምሩና ንስሐ ግቡ፡፡ በእናንተ ላይ የፍርዱ ሰዓት ተቃርቧልና!!!

ከአሁን ወዲያ አምላካችሁ በእናንተ ወንጀል ምክንያት በሰው ዘር ላይ የሚፈፀመውን የፍትህ መጓደል ዝም ሊል አይችልም፡፡ ከአሁን ወዲያ የሚገባችሁን ለማድረግ ዝም አንልም፡፡ ትሁት በመሆን መንገዳችሁን ፈትሹና ስለ እናንተ የቀረበው ክስ እውነት እንደሆነ መርምሩ፡፡ በመካከላችሁ ያሉትን የድሆች ጩኸት ንቃችሁ ስለ ምህረት ወደ እኔ የምትጮኹትን ጩኸት ልስማን? ፍርድ የሚመጣው ከሰሜን ሲሆን ፍርዱም በደጃችሁ ነው፡፡ በመካከላችሁ ስላለው ፍትህ ማጣትና ግፍ ንስሐ ስትገቡ፣ እንዲሁም ልዩነት በሌለው ህይወት ስትኖሩ የነበረውን ህይወት ለመለወጥ ጥረት ስታደርጉና ራሳቸውን ለመከላከል ለማችሉት ስትቆሙላቸው ፀሎታችሁን እንደምሰማ እወቁ፡፡ ቅዱሱ መንፈሴ በልባችሁ ውስጥ ብርሃንን በማብራት፣ የነፍሳችሁን ሁኔታ በእውነት እንድታውቁና በፊቴ ሙሉ ንስሐ እንድትገቡ ይረዳችኋል፡፡ በዚህም ክፉ ድርጊታችሁንና ፍትህ አልባ መሆናችሁን በማሳየት እንደገና በእውነት ላይ እንድትመሰረቱ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሁሉ ግን በፍቅር እወዳችኋለሁ፡፡ ስለምወዳችሁ እንድትነቁ እየጠበቅኋችሁ ነው፡፡ አሜሪካ ተነሱ !!!

## እንጉዳይ ቅርፅ የመሰለ ዳመና በኒዮርክ ከተማ ላይ - ዲስምበር 29 ቀን 2020 ዓ.ም.

### Musheroom cloud on New York City, Desember 29, 2020

ለአለም ማላጆች በሙሉ ጌታ ጉብዝናን፣ ጥበብንና ብርታትን ያካፍላችሁ፡፡ አሜን፡፡

ባለፈው እሁድ የጌታን ዕራት ስንወስድ እንጉዳይ ቅርፅ ያለው ኒኩላር በክፍሉ ውስጥ አየሁ፡፡ አብረውኝ ለነበሩትም ይህንን ሳሳያቸው ሁሉም በግልፅ አዩት፡፡ አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ ሲሆን ጌታ ሁላችንም እንድናይ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ፡፡ ስለዚህም ይህ ለእኛ ያልተለመደ ነገር አልነበረም፡፡

ለፀሎት በጌታ ፊት ስቀርብ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጀመረ . . . " በኒዮርክ ከተማ ይፈፀማል የተባለውና ለመፈፀም ብዙ ጊዜ የፈጀው አሁን ሊሆን ተቃርቧል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ምንም ለማያቁትና በሚሆነው ነገር ለሚጎዱት ታናናሾች ልቤ እስከ ሞት ድረስ ታሟል፡፡ ሁላችሁም ለታናናሾች እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም ወዲያው ወደ እኔ እንዲወሰዱ ነው፡፡

ጌታ በዛ ከተማ እኮ ብዙ መልካም ሰዎች አሉ ፡፡ ኢፖች ታይም እንኳን በዛ ናቸው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " መልካሞቹ ወደ ቤት ወደ እኔ ይወሰዳሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እስከ መጨረሻው ፍርድ ድረስ በምድር አፈር ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ለሁሉም ፀልዩ፡፡ ስቃይ ሊደርስባቸው እንዳለው አይነት ማንም እንዲይሰቃይ አልፈልግም፡፡ ሞት በፍጥነት እንዲወስዳቸው ፀልዩ፡፡ በራሳችሁ የባህር ኃይል ክህደት ይፈፀማል፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ እንደሰማሁት ከሆነ ይህ ሊሆን ያለው ነገር በእኛ ባህር ኃይል ላይ በፐርል ሃርቦር እንደተደረገው ጥቃት ዓይነት ነው፡፡ እናም የማምነው በፐርል ሃርቦር አየሩን ሲቆጣጠሩ የነበሩ ሰዎች ጥቃቱን እንዳይመክቱ ተነግሯቸው ነበር፡፡ ምናልባትም አሁን ሊሆን ያለውም ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . . "ክፉ ሰዎች ከክፉ አሰራራቸው ጋር፣ እንዲሁም የባህር ኃይላችሁ ክህደት ያለበት ነው።"

ጌታ ማየሚስ?

"ያም በጊዜው ይሆናል። ነገር ግን በዚህ የጊዜ ሰሌዳ አይደለም። አሁን እንደታቀደው ዋናው ኢላማ የኒዮርክ ከተማ ነው። በቀደሙት ጊዜያት ያልኩትን አስታውሳለሁ። ነገር ግን የጊዜ ሰሌዳ ማስተካከያዎች ከሁኔታዎች ጋር ይለዋወጣሉ። አባቴ የሚሰራው ነገር ሁሉ አግባብ ያለውና ትክክል ነው። ብዙ ጊዜ የቆየ ነገር አሁን ግን እየመጣ ነው። ይህም ቢሆን ግን ጊዜው እየተቃረበ ሲመጣ ልቤ ተለያይቶ ሊቀደድ ነው።

"የጊዜ ሰለዳውን ያለመጠየቅሽ ብልህነት ነው። የተሰጠው ማስጠንቀቂያው ብቻ ነው። ምክንያቱም ጊዜው የሚወሰነው ከተለያዩ ሁነቶች ጋር ተያይዞ ነው። እንዲህም ቢሆን ግን ጠላቶቻችሁ የሆኑ ከእናንተ ጋር የሚኖሩ አሉ። እነርሱ በአጋንንት እምነት ይህም በኮሚኒስት ፖለቲካ ዘይቤ አይናቸው ታውሯል። እነርሱ እምነት አልባ የሆነውን አስተዳደር በማምጣታቸው ለሰው ልጆች ውለታ እንደሰሩ ነው የሚቆጥሩት። ለእነዚህ አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ ፀልዩ፣ መንግስትን ደግሞ አስጠንቅቁ። ፓርቲውን በሚቃወሙ ከሃዲዎች ብዙ ነገር ይጠፋል። ለእነዚህም ፀልዩ። ክሌር እንደዚህ ዓይነት መጥፎ ዜና ለማምጣት የልቤ ሃሳብ አልነበረም። ነገር ግን የእንጉዳዩን ዳመና አይተሻል። ያ ደግሞ መሆኑ የማይቀር እንደሆነ የሰጠሁሽ ምልክት ነው።"

ጌታ ዋሽንግተን ዲሲስ?

"እስካሁን ገና ነው። አሁን በዚህ ጊዜ እንድትፀልዩ የምፈልገው ስለ ሁለት ነገሮች ነው። በዚህ አገር የሚኖሩ ሬድ ቻይናዎች እንዲነቁና ኮምኒዝም በእውነቱ ከሆነ እንደማይሰራ ነው። ያ በቲዎሪ ብቻ የሚሆን ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የሚሰራው ፍፁም ሰው ባለበት፣ አድልዎ የሚደረግለት ቡድን ወይም ግለሰብ በሌለበት ነው። ሰው ግን የተበላሸ በመሆኑ ከእኔ ውጪ የማይሆንና እኔ ልገዛ ካልመጣሁ ሊሆን የማይችል ነው።

"በቻይና ያላችሁ ህዝቦቼ ደግሞ ለአገራችሁና እንዲሁም በዚህ ነፃነት ባለበት አገር እንዲኖሩ ለተተከሉት እንድትፀልዩ እለምናችኋለሁ። ይህም እንዲለወጡና በዚህ ምድር እየኖሩ እስካሁን መልካም ሲያደርጉላቸው የነበሩትን ሰዎች ከውስጥ ሆነው በመነሳት እንዳያጠፏቸው ፀልዩ። ከእኔ ጋር እንዲገናኙ ፀልዩ። ይህ ነው ሁሉን ነገር ሊለውጥ የሚችለው።"

## ታይቶ የማይታወቅ ጊዜ ከፊታችን እየመጣ ነው - ጄንዋሪ 13 ቀን 2021 ዓ.ም

## The time we are entering shall be like no other, January 13, 2021

ኸርት ዱዌለርስ ጌታ ሰላሙን፣ እንዲሁም በእነዚህ ቀናት እጆቹ እየተቀሳቀሱ እንደሆነ እንድታምኑትና በእርሱ ላይ ለመደገፍ እንድትችሉ ችሎታ ይስጣችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ጌታን፣ ግርማዊነቱንና ሉአላዊነቱን ሁልጊዜ ከፊታችን እናስቀድም። ምንም ነገር እየሆነ ቢሆንም ሰላማችንን ለመጠበቅና በእርሱ ፍፁም ፈቃድ ውስጥ ለመቆየት እርሱ ለሁሉም መልስና መልካም መንገድ እንዳለው እርግጠኞች መሆን አለብን።

ጌታ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ነገር እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ይህም ቢሆን ግን መልካም መሆንህን ስለማውቅ፣ በስተመጨረሻም ከእነዚህ ነገሮች መልካም ነገር እንደምታወጣ በማወቄ ሰላሜን የማገኘውና ደህንነት የሚሰማኝ ራሴን በአንተ ልብ ላይ በማሳረፌ ብቻ ነው፡፡ እዚህጋ እንድ ተጨማሪ የምናገረው ነገር ቢኖር ምን ማመን እንዳለባችሁ ግራ ለተጋባችሁ ሰዎች ከዚህ መልዕክት መጨረሻ ላይ የታመኑና የተረጋገጡ ምንጮችን ትቸተላችኋለሁንና እነርሱን መመልከት ትችላላችሁ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ምን ልትለን ትፈልጋለህ?

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ኃይለኛ ጫጫታ በበዛበት ወቅት በተለይም አይናችሁን ከእኔ ላይ ካነሳችሁ እናንተን መምራት ቀላል አይሆንም፡፡ እነዚህ ወቅቶች የብጥብጥና የማንፃት ጊዜያቶች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ፍፁም ቀላል የሆነ ጉዳይ አይደለም፡፡ በጥንቃቄ እንድታሰቡ የምፈልገው በቅርቡ ሊሆን ላለው ንጥቀት ሰዎችን ሁሉ ወደእኔ ለመሳብ የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ ነው፡፡ በግራ መጋባት ወቅት እናንተ ብርሃንና የማትነቃነቁ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም መንገጫቀጮችና ታስበው የሚደረጉ የውሸት ክስተቶች ሰዉን ለበለጠ ግራ መጋባት በማጋለጥ ሰውን ሁሉ ከእውነት እያራቁት ይሄዳሉ፡፡

"ፕሬዜዳንት ትራንፕ እስካሁን የኔ ምርጫ እንደሆነ መቼም አውቃችኋል፡፡ ነገር ግን እርሱ እየተጋፈጠ ያለው ለሙቶ አመታት ሲካሄድ ከነበረ ብልሽት ጋር ነው፡፡ በተለይም ለክፍለ ዘመን ሲካሄድ የነበረው የመንግስታችሁ ብልሽት እርሱ የፕሬዚዳንትነቱን ቢሮ ሲረከብ በቢሮው ውስጥ የጠበቀው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም አሜሪካን መልሶ ለመገንባት የራሱንና የልጆችን ህይወት አድጋ ላይ ጥሏል፡፡ የእናንተ ፀሎት ነው ህይወቱ እንዲጠበቅና ሥራውንም እንዲያስኬድ የረዳው፡፡ በአሁን ሰአት ከህብረተሰባችሁ ብዙ ዕረከን ያላቸው ተውኔቶች ናቸው እየተወገዱ ያሉት፡፡ እየጠለቅን በሄድን ቁጥር ፍፁም የሆነው የሰይጣን የጨለማ ሥራ እየተገለጡ ይሄዳሉ፡፡

"ለዚህ ነው አንድ የተበላሸ ነገር ሲገጥማችሁ ወደታችኛው መሰረት በመሄድ ማፅዳት መጀመር ያለባችሁ፡፡ አሁን እያያችሁ ያላችሁት የዛን ምልክት ነው፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ እየተጋፈጠ ያለው እጅግ ከበረታ ክፉ ጋር ስለሆነ ከምንግዜውም በበለጠ የእናንተ ፀሎት ያስፈልገዋል፡፡ በአሁን ጊዜ ሁለት ነገሮችን ነው እያያችሁ ያላችሁት ፡፡ አንዱ የተበላሸ መንግስት ሲሆን ሌላው ደግሞ ሊካድ የማይቻለው ከቻይና ጋር የሚገጥማችሁ የኑክላር ጦርነት ስጋት ነው፡፡ ሊገባችሁ የሚያስፈልገው ይህ በአንድ ሌሊት የመጣ ጉዳይ አይደለም፡፡ ፕሬዚዳንታችሁ እያደረገ ያለው ፈቀቅ ብሎ በመቆም ጠላት ራሱን እንዲያጋለጥ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም ትክክለኛው አጋጣሚ ሲመጣ እርምጃ መውሰድ ይጀምራል፡፡ እስከዛው ግን የእናንተ ትዕግስትና ድጋፍ ፍፁም አስፈላጊ ነው፡፡

"ክሌር ቻይና አገራችሁን እንደምትወር ብዙ ራዕይና ህልም ሰጥቼሽ ነበር፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ይህ እውነት ነው ነገር ግን እንዲህ ቅርብ አልመሰለኝም ነበር፡፡ አንዳንዱን አስታውሳለሁ፡፡ ለምሳሌ በባህሩ ዳርቻ በኩል ፍሎሪዳን ሲወሩ እንዲሁም ደግሞ የደፈጣ ተዋጊዎች በደቡብ ምስራቅ ጫካ ውስጥ ተደብቀው ማየቴን አስታውሳለሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . ." ክሌር ቻይናዎቹ አዳጋች ኃይሎች ናቸው፡፡ እነርሱ አገራችሁን ለመውሰድ ለብዙ አመታት ሲያቀዱና ሲጋጁ ነበር፡፡ በተጨማሪም እንዲህ ልበላችሁ እነርሱ በመጥፎ ሁኔታ ውጤታማ ሊሆኑ ደርሰዋል፡፡

ፕሬዚዳንታችሁ ከውስጥና ከውጪ ብዙ ግርግሮች ገጥመውታል፡፡ ነገር ግን እርሱ ኀበዝና በፊት የሰራውን ኃጢያት ሁሉ የተናዘዘ፣ በሚያስፈልገው ነገር ምክር ለመቀበል በእኔ ላይ የተደገፈ የእግዚአብሔር ሰው ነው፡፡ ለእርሱ የምታደርጉለት ነገር ቢኖር በአጠገቡ ያሉ ሰዎች ምንም ይበሉ ምንም እርሱ ግን የእኔን ድምፅና ፈቃድ ጥርት ባለ መልኩ መለየት እንዲችል እንድትፀልዩለት ነው፡፡ አብረውት ካሉ ከሁሉም ሰዎች በበለጠ ይህ ችሎታ ለእርሱ ያስፈልገዋል፡፡ እርሱ የፅድቅ ምንነት ይገባዋል ነገር ግን የሌሎቹ ጋጋታ ድምፅ አንዳንዴ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን በውስጡ ያለው የመለየት ችሎታ ጥሩ ነው፡፡

"እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ በመከራ እያሳለፈ ያለው ወቅት በምድር የወደደው ነገር ነው፡፡ በአጠገቡ ምን ያህል ከዳተኞች እንደሚያጋጥመው አልተገነዘበም ነበር፡፡ ይህ አጋጣሚ የሰው ልጆችን የውስጥ ፍላጎት የገለጠ እጅግ የሚያም ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እርሱ ሰው ብቻ ስለሆነ አንዳንድ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች በጥብጠውታል፡፡ ስለዚህም በልቡ ውስጥ ያለው ቁስልም እንዲፈወስ ፀልዩለት፡፡ እንዲሁም በልቡ መራራ ተክል እንዲበቅል ፈቃዱን እንዳይሰጥ ፀልዩለት፡፡ እውነተኛ ክርስቲያን ስትሆኑ ብዙ የምትማሩት ነገር አለ፡፡ ነገሩ አንቺና ህዝቁኤል "ህፃናት በአሸዋ ሳጥን ውስጥ ከሆኑ እናቶች ጉዳት የለባቸውም፡፡" እንደምትሉት ነው፡፡ ይቅር ያለማለት ከሁሉም ህመሞች ይልቅ ለማሸነፍ የሚያስቸግር ነው፡፡ በእኔ ፀጋ ግን ማሸነፍ ይቻላል፡፡ የጥንት አባባል እንደሚል "ይቅር ያለማለት ለጠላትህ ያዘጋጀኸውን አንድ ኩባያ መርዝ አንተ ራስህ ጠጥተህ እርሱ ሳይጎዳ ነፃ ሆኖ ሲሄድ እንደማለት ነው፡፡"

"ይህንን አስታውሱ እርሱ እንደ ክርስቲያን፣ እንደ ፕሬዜዳንትና እንደ ፖለቲካኛ ሰው ገና እያደገ ነው፡፡ እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች ሁሉ ለእርሱ ገና አዲስ ናቸው፡፡ የተጎዳ ነፍስ የሚለው አመለካከት እንኳን ለእርሱ አዲስ ሐሳብ ነው፡፡ አንቺ በዚህ ዙሪያ ብዙ አስተምረሻል፡፡ በአለም ላሉት ግን ድካምና ህመም ፍርድ የሚሰጥበትና እንደ ቅጣት ተደርጎ የሚቆጠር እንጂ የበለጠ ፀጋን እንደሚያመጣ እንደ ፆም ስጦታ ተደርጎ አይቆጠርም፡፡

"ሁላችሁም እንድትረዱ የምፈልገው በግልም ይሁን በአለም የሚደንቅ ጥርመሳ እየመጣ ነው፡፡ ነገር ግን ሁላችሁንም ውድ ዋጋ ያስከፍላችኋል፡፡ መስዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ደም እስካሁንም የቤተ ክርስቲያን ዘር እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ እናም ቻይና ብዙዎች እስኪሞቱና ፍፁም እስክትሸነፍ ድረስ  ወደኋላ አትመለስም፡፡ በራሳችሁ ምድር ደም ይፈሳል፡፡ ነገር ግን ደግሞ ይህንን አስታውሱ እኔ መጥቼ በምድር ላይ ከመግዛቴ በፊት በራዕይ የተፃፈው ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡ ይህ ነው አስቀያሚው የማንፃት ሂደት፡፡ ነገሩን የሚያስፈፅሙ  ተዋንያን ሁሉ በመድረክ ላይ ናቸው፡፡ ንጥቀት ሲካሄድ ወዲያው ይጀምራል፡፡ እስከዚያው ግን  መጨረስ ያለባችሁን ለመጨረስ የምትችሉትን ያህል እንድትሰሩ እፈልጋለሁ፡፡ መልዕክቶቹን ችላ አትበይ፡፡ ህዝቤ በየቀኑ ድምፄን መስማት ያስፈልገዋል፡፡

"የኔ ውዶች እንዲገባችሁ የሚያስፈልገው መልካም አጋጣሚ የሚኖረው በችግርና በመከራ ወቅት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ደግሞ በጣም የሚያም ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ አሮጌ ልማዶችና መንገዶች ሞተው አዲስና ትኩስ የሆነው የወይን ጠጅ  መጠጫ መምጣት አለበት፡፡  ብዙ የሞቱ ሰዎች ከሙታን ሲነሱ የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ ማግኘቱና ትልቁ የማንፃት ጊዜ እንደሆነ ምስክር ይሆናሉ፡፡ ይህም ምስክርነት የተነጠቁ ሰዎች ተጠልፈው የተወሰዱት በኤሊየንስ ሳይሆን ስለ ንጥቀት የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ መሆኑን  የሚገልፅ ስለሚሆን ነው፡፡ ብዙዎችም እንደ ሰማይ ከዋክብት ይደምቃሉ፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ለራሳቸው ህይወት ዋጋ ሳይሰጡ ለእኔ ምስክር ለመሆን ብቻ ስለሚኖሩ ነው፡፡ እንዲሁም ልጆች እንደ ታላቅ የእምነት ተዋጊዎች ይነሳሉ፡፡ ለማገልገል ዕድሉን በመጠባበቅ ላይ ያሉም ተቀብተው አገልግሎት ይጀምራሉ፡፡

"በጥልቀት መልኩ መከናወን ከምትጓጉት መካከል አብዛኛዎቻችሁ ጠርምሳችሁ ትወጣላችሁ፡፡ ይህንን አለምና ያላችሁን የክብር ሥፍራ ዋጋ ሰጥታችሁ የነበራችሁ አብዛኛዎቻችሁ ደግሞ ይህንን ሐሳብ ትታችሁ የኔን ምህረት፣ ክብር በማወጅና የግል ጥያቄያችሁን በመተው፣ ለእኔና ለፈቃዴ ብቻ በመኖር የነፃ ህይወት መኖር ትጀምራላችሁ፡፡ ሌሎች ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አለምን ፈልገው ወደኋላ በመመለስ ስም አልባ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ከእኔ ይልቅ አለምን መርጠዋልና ከእኔ እየራቁ እየራቁ ይሄዳሉ፡፡ ልጆቻችሁ ከእነዚህ ውስጥ እንዳይሆኑ ፀልዩ፡፡

"ደማቅ ቀይ ሰማይ ባያችሁ ጊዜ ነፃ የምትወጡበት ወቅት መሆኑንና ልወስዳችሁ እየመጣሁ እንደሆነ ያን ጊዜ ታውቃላችሁ፡፡"

*(ክሌር)፡- ጌታ በኒው ሜክሲኮ ፀሐይ ስትጠልቅ ብዙ ጊዜ በጣም ደማቅ ቀይ ነው፡፡*

ጌታም . . . " እያልኩ ያለሁት እንደ ደም የቀላ ማለቴ ነው፡፡ እንደ ደም የቀላ ሰማይ ሆኖ አንዳንድ ቦታ ላይ የጠቆረ ነው፡፡ እንዳውም የደረቀ ጥቁር ደም የሚመስልና ወፍራም ቀይ ሰማይ ነው፡፡ ይህም እስካሁን ካያችኋቸው የፀሐይ መጥለቆች በጣም የተለየ ነው፡፡ ይህንን ባያችሁ ጊዜ እኔ በበሩ ላይ እንደሆንኩና ጥሼ ልመጣ እንደተዘጋጀሁ እወቁ፡፡ አትፍሩ ነገር ግን እኔን ለመቀበልና ወደ ቤት ለመሄድ ራሳችሁንና ልባችሁን ቀና በማድረግ ደስ ይበላችሁ፡፡ ይህ አባባል ለእናንተ የማይመች ቢሆንም ተፈፅሞ ታዩታላችሁ፡፡

"ክሌር አምነሺኝ እየፃፍሽ ስለሆነ አመሰግንሻለሁ፡፡ ልጄ እባክሽ ጠንካራ እምነት ይኑርሽ ብዙ የምነግርሽ ነገር አለ፡፡ እባክሽ እምነትሽን አጠንክሪ፡፡ እናም የኔን ባህርይ አስታውሺ፡፡ ሙሽራዬ ዳቦ ስትጠይቀኝ ድንጋይ እሰጣታለሁን? እምነትሽን አጠንክሪና ብዙ ሚስጥራትን እገልጥልሻለሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ይህንን እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

"መለስ ብለሽ የነበርሽበትን ህይወት ተመልከቺ፡፡ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ደርሰሽ የነበረበትን ጊዜና እኔ ደግሞ እንዴት እንደደረስኩልሽ አስቢ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሁልጊዜ ያንን እያስታወሱ ይኖራሉ፡፡ እና አንቺም እንደነርሱ መሆን ትፈልጊያለሽ፡፡ ስለዚህ እባክሽ ልብሽን ክፈቺና የመዳንን ብርሃንና የታማኝነቴን እውነት ተቀበዪ፡፡ በዚህ መልዕክት ላይ በማረፍ በክንዴ ላይ ለመደገፍ ተጠጊ፡፡ የልቤ ምት ያጠንክርሺ ደግሞም በረከቶቼ ያቁሙሽ፡፡ እንዲሁም ለሁላችሁ መልእክቴ ቃሌ የተሞላው የማይቻለውን በማድረግ የታሪክ ክንውኖች እንደሆነ በማስታወስ ለማይቻለው ነገር ልባችሁን ክፈቱ፡፡ እናም እየገባችሁበት ያለ ይህ ወቅት እስከዛሬ ታይቶ የማይታወቅና የማይቻል የሚባለውን ነገር በማከናወን በየዕለቱ የምትለማመዱበት ወቅት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው እኔን በብቸኝነት ለሚፈልጉና ልባቸውን ላዘጋጁ ነው፡፡

"በአለም ዙሪያ መቅሰፍቶች እየተከሰቱ ባለበት በዚህ ጊዜ፣ በህይወት ኖራችሁ የእኔ የፍቅርና የተስፋ መልዕክተኞች በመሆናችሁ በብዙ ብርታትና እምነት ወደፊት ቀጥሉ፡፡ ይህም ተስፋ ክፉ የሌለበትና ብልሽት አልባ የሆነው መንግስተ ሰማይና የዘላለም ህይወት ነው፡፡

የጌታ መልዕክት በእዚህ ላይ ያበቃል፡፡ እየፀለያችሁልን ስለሆነ፣ ደግሞም ደብዳቤ ስለምትፅፉልንና ና ኢሜል ስለምታደርጉልን አመሰግናችኋለሁ፡፡ መልዕክቶቻችሁን ሁሉ ማንበብ ባለመቻሌ ግን ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ በተጨማሪም

ስለምታደርጉልን ድጋፍ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡ ጌታ በሰላሙ ይባርካችሁ፡፡ ከዚህ በታች የፃፍኩላችሁን የታመኑ ምንጮች ማየት አትርሱ፡፡ ከእነዚህ ምንጮች ጥሩ ግንዛቤን መጨበጥ ትችላላችሁ፡፡

## የወደቁ መላዕክቶች ወደ ምድር መምጣትና መደረግ ያለበት ጥንቃቄ - ፌብርዋሪ 9 ቀን 2021 ዓ.ም
## The Name of Jesus Routes Demons, February 9, 2021

ጌታ ኢየሱስ እባክህ ፍርሃታችንን አሸንፈን የሚያስፈልገውን መረጃ ለልጆቻችን ትተን እንድንሄድ አበርታን፡፡ አሜን፡፡

ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ ጌታ በተደጋጋሚ ስለ ንጥቀት እንድናስብ እያደረገን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጥያቄዎችን የሚያመጣ ነው፡፡ አሁን ግን እየተማርኩ ያለሁት ይህንን ሐሳብ በመተው በእርሱ ላይ ማረፍን ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው ቀላል አይደለም፡፡ ነገር ግን እየተካሄደ ያለው የጌታ ጥበቃ ነው፡፡ እናም አሁን እርሱ እየጠየቀን ያለው በእርሱ ላይ እንድናርፍ ነው፡፡ ነገር ግን የንጥቀቱን ሂደት እያሰብኩ እንዲሁም ንጥቀቱ በቅርቡ የሚያስከትለውን በማሰብ ገና ብዙ መሰራት ያለበት ነገር እንዳለ በመገንዘብ፣ ብዙ መስራት እፈልጋለሁ፡፡ ጌታ ተጨማሪ ጊዜ ቢሰጠን ለሚቀሩት የሚያስፈልግ ብዙ ነገሮችን ትቼ ለመሄድ ራሴን ለሥራው አሳልፌ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ፡፡ በእውነቱ ከሆነ ጌታ ወደኋላ ለሚቀሩት ነፍሶች፣ እንዲሁም ያልዳኑ ነፍሶች በአጥፊው እሳት ወይም በአስቀያሚው ጦርነቱ እንዳይያዙ እንዲፀልይ ለህዝቄኤል ነግሮታል፡፡

ከሁሉ የሚበልጠው ግን በአሁኑ ጊዜ በአገራችን እየተካሄደ ያለው ነገር ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ስር እንደሆነ እየነገረንና ሰላሙን እየሰጠን ነው፡፡ እርሱ ጌታ ነው፣ እርሱ የአሜሪካም ጌታ ነው ደግሞም የአለም ሁሉ ጌታ ነው፡፡ ብዙ መልካምን ለውጥ ካመጣው አስተዳደር ጋር እርሱ አብሮ ነው፡፡

(ክሌር)፡- በቅርቡ ከሌላ ፕላኔቶችና ከምድር ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጡራን ወደ ምድራችን መጥተው በማረፍ ጥፋት ያስከትላሉ የሚል ወሬ ሰምቼ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥም ቆም ብዬ እንዳስብና ትንሽ እንድፈራ አድርጎኛል፡፡ በዚህም ኢየሱስ ራሴን ወደ ልቡ ጠጋ አድርጎ አጥብቆ ያዘኝ፡፡ እኔም በእርሱ ላይ ጥብቅ አልኩ፡፡ በቅርቡ ፍፁም ክፉ የሆኑ ፍጥረታት እነዚህም የወደቁ መላእክቶች (demone alien) መጥተው ምድራችን በመውረር ሽብርን እንደሚያመጡ እንዳስታውስ ተደርጌ ነበር፡፡ እነዚህ ደግሞ ሰውን የሚበሉ ፍጥረታት ናቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ በእርግጠኝነት ሰውን እንደሚበሉ አውቃለሁ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . ." ይህንን ርዕስ ከአንቺ ጋር ለመነጋገር በፍፁም አልፈልግም ነበር፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ይህ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ ድርጊት በከፍተኛ ሁኔታ በሚፈፀምበት ወቅት በአለም ላይ መደነቅንና ፍርሃትን በማምጣት አለምን ሽባ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም የአንዳንዶችን ልብ ቀጥ የሚያደርግ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ኢየሱስ ይህ ከገሃነም በቀር ማሰብ ከምችለው ከማንኛውም ነገር በላይ አስፈሪ ነው፡፡

ኢየሱስም . . ."አዎ ይህ በምድር ላይ ትንሹ ገሃነም ነው፡፡

"ብዙ የምነግርሽ ነገር አለ፡፡ ነገር ግን ጊዜ ልትሰጪኝ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ልትሰጪኝ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጅማሬው ነው፡፡ ክሌር ከአንቺ ጋር ብዙ ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ነው ስለ እነዚህ ነገሮች እንድነግርሽና በዚህ ውስጥ የሚያልፉትን ልብ እንድታዘጋጂ በማሰብ ከአለም ጉዳዮች እንድትለዪ የምፈልገው፡፡ ከሁሉም በበለጠ ግን ታምራዊ በሆነ መንገድ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ እነዚህ ጊዜያቶች ለታምራቶችና ጊዜው እንዲያጥር ለማድረግ ብዙ ጩኸትን ይጠይቃል፡፡ ይህም ሰዎች ከሞት እንዲተርፉ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህም ታምራቶች እጅግ የሚታዩ ከመሆናቸው የተነሳና እንዲሁም ይህ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ህልም ስለሆነ በመንግስተ ሰማይ ያሉ እንኳን በዚህ ውስጥ ባለመሳተፋቸው ቅር ይላቸዋል፡፡

"አዎ የሚያስፈራ ጊዜ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ዋናው ነጥብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማሸነፍ መቻሉ ነው፡፡ ማንም ሰው ያለ እርዳታ አይሆንም፡፡ ነገር ግን እኔ ማን እንደሆንኩ አይኖቻቸው ተከፍቶ ማየትና እኔ አዳኛቸውና ጠባቂያቸው እንደሆንኩ መቀበል አለባቸው፡፡ ይህም በአለም ላይ ሊሆን ያለው ነገር እንዲሆን ያደረገው አንዱ ዓላማ ነው፡፡

"የተወደድሽ ክሌር እነዚህ ነገሮች እጅግ ጨለማና አስቀያሚ ናቸው፡፡ ከሙሽራዬ ጋር ማሳለፍ የምፈልገው ጊዜ በዚህ መልኩ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአይምሮሽ ውስጥ እጅግ የከበደ እንደሆነ ስለማውቅ ነው ይህንን እያወራሁ ያለሁት፡፡ በፊት እንደነገርኩሽ ኒብሩ የምትባለው ፕላኔት ነች እነዚህን ሁሉ ይዛ ያለችው፡፡ ይህቺ ፕላኔት በኢጋንንት የተወረረች ፕላኔት ናት፡፡ እነርሱ በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ መገኘት የሚችሉ ስለሆነ ጊዜና ቦታ ለእነዚህ ፍጥረታት ምንም አይደለም፡፡ ይህ ማለት ከአንዱ ወርድና ስፋት ወደ ሌላኛው መሄድ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እናንተ ወደ ጨረቃ ለመሄድ እንደምታስቡት ሳይሆን እዛ ለመሄድ ስታስቡ በዛው ጊዜ እዛው መገኘት ማለት ነው፡፡

"አዎን ከአንዱ ወርድና ስፋት ወደ ሌላው ወርድና ስፋት በሮች ተከፍተዋል፡፡ የሰው እብሪት ይህንን አድርጓል፡፡ እኔ ለራሱ ደህንነት እንዲሆን በማለት የዘጋሁትን በሮች በዕብሪቱ ምክንያት ከፍቷል፡፡ እናም በዚህ ውጤት ይኖራል ደግሞም ይሞታል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን ደግሞ ተፈቅዷል፡፡

"አማኝ ስሜን ሲጠቀም ስሜ እጅግ ኃይል ያለውን የመሳሪያ ሥፍራ ይወስዳል፡፡ ነገር ግን እጅግ የሚያሳዝነኝ ነገር ሰዎች ሃይማኖት በጦርነት ላይ ምንም ሥፍራ እንደሌለው እንዲያምኑ መደረጋቸው ነው፡፡ በዚህም እጅግ ተሳስተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለጉዳታቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ የእኔ መላእክቶች ጥይትን እንዲሁም ሚሳይልን እንኳን ለማቆም ኃይል እንዳላቸው ምንም መረጃው የላቸውም፡፡ አለም እንደዚህ እንዲያስቡና በደንብ ቢጠቀሙበት በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ የሚሰራውን መንፈሳዊ ጦር እንዳይጠቀሙበት ተደርገዋል፡፡ እነዚህም ፍጥረቶች በተለያየ ወርድና ስፋት/inter dimensional/ የሚቀሳቀሱ ናቸው፡፡

"በሌላ አነጋገር ጠላቶቻችሁን በእኔ ስም ለመዋጋት ከእኔ ጋር በእውነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያስፈልጋችኋል፡፡ ይህም በሐዋርያት ምዕራፍ 19 ከቁጥር 13 ጀምሮ በምሳሌ እንደቀረበው ነው፡፡

<u>*"አጋንንትንም እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶች። ጳውሎስ በሚሰብከው*</u>

<u>*በኢየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን*</u>

<u>*ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ። የካህናትም አለቃ ለሆነ አስቄዋ ለሚሉት ለአንድ*</u>

<u>*አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት። ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፡- ኢየሱስንስ*</u>

*አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቆስለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም። ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፥ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፥ የጌታም የኢየሱስ ስም ተከበረ፡፡"*

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ ... "ይህ ወቅት ከየትኛውም ጊዜ መወዳደር የማይችል ተስፋ የሚያስቆርጥ ጊዜ ነው፡፡ ከሁሉም የሚብሰው ደግሞ ሰዎች እነዚህን ጭራቆች ለመግደል መሳሪያ ይዘው አልሰራ ሲላቸው የሚደርስባቸው ተስፋ መቁረጥ ነው፡፡

"ተወዳጆች እናንተ ከሄዳችሁ በኋላ ጊዜው ሲደርስ ልጆቻችሁ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት የምትተዉላቸው አንዳንድ ነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡ እኔን በመንፈስና በእውነት የያዙ በወደቁ መላዕክቶች ላይ ይህ ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡ በፊት እንደነገርኳችሁ ከወደቁ መልአክቶች (*alien)* ውስጥ መልካም የሚባል በፍፁም የለም፡፡ ሁሉም በማታለል ሰዎች እንዲያመኗቸው ራሳቸውን የደበቁ የተለያየ ድርሻ ያላቸው አጋንንቶች ናቸው፡፡ ልታምኗቸው አትችሉም፡፡ ሲናገሩ እጅግ ለስላሳና የረጋ የሚመስሉት እንኳን በውስጣቸው ንዴት የተሞሉና ሲመቻቸው ወዲያው የሚባሉ ጭራቆች ናቸው፡፡ ወዳጅ መስለው የሚቆዩት ሌሎቹን በመረባቸው ውስጥ ለማስገባት እንዲመቻቸው ነው፡፡ እናም እናንተ ስትሄዱ የሌለ ታሪክን በመፍጠር ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ከዚህ ያለፈ ጥያቄ የሚያቀርብ ካለ ምግባቸው ይሆናሉ፡፡

"በምንም አይነት መልኩ ቢሆን እነዚህን የወደቁ መላዕክቶች (*demon aliens)* ወደቤታችሁ እንዲገቡ እንዳትጋብዟቸው፡፡ ስሜን ጠርታችሁ አባሯቸው እንጂ በምንም አይነት መንገድ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት እንዳይኖራችሁ፡፡ በዚህ አለም የአሁኑ ትውልድ እግዚአብሔር የለም የሚል አስተሳሰብ እንዲኖር ለማድረግ መሰረቱ ተገንብቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ እኔ ማን መሆኔን እስኪረዱና አዳኛቸው አድርገው እስኪቀበሉኝ ድረስ እኔን ማወቅ አይችሉም ደግሞም ኃይል ያለውን ስሜን አይጠቀሙም፡፡ ስለዚህ ይህንን አሁን የምነግራችሁ ሌሎችን እንድታዘጋጁ ነው፡፡

ጌታ ሌላ ልትለን የምትፈልገው ነገር አለ?

"ለማለት የምፈልገው አንድ ነገር እያንዳንዳችሁን እጅግ እንደምወዳችሁ ነው፡፡ ለአገልግሎት ከንጥቀት ወደኋላ ለመቅረት የፈቀዳችሁትን ደግሞ አመሰግናችኋለሁ፡፡ በጣም በሚያስደስት ሁኔታ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ በዛን ጊዜ ነገሮች የሚካሄዱት አሁን እንደሚካሄዱት ሁኔታ ሳይሆን ከተፈጥሮ ሁኔታ ባለፈ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ያለ እርዳታ አልተዋችሁም፡፡ ነገር ግን ቀናችሁ ሁሉ በፀሎትና በማድመጥ መሞላት አለበት፡፡ ይህንን ችሎታ ነው እንዲያዳብሩ የምረዳቸው፡፡ ይህም በውስጥ ያለውን የውይይት ምልልስ በመዝጋት ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ያለውን የእኔን መገኘት የሚያስከትል ነው፡፡

"ብዙ ብልህ ሰዎች ብዙ የሚገርም ነገርን የሚሰሩ ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ብቻ አስታውሱ ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና። እናንተ ፀልያችሁ እኔ ምንም ስሜት የማይሰጥ አንድ

ነገር እንድታደርጉ ስመራችሁ ምንም ይሁን አድርጉት፡፡ የእናንተ መታዘዝ ነው ከጠላቶቻችሁ እጅ ፈልቅቆ ነፃ የሚያወጣችሁ፡፡

(ከሌር)፡- እናም ያንን ሲል "ምንም ይሁን ምንም ብቻ አድርጉት፡፡" በዚህ ጊዜ "ዘ ቾዝን" የሚለው ፊልም ትዝ አለኝ፡፡ ክፍሉም የቃና ገሊላ ሰርግ የሚያሳየው ነበር፡፡ ሰዎቹ ወይን አልቆባቸው ነበር፡፡ እነርሱም የማንፃት ስርአትን ለመፈፀም ውሃ የያዙትን የድንጋይ ጋኖችን ባሉበት ክፍል ቆመው ነበር፡፡ እናም ኢየሱስ ጋኖቹን ውሃ እንዲሞሏቸው ነገራቸው፡፡ ይህ ምንም ስሜት የሚሰጥ ነገር አልነበረም፡፡ ሰውዬው ወይን አልቆብኛል አለ እንጂ ውሃ አልፈልገም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ "ቶማስ ሁሉ ነገር ስሜት ላይሰጥ ይችላል ነገር ግን ምን እንደሚሆን ዝም ብለህ ተመልከት" አለው፡፡ ከዚያ በኋላ ያለው ሁሉ ታሪክ ነው፡፡ ጌታ በጋን ውስጥ ያለውን ውሃ ሁሉ ወደ ወይን ቀየረው፡፡ ይህም የሆነው ሰውዬው አድርግ እንደተባለው ዝም ብሎ በማድረጉ ነው፡፡ የተባረከችው የጌታ እናት "እርሱ የሚላችሁን አድርጉ" ብላቸው ነበር፡፡ እነርሱም እንደተባሉት ሲያደርጉ ከሚያስፈልጋቸው በላይ የወይን ጠጅ አገኙ፡፡ ከዚህም በላይ የወይን ጠጁ ጣዕም ማንም ቀምሶ የማያውቀው አይነት እጅግ ጣፋጭ ነበር፡፡ ይህ ሊሆን ደግሞ ግድ ነው፡፡

የተወደዳችሁ ቤተሰቦች በታኦስ በእኔ የሆነውን አንድ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ በቅርቡ በበጋ ወራት ዩፎ(UFO's) በታኦስ ሰማይ ላይ አየን፡፡ አንደኛው በአካባቢያችን ባለው በኦልማርት ሰማይ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር፡፡ የተንጠለጠለው ልክ ኮከብ የሚመስል ነው፡፡ ሰው ይህንን ተገንዝቦ እንደሆነ አላውቅም፡፡ በዛው ምሽት በሙቅ ውኃ ውስጥ ተዘፍዝፌ ሰማዩን እያየሁ እያለ ተመሳሳይ የሆነ ብርሃን ተንቀሳቅሶ እኔ እያየሁ ወዳለሁበት ተራሮች ምስራቅ ክፍል ሲቆም አየሁ፡፡ ምን ማለት እንዳለብኝ በፊት አውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሳላውቀው ከአንደበቴ አፈትልኮ የወጣው ቃል "ጌታ ከክፉ አድነን" የሚል ነበር፡፡ በዛችው ደቂቃ ውስጥ ቆሞ የነበረው በመሄድ ጭራሽ ጠፋ፡፡ ጌታ የነገረኝ ነገር እነዚህን ነገሮች ጭራሽ እንዳላያቸው ነው፡፡ ጭቅላታችሁን የሚነካ መንገድ አላቸው፡፡ በዚህ ከተማ ያለች አንዷት ሴት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኳስ ሜዳ ላይ ሲያርፍ አይታ በእነርሱ ተነደፈች፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ በፀጉሯ ላይ መላጣ ስፍራ አላት፡፡ እናም እነርሱን ስታይ አንድ ነገር እንደሆነች ትናገራለች፡፡ እንደዚሁም ሌሎችን አውቃለሁ በእነርሱ ተጠልፈው የነበሩ ሰዎች በራሳቸው ላይ መላጣ ስፍራ እንዳላቸው፡፡

ኸርት ድዌለርስ እባካችሁ ልባችሁን ለኢየሱስ ብቻ ጠብቁ፡፡ እንዲሁም እነዚህ ፍጥረታት እኛን የፈጠሩ አምላክ ናቸው የሚለውን ውሸት አትቀበሉ፡፡ በፍፁም አይደሉም፡፡ እነርሱ የወደቁ መላዕክቶች፣ ከመንግስተ ሰማይ የተባረሩ እና ከሰው አካል ቁራጭ ለራሳቸው አካልና ዘረመል(DNA) ያዘጋጁ ናቸው፡፡ በእነርሱ የተጠለፉ ሰዎች አንድ መልካም ነገር እንኳን አድርገው እንደማያውቁ ይነግሯችኋል፡፡ እነርሱ ሽብር ፈጣሪዎች፣ አካልን የሚያጎድሉና የሚደፍሩ እንዲሁም የሚጠልፏቸውን የሚገድሉ ናቸው፡፡ ስለዚህም ስልጣናችንን ተጠቅመን ከአካባቢያችንን እንዲሸሹ ማባረር እንጂ ከእነርሱ ጋር ተካፋይ ለመሆን ፍፁም ምክንያት የለንም፡፡

ደግሞም የመጡት ምድርን ለመርዳት ነው የሚለውን የውሸት የፈጠራ ታሪክ በመስማት ተታላችሁ አትሳቡ፡፡ ይህ እውነቱን ለመደበቅ የተዘጋጀ መሸፈኛ ነው፡፡ ወደ ምድር የመጡበት እውነተኛው ምክንያት እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ለማጥፋት ነው፡፡ በተለይም በእግዚአብሔር ሐምሳል የተፈጠረውን ሰው ፈቃዱን በማግኘትና ከእነርሱ ጋር እንዲተባበር በማድረግ ምድርን ተቆጣጥረው ለማጥፋት ነው፡፡ በመጨረሻም ይህ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈቅዳል፡፡ ነገር ግን ደግሞ ጣልቃ ይገባና እስከ መጨረሻው በእሳት ባህር ውስጥ ይጥላቸዋል፡፡

## ትልቁ መንቃት/ዘ ግሬት አዌከኒግ/ ምንድነው? - ማርች 8 ቀን 2021 ዓ.ም

**What is the great awakning? – March 8, 2021**

እስካሁን አይተንና ሰምተን የማናውቀውን የአለሙን ድንቅ ነገር ለመረዳት እንድንችል ጌታ አይኖቻችንን፣ ልባችንና አይምሮአችንን ይከፈት፡፡ አሜን፡፡

የተወደዳችሁ ቤተሰቦቼ የተማርኩትን ነገር ለእናንተ ለማካፈል በደንብ እንዲገባኝ ለማድረግ ሳምንቱን ሙሉ እየሞከርኩ ነበር፡፡ አንድን መልዕክት ለማቅረብ ለሦስት ቀናት ያህል ስታገል ነበር፡፡ በመጨረሻም መልዕክቱ እንዲገባችሁ መሰረታዊ የሆነውን ነገር እንዳልገለጥኩላችሁ ተረዳሁ፡፡ ይህም ለአለማችን ሊቀርብ ያለው አዲስ ኃይል ነው፡፡ ስለዚህም ነገሩን እንደገና ከስር መሰረቱ መጀመር አለብኝ፡፡ መልዕክቱም ይህ ነው፡፡

ነገሩ የጀመረው ፕሬዚዳንት ትራምፕ በነበረበት ጊዜ ጎን ለጎን ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ በመጀመሪያ ያጋጠሙኝ ቡድኖች ነበሩ፡፡ ከዚህም ቡድን ውስጥ ዶክተር ቻርሊ ዋርድ የሚባል ክርስቲያን አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በቢት ሹት፣/Bit Chute/ በራምብልና በቴሌግራም ነው፡፡ በፊት በፊት በዩ ቲዩብ ላይም ነበር፡፡ አሁን ግን ከዚያ አስወጥተውታል፡፡

ይህም ሰው ከአለም ላይ ብዙ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ስለሚሰበስብ ቴሌግራም ቻናሉን ሰብስክራይብ አደረግሁ፡፡ እነዚህም መረጃች ሆን ተብለው ከህዝቡ የሚደበቁና ከሚታየው በስተጀርባ የሚገኙ ድርጊቶችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ እርሱና ሌሎች ብዙዎች ይመጣል እየተባለው ግሬት አዌከኒግ ወይም ትልቁ ከእንቅልፍ መንቃት እየገለፁ ይገኛሉ፡፡ እንደሚመስለኝ ይህ ነገር በአለም ላይ እየተካሄደ ካለው ቆሻሻን ከማንፃት ጋር፣ እንዲሁም በጥልቁ መንግስት የተወሰደውን የአሜሪካን የፋይንናንስ ሁኔታ እንደገና ለአሜሪካ ህዝብ ከመመለስ ጋር የተያያዘ ሲሆን ያገኘሁት ግን ከዚህም እጅግ ጥልቅ የሆነ ነገር ነው፡፡

በአጭሩ ስገልፀው በቅርብ ጊዜ አለምን የሚለውጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየመጡ ነው፡፡ ይለውጣል ስላችሁ ፍፁም የሚለውጥ ማለቴ ነው፡፡ እነዚህም ነፃ ኢነርጂ/ኃይል/፣ ማንም ሰው ሊጓዝበት የሚችል የአየር ላይ ትራንስፖርት፣ እንዲሁም ከዚህ ሁሉ የሚደንቀው ደግሞ የህክምና አልጋዎች /Med beds- ሜድ ቤድስ/ ጉዳይ ይገኙበታል፡፡ አቫተር/ Avatar/ የሚለውን ፊልም አይታችሁ ከሆነ ትክክለኛውን የሰው አካል ወደ አቫተር ወይም የአቫተር አካል ወደ ትክክለኛው የሰው አካል ሲለውጥ ያያችሁት ነው የህክምና አልጋዎች ወይም ሜድ ቤድስ የሚባለው፡፡ እነዚህ ሜድ ቤድስ የሚያደርጉት ነገር የእናንተን ዘረመል ያነቡና በፕላዝማ ኤነርጂ አማካኝነት አካላችሁን እጅግ ምቹ ወደሆነ አሠራር ይመልሱታል፡፡

"እነዚህ የህክምና አልጋዎች ወይም ቤድ ሜድስ ልባችሁን እንደገና ፍፁም ሊገነቡት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም አራተኛ ደረጃ የሚገኘውን ሊምፎማ የሚባለውን የካንሰር አይነት/Lymphoma/ በ10 ደቂቃ ውስጥ ያድኑታል፡፡ እግሮችንና እጆችን እንዲሁም ማንኛውንም የአካል ክፍል መልሰው ያበቅላሉ፡፡ ይህም የሚከናወነው ህመም ሳይኖርና በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰውነታችሁን በመጠገን እንዳያረጅ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህ በጣም የሚደንቅ ነገር ነው!!!

ቻርሊ፣ ሮበርት ዴቪድ እስቲል እንዲሁም ስምኦን ፓርክ የሚባሉትን ሰዎች ያካሄዱትን ውይይት ስሰማ የ5D አለም የሚለውን ሲደጋግሙት ሰማሁ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወርድና ስፋቶችን (dimensions) ነው፡፡ እነርሱ እንደሚሉት አብዛኛዎቻችን የምንኖረው በ3D አለም ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን የ5ኛው ወርድና ስፋት ደረጃ (5D) የበለጠ ፈርጀ ብዙ ወርድና ስፋት ያለው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ የ4D አለም የሚያመለክተው የሰውን አስተሳሰብ ማወቅን፣ በቦታው ላይ በአካል ሳይገኙ ነገሮችን ማየትንና መስማትን፣ እንዲሁም በቃል መነጋገር ሳይኖር ከሰው ጋር መግባባት መቻልን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ደግሞ በመንግስተ ሰማይ እንደሚቻልና አሁንም በፀሎት ወቅት ይህ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን በዚህ በሚወራው ግሬት አዌከኒንግ ወይም ትልቁ

ከእንቅልፍ መንቃት ይህ ችሎታ እንደሚኖርና ይህም ደግሞ ከአሉታዊ አስተሳሰብ በመውጣት አውንታዊና ተስፋ ሰጪ ወደሆነ ሽግግር እንደሚደረግ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት/ bilocation/ የ5ኛው ወርድና ስፋት ክስተት ምሳሌ ይመስለኛል፡፡ ለእነዚህ ቃላቶችና አባባሎች አዲስ ስለሆንኩ ስህተት ከሰራሁ እባካችሁ አርሙኝ፡፡

በሜድ ቤድስ መታከም ምን እንደሚመስል ትንሽ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ያህል ምሳሌ ልስጣችሁ፡፡ ለህክምና ቀጠሮ ትይዛላችሁ፣ ወደ ህክምናው ሄዳችሁ ክዳኑ መስታወት ሆኖ ወደሚያሳይ መሳሪያ ላይ ትወጣላችሁ፣ ከእናንተ ዘረመል ጋር በሚስማማ ፕላዝማ ኤነርጂ ይመረምራችኋል፡፡ ከዚያም ማሽኑን የሚያንቀሳቅሰው ሰው በተገኘው የምርመራ ውጤት መሰረት እንድትድኑ ፕሮግራም ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም በደቂቃዎች ውስጥ ከማንኛውም በሽታ ፍፁም ድናችሁ ትወጣላችሁ፡፡ እግር ወይም እጅ ከሌላችሁ ይበቅልላችኋል፡፡ የልብ ድካም ካለባችሁ አዲስ ልብ ይኖራችኋል፡፡ አይምሮን የሚያዛባ ነገር ካጋጠማችሁ ያክማችኋል፡፡ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት የስነ ልቦና ቀውስ የደረሰባቸውን በዚህ ማሽን ማከም ተችሏል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን በአለም ላይ እየተካሄደ ያለው ነገር ከምድር በታች ካሉ ከተሞችና ከመሽሎኪያ ዋሻዎች ህፃናቶችን ከቦታ ወደ ቦታ ከሚያዘዋውሩት እጅ እየታደጓቸው የደረሰባቸውን የአይምሮ ጉዳትና የማይፈለጉ ሐሳቦችን በዚህ አይነት መንገድ እያከሟቸው ይገኛል፡፡

ይህ ለሰለጠነው አለም ምን ማለት እንደሆነ ትረዳላችሁ??? ይህ ማለት ከአሁን ወዲያ ጎጂ ለሆኑ መድኃኒቶች የሚወጣ ውጪ የለም! ኦፐራሲዮን የለም! አርቲፊሻል እግሮችና እጆች አያስፈልጉም! አይነ ስውርነትና ያለመስማት የለም፣ ኦቲዝም የለም! የአይምሮ መዛባት የለም! በጉዳት ምክንያት የሚከሰት የአይምሮ መታወክና ድባቴ የለም! ማለት ነው፡፡ ይህ ህክምና የሚከናወነው ደግሞ በጥቂት ደቂቃዎችና ካለምንም ህመም ነው፡፡

በተጨማሪም ነዳጅ፣ የተመሰቃቀሉና አየሩን የሚበክሉ መኪናዎች አያስፈልጉም፡፡ ለኤልክትሪክ ወይም ለማሞቂያ ክፍያ አያስፈልግም፡፡ እንዲሁም በእንጨት የሚሰሩ ምድጃዎች ወይም በጋዝ የሚሰሩ ማሞቂያዎች አያስፈልጉም ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ አለም ከአሁን ወዲያ ምን እንደሚመስል ልትገምቱ ትችላላችሁ? እጅግ መልካም ከመሆኑ የተነሳ እውነት ይሆናል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን ታስላ/ Tesla/ የእነዚህን ቴክኖሎጂ ጉዳይ ግልፅ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ቢሆን ግን በስግብግብ ሰዎች ምክንያት እስካሁን ግልፅ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡ አሁን ግን እነዚህ ስግብግብ ሰዎች ተይዘው በሚሊታሪ ፍርድ ቤት ቀርበው እየተፈረደባቸው ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙዎቹ ገንዘብ እየተከፈላቸው አሜሪካን ለማጥፋት ከተነሱ ከአለም ከተወጣጡ በጣት ከሚቆጠሩ ክፉ ሰዎች ጋር በማበር ይሰሩ እንደነበረ መረጃው ይፋ በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሰዎች የፈፀሙት ነገር እጅግ ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ይህም ህፃናትን በማሰቃየት፣ ከእነርሱ ደም በመውሰድ፣ የወሲብ ባርያ በማድረግ፣ እንዲሁም ህፃናቱን በመግደል እንደ መዝናኛ በመቁጠራቸው ነው፡፡

የተወደዳችሁ የዚህ አለም የጨለማው ወገን ከምትገምቱት በላይ ከምንም ነገር እጅግ የጨለመ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የአገሩ አርበኞችና መልካም የሆኑ የሰራዊቱ መሪዎች ወደ ትራምፕ በመሄድ የተደረገውን ጭካኔ የሞላበት አድራጎት በማቅረብ አገሪቷን ወደ ቀደመ ሁኔታዋ ለመመለስ እንዲረዳቸው ጠይቀውት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ አሁን ባለው አስተዳደር ፊት ለፊት የሚደረገው ሁሉ እንዲሁ ለታይታ የሚደረግ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ሰዎች ይህንን ጨዋታ እንዲጫወቱ የተደረጉ ሰዎች እንጂ ትክክለኞቹ አይደሉም፡፡ ይህ ሁሉ በቅርብ ግልፅ ይሆናል፡፡ እስከዛው ግን እንደሚታየው ሆኖ ይቀጥላል፡፡

የጊዜውን ሁኔታ ስከታተል በአርበኞቹ አመለካከት መሰረት የሚመጣውን አለም የሚለውጠውን የ5D አለም እንድተዋወቅ ተደረግሁኝ፡፡ ነገር ግን ባየሁት አንድ ነገር ተቸግሬያለሁ፡፡ ይህም በቪዲዮው ሜድ ቤድ /med bed/ የሚባለውን ያስተዋወቀችውና መረጃውን የሰጠችው ሴት በመጨረሻ መግለጫዋ ላይ ይህ ቴክኖሎጂ ከዚህ ምድር ባልሆኑ ማስተሮች እንደተሰጠ ገለፀች፡፡ በሌላ አነጋገር ከሌላ የሰለጠነ አለም የመጡ ሰዎች ማለት ነው፡፡ እናም ፕሮግራሙን ጨርሳ ስትወጣ እራሷን የገለፀችው ካሚራ በሚል ስም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሰውና እንስሳት በላቦራቶሪ ተዳቅለው የተሰጣቸው ሳይንሳዊ መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰውነቱ የአሳማ ሆኖ ራሱ የሰው ማለት ነው፡፡ እናም ጨርሳ ስትወጣ የተሰማኝ ነገር ከተፈጥሮ ህግ ውጪ (psychic) ከእኛ ጋር ለመገናኘት ከጋላክቲክ ፈደሬሽን ኦፍ ላይት (Galactic Federation of Light) የተመደበችልን እንደሆነ ነው፡፡

አሁን ይህንን እንመልከት፡፡ እኔ እንደማምነው የሜዲካል አልጋዎቹ /The med beds/ በራሳቸው አዲስ ቴክኖሎጂ ከመሆን ሌላ ገለልተኛና ምንም ያልሆነ ነገር ነው፡፡ ይህም ልክ ኢንተርኔትና ኤም አር አይ/ MRI/ ቴክኖሎጂዎች ገለልተኛ እንደሆኑ ሁሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ችግሩ ሜድ ብድስ የተባለው ማሽን ከኤሊየንስ /aliens/ ጋር መያያዙ ነው፡፡ እናም ቀድሜ እንደነገርኳችሁ ኤሊየንስ የወደቁ መላዕክቶችና አጋንንቶች ሲሆኑ አካል ለብሰው ወደ ምድር የመጡ ናቸው፡፡ እኔ እንደማምነው ከሆነ እነዚህ የሚንቀሳቀሱት በ5ኛው ወርድና ስፋት አለም (The fifth-dimension) ውስጥ ነው ወይም የተሰሩበት ነገር (substance) በተለያየ ወርድና ስፋት/ (inter-dimensional) መንቀሳቀስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው በቅፅበት መታየትና መሰወር የሚችሉት፡፡ እኛም በመንግስተ ሰማይ እንደዚህ እንደምንሆን አምናለሁ፡፡ በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ልምምዱ ያላቸው ደግሞ የሚንቀሳቀሱት በልዩ ልዩ ወርድና ስፋት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ምንም ክፋት የለውም፡፡ ይህ በፊሊጶስ ህይወት ውስጥ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ሲያገለግል ተከስቶ ነበር፡፡

ነገር ግን ይህ ሜድ ቤድስ እና የ5D አለም ሲቀርብ ከተሰጠው መረጃ ማጠቃለል የሚቻለው እነዚህን ቴክኖሎጂዎች የሰጡን እጅግ የሰለጠኑ አካላት እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እና ደግሞ መንፈሳዊ የበላይነት እንዳላቸው ለማሳየት ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰላም፣ ስለ ብርሃን፣ ስለ ስምምነትና ስለ አዲስ አለም ይናገሩ ነበር፡፡ የኔ ጥያቄ "ጌታችሁ ማነው?" የሚል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእናንተ ጌታና አዳኝ እንደሆነ ትመሰክራላችሁ? ወይስ የአዲሱ ዘመን እንቅስቀሴ እንደሚያምነው ከሌላ አለም የመጡ ጌቶችን /ascended master/ ታምናላችሁ? ለእናንተ ኢየሱስ ማነው?

በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ መካከለኛውን ትራንስ/ a trance medium/ ሳጠና ኢየሱስ የሚቆጠረው ከላይ ከመጡት ብዙ ጌቶች እንደ አንዱ ጌታ ተደርጎ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ በድንቅና በምልክቶች ተገልጦልኝ እርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ገለጠልኝ፡፡ ሌሎቹ የተባሉት ነገሮች ሁሉ ውሸትና ሰዎችን ለማሳትና በመጨረሻም በአንድ ሰው ውስጥ የሚያድረውን ሰይጣን እንዲያመልኩ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም ማጭበርበር ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ መልዕክቱ በሁለተኛው ምዕራፍ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ትልቁ ማሳት ብሎ የገለፀው ነው፡፡

"ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" (2ኛ ተሰሎንቄ 9-12)

አሁን እኔን ያሳሰበኝ ነገር ሰይጣን ይህንን አዲስና ገለልተኛ የሆነውን ቴክኖሎጂ እንደ ትሮይ ፈረስ መጠቀሙ ነው፡፡ ይህም የሰዎችን ልብ ከእግዚአብሔር የሚመልስና ከላይ የመጡ የሚባሉትን አካላት እንዲያመልኩ የሚያደርግ፣ እንዲሁም ፍፁም ልዩ ቅርፅ የያዘ ሃይማኖት የሚያስተዋውቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ሃይማኖት መሰረታዊ ኃሳቡ ኃጢያትን የሚፈቅድና ሰዎች እንደፈለጉ እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ እኔ እንደማምነው ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ያዳነኝ አንድ ነገር ቢኖር እውነትን ብቻ ፈላጊ በመሆኔ ነው፡፡ ያገኘሁት ፍፁም እውነት መሆኑን እስከማወቅ ድረስ በምንም ነገር መረጋጋት አልቻልኩም ነበር፡፡ እናም በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ እኔ የማምነውን የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ አማልክትን እንዲሁም አንድ፣ እውነተኛና ህያው የሆነውን አምላክ ልዩነት በፀጋው ሲገልፅልኝ በውስጥ ማንነቴ በዘመኔ ሁሉ ስፈልገው የነበረው እውነት ይህ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ በተጨማሪም እርሱን በመከተሌ ያገኘሁት ፍሬ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ መራኝ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም አልሜ የማላውቀው መከናወን ደግሞ በህይወቴ ተከሰተ፡፡ በእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ውስጥ እየኖራችሁ መሆኑን እንደማወቅ ደስ የሚያሰኝ ስሜት የለም፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ስትሆኑ በዙሪያችሁ የምትሰሩትን ስራ በሚያግዟችሁ ሰዎች ትከበባላችሁ፡፡ በዙሪያችሁ ከተከበባችሁት ረብሻ በላይ በሰላም ትኖራላችሁ፡፡ እንዲሁም ህይወታችሁ በምትኖሩት እውነት ፍሬ ያፈራል፡፡ እናም ደግሞ ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕት ሌሎችን ወደ እርሱ በማምጣት የእግዚአብሔር ወዳጆች ትሆናላችሁ፡፡

ጌታ ስለዚህ ነገር ልትለን የምትፈልገው ነገር አለ?

ኢየሱስም . . . " በአየር ላይ በተለያየ ቀለም ፣ በተለያየ ቅርፅና መጠን አካል ለብሰው የሚመጡትን ኢጋንንትና መላዕክት የሚመርጡ በትልቁ ማጭበርበር ውስጥ ተጠምደው ይጠፋሉ፡፡ ይህም የአውሬውን ምልክት በመቀበልና ይህንን አሳዛኙን ማታለያ በማመናቸው ነው፡፡ ይህንን የማጭበርበሪያ መንገድ የሚያምኑ እውነተኛ መንፈስን የመለየት ፀጋ የሌላቸው ናቸው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን ተራና ርሑሩህ የሆኑት፣ እንዲሁም ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው በዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉ መሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም የተወሳሰበና የበራላቸው ምሁራኖች በዚህ የሚጠመዱ ናቸው፡፡ እነዚህም እግዚአብሔርን እንደ አናፂ ወይም በትንንሽ ሁኔታ ውስጥ አለ ብለው የማይቀበሉ፣ እንዲሁም በሰራተኛው መደብ ወይም ዳግም በተወለደው ተራ አማኝ ውስጥ አለ ብለው የማይቀበሉ ናቸው፡፡

"በመንፈስ የሚያውቁኝ ብቻ ናቸው የሚፀኑትና ከወደቁ መላዕክቶች ጋር ስምምነት የማያደርጉት፡፡ እኔ ከላይ ከመጡት ከእነርሱ ማስተሮች እንደ አንዱ እንደሆንኩና ያስተማርኩት ግን ስህተት እንዳለበትና ኃጢያት እንደሆነ ለህዝቡ ያቀርባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በፍፁም ልባቸውና ማንነታቸው ከእውነት ጋር የተጣበቁ ይህ አባባል የሚያሳስት ነገር እንዳለበት ይጠረጥራሉ፡፡

"በስራ ላይ ሊውሉ ያሉ ቴክኖሎጂዎች በራሳቸው ገለልተኛና መልካም እንደሆኑ በደንብ ግልፅ ላደርግላችሁ፡፡ ነገር ግን ገበያ ላይ የሚውሉት ከበላይ ከመጡ አለም አቀፋዊ ስልጣኔ ካላቸው ከጋላክሲ አካላት ነው በሚል መረዳት ጋር ተያይዟል፡፡ በሌላ አነጋገር ይህንን ሁሉ ስቃይ ሊያስወግድ የሚችል ቴክኖሎጂ የሰጠን አካል እንዴት ክፉ ሊሆን ይችላል? የሚል የሚያስት አመለካከትን ለማምጣት ነው፡፡ መልሱ ቀላል ነው፡፡ እነዚህ አካል ለብሰው የመጡ የወደቁ መላዕክቶች ናቸው፡፡ እነርሱ እጅግ ብልህና ስለተለያዩ የአለም ወርድና ስፋት ፊዚክስ (*inter-dimensional physics of the worlds)* በደንብ የገባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም በመነሳት ለሁኔታው እንዲስማማ በማድረግ የሚያሳምን ውጤትን ይዘው መጥተዋል፡፡

"ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን አድርገው የሚያቀርቡት በጎ አድራጊና ከሁሉ የላቀ ንቃተ ህሊና ያላቸው አስመስለው ነው፡፡ እናም እነርሱ እኔን እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው አይቀበሉም፡፡ ምክንያቱም የእነርሱ ጌታ ሰይጣን ስለሆነ ነው፡፡ እውነተኛ ፍላጎታቸው እናንተንና መልካም የሆነውን ሁሉ ለማጥፋት ነው፡፡ እኔን እንደ አዳኝ አድርገው ያልተቀበሉትን ሲያዩ ይተማመናሉ፡፡ ምክንያቱም ለስህተትና ለትልቁ ማታለል ስለተውኳቸው ነው፡፡

"በእውነትም ይኼ ትልቁ ማታለል ነው፡፡ ይህ ደግሞ መንፈስን የመለየት የሰላ ችሎታ፣ ቃሉን የማወቅና ከወጥመዱ የመራቅ ጉብዝናን ይጠይቃል፡፡ ልጆቼ ሰይጣን መንግስቱን በአንድ በኩል ለማምጣት ካልቻለ በሌላ መንገድ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም ከእኔ ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት ከሌላችሁ እነርሱ በሚሰጡት ሥነ - አመክኖ (*logic)* ትደገፋላችሁ፡፡

"ህዝቤ እባካችሁ በሙሉ ልባችሁ ከእኔ ጋር ተጣበቁ፡፡ በተጨማሪም የነቁትን፣ ነገር ግን በስህተት ውስጥ ያሉትን አስጠንቅቋቸው፡፡ የሚስቱት አብዛኛዎቹ በተለየ መልኩ መልካምና ደግ ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በጠለቀ ወዳጅነት ደረጃ አያውቁኝም፡፡ ከእኔ ጋር ያላቸው ግንኙነት ከተለመደው የሃይማኖት ልምምድ ያለፈ አይደለም፡፡ ስለዚህም መንፈስን የመለየት እውቀታቸው የተጣመመ ነው፡፡ በሃይማኖት ስላደጉ ብቻ ስለ ክርስትና እምነት ማወቅ ያለባቸውን ሁሉ እንደሚያውቁ ነው የሚያምኑት፡፡ በእውነት የሚያውቁ ቢሆን ኖሮ ትልቁን ማታለል ለይተው ያውቁት ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ኢየሱስ ነኝ ከሚል አካል ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከእነርሱ ጋር ያለሁት እኔ ሳልሆን አታላይ ኢጋንንት ነው፡፡ ይህም በእሳት ምሰሶ ውስጥ ተገልጬ አንቺን ከተመሳሳይ ኢጋንንት ነፃ እንዳወጣሁሽ ማለት ነው፡፡

"እያንዳንዳችሁን እጅግ አፈቅራችኋለሁ፡፡ ነገር ግን ሊገባችሁ የሚያስፈልገው ነገር ጠላት የእናንተን ትኩረት ለመቀየር አክራሪ ከሆኑት፣ እንዲሁም መፅሐፍ ቅዱስን ተጠቅመው ስህተትን ከሚፈልጉና ከሚተቹ ጋር ለማገናኘት ሙከራ ያደርጋል፡፡ ይህ ሃይማኖት እንጂ ወዳጅነት አይደለም፡፡ ለእናንተ ያለኝ ፍቅር ገደብን አያውቅም፡፡ ደግሞም ልቤ በመንግስተ ሰማይ ለእናንተ ያቀደው መልካም እቅድ እንጂ ሌላ ምንም የለውም፡፡ ስለዚህም እባካችሁ አጥፊ ኃይል ይህንን አስደናቂ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ የእናንተን መተማመን ከዚያም አምልኮን ለማግኘት ሊጠቀምበት እንደሚችል ለአንዳፍታም እትዘንጉ፡፡

"ውዶች ጌታ እኔና እኔ ብቻ ነኝ፣ ሌላ ማንም የለም፡፡ ለእናንተ ያለኝ እቅድ ሁሉ አዎንና አሜን ብቻ ነው፡፡ የምሄደው ሥፍራን ላዘጋጅላችሁና እኔ ባለሁበት እናንተም እንድትሆኑ ነው ብዬ ነግሬያችኋለሁ፡፡ ውዶች በሰማይ ሥፍራን ሳዘጋጅላችሁ ከላይ እስከ ታች እያንዳንዱ ነገር የተሰራው እናንተ ከምትወዱት ነገር ነው፡፡ የተወደዳችሁ እያንዳንዱን የልባችሁን ጥቃቅን ፍላጎት አውቃለሁ፡፡ እናም ስታልሙት የነበረውን ህይወት ለእናንተ ለመስጠት ደስተኛ ነኝ፡፡ ይህም እኔን አምናችሁ ለእኔ በመኖራችሁ የሚደረግላችሁ ስጦታ ነው፡፡

*"ስለዚህ መፅሐፍ ቅዱስን፣ እንዲሁም ከእኔ ጋር እውነተኛ ወዳጅነትን ችላ አትበሉ፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ነገሮችን ሲያቀርቡ ያልተጣራና ጠባብ በሆነ መንገድ ነው፡፡ በሚቀጥለው መልዕክት ስለዚህ ማጭበርበር /deception/ ሰፋ ባለ ሁኔታ እገልፀዋለሁ፡፡ እኔን ማወቅ የላቀ መፅናናትና ደስታ አሁን ከእናንተ ሞልቶ ይፍሰስ፡፡ አሜን፡፡"*

## የወደቁ መላዕክት/*Aliens*/ መጓጓዣዎች አየሩን ሁሉ ይሞሉታል - ማርች 10 ቀን 2021 ዓ.ም.
## Alien Vehicles Will Fill the Skies – March 10, 2021

ጌታ ብርታቱን፣ ጥበቡንና ፅናቱን ይስጣችሁ፡፡ ቅዱስ ስሙን እንድትጠብቁና በሁኔታዎች ሁሉ እንድትጠቀሙበት ያስተምራችሁ፡፡አሜን፡፡ ይህንን ቪዲዮ ከማዳመጣችሁ በፊት ዘ ግሬት አዋከኒንግ ምንድነው? የሚለውን ቪዲዮ መጀመሪያ እንድታደምጡት እመክራችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ይህንን መልዕክት በደንብ ለመረዳት ያ ቪዲዮ መሰረታዊ የሆኑ ብዙ መረጃዎችን ስለሚሰጣችሁ ነው፡፡

የተወደዳችሁ የምጀምረው በምስራቹ ቃል ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስን ካወቃችሁትና ዳግም ተወልዳችሁ ጥልቅና እውነተኛ እምነት በጌታ ካላችሁ ስነ - ፍጥረት ሁሉ ለስሙ የማይታዘዝበት ምንም ሁኔታ የለም፡፡ ሰው፣ እንስሳት፣ ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጥረታት(ET)፣ በሽታ፣ ጅራታማ ኮከብ ፣ የእሳተ ጎሞራ ቅልጥ ድንጋይ ፣ ሱናሜ የትኛውም ይሁን የጌታ ኢየሱስን ስም ሊቋቋም እንደማይችል ተማመኑ፡፡ ይህም በፍፁም እምነት "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቁም" ብሎ ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ሂድ፣ በቃ ተዉ፣ ታሰር ወዘተ በማለት ነው፡፡ የትኛውም ፍጥረት ቢሆን የእርሱን ኃይል ሊቋቋም የሚችል የለም፡፡ ችግር የሚገጥማችሁ ግን እነዚህን ቃላት በፍፁም እምነት ካልተናገራችሁ፣ ያዘዛችሁት የእርሱ ፈቃድ ካልሆነና በስሙ ኃይል ካላመናችሁ ብቻ ነው፡፡ ማወቅ ያለባችሁ በጣም አስፈላጊው ነገር በመጀመሪያ ዳግም መወለድ እንዳለባችሁና ከእርሱ ጋር ቤተሰባዊ መቀራረብ ያላችሁ መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ስሙን ለመጠቀም ልዩ መብት አላችሁ፡፡

ይህንን ነጥብ ግልፅ ለማድረግ ከዚህ በፊት ያወራሁላችሁን አንድ ታሪክ ደግሜ ላውራላችሁ፡፡ አዲስ ዳግም የተወለደ አንድ ሰው ከክርስቲያን ጓደኛው ጋር በመሆን በተራራ ላይ በእግር እየተጓዙ እያለ በድንገት አንድ ሴት ድብ እየጮኸች በፊታቸው መጣች፡፡ እነርሱ ያላዩት ልጇ ለካ በሳሩ ላይ ነበር፡፡ አዲስ ዳግም የተወለደውም ክርስቲያን ነገሩ ምን እንደሆነ እንኳን በደንብ ሳይረዳ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አቁሚ" አላት፡፡ ድቧም የምታደርገውን አቁማ፣ ወደ ጎን መንገዷን ቀይራ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ ይህ ሰው ጌታ ኢየሱስን አዳኝ አድርጎ የተቀበለው በቅርብ ነው፡፡ ነገር ግን ያ ድቧን ለማቆም ሥልጣን እንዲኖረው ለማድረግ በቂ ነበር፡፡ ምናልባት ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሆኑ ፍጥረታት (ET) ቢያጋጥማችሁ አንድ የገጠመኝን ደግሞም ብዙ ጊዜ የነገርኳችሁን ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ በምሽት ውጪ ቁጭ ብዬ እያለሁ ከእኛ ቤት ብዙም ሳይርቅ አንድ ተጓዥ አይሮፕላን በዛፎቹ ላይ አየሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ምንም ሳላስብ "ከክፉ አድነን" አልኩኝ፡፡ እናም በዛው ቅፅበት ፍፁም ጠፋ፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ እኔን ተጠቅሞ የተናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ በዛን ጊዜ ተናገርኩት ምንም ሳላስበው ነው፡፡

በዮሐንስ 15፡ 7 ላይ እንዲህ ተፅፏል፡፡ "<u>በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል</u>፡፡"

እንዲሁም በማቴዎስ 17 ፡20 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡፡ " <u>እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፣ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም</u>።" ማቴዎስ 17፡20

<u>"ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ፣ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል</u>፡፡" ማቴዎስ 21፡21

የተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ ፍፁም በሆነ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ሲነገራቸው እንደሚበረከኩ ጌታ በግልፅና በትክክል የተናገረበት ሌላ ቦታ የለም፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ገደብ አበጅቼ "አዎ ዛፍ ልትረግሙና ሊደርቅ ይችላል፣ ስለ ሱናሜ ግን አላውቅም ልላችሁ አልችልም፡፡" ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፡፡ ቀይ ባህርን ከፍሎ እስራኤላውያኖችን ከሞት ካሻገራቸው፣ በአንፃሩ ደግሞ ባህሩን ወደ ቦታው መልሶ ጠላቶቻቸውን ሁሉ ካጠፋ፣ ሱናሜንም ለማጥፋት ፈቃዱ ከሆነ ያደርገዋል፡፡ የእርሱን ፈቃድ ለማወቅ ደግሞ ከጌታ ጋር ወዳጅ ከሆናችሁ ፈቃዱን ለመለየት ማስተዋሉ ይኖራችኋል፡፡ እንደ ፈቃዱ ብትለምኑ ደግሞ እርሱ ያደርገዋል፡፡

እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ሉቃስ 10፡19

ቤተሰቦች ያለሁት እየገነባኋችሁ ነው፡፡ ምክንያቱም እዚህ የምትቀሩ እነዚህ ዘግናኝ ፍጥረታት እናንተን ኢላማ እንዳያደርጉ ለማስቆም የስሙ ኃይል ያስፈልጋችኋል፡፡ አሁን ምን እየጠበቃችሁ እንደሆነ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡ በመጀመሪያ ግን ይህንን አጥብቄ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ በጎ አድራጊ የሚባል ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሚመጡ ፍጥረታት የሉም (ET)፡፡ በፍፁም አንዳቸውም በጎ ወይም መልካም አይደሉም፡፡ ሰይጣን ከሦስተኛው ሰማይ ሲጣል አንድ ሦስተኛውን መላዕክት ከእርሱ ጋር ይዞ እንደወጣ የሚታመን ነገር አለ፡፡

በራዕይ መፅሐፍ ምዕራፍ 12 እንዲህ ተፅፏል "ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው።"(ራዕይ 12፡3-4)

እንዲሁም በቁጥር ሰባት "በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፡፡ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም። ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።"(ራዕይ 12፡7-12)

ከእኛ ከባቢ አየር ውጪ የሚመጡ ፍጥረታት (ETs) ለሰው ልጅ የሰጡት ቴክኖሎጂዎች አንድና አንድ የሆነውን አጀንዳቸውን ለማስፈፀም እንደ ትሮይ ፈረስ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህም አጀንዳ በምድር የሚኖር ማንኛውም ሰው ሰይጣንን እንዲያመልክ፣ እንዲሁም ሰው የሚባለው ፍጡር ሁሉ ወንድ፣ ሴት፣ ህፃን ሳይባል ሁሉንም ጎትተው ወደ ገሃነም ከእነርሱ ጋር ለመውሰድ ነው፡፡

አሁን ደግሞ ስለ ሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነገረውን እንመልከት፡፡ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ ከፈጠረው ፍጥረታት ደግሞ ሉሲፈር የሚባል መልአክ ነበር፡፡ ይህ መልአክ ከወደቀ በኋላ ግን ስሙ ሰይጣን ተብሏል፡፡ ይህም መልአክ ወደቆ ሲጣል ከመላዕክቶች አንድ ሶስተኛውን ይዞ ነው የተጣለው፡፡

"በበታችህም ብል ተነጥፎአል፥ ትልም መደረቢያህ ሆኖአል ብለው ይመልሱልሃል።አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!አንተን በልብህ። ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ።" (ኢሳያስ 14፡11-14)

"እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።" 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4

"ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።" (ሉቃስ 10፡17-20)

እንዲሁም "በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።" (መዝሙር 91፡13)

እናም እነዚህ ድንገት የሚገለጡ የወደቁ መላዕክቶች/aliens/ ከቃሉ እውነት ጋር እንዴት እንደሚያያዙ፣ ይህ ሁሉ እንዴት ሊሰራ እንደሚችል እንዲገባኝ እየታገልኩ ነበር፡፡ በተለይም ባሳለፍናቸው ጊዜና ወቅቶች አንዳንድ ስለወደፊቱ የተነገሩ ትንቢቶች በሚደንቅ ሁኔታ መፈፀማቸውን እያሰላሰልኩ እያለሁ የኔ ድንቅ ኢየሱስ በምህረቱ ሐሳቤን አቋርጦ ወደ እኔ መጣ፡፡ እርሱ እንዴት መልካም ነው!

ኢየሱስም እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ. . ." ውዴ ግራ እንደገባሽ አውቃለሁ፡፡ በመጀመሪያ ሊገባሽ የሚያስፈልገው በቃሉ የተገለጡ ምልክቶች በብዙ አይነት የስልጣኔ ደረጃዎች፣ በብዙ አይነት የጊዜ ደረጃዎች፣ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሯቸው እንደሚችልና ራሳቸውን ለመድገም እንደሚችሉ ነው፡፡ ለምሳሌ በታሪክ ውስጥ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህም ኔሮን፣ ካሊጉላ፣ ሂትለርንና ሌሎችንም መውሰድ ትችያለሽ፡፡ እነዚህ ሁሉ የክርስቶስ ተቃዋሚ ተብለው ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነደዚህ እያልኩ ብዙ ልዘረዝር እችላለሁ፡፡ ነገር ግን መልዕክቱን ረዥምን የማይቻል ከማድረግ ይልቅ በርዕሱ ላይ እናተኩር፡፡

"የወደቁ መላዕክት/*demon aliens/* ወደ ምድር እንደሚጣሉና ተገልጠው ሰማዩን እንደሚሞሉት መገንዘብሽ ትክክል ነው፡፡ ደግሞም ብዙ አጋጣሚዎች ተከስተው እንደነበረና ክስተቱም እየቀጠለ መሆኑም እውነት ነው፡፡ መንግስታት ከእነርሱ ጋር ስምምነት ገብተዋል፡፡ የገቡትም ስምምነት የወደቁ መላዕክቱ ሰዎችን ጠልፈው ከምድር በመውሰድ ሰዎችን የሚመስልና አጋንንቶች ሊኖሩበት የሚችሉበትን ሰውነት ለመፍጠር የጀመሩትን ምርምር እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ነው፡፡

(ክሌር)፦ ነገር ግን በቅርቡ እንደሰማሁት ፕሬዚዳንት ትራምፕ ግሬይ ኤሊየንስ ከሚባሉት ጋር ስምምነቱን አላደሰም፡፡ ከዚህም የተነሳ ከእኛ ሶላር ሲስተም (*solar system*) ወይም ከምድር ክልል በአጃቢ እንዲወጡ እየተደረጉ ነው፡፡ ከምድር በታች በሚገኙ ከተሞች የነበሩ የምድር መሽሎኪያዎች እንዲጋዩ በተደረጉ ጊዜ እንኳን እነዚህ ግሬይ (*gray*) የሚባሉት ፍጥረታት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እጅግ በብዛት ይገኙ ነበር፡፡

ኢየሱስም . . ."ዋናው ቁም ነገር በመጀመሪያ ደረጃ ሰይጣን ለስልጣን፣ ከበላይ ሆኖ ለመግዛትና ለመመለክ ከፍተኛ ጉጉት አለው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የማይረካ ቅናት በሰው ልጆች ላይ ስላለው ሰዎችንና ምድርን ለማጥፋት ከፍተኛ ፍላጎት አለው፡፡ ለዚህ ነው ጥላቻው እጅግ የጋለው፡፡

"ሰዎችን የሚጠላው ደግሞ በእኛ ማለትም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በመወደዳቸው ነው፡፡ እንዲሁም ምድርን የሚጠላት በእኛ ውብና ማራኪ ተደርጋ ለሰው ልጆች ስለተሰራች ነው፡፡ እኛን መንካት አይችልም፡፡ ነገር ግን እኛ የፈጠርነውንና የወደድነውን በመጉዳት በተዘዋዋሪ እኛንም ይጎዳል፡፡

"ስለዚህ የሰይጣን አጀንዳ ሁለት ገፅታ ያለው ነው፡፡ በአንድ በኩል ሰዎች እንዲያመልኩት ማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎችንና ምድርን ማጥፋት ነው፡፡ ስለዚህም ለሰዎች እጅግ የበላይ የሆነ ቴክኖሎጂ ቢሰጥ፣ ይህም ከፍተኛ የሆኑ መላዕክቶች ብቻ የሚያውቁት ሲሆን፣ በዚህም ራሱን አምላክ አድርጎ በማቅረብ አምልኮን ይቀበላል፡፡ አንቺ መልካም የሚባል ከከባቢ አየር ውጪ የሚመጣ ፍጡር( *extra-terrestrial)* ወይም ኤሊየን (*alien*) የለም ብለሽ የተናገርሽው ትክክል ነው፡፡ እነርሱ ሁሉም አጋንንቶች ሲሆኑ ለራሳቸው የተለያየ አይነት ሰውነት የፈጠሩ ናቸው፡፡ ይህም የምድር የሆነውን፣ እኛ ፈጥረን ከአብ ልብ ውስጥ መንፈስ የሰጠነውን ለመበዝበዝ ነው፡፡ እናም መልካምና ደግ ነን በማለት ሊያሳምኗችሁ ይሞክራሉ ደግሞም ይህንን ተቀብለው የሚያምኑ ይኖራሉ፡፡ መልካም ፖሊስ እና መጥፎ ፓሊስ በመባል የሚገለፀውን አባባል ታውቃላችሁ፡፡ ሁለት ፖሊሶች አንደኛው ጥሩና አዛኝ የሆነ ሌላኛው ደግሞ ንቁና ለስራው የተሰጠ ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ፖሊሶች ናቸው፡፡ እነዚህም የወደቁ መላዕክትና አጋንንቶች በጭንቅላታችሁ እነደዚህ ሊጫወቱባችሁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም "እነዚህ መልካሞቹ ናቸው፣ እነዚያ ግን መጥፎዎቹ ናቸው፡፡ አ! ሌላው ደግሞ መጣ በእውነት መልካም የሆነና ሁሉንም ነገር የሚያሳርፍ" ትላላችሁ፡፡ አይደለም፣ በፍፁም እንደዚያ አይደለም፡፡ ይህ ማታለያ ነው፡፡ ምንም የማይዛነፍ ማታለያ ነው፡፡ ሁሉም አንድ ቡድን ናቸው፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡፡ "ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።" (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡3-4)

በዚህ ክፍል የቆሮንቶስን ሰዎች ከመንገድ እየወጡ ስለሆነ እየገሰፃቸው ነው፡፡ በቁጥር 12 ላይ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡፡" ነገር ግን በዚያ በሚመኩበት እንደ እኛ ሆነው ሊገኙ፥ ምክንያትን ከሚፈልጉቱ ምክንያትን እቆርጥ ዘንድ አሁን የማደርገውን ከዚህ ወዲህ ደግሞ አደርጋለሁ። እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።"(2ኛ ቆሮንቶስ 11፡12-15)

"እነዚህ ፍጡሮች እኛ የፈጠርነውን በመወሰድ አጋንንት በዛ ውስጥ እንዲኖሩበት ለማድረግ እንደገና ሰሩት፡፡ ይህ ፈደሬሽን አፍ ላይት ወዘተ . . . የሚባሉት በጣም ብልህ የሆኑ የወደቁ መላዕክቶች ሲሆኑ ሌሎቹ አካል የለበሱት አጋንንቶች ደግሞ እንደ ሰይጣን መንግስት አደረጃጀት በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፡፡ ፕሌዲያንስ *(Pleiadeans)*፣ ቬኑሲያንስ *(Venusians)* ፣ ነጭና ረጃጅሞች *(Tall whites )*፣ ተዳቅለው እንደ ሰው ሆነው የሚታዩ፣ እንዲሁም ግራጫዎቹ (*grays*) ሁሉም ከአጋንንቱ አለም የመጡ የመናፍስት አካላት ሲሆኑ በእግዚአብሔር አብ ላይ አምፀው ከመንግስተ ሰማይ የተባረሩ ናቸው፡፡

"እነዚህ ከሦስተኛው ሰማይ ቀድሞ የተባረሩ ሲሆኑ አሁን ደግሞ በቅርቡ ከሁለተኛው ሰማይ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ተባረው ወደ ምድር ይጣላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ነው እጅግ ብዙ በሆነ መጠን መታየት የሚጀምሩት፡፡ ክብ የሆነውና ሌሎች ቅርፅ ያላቸው የአየር ላይ መጓጓዣዎቻቸው ሰማዩን ሁሉ ይሞሉታል፡፡ በዚያን ጊዜም ሞኞችን ወደ መጓጓዣዎቻቸው እንዲገቡ ይጋብዟቸዋል፡፡"

(ክሌር)፡- እዚህጋ ህዝቅኤል ከአመታት በፊት በህልሙ ያየውን አንድ ነገር ልንገራችሁ፡፡ ባለቤቴ ህዝቅኤል የአየር መጓጓዣዎችን ስለሚወድ በህልሙ ወደ አንድ መጓጓዣ ለመግባት እየተጓዘ እያለ ጠባቂ መልአኩ "አይሆንም ወደዛ እንዳትገባ" በማለት ከለከለው፡፡ ስለዚህም ሳይገባ ተመለሰ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ህዝቤ ከእነዚህ ኢጋንንቶች ጋር ምንም የምታደርጉት ጉዳይ የላችሁም፡፡ እነርሱ እውቀታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መላዕክቶች ስለሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ፍላጎታቸው እናንተ እንድትጠፉ ነው፡፡ ስለዚህም ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር አይኑራችሁ፡፡ እደግመዋለሁ፣ ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር አይኑራችሁ፡፡ ከአጠገባችሁ እንዲሄዱ በእኔ ሥም እዘዟቸው፡፡ ይህ ደግሞ እነርሱ ማን እንደሆኑ ለማወቅ የምትፈልጉትን ግልፅ የሚያደርግና ፍጥረታቸው በትክክል ምን እንደሆነ የሚያሳያችሁ ይሆናል፡፡

"ብዙዎች እነዚህ እጅግ የተዋቡ ፍጥረታት ከላይ የመጡ የበላይ አካላት፣ በሞራል ደረጃም የበለጠ ስነ ምግባር ያላቸው ይመስላቸዋል፡፡ እውነቱ ግን ፍጡራኑ ያመፁ መላዕክቶች ሲሆኑ ወቅቱ ሲደርስ በሁለተኛው ሰማይ ላይ እንዳይኖሩ የተከለከሉና ወደ ምድር የሚጣሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ለሚሊኒየም ያህል አይምሮንና ኢነርጂን በመጠቀም ታላቅ ምኞት ያላቸውን ሰዎች በማታለል፣ በማግባባት፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎችን በመስጠት፣ የሰዎችን አመኔታና ድጋፍ አግኝተን ይረዱናል በማለት ተስፋ ሲያደርጉ ነበር፡፡ የዚህ ሁሉ የሰይጣን ልፋት በእግዚአብሔር መልክና ሃምሳል የተፈጠረውን የሰው ልጅ አምልኮ ለማግኘትና ሲመኝ የነበረውን ከእግዚአብሔር የበለጠ ክብር ለማግኘት ነው፡፡

በ2ኛው ተሰሎንቄ ጳውሎስ የሚናገረው ስለዚህ ነው፡፡ "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

(ክሌር)፡- እዚህ ላይ አንድ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ እኔ እንደማምነው ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ያዳነኝ አንድ ነገር ቢኖር እውነትን ብቻ ፈላጊ በመሆኔ ነው፡፡ ያገኘሁት ፍፁም እውነት መሆኑን እስከማወቅ ድረስ በምንም ነገር መረጋጋት አልቻልኩም ነበር፡፡ እናም በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ እኔ የማምነውን የአዲሱን  ዘመን እንቅስቃሴ አማልክትን እንዲሁም አንድ፣ እውነተኛና ህያው የሆነውን አምላክ ልዩነት በፀጋው ሲገልፅልኝ በውስጥ ማንነቴ በዘመኔ ሁሉ ስፈልገው የነበረው እውነት ይህ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ በተጨማሪም እርሱን በመከተሌ ያገኘሁት ፍሬ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ መራኝ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም አልሜ የማላውቀው መከናወን ደግሞ በህይወቴ ተከሰተ፡፡ በእግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ውስጥ እየኖራችሁ መሆኑን እንደማወቅ ደስ የሚያሰኝ ስሜት የለም፡፡

ኢየሱስም ቀጠለ . . ." በደመናት ከሰማያት ስመጣ ሲያዩኝ፣ ይህ ማታለል ይሰበራል፡፡ እናም  እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን እውነቱ እንዳለ ተገልጦ ያዩታል፡፡ እኔን የማያውቁ እርሱን ያመልኩታል፡፡ በዚህም ለስልጣን ያለው ጥም ይረካል፡፡ ይህም የሚሆነው እኔ መጥቼ ለአንድ ሺህ አመት ወደ ተዘጋጀለት እስኪጣል ድረስ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋችኋል፣ "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

"ህዝቤ እነዚህ አዲስ ቴክኖሎጂዎች ማለትም ተሴላ(*Tesla*) ፣ ሜድ ቤድስ *(Med Beds)* ፣ ነፃ ኤነርጂ (*free energy*)፣ 5ጂ ንቃተ ህሊና (*5G consciousness*) የሚባሉት ሁሉ እኔ በፈጠርኳቸው የሥነ ፍጥረት (*universe*) ክፍል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ እናም እነዚህ መላዕክቶች እንደዚህ አይነቱ ነገር ስለሚገባቸው ይህ የሆነው ከእነርሱ ከፍተኛ ንቃተ ህሊና ክፍል አንዱ ብቻ እንደሆነ፣ ይህም ደግሞ አምላክ ከመሆናቸው ጋር የተገናኘ መሆኑንና ከእናንተ የበለጠ ንቃተ ህሊና እንዳላቸው ለማሳመን እየሞከሩ ነው፡፡ እነዚህ የወደቁ መላዕክቶች እኔ ከፈጠርኩት የሥነ ፍጥረት ክፍል አባል ናቸው፡፡ እናም እንዴት እንደሚሰራ ለማየት ችሎታው ስላላቸው ያንን በማንቀሳቀስ አሰቃቂ ለሆነው ህግወጥ ውጤት ተጠቀሙበት፡፡ እነዚህንም ቴክኖሎጂዎች እንደ ትሮይ ፈረስ በማድረግ ነፍሶች እንዲያምኗቸው ለማድረግ በኃይልና በታምራት፣ እንዲሁም በምልክቶች፣ ከተቻለ የተመረጡትን እንኳን ለማሳት ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ እንደሚሆን ደግሞ በቃሉ ተገልጿል፡፡ እያልኩ ያለሁት ፈጠራዎቹ በራሳቸው ገለልተኛና እንዳውም ጥሩ ናቸው፡፡ ቢሆንም ግን እነዚህን ቴክኖሎጊዎች ያመጡላችሁ አካላት አጋንንቶችና የወደቁ መላእክቶች ናቸው፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ጋላክቲክ ፊደሬሽን ኦፍ ላይት (Galactic Federation of Light) ምንድነው?

ኢየሱስም . . . " ይህ ያገኘሽው አባባል እነርሱ "አዲስ" ብለው ከሚጠሩት ከመንፈሳዊ እንቅስቃሴ አባባሎች አንዱ ነው፡፡ ሰይጣን ከመውደቁ በፊት ሉሲፈር፣ የብርሃን ተሸካሚ፣ ይባል እንደነበረ ይህንን አስታውሺ፡፡ ይህ አሁን የምናገረው በቃሉ የተፃፈውን ትልቁን መሳት ተብሎ የተጠቀሰውን ነው፡፡"

"<u>ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል</u>።" (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡10-11)

ኢየሱስም . . . የኔ ፍቅር ይህ ግልፅ የሆነ ስዕል እንደሰጠሽ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በዚህ ነገር እንዴት ብዙ እንደታገልሽ አውቃለሁ፡፡ አሁንም ግን የሚያሳሳት መስሎ ይታይሻል፡፡ አሁን ደግሞ ሁሉም ኸርትድዌለርስ እንዲገባቸው አድርጌ ልግለፀው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ድንቅ እንደሆነ ልንገራችሁ፡፡ ነገር ግን ችግሩ ያለው ቴክኖሎጂውን የሰጧችሁ አካላት በአይምሮአቸው የሚያስቡት እናንተን ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ ከመኖሪያ ሥፍራቸው ተፈናቅለው ወደ ምድር የመጡት ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው ነገር አልቆባቸው አይደለም፡፡ እነርሱ ወደ ምድር የመጡት መላዕክቶቼ ከሁለተኛው ሰማይ አስገድደው በማባረር ወደ ምድር ጥለዋቸው ነው፡፡ የዚህም ምክንያት እኔ መጥቼ ሁሉን ነገር ከማስተካከሌ በፊት መካሄድ ያለበት ትልቁ የማንፃት ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡ ሁሉንም አንድ ላይ ሰብስቤ ወደ እሳቱ ባህር እጥላቸኋለሁ፡፡ እና ደግሞ መንግስት በትክሻዎቼ እንጂ እነሱ እንደሚሉት በጋላክቲክ ፈደሬሽን ኦፍ ላት *(Galactic Federation of Light)* አይደለም፡፡ ይህ የሰይጣንን አሰቃቂ አጀንዳዎች ለመሸፈን ብቻ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበው ለምሑራኖች ሲሆን እነርሱ ሃይማኖትን ጠልቀው ያልቀመሱና ሃይማኖትን ቀላልና የተራ ሰዎች አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው፡፡ ስለዚህም ምሑራኖቹ ከማይታየው አለም የሚፈልጉት ጥበብን ስለሆነ ዝንባሌያቸው ወደ መንፈሳዊው አለም ሚስጥራት ነው፡፡"

(ክሌር)፡- የተወደዳችሁ እስካሁን ካቀረብኩላችሁ መልዕክቶች ሁሉ እንደዚህ የከበደኝ የለም፡፡ የማስጠነቅቃችሁ በሰው ልጆች ላይ ሁሉ ሊወድቅ ያለው ትልቁ መሳት እየመጣ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማታለል በ60ዎቹ የአኳርስ ዘመን በመባል፣ አሁን በዚህ ዘመን ደግሞ ትልቁ መነቃቃት ወይም ዘ ግሬት አዋክኒንግ (The Great Awakening) ፣ የ5D አለም፣ በሚል

በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ውስጥ መሰረቱን ጥሏል፡፡ አሁን የደረሰበት ደረጃ ግን በሙሉ አቋሙ አካል ለብሶ የምድሪቱን ሰዎች ለማጥመድ ተዘጋጅቷል፡፡ ውዶች አይኖቻቸው እንዲከፈትና ነፃ እንዲወጡ ፀልዩላቸው፡፡ እንዲሁም ፈተናው ሲመጣ ፀንታችሁ እንድትቆሙ ለራሳችሁ ፀልዩ፡፡

"መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፡፡" (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1-2)

እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና ( በዘመናችን እንደ ሜታፊዚክስ ትምህርት)፣ እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና (በዘመናችን እስፐሪቹአል ኢነተሌክቹዋሊዝም እንደሚባለው) በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።(ቆላስያስ 2፡8)

ጌታ ኢየሱስም . . . "በሌላ አነጋገር 'እኛ የበራልን ክርስቶስን በሚመስሉ አካላት፣ ይኸውም ከላይ በወረዱ ጌቶች ወይም አለቆች ነው፡፡' በሚሉት አትማረኩ፡፡ እነዚህም በእኔ አማካኝነት ደህንነት አያስፈልግም የሚሉ ናቸው፡፡"

"ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" (ራዕይ 12፡9)

(ክሌር)፡- ይህ ክፍል በሌላ አነጋገር ሲገለፅ እርሱና መላዕክቶቹ ከ2ኛ ሰማይ እንዲወርዱ የተደረጉት በኃይል ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ ይህ የተከናወነው ሰይጣን ከሶስተኛው ሰማይ ሲጣል ነው ብላችሁ ትሚገቱኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ማስታወስ ያለባችሁ አንድ የእግዚአብሔር ቃል በተለያየ ጊዜ ለሚከሰቱ እውነቶች ሁሉ የሚሰራ ነው፡፡

"በዚያን ጊዜም ማንም እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ፥ ወይም። እነሆ፥ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ። እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኋችሁ። (ማርቆስ 13፡21-23)

(ክሌር)፡- የኔ ውዶች ከሰው አቅም በላይ የሆኑ ሰዎች እንደገረሙና እንደደነቁ የሚያደርጉ በጣም አስደናቂ ነገሮች ለዕታ ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ኃይል ስላላቸው ያጠመዳሉ፣ ያሰምጣሉ ሰዎችም በእነርሱ ይረታሉ፡፡ ይህንን ብቻ አስታውሱ እነዚህ ነገሮች በተለያዩ ወርድና ስፋት (interdimensional) ማንነት ባላቸው አካላት ኢነርጂዎችን በማንቅሳቀስ ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ልክ ባለ ሦስት ወርድና ስፋት ያላቸው ስዕሎችን በአየር ላይ ማንጠልጠል እንደሚቻል ማለት ነው፡፡ ይህንን ማጭበርበር ሊለዩ የሚችሉት ከፍ ያለ ወይም የሰላ መንፈስን የመለየት ችሎታ ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ሙሽሮቼ አፍቅራችኋለሁ፡፡ ቀኑ እየመጣ ነው፣ በእውነትም እየመጣ ነው፡፡ መመልከታችሁን ቀጥሉ፡፡ አሁን እንኳን ቢሆን ወደ ጥፋት ከገባችሁበት ወጥታችሁ ወደ መጀመሪያ ፍቅራችሁ ተመለሱ፡፡ የተወደዳችሁ እየጠበቅኋችሁ ስለሆነ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡ ከእኔ ጋር የቀረበ ወዳጅነት ሲኖራችሁ ሌላ አምላክ እንድታመልኩ ከሚመጣባችሁ ፈተና ታመልጣላችሁ፡፡ አንድ ሆነው ከሚሰሩ፣ ነገር ግን ደግሞ በሶስትነት ከተገለጡ ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ እኔ የእናንተን መልክ ይዤ፣ እንደ እናንተ ተወስኜ፣ ሰውነቴን ለስቃይ አሳልፌ ሰጥቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ እናንተን የእኔ ለማድረግ ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ መርሳት የሌለባችሁ በፍፁም ንፅህና በዘላለማዊ እጆቼ በጥንቃቄ እንደማቅፋችሁና ፍቅሬን በፍፁም እንደማታጡት ነው፡፡ ለመገኘቴ አይኖቻችሁን ከፍታችሁ እዩ፡፡ ይህ

ፍቅር ደግሞ ገደብ የሌለው ነው፡፡ በክንዶቼ እረፉ፣ በቃሎቼ ላይ እርፉ፣ ቃል በገባሁላችሁ ላይ እረፉ፡፡ እናም ደግሞ በእኔ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ልብ፣ አንድ አይምሮና አንድ አካል እንደሆንን ሙሉ መተማመን ይኑራችሁ፡፡"